
ዓለማየሁ ገላጋይ

# በፍቅር ሥም



2ኛ ዕትም

# በፍቅር ሥም

© መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
2009 ዓ.ም

ዓለማየሁ ገላጋይ

አንደኛ እትም - ጥር 2009 ዓ.ም.
ሁለተኛ እትም - ጥር 2009 ዓ.ም.

**የሽፋን ስዕል፡-** Saul Bass

**በውስጥ ገፅ የክፍል ሶስት ስዕል፡-** Henri Matisse

Nu bleu IV-1952

**ትየባ ፡-** ቤተልሔም አመነሸዋ

**የሽፋን እና የውስጥ ገፅ ቅንብር፡-** ኒሥ ጥበብ 0911029833


**ሕትመት፡-** ሐሪቴጅ ኅትመትና ንግድ ኃላ/የተ/የግ/ ማኅበር

# ምሥጋና

ለመዓዛ ብሩ

እና

ለአበበ ባልቻ



# ክፍል ፩

## ከልውጥውጡ - በፊት

**“እግዚአብሔር አምላክም ለማየት ደስ የሚያሰኘውን፣ ለመብላትም መልካም የሆነውን ዛፍ ሁሉ ከምድር አበቀለ…”**

**(ዘፍጥረት 2፥9)**

# መታሰቢያነቱ

ይሄ ክፍል፣ በጥበብ እና በሕይወት ጉዞ ላይ ጥቶ መነጠልን እስኪያሳርፍበት ድረስ አብረውኝ ለነበሩት፡-

ለሃያሲ አብደላ እዝራ

እና

ለደራሲ አስማማው ኃይሉ (አያ ሸረው)

መታሰቢያ ይሁንልኝ።

፱

## እኔ፣ ጠቢቡ ሰሎሞን እና አባቴ

በሴት የመከበብን ጥቅም የምናውቀው እኔና ጠቢቡ ሰሎሞን ብቻ ነን. . .

. . .ህይወቴን ሳስበው በሴቶች የተዋቀረ ዕድት ሆኖ ይታየኛል። ከዕድት የሚገኘው ደስታ እንዳይጎድልብኝ በዙሪያዬ "ሽር-ብትን" የሚሉ ሰባት ሴቶች አሉ።

"እንተ? ታለሰው? ተነሰ. . ." (እናቴ)

"ተይው ትንሽ ይተኛ" (የመጀመሪያ እህቴ)

"ይርበዋል፣ ተነስቶ ይብላ" (የእሷ ተከታይ)

"እንቅልፍ ሲጠግብ አውቆ ይነሳ የለ?" (የተከታይ ተከታይ)

"እሉ ከተኛ መች ይርበዋል? ይቀሰቀስ" (እናቴ)

"ይልቅ ስትቀሰቅሱት እራሱን እንዳያመው" (አራተኛ ተከታይ)

ሴቶቹ ለእኔ ምቾት ሲራኮቱ አድፍጬ አስማቸዋለሁ። ይሄን ጊዜ አባቴ ሰርቶ-ሰርቶ እንደደከመ እህያ የፈዘዘ ትዝብቱን በቦዙ ዓይኖቹ ይልክ ይሆናል።

"አውቆ ነው፤ ነቅቷል" (የእኔ ታናሽ እህት) በታናሽ እህቴ ከተሰማው ሁሉም ይኮረኩሩኛል። ይኸዋ. . .

"ቂቂቂቂቂ. . ." ይቺ ናት ዕድት!! ይቺ ናት ገነት!!

ከጉያ ከሚወጣ ሳቅ ጋር በተድላ እደኩ። ወይም ከሴቶች ጣት የሚፈልቅ ደስታ በብብቴ በኩል አድርጎ ወደ ልቡናዬ እየፈሰሰ. . .

በሴት የመከበብን ጥቅም የምናውቀው እኔና ጠቢቡ ሰሎሞን ብቻ ነን። እሃ! ይቅርታ፣ ለካ አንድ ሰው ቀርቷል። የጠቢቡ አባትም አለ፤ ንጉስ ዳዊት።

ሴቶች ዕጣ-ፈንታዎቼ ናቸው፤ ከፈጣሪ የተቸሩኝ ምቾቶቼ። ሳድግ ሰባት ሚስቶች አገባና ሴቶቼን አሥራ አራት አደርጋቸዋለሁ።

ወላጆቼ ስድስት ሴት ልጆች ከገፈገፉ በኋላ እኔን አገኙ። ሌላ ወንድ ልጅ ፍለጋ ሞክር ሲያደርጉ የእኔ ታናሽ ሴት ሆነችባቸው። ፈሩ፤ ሁለተኛ ወንድ ልጅ የሚገኘው ሌሎች ስድስት ሴቶች ከወለዱ በኋላ እንደሆነ ተገልጦላቸው ከመውለድ ትግባር አፈገፈጉ።

"እሱን ይባርከው፣ እንደአባቱ ቀጭ'ቃጨ ካልሆነ ይበቃል" ትላለች እናቴ፣ አባቴ ደግሞ፡-

"እግዚአብሔር የሰጠኝን ወንድ ልጅ ጣ! የገዛ ሚስቴና ልጆቼ ነጠቁኝ ጣ!" ይላል። ሲያወራ ፊደሎቹን እየተመሰና ቃላቶቹን እያጣጣመ ስለሆነ ጣ! የሚል ድምፅ ይሰማል።

አባቴ ከማልጎምጎም አልፎ ጋሽ ተገኜን አማላጅ አድርጎ እናቴ ላይ ላከ። ጋሽ ተገኜ እንዲህ አሏት፡-

"መቼም እንደምታውቂው ቢዘን (የአባቴ ሥም ነው) በወንድ ልጅ እንደእኔ አልተባረከም። ስለዚህ አንድ ልጁን ለእሱ ተይለት። እንቺ ሴቶቹ ላይ በርቺ። ለልጁም ቢሆን ወደ አባቱ ቢያደላ ደግ ነው።"

እናቴ ጋሽ ተገኜን ታከብራቸዋለች። እኔ ስወለድ አባቴ ደስታውን የገለጠው የጋሽ ተገኜን ጠበንጃ ገፍፎ በመተኮስ ነበር። ወዲያው አብዮት ጠባቂዎች ሲመጡ ‹አይ እንግዲህ ቢዘን አበቃለት› ተባለ። ግን አባቴ እንዳይታሰር ጋሽ ተገኜ እራሳቸውን አሳልፈው ሰጡ።

"ጓዶች፣ እኔ ነኝ - ባርቆብኝ ነው" አሉ።

"ምነው ጓድ ተገኜ? ለፀረ-አብዮተኛ ሽፋን እየሰጠህ ታስጨርሰን?" ተብለው ሦስት ቀን ታሰሩ። የቀበሌ ፍርድ ሸንጎ ቀርበው የጥይት ዋጋ አስራ አምስት ብር ተቀጡ አሉ። ይሄ የጋሽ ተገኜ ድርጊት ለቤተሰባችን ትልቅ ውለታ ሆኖ ሲወሳ ይኖራል። ቢሆንም እናቴ የጋሽ ተገኜን አማላጅነት አልተቀበለችም።

"ልጄን አልተውም! ከመላእክት እስከ አጋንንት ደጅ የረገጥኩበትን ልጄንማ አልተውም! እሳቸው እንደ ጅኒ በረሃ ለበረሃ

ሲዞሩ እኔ ነኝ መከራ አይቼ ያሳደኩት። እንዴት ነው ልጅሽን ተይ ማለት?"

አንዳንዴ የእናቴ ነገር አይገባኝም፤ አጋንንትና መላእክት ቤት አላቸው? ወይስ ነገር አሳመርኩ ብላ ነው? ያም ሆነ ይህ ጋሽ ተገኔ በአማላጅነታቸው መግፋት ቀርቶ አንድ ምላሽ መስጠት ተሳናቸው። ሽንፈታቸውን እንዴት አድርገው እንደነገሩት አይታወቅም አባቴ ተስፋ የቆረጠ መሰለ። ጥሩ ምግብ እንዳየ ሰው አፉን እጓጉቶ እንዲህ እያለ በማማቱ ቀጠለ።

"እግዚአብሔርን ሌት ተቀን አስቸግሬ፣ ጣ! የሰጠኝን ወንድ ልጅ ጣ! የገዛ ሚስቴና ልጆቼ ነጠቁኝ፤ ጣ!"

በሴት የመከበብን ጥቅም የምናውቀው እኔ፣ ጠቢቡ ሰሎሞንና አባቴ ንጉስ ዳዊት ነን። አባቴ ከዚህ ጥቅም ሊያናጥበኝ ተግቶ ነበር። እናቴና እህቶቼ በረቱበት እንጂ። ሲቸግረው አርግማን መሰል ብሒል አመጣ፤ እንደለመደው በወፐ ቀማሽ ስልት አፉን እያጣጣመ እንዲህ አለ፦

"ወንድ ልጅ እግዚሐር አሳይቶ ነሳኝ፤ ጣ!"

እናቴ ተንቀጠቀጠች፦

"እንቱ ሰውዬ! በልጄ ላይ እያሟርቱ፤ ይሄ ልጅ አንድ ነገር ቢሆን ተርስዎ እራስ አልወርድም።"

አንዳንዴ የእናቴ ነገር አይገባኝም። እኔ ሞቼ እሷ አባቴ እናት ላይ ፊጥ ብትል ምን ይጠቅመኛል?

"ጅኒ ይመስል በረሃ ለበረሃ ሲንከራተቱ የለከፍዎ ካለ ጠበል እንውሰድዎ እንጂ ይሄ ህጻናት ልጅ ምን ያድርግዎ?"

"እ-ህ፣ ጅኒ አልሽ?" አለ አሉ አባቴ በትዝብት።

"ታዲያ ምን ልበልዎ?" እናቴ ሳትረግብ አልቀረችም።

"ኦ-ሆሆሆይ. . . እኒህ ፈሪሳ! በምን አይናቸው ልጄን አዩብኝ?" ብትልም የአባቴን አይን በድፍረት አላየችም።

"ላንቺና ለሀገሬ መሰሎች በረሃ-ለበረሃ የተንከራተትኩት ጣ!"

"እሱን እርስዎ ያውቃሉ፤ ልጄን ለቀቅ ያድርጉ ብቻ" የአልሞት ባይ ተጋዳይ ምላሽ ይመስላል። "በምን አይናቸው አዩብኝ? የግድ አሽከሬ ካልሆነ ነው?"

ለካ አባቴ የሚፈልገው የእሱን ካፖርትና በትር ይዤ በየጠጁ ቤት እንድንጠለጠል ኖሯል?

-አንተ? አንበሳ? የማነህ ልጅ? ጎሽ-ጎሽ ጎሽ!! (እኔን)

-ቢዘን፣ ለካ ባለሙያ ኖረሃልና... (እሱን)

አባቴ ከዚህ ሌላ ዓለም የለውም። መሃል አዲስ አበባ፣ ያውም ጉለሌ ላይ እየኖረ ህግ የሌለ ይመስል ደም መላሽ ወንድ ልጅ ይቋምጣል። የጋሽ ተገኜን ልጆች እየቆጠረ ኑሮውን ያማርራል። ከዚህ ጋር እያያዘ ጨው የሌለው ወሬውን ያጣጥማል። እሱ ሲያወራ እኔ ብጠግብ እንኳን ምግብ ያምረኛል።

"ቤቱ የሴት አድር ነው፤ ጣ! ዘወትር ጫጫታ ጣ!. . .ለፍተን ለፍተን ሴት ወለድን. . ." ይላል ሀዘን ቅልቅል እንጉርጉሮ ያሰማል፤ ድምፀ-መልካም ነው። እናቴን በልጅነቷ እንደወፍ ያረገፋት በእንጉርጉሮው ሳይሆን አይቀርም። ዛሬ-ዛሬ ደሞ በዚያው እንጉርጉሮው በነገር ይደነቋቊላታል።

"አባክሽን ሚስቴ፣ ውለጅ ወንድ መንታ

ግራ እጄ ሲመክት፣ ቀኝ እጄ ተመታ"

በዚህ ዘመን መንታ ቀርቶ አስር ወንድ ልጅ ቢወለድ ለዱላ መከሰስ እንጂ ብድር መመለስ አይፈቀድም። ካልሆነ በወንድ ልጅ ጅሪ የሚተማመን ፀቡ ከመንግስት ጋር ነው። ይሄን አባቴ አይረዳም። በየደረሰበት "ቢዘን ሽልል-ፎክር" ይባላል። አባቴ ሲሽልል አያጣጥምም። "ጣ" ሳይል ሽለላውን ኸው አድርጎ ይጠማዋል። በሽለላ አጨላለጡ የጀግና ልብ ይቀሰቅሳል። ገመናውን የማውቅለት ግን እኔ ነኝ። አቤት ከገባ በኋላ የተሰፈረ ዱቄት የመሰለ ጋቢውን ትከሻው ላይ ቆልሎ በአብረት አይመዝንም። እናቴን ይፈራታል፤ ነገር ፈልጋ ስታጨነቁርበት የሚገባበት ይጠፋዋል። ይሄንን ሳይ አባቴ አርባ አመት ሙሉ የተዋጋቸው ጠላቶች እናቴን ቢያገኙ ቶሎ እጅ ይሰጡ ነበር እያልኩ እስቃለሁ።

"ትይ እንጂ እንቶቼ፣ ጣ!" ይላል።

"ዝም በሉ አንቱ መልቲ!" ትላለች እናቴ

"መልቲነቴ የታየሽ ዛሬ ነው? ጣ! ተይ እንጂ ጣ!" ተኝቶ ማድፈጥን በመምረጡ አልጋ ላይ ይወጣል።

"እኔና ልጆቼን በየጠጅ ሸንጎው እንዳብጠለጠሉ አሉ። እንግዲህ ምን ይሁን? እኛ ሴቶቹ መስሎኝ ቤቱን ቀጥ አድርገን የያዝን። የእርስዎ ጡረታ ነው ይሄን ሁሉ ቤተሰብ ቀጥ አድርጎ የያዘ? ደርሶ ወንድነኝ ማለት. . ."

"ለወንድነቴ ምን ታወጪለታለሽ? ጣ! ተይ እንጂ እንቶቹ? ጣ! ወንድነቴ ጎድሎ የት ቦታ አሳፈርኩሽ ጣ!" አባቴ ማጣጣም ካበዛ ፈርቷል ማለት ነው።

"ሰባኪ! እርሶ ሰውዬ ከልጆቼ ላይ ይውረዱ! ኋላ፣ ኋላ፣ ኋላ. . . ጉድ ይፈላል!"

እያልጎመጎመ ይሸፋፈናል። እዚህ ላይ የሴት ልጆቹን ሆድ ይበላል። "በቃ ተይው! በቃ ተይው!" ይሉሉታል። ሲነጋ ግን ያው ነው "ለፍተን ለፍተን ሴት ወለድን ጣ!" ይላል።

ከቤት ውጭ ከሆነ እናቴ አይኗን ለጸብ አታጨነቁርም። ሙሉ ትኩረቷን ለጉልቷ የሰጠች በመምሰል የድንችና የቲማቲም ካብ እየናደች ትደረድራለች። እንደ አባቴ ብርድ ልብስ መሸፋፈኛዋ ድንችና ቲማቲም ነው።

"ሴት ግሥላ አረባለሁ። ጣ! እንቺ ሴት ግሥላ፣ ጣ! ልጆችሽ ሴት ግሥላ፣ ጣ!..." ወሬውን እያጣጣመ. . .

"እኔ ኒያላ" ሲል ነው ብዬ እጠብቃለሁ።

"እንዲሁማ አርብቼ አልተዋችሁም"

እናቴ ደጅ ክፉ አይወጣትም "ምን ሊያደርጉን?"

"እጨርሳችኋለሁ፣ ጣ!"

"እረ ተጨ አንቱ ሰውዬ፣ ግፍ ፍሩ" አውቃ የተሸነፈችለት ትሆናለች።ንግግሯ ውስጥ ለማታ መዛት አለ። ይሄንን የምናውቅለት

ግን እኔና ቤት ልጆቹ ብቻ ነን። ጋሽ ተገኜ የእናቱን ማድፈጥ እያተው ተሸውደዋል።

"ቢዘን'ኮ ወንድ ነው፣ ቤቱን ሰጥ ለጥ አድርጎ የያዘ" ይላሉ (ሚስቱን እንዳይሉ)

ገመናውን የምናውቅለት ግን እኔና ቤት ልጆቹ ነን። እናቱ ለነገር አቶብቁባ አይኗን እንደ አነጣጥሮ ተኳሽ ስታጨነቁርበት ጠበንጃ እንደተወደረበት ሁሉ መግቢያ ያጣል።

"ተይ እንጂ እንጓቼ፣ ጣ!"

"ዝም በሉ አንቱ መልቲ"

በሴት የመከበብን ጥቅም የምናውቀው እኔ፣ ጠቢቡ እና ንጉሱ ብቻ ነን። አባቴ የጥቅሙ ተሳታፊ ቢሆንም ተንትኖ አይረዳውም። እንደውም ይፀየፈዋል። አንድ ጊዜ ሁነኛው ጠጅ ቤት እምባጓሮ ይፈጠርና ሰው መጥቶ ይነግረናል።

"ተጋደሉላችሁ!"

"ማን?"

"ጋሽ ቢዘን"

"ከማን ጋር?"

"ከቢዘን ጋር"

ይሄ ቢዘን የሚሉት የአባቴ ስም በሀገር ብቻ ሳይሆን በአለምም ደረጃ ያልተለመደና ብቸኛ እንደሆነ ለመደምደም ያልቻልኩት ይሄ የአባቴ ሞክሼ ሩፋኤል መገኘቱ ነው። የአባቴ ሞክሼ አካባቢውን በጦርነት ቁርሾ ያምሳል። ከጠጅ ሸንጎ ሲመለስ ድምጹን ከፍ አድርጎ. . .

"አፋበትን ሳታይ፣ ወንድ ነኝ አትበይ፤

ከረንን ሳታይ፣ ወንድ ነኝ አትበይ፤

ተሰነይን ሳታይ፣ ወንድ ነኝ አትበይ፤

መንድፍራ! ቃሮራ! አቁርዳት! ናቅፋ!"

ይላል አባቴ ይሄን ከሰማ "እውነቱን ነው፣ ጣ!" ይላል።

"አሰበለዚያማ እንጓችን መሆን ነው፤ ጓዳ ማፍጠጥ፣ ጣ!"

ሁለቱን ቢዘኖች ዛሬ ምን አጣላቸው?

ግር ብለን ስንሄድ አባቴ ከሞክሼው ጋር እንደተናነቀ ደረስን። ስንቴ ወድቀው፣ ስንቴ ተነስተው፣ ስንቴ መተናነቃቸው እንደሆነ እንጃ። የአባቴ ፀብ እንደ ዶሮ ድብድብ መውደቅና መጣል የለበት ይሆን? ይሄን ያህል ጊዜ ቆመው ምን ያደርጋሉ? ጠሪው አይቶ፣ ወደኛ መጥቶ፣ አብራርቶ፣ አንጋግቶ . . . እስኪመለስ ቆመው ምን ይሰራሉ?

እቴቴ (የመጀመሪያ ልጁ) ሞክሼውን ከማጅራቱ ይዛ ስትጎትተው ሚዛኑን ስቶ ወደኋላው ወደቀ። የአባቴን ክሳድ አንቆ ስለነበር አባቴም እላዩ ላይ ተደረበ።

ፀቡ በሁለቱ ቢዘኖች ግራ መጋባት ቢቋረጥም እህቶቼ ተተክተው ቀጠሉት። ጫጫታቸው እንዳለ ሆኖ ጨማቸውን አውልቀው የተቃራኒውን ቢዘን ፊት ሾላ እስኪመስል ጠፈጠፉት። እኔ ጫማዬን አውልቄ ብይዝም አንዴም ላሳርፍበት አልቻልኩም። ተጧራሪው ቢዘን የፀቡ ስልት ድንገት ስለተቀየረበት ማገናዘብ ተስኖት ፈዞ ቀረ። በሰጡዬው ፋንታ በመጨረሻ ያስቀሰው አባቴ ነበር።

"ወይኔ! ጣ! ወይኔ ፀቤን የሴት አደረጉብኝ! ጣ! በሰንት መከራ የተገኘ ፀብ፣ አረከሱብኝ፣ ጣ!"

የወንድ ፀብ ለዝንት ዓለም ቀሞ መወዛወዝ ነው እንዴ?

ከዛች ዕለት በኋላ አባቴ ከበስተጀርባው የሚባለውን እየሰማ ተትከነከነ። "በሴት ልጆቹ እየተመካ" ይሉታል እሱ።

አባቴ ፍዝዝ እንዳለ ያጉተመትማል።

"ተገኔን ወንድ ልጅ ያጠገብክ አምላክ፣ ጣ! ምን አልኩህ? ጣ! ምን በደልኩህ? ጣ! በሴት ግሥላ ከበብከኝሳ? ጣ!"

## ፪

## እኔ፣ እናቴና የአባቴ ቃርን

"ልጄን አልተውም! ከመላእክት እስከ አጋንንት ደጅ የረገጥኩበትን ልጄንማ አልተውም!. . ."

(እናቴ አባቴን)

"ልጄን ተዉ፣ ከአባ ኪሮስ እስከ ዲያብሎስ ደጃፍ የተንከራተትኩበት ..."

(እናቴ ሴት ልጆቿን)

እስከቅርብ ጊዜ ድረስ እናቴ ለእኔ እንደዚያ መሆኗ ከፍቅር አይተረጎምልኝም ነበር። በእኔ አመካኝታ አባቴንና እህቶቼን የምትነዘንዝ ይመስለኝም ነበር። አንድ ቀን ድንገተኛ ህመም ስትዞ ሲይዛት ያሳየችው ሁኔታ ከልጆቿ ሁሉ እኔን አብልጣ እንደምትወደኝ ገለፀልኝ። ሞት አራስጌዋ ቆሞ ካልወሰድኩ እያለ ሲተናነቃት እናቴ ትወተውት የነበረው ስለእኔ ሆነ።

"ልጄን፣ ልጄን አደራ፤ እስላም ክርስቲያኑን ደጅ የጠናሁበትን ልጄን አደራ፤ በምድር የሰጧችሁን በሰማይ እጠይቃችኋለሁ። እንዲች ብሎ የከፋው እንደሁ በሰማዩ ጌታ ፊት ልፋረዳችሁ ቃል ለምድር ለሰማይ ..." አለች።

ቂም አትርፋ ሳትሞት ቀረች።

"አንቺማ እኛን መቼ እንደልጅ ታይናለሽ?" አለች እቴቴ። የእህቶቼ ሁሉ ቅሬታ ነው። እቴቴ ከሞላ ጎደል የእናት ባህርይ አዳብራለች። የመጀመሪያ ልጅ በመሆኗ እናቴ ግማሽ ያህል ልጆቿን ስትወልድ ያረሰቻት እርሷ ነች። በእናቴ የተወለደበትን ልጅ ተረክባ እየተንከባከበች ስለምታሳድግ የእናትነት ሚና ነበራት። ስለዚህ ወልዳ የጨረሰች ሳይመስላት አልቀረም። ትዳር የመመስረት ይሁን ፍትረኛ

የመያዝ አዝማሚያ አታሳይም። እንደውም የባል እማላጅ ቢመጣ ባሏ እንደሞተባት ጋለሞታ ሁሉ፦

"እስኪ ተዉኝ፣ እኔ ባሌ ልጆቼ ናቸው" የምትል ይመስለኛል። የልጆቹ ሁሉ ቀጪና ገላማጭም ናት። ያጠፋች ልጅ ካለች የምትፈራው እሷን ነው። እናቴ እራሷ ከእኔ ውጭ ልጆቿ ልክ ያልሆነ ነገር ሲያደርጉ ስታይ፦

"በሉ ይሄን እቴቴ እንዳታይ፣ አያገባኝም!!" ትላለች።

እግዚአብሔርም የእቴቴን ቀጪና ኮስታራነት የተቀበለው ይመስላል። ምክንያቱም መኮሳተሪያዋ ላይ ፍንክት እንዲኖር አድርጎ ስትስቅ እንኳ ሰው ስራሽ ኩስትርናዋ እንዳይደበዝዝ ሆኗልና። እኔ ላይ ብቻ የበላይነት የላትም። ታዲያ ስትቆጣኝ በሆዴ፦

"እንኳን ለሰው ሰራሽ ቁጣ፣ ለተፈጥሮም አልደነግጥ" ማለት ለምጃለሁ።

በእመዐ ለእቴቴ አልገዛ ያለችው ብቸኛዋ እህቴ የእኔ ታላቅ ቻይና ናት። እናቴና አባቴ ወንድ ልጅ መውለድ ላይ ተስፋ ቆርጠው ስለነበር እሷን በወንድነት ማበረታታት የያዙት። የወንድ አለባበስና የፀጉር አቆራረጥ አላት። የቤት ውስጥ ስራ አትሰራም። እኔ ከተወለድኩ በኋላ ቻይናን ወደ ሴትነት ለመመለስ ሞክረው በክንቱ ታክቱ። ቁጣ በደረሰባት ቁጥር በእመዐ ቤታችንን ስትዞር ታመሻለች። አባቴ "መቀጪ" ይላታል።

"የልብዎትን አይቶ ሰጥዎት" ትላለች እናቴ።

"ወንድ ሆናልኝ በነበረማ"

ቻይና ካለች ታፈጣለች፣ ማንንም አትፈራም። ማንንም "ሂሽ!" ትላለች።

"አለባት አገርግር፣ የጤናዋ መስሎሽ?"

"እሰይ!" ትለቀለች "ሂሽ!" የልምዷን በአባቴ ላይ ታደርሳለች።

እስዋን ትቶ እናቴን በነገር ይወጋታል።

"እኔ የምለው፤ ቻይና በምን መጣብን? መልኳም የነሱ ነው፤ የእግር ቦክስ ያስመረጣት አንዳች ነገር ቢኖር ነው እንጂ..." ካራቴ ማስልጠኗን ነው።

እናቴ ለነገር ታጨነቁራለች፡-

"ቻይናዎችን አዚያው ይፈልጉ፤...ምን ሊሉ ነው? እስዎ ሰውዬ'ኮ... ኦ-ሆሆሆ ሆይ..."

እናቴ ሳታመር ከአባ ጋር ነገር ስትመላለስ አንዳች ደስ የሚል መንፈስ ይረብባታል። ይሄንንም አባቴም ሳይወደው አይቀርም። በልጆቹ ደጋግሞ ይወጋታል። ሦስተኛዋ ልጅ ስምረት በምን እንደሆን ሳይታወቅ የቤቱ ገንዘብ ሚኒስቴር ሆናለች። አባቴ መጠጫ ፍራንክ የሚጠይቀው እሷን ነው። አዘውትራ የሚጠይቀውን ያህል ስለማትሰጠው "እንግሊዝ ናት፤ 'ምኑን ስምረት አላችኋት?" ይላል። እናቴ ካለች ነገሩን ያስረዝማል፡-

"መልኳም የእንግሊዝ ነው፤ አፍንጫዋ ትያለሽ፣ ቁመቷ ትያለሽ፣ ቅላቷስ ብትይ. . . እኔ የምለው እንግሊዝ ከወጣ ነው የተወለደችው?"

"እንግሊዞትን አዛው እርሶ ዘንድ ፈልጉ"

"ምን ልበል አንጓቼ? ጣ! ቢቸግረኝ'ኮ ነው ከጠባይ ትያለሽ... አ..."

"እኒህን ሰውዬ አንድ የሚላቸው ጠፋ? እንዴት እንዴት ነው የሚያናግራቸው? ያልዘሩት የበቀለ ይመስል፤ ከቅላቷ ውጭ ቁርጥ እርሰዎን..."

"ፀባይዋን አልኩ እንጂ፣ ጣ!" ነገሩን አጣጣመ።

"አይ-እንግዲህ" ገለል ትላለች። ጥቂትም የምታመረው በአበባ ሲናገራት ነው። አበባ መልኳም ፀባይዋም የደበዘዘ ነው። ለጥቁረት ያደላ መልኳን ለጭለማ ያደላ ቤታችን ውስጥ ቀብራ እንደሰልጡን

እንስሳ በዐጥታ ያገኘችውን ሥራ ታሻምዳለች። እራሷን ከተተፋት እሀቶቿ ጋር አታፎካክርም። የዘወትር ፀሎቷ "የሚሰራ አታሳጣኝ" ይመስላል። "ኢየሱስ" የበዛበት መዝሙር እየዘመረች የእኔን፣ የቻይናንና የአባዬን አልጋ ታነጥፋለች፣ ባያድፍም አንሶላ ታጥባለች፣ በአንሶላው እጣቢ የቤቱን ሳጠራ ለመወልወል ጀንያ ትዘፈዝፋለች፣ እሱ እስኪ.ርስ... "ቸርች" ከልሄደች ውሎዋ ይሄው ነው።

አባዬ ከእናቴ ጋ መቃለድ ሲያምረው አበባን ትክ ብሎ እያየ፦

"ተሳስተናል"

"ምን?"

"ይቺን ልጅ አሸሻ ማለታችን ጣ! መሳቂያ ሆነናል! ጣ!" እናቴም አባቴም አበባን አሸሻ ነው የሚሏት። በትክክል መጥራት የማይችሉትን ሥም ለምን አወጡላት? አበባ እንጂ አሸሻ ይባላል?

"እንዴት?"

"እንዴት ትያለሽ? ጥቁር አሸሻ አለ እንዴ?"

"እስዎ ሰውዬ'ኮ... ኦሆሆይ! የበረሃ ጅኒዎት ነው የሚያስቀባጥርዎት፤ አሁን ወግ ማውጋትዎ ነው? እንዴት ያለው ነገር ነው እባካችሁ..."

አባቴ የእናቴን መጠነኛ ማምረር ተከትሎ ማፌገፌግ ሲገባው በነገር ይገፋል...

"ለመሆኑ አፍሪካ ህብረቱ ሲቋቋም ተረግዛለች?" ይላል።

"አፍሪካዎትን እዛው እርስዎ ዘንድ ይፈልጉ፤ እኒህ አናጋሪ። እናቴ ጨለማ የመሰለች ጥቁር ነበረች ሲሉም አልነበር? ያልዘሩት የበቀለ ይመስል? እኔን ታፍሪካ ወድቃለች ሊሉኝ ነው? አሁን ሰው ቢሰማ ምን ይላል? እኚህ አናጋሪ..."

ቤተሰቡ ላይ እየረበበ የሚሄደው ስሜት የሚያቁነጠንጥ ሙቀት ይሰትብኛል። ሁሉንም እያፈራረቅሁ እመለከታለሁ። እንዲህ ያሉ

ጨዋታዎች ከአባቴ የሚተሰተሱት ጥሩ ስሜት ፈጥሮ የጠጅ ገንዘብ ለመጠየቅ እንደሆን እየቆየ ተገለፀልኝ። እናቴም ይሄ ገብቷታል።

"የጠጅ ሽንገው አልሳካ ሲል የእኛን ልብ ያወልቁታል" ትላለች።

አባቴ ከአፏ ነጠቅ አድርጎ "እንግሊዝ ልጆ የት ሄዳ? እርግጥ የምትሰጠኝ አያዛና ይሆናል እንጂ መታደሚያዬን አትነሳኝም።"

ስምረት የገንዘብ ነገር በወጪነት ሲነሳ ሽምቅቅ የሚያደርጋት አንዳች ነገር አለ። ገንዘብ በገቢነት ከመጣ ደግሞ፣ ፈታ፣ ፈገግ፣ ልምጥምጥ... ትላለች። ይሄን የሚያውቁ እህቶቼ እየተጎሻሸሙ ይልጥጥታል። ከገንዘብ ጋር የተያያዘ ባህሪዋ ለእነሱም ደርሷቸዋላ።

አባቴ ጡረታውን ተቀብሎ የሚያስረክበው ለእሷ ነው። ከዕለት የጠጅ ወጪው ገፋ አድርጎ ካስቀረ በልምምጥ...

"ነገ፣ ተነገወዲያ ጠጅ የለም? ምን ያደርግልሃል ይሄ ሁሉ? ተቀምጦ ለሌላ ቀንህ ቢሆን አይሻልም?..." ትለዋለች።

"እንግሊዝ እጅ ገብቶ ሊወጣ? ጣ!"

"ስጥቼህ አላውቅም? ጠይቀህ የከለከልኩህ ቀን አለ?..."

እናቴ ካለች ስረቅ እያደረገች በፍቅር ታያቸዋለች... "ትርፍ ብር ምን ያደርግልዎታል?"

"ጠጅ ቤት ገብቼ ገንዘብ አለቀ አላለቀ ስል አልገኝም፤ ጣ!"

"ተው እሺ..."

"ተያቸው፤ ደርሶ መኳንንት መሆን"

ይወጣል። ጡረታ የተቀበለ ቀን ከጠጅ ሽንገ መልስ ነገር ይኖራል። እቤት እስኪገባ፦

"ጠንቋይ እየተሉበኝ፣ ጣ! የጠንቋይ ልጅ እያሳደኩ ጣ!" ይላል። "ሶሻሊዝም ይባላል፤ እዚህ ደሞ የጠንቋይ በዝባዥ በአደባባይ ይፈንናል ጣ!"

ቡሬት የጠንቋይ ልጅ የሚለኝ እኔን እየመሰለኝ ገራ እጋባ ነበር። በኋላ እናቴ የማታፍርበትን የአውሊያ ገድል እያነሳች ፊት ለፊት ስትሞግተው በወርም፣ በሁለት ወርም እኔን ይዛ የምትሄድበትን የኦፋ-አቡኮ አውሊያ እየተች እንደሆነ ገባኝ።

"ሞላው ጉለሌ፣ ከሽጎሌ ሚዳ እስከ ጡረታ ድልድይ የሚያወጋውን ዛሬ ሰምተው ይትከነከኑበታል፤ ምን ይሁን እንግዲህ? ግደሉኝ፣ ንጠቱኝ፣ መና አስቀርልኝ... እያልኩ አልሄድ። በማገኛት ላይ በረከት አውርዶልኝ፣ ልጆቼን ባርክልኝ፣ ለእርስዎም ልብ ስጥልኝ ብል ጥፋቴ ተምን ላይ ነው? ኧረ ወዲያ ቂሶቹስ ቢሆኑ በደፈናው ከሚያወግዙ እዚሁ ከደብር በበትሎ ሲመጣላቸው አያግዱትም ኖሯል። ኦፋ አቡኮ ሩፋኤልን ተሳልሞ ሲመለስ መንገድ ከመልቀቅ ሌላ ፊቱን ያጠቆረ ቄስ አለ ወይ?..."

"ተይ እንጂ እንጓቼ ጣ! መምሬ ቀለመ አግኝተውኝ፣ በቃችሁ ቁረቡ ቢሉኝ..." ለመከናነብ እየተንደፋደፈ"

"እሳቸው ደሞ፣... ተኔም በላይ ቀራቢ የለም..."

"ለዚህስ እኔም ምስክር ነኝ ጣ! ያውም ባልሽ የሞተብሽ ቀራቢ ጣ! እሌጋ ከለየሽ'ኮ በዚህ ልጅ ዕድሜ..."

እናቴ ሀፍረቷ ይመጣባታል። "በልጅ ፊት ምን ሊሉ? እሰዎ እኮ የበረሃ ጅኒዎ... ኦ-ሆ-ሆ-ሆ...ይ"

"ትኩስ - ትኩሱን እያበላሽ ጣ! ጨው እየሞጀርሽ፣ ጣ! በርበሬው እንኳን ቢታገስልኝ..."

"ኧረ አንቱ ሰውዬ፣ ተነኩ እንዴ?... በዚህ ጠባይዎ ስጋወደሙ ቢቀበሉስ ለመለከፍ ካልሆነ... አይ በቃ እንግዲህ"

እናቴ ነገር ዘጋች፤ እሷ የዘጋችውን አባቴ ለመክፈት ሳይሞክርም። በተለይ እቤት ከገባ በኋላ በእሷ የበላይነት የሚተዳደር ወሬላቸው በእሷ ደምዳሚነት ይጠናቀቃል። የወሬ ዱካ ለማጥፋት በልጆቿ ላይ ትዕዛዝ ታበዛለች።

"እሺሻ፣ ሰምረት፣ እቴቴ፣ በሉ በጊዜ እንተኛ! ነገ በሌሊት ከላ እንወጣለን። ለትዳሟ ገበያ መደቡ ተራቆቷል..."

እናቴና ልጆቿ የጉልት ዕቃ ለማሟላት ከቤት የሚወጡት በሌሊት ነው። ሲሄዱ አይቻቸው ባላውቅም ቆይቼ የሰማሁት የቅጥል ስማቸው አይነ ሀሊና በጉልህ እንድመለከታቸው አረድቶኛል። "የቢዘን ፋርጎ" ይሏቸዋል እሉ የሩፋኤል ወመኔዎች። ቻይና ይሄን የሰማች ቀን ሄዳ ተደባድባ ተመለሰች።

"ምን ሆንሽ?" ስትባል፦

"ምን ሆንኩ?" የውጪ ውሎዋን ይዛ ወደ ቤት አትገባም።

"የአባቷን የበረሃ ጅኒ ወርሳ..." ትላለች እናቴ።

"ወንድ ሆነሽልኝ በሆነ ጣ!" ይላል እሱ።

ቻይና እራቷን ሳትበላ ተከናንባ ትተኛለች። ከቤተሰቡ ሁሉ ለአባቴና ለእኔ ታናሽ እህት ለአበዛሽ ብቻ ልዩ ፍቅር ያላት ይመስላል። አበዛሽ አይፀደ ፊቷን ቻይና ፊት ላይ ስትደቅን ቻይና አኩርፋ፦

"ምን ሆንሽ?" ትሊታለች።

አበዛሽ ትኩረት ሁሉ እኔ ላይ ሆኖ እንክብካቤ በማጣት የተጎዳች ናት። እኔ ተወልጄ ወላጆቼ ለዳግም ወንድ ልጅ ሞከር ቢያደርጉ ሴት ሆነችባቸው። "አበዛሽ" ብለው ወደ ጎን ገፉ አደረጓት። እቴቴም ሙሉ ትኩረቷ እኔ ላይ ሆኖ ችላ አለቻት። ስለዚህ በአካልም በመንፈስም የጫጨች ሆነች። ገና ትኩር ብለው ሲያዩዋት "ልቤን!" ትላለች። እውነትም ላብ አስምጧት ቅርት ትላለች። ውኃ! ውኃ! ውኃ!...

ቻይና ከቤተሰቡ ሁሉ እኔን የምትጠላኝ ይመስለኛል። ገና ስታየኝ "ሂሽ!" ትለኛለች! በፊት-በፊት የተመታሁ ያህል ጨኺ አለቅሳለሁ። እናቴ ልጆቿን እንጋግታ ትመጣባታለች። የቢዘን ፋርጎ ግብሩ በግላጭ ይቀርብልኛል። ቻይናን ማን ይዞ...

"እመለጠች? የሰንቆን ውቃቢ ደጅ የጠናሁበት ልጄን እናት እናቶን ብላ ልትገድልብኝ?"

እኔና ቻይና አይንና ናጫ ነን። የቃል ኪዳናዊ ወንድነቷ ዋጋ ያጣው እኔ ስወለድ ስለሆነ ሴትነቷ ተረጋግጦ ትዳር እስክትይዝ በጠላትነት እንቆያለን ስል አስባለሁ።

"ሂሽ! ሴታ ሴት!" ትለኛለች።

"ዋ-ይ" እላለሁ። የቢዘን ፋርጎ ያራውጣታል።

ይቅርታ፤ ቻይና ከአባታችንና ከትንሿ እህታችን በተጨማሪ ውሻችንንም ትወደዋለች። ፀባዩ ታይቶ "ገልጆ" ተብሏል። ሰንሰል ስር መሬት አጎድጉዶ ይኖራል። እንደተፈጥሮ ምስጢር የሚቆጠር እንደሆነ እንጃ እንጂ ሰንሰሉ ሆዱን እያሰፋ፣ ጥላውን እያንሰራፋ ጥሩ የውሻ ቤት ወጥቶታል። ቻይና ገልጆንም እንደተገፋ ቀጥራው ይሆናል የምትወደው።

"ገልጆ - ሠላም ነው?" ትለዋለች።

ገልጃጃ ሰላምታ ያቀርብላታል።

እኔን ቻይና እንድትወደኝ እንደአባቴ በእናቴ መጨቆን፣ እንደእህቴ በእናቴ መዘንጋት፣ እንደ ገልጆ፣ የማይታሰብለት ገልጃጃ መሆን አለብኝ? እንዳንዴ አባቴ በሚጠራት "መቀጬ" እያልኩ አበሽቃታለሁ።

"ሂሽ! ሴታ ሴት" ትለኛለች።

# ፪

## እኔ፣ አፋ አቡኮ እና አባ ኪሮስ

ቻይና "ሴታ ሴት" ስትለኝ ጭንቅላቴ ውስጥ የሚመጣልኝ የእሷ ንፅፅር ነው። ስውነቷን በስፖርት ስላወነደች፣ ካራቴ ስለምትማር፣ ሚዳ ስለምትውል፣ ስለምትደባደብ፣ ቤተሰቡን ስለምታስጨንቅ…

…እኔ እነዚህን ሁሉ አላደርግም። በተለይ ከቤቴ ውጭ ለአፍታ እንኳ ከቆየሁ ዋስትና አይሰማኝም። ከጉድጓድ ውጭ እንደተገኘች አይጥ ለሁሉ ዱላ የተጋለጥኩ ይመስለኛል። ቤቴ ስገባ ንጉስ ነኝ። እንደ ጠቢቡ እና ንጉሱ ያለ ተንከባካቢ አልወልም።

ቤታችን ሽንጣም ነው። በጭቃና በጨፈቃ የተዋቀረ አውቶቡስ ይመስላል። ዘወትር ተአምርና ገድል የሚሆንብኝ ነገር እዚህ ሞተሩ የወረደ ስንካላ የአፈር መኪና ውስጥ አስር ሰው የመኖሩ ጉዳይ ነው። እኔ፣ አባቴና ቻይና ቆጥ መሳይ የአጠና አልጋዎች ተሰልፈው ቤቱን ድንገተኛ ክፍል አስመስለውታል። አልጋዎቹ ለቤቱ እንዲመቹ ተደርጎ በአናጢ የተዋቀሩ ናቸው። ከሦስታችን ውጭ እናቴን ጨምሮ ሴቶቹ የት፣ እንዴት እንዳደሩ ማወቅ አልችልም። አምሽተው ይተኛሉ። በማለዳ ይነሳሉ። ስገምት ሴቶቹ የሚተኙት እንደአውቶቡስ ተሳፋሪ በመደዳ ተቀምጠው ነው። ወይም መቀመጫ እንደጣ የአውቶቡስ ተሳፋሪ የማሪያውን ማገር በመያዝ ቆመው እየተወዛወዙ ያድሩ ይሆናል። አላውቅም።

ይሁንና ቤታችን በሴቶቹ ወግ-ወጉን ያያል። ሳሎን፣ መኝታ ቤት እና ዕቃ ቤት ተብሎ ተከፋፍሏል። ለወሬ እንዲመች ሳይሆን አይቀርም። እናቴ ጉልት ተቀምጣ ልጆቿን ስትልክ ድምጿን ከፍ ታደርግና

"እሸሻ መዘፍዘፊያውን አምጪ፣ ድንቹን ሳለቅልቀው" ትላለች።

"ምኑጋ ነው? ሳሎን ነው?"

"ሳሎን መዘፍዘፊያ ይቀመጣል? የሚዘፈዝፍ ይዘፍዝፍሽ"

"መኝታ ቤት?"

"መቃብር ያስተኛሽ እቴ! ዕቃ ቤት ነው እንጂ…"

ሳቁ ይመጣል። ቤታችን በሀሳብ ተከፋፍላለች እንጂ በአምሳል አንድ ነች። የሳሎን፣ የመኝታ ቤትና የዕቃ ቤት ድንበር የዐናው እንደኪክሮስና ኪንትሮስ በሀሳብ መስመር እንጂ የቶመ፣ ወይም የተጋረደ ነገር የለበትም። እዚች የጭቃ አውቶቡስ ውስጥ በኋላ በር በኩል ስገባ ተሳፋሪ በግምት እስከ ትኬት ቆራጪ ድረስ ሳሎን መሆኑ ነው። ከትኬት ቆራጪ እስከመካከለኛው በር ድረስ መኝታ ቤት ሲሆን ከዚያ ወዲያ እስከ ሾፌሩ ዕቃ ቤት ነው።

በእኛ የጭቃ አውቶቡስ ተመስገን ተመስገን ከማለት አልፈን በሰፈርተኛው ላይ እንኩራራለን። ምክንያቱም የአንዳንዱ ቤት ሚኒባስ ነዋ! ኧረ ሞተር ብስክሌት የሚያክልም ቤት አለ እሉ። ባልና ሚስት አግዳሚ ወንበር ላይ ፊትና ኋላ ተፈናጥጠው ሲያድሩ እየታየኝ በእኛ ቤት ኩራቱን እፋፍሚአለሁ።

ቤታችን ከመጥበቡ (እንደ አንተ እንደ እንቺ እያልኩት ነው) አረግራጊነቱ የቤተሰቡ ስጋት ነው። አውሎ ነፋስ ቀርቶ የአባቱ ሞክሼ ቢዘን ከበስተኋላ ሆኖ ሲጮህ መናጥ ይቀናዋል።

"ናቅፋን ሳታይ ወንድ ነኝ አትበይ!"

ነቅነቅ...

"ባሬቱን ሳታይ ወንድነኝ አትበይ!"

ቃ-ቃ-ቃ-ቃ...

"ተሰነይን ሳያሳይሽ ባልም የለሽ!"

ጨ-ጨ-ጨ-ጨ...

አባቱ ካለ "ይሄ ቤት ቋሚውን ምሰጥ በልቶታል ጣ!" ይላል። "እንደው አኮቋኩቦ ነው ያለው ጣ!"

ሌላው ቀርቶ የእድር ለፋፊዋ እማማ አጀቡሽ ግድግዳችን ሥር ቆመው ጡሩንባቸውን ሲለቁት ቤታችን ዝናብ እንዳካፋበት ውሻ ይርገፈገፋል።

"የፈጣሪ ያለህ፤ ሴት እንዲህ ይነፋል? ጣ!"

"የሩፋኤል አካባቢ መረዳጃ እድር..." አፋቸውም ከጡሩንባው በላይ ቧሬ ነው። ቤታችን፦

ነቅ - ነቅ - ነቅ... በማለት አፀፋውን ይመልሳል።

መጀመሪያስ ጡሩንባ የመንፋት ዝንባሌ እንዴት አሳዩ? እንደሌሎቹ ሴቶች ጉልት አይነግዱም? ልብስ አያጥቡም? ጠላ አይጠምቁም?...

ምን ሴጣን ጡሩንባ አስመለከታቸው? የእድሩ ስፋራ "ወልዴ ጡሩንባ" ነበር። ታዲያ የእማማ አጀቡሽ ወልዴን መተካት የጤና ነው? ወልዴ ጡሩንባ መስፈፊያውን በአራስ ልጅ ደንብ በመታቀፊያ ጠቅልሎ "አደራ በምድር አደራ በሰማይ፤ ይሄ ጡሩንባ የሚነፋው ቢጠፋ በሰማዩ ጌታ ፊት አፋረድሻለሁ" ብሏቸው ይሆን?...

እማማ አጀቡሽ ሲሞቱ የጡሩምባው ተረካቢ የግድ የግድ ቻይና መሆን አለባት። ያኔ ቻይና ጡሩንባውን ስትነፋ ቤታችን እንደባርኔጣ አየር ላይ ተንሳፎ ክሽህ ሆኗል። ሜዳ በታች ይገኛል። በቻይና ሳላግጥ ውስጣዊ እርካታ ተሰማኝና ፈገግ አልኩ። ግን በድስቱ አህቶቼ ይወዱኝ የለም? ለምን የእንደ ቻይና ጥላቻ እንዲህ ይቀጠቀጠኛል? እነሱ የማያደርጉልኝ እንዱንም ቻይና አትሞክረውም። ልብሴን ተሻምተው ያጥቡልኛል፤ ጭኖቻቸው ላይ ተቻቹ እራሴን ለመዳበስ ይሻሙልኛል፤ ስለኔ የሚያደርጉትን ሩብ እርስ በእርስ አያደርጉትም። እንደ የእኔን ልብስ ከራሷ ጋር ሲታጥብ ቤሳዋ እንዴት ክኒቱራ እንዲን ከደባለቀችው-

"የሞኝ ጉልበት ማድረቅ ነው?" ብላ ታስትንጥረዋለች። የእኔን ግን እንደ ያጠበችውን ሲሰኛዋ አልጠራም ብላ ትደግመዋለች። ኸረ ይሄ ሁሉ ቀርቶ የሽሚያ መሳሚቸው አይበቃኝም? የሁሉም አሳሳም ተመሳሳይ ነው። ጉንጬን አፋቸው ውስጥ ይከቱትና ምጥጥ አድርገው ሲለቁት "እምቧ" የሚለው ድምፅ ትልቅ ጭብጨባ ሆኖ ከሩፋኤል ግንብ ጋር ይጋጭና የገደል ማሚቶው ተመልሶ አቤት ይገባል። "እምቧ፣ እምቧ፣ እምቧ..."

እኔ ጉንጬ ላይ ልቤ ይወተፍና ይነዝረኛል። በቀዳዬ ቀዳዶች ደሜ ያቸፈቸፈ ያህል ይቀጠቅጠኛል፤ እንዳንዴ አስቀሳለሁ። አህቶቼ ግን ይሄ አሳሳም ያስፈልጋቸዋል፤ ያረካቸዋል፤ ሱስ ሆኖባቸዋል... እንደ የቤላዋን አሳሳም ብትንቅፉም እስካድግ ድረስ ተነጋግረው አልተውኝም።

"እምቧ"

እንቺ? ልትበይው ነው እንዴ?

"እምቧ" እሷ መልሳ

ካልፈለገ ለምን ትስሙታላችሁ? ና ልጄ! እነዚህ ቡዶች፣ ትፉበት "እምቧ" እሷ ደሞ። የፈዛዛዋንና የደካማዋን የአበባሽን አሳሳም'ኳ መቋቋም ይሳነኝ ነበር። አለምን የሚያጠባት ጦርነት ሳይሆን ፍቅር ነው። መሸሸጊያ ይጠፋኛል። ቢጨንቀኝ ሰማ የጠገበችኝን ከለላ አድርጌ ከተጨማሪ መሳም እጠለላለሁ። ሲስሙኝ ቀርቶ ሲምሉብኝ እንኳ በሽሚያ ነው።

"ታስ ይሙት!"

ታስ የቤት ስሜ ነው። እኔ ስወለድ አባቴ የጋሽ ተገኜን ጠበንጃ ገፍሮ ከተኮሰ በኋላ፤ አብዮት ጠባቂዎች ተኩሱን ሰምተው ከመምጣታቸው አስቀድሞ ወደ ቤት ገባ፤ እሳመኑም፡-

"ወንድ ነው አላችሁኝ? ጣ!"

"እዎ" አለች እናቴ ከልጅ ምጥ በላይ የደስታ ምጥ ጨክኖባት ተዳክማ

"ተሳስታችሁ እንዳይሆን ያስተኮሳችሁኝ ጣ!"

"እራስዎ አያዩትም?"

"አዬ መቼስ ሰው ካልሞተ የምኖቱን አያጣም ጣ! ሰው ካለ ጣ! ስሙን ‹ታስሰው› ብዬዋለሁ" አለ።

"ታስሰው" ተባልኩ። ሲያሳጥሩት "ታሰ" ይሉኛል። ሲያቆላምጡኝ። "ታሴ"

"ታስ ይሙት!" ይላሉ።

እናቴ ተቃወመች "ክቅዱስ እስክ አርኩስ የተማፀንኩበትን ልጄን፤ ምነው? መማያ አጣችሁ? አባታችሁ እሱ አይደለም ወይ? ኧረ ባፋችሁ ውኃ ይሙላ እቴ! የምን ይሙት፣ ይሙት ነው?...."

ከዚህም በኋላ በእኔ መማል አልቀረም። በአባታቸው ይምሉና መተማመን ሲያቅታቸው "እስቲ ታስ ይሙት በይ?" ይባባላሉ።

"ታስ ይሙት!" ካለች እውነት ነው። እልምልም ካለች ውሸት ነው። እኛ ቤት በእኔ ስም በውሸት የምትምል ብቸኛዋ እህቴ ቻይና ናት። በማሽፍ ፊቷን አጨማዳ

"ሂሽ! ሴታ ሴቱ ይሙት!" ትለኛለች።

ጨኪ አስቅሳለሁ። ቀዳሚዋ እቴቱ ናት፤ የግንባሯ ጠባሳ የዚህ ጠባይዋ ሽልማት ሳይሆን አይቀርም። ከእቴቱ ቀጥሎ ፋርጎው ይቀጣጠላል። ቻይና ግን የለችም። እናቴ ካለች፡-

"አመለጠች? ይቺ ጠባ ከእኔ ነው ከእሱ? ሰንቴን ዳገት ፋጭሬ ያገኘሁትን ልጅ ትግደለው?..."

እናቴ ስለእኔ መፋጨሯ ያበቃ ይምስላት እንጂ እንደቀጠለ ነው። ትንሽ ካተኮሰኝ ልብሴን ታወልቅና ገላዬን በሳንቲም አሻሽታ ረከቦት ላይ ታስቀምጠዋለች፤ ለአርኩሱ መንፈስ መሆኑ ነው። በማለዳ ጧፍ ገዝታ

ሩፋኤል ትሄዳለች ለቅዱሱ መንፈስ መሆኑ ነው። ሎሚ፣ ኑግ የተቀባ ቂጣ፣ የማሽላ ቆሎ... ከሆነ የእርኩስ መንፈስ መሆኑ ነው። የቅዳሴ ጠበል፣ እምነት፣ ሚሮን... ከሆነ የቅዱስ መንፈስ መሆኑ ነው...

...የእናቴ ስለኒ መፋጨር አሁንም አላባራም። ወደፊትም እንጃ፣ በግራዋ መቃጠብ፣ በድኒ መቃጠን፣ በርሚጦ መቃጠር... ከብዙ ሞት እንደምትቃደገኝ ታምናለች። ገላዬ የቃበሰበት ሳንቲም ረከቦቱን ሲሞላ ጥቂት ቀርቶታል። የሳንቲሞቹን አተላ የጠጣ ክብ ፊታቸውን ስመለከት ዳፋዎቼን ሁሉ እንዳቀው ይዘው የሚሰቃዩ ይመስለኛል። ደግነቱ ቻይና እየሰረቀች አመናምናቸዋለች። በቻይና ሌብነት ውስጤን ደስ ይለዋል። ገመምተኞቹ ሳንቲሞች በገመምተኛ ጎናቸው ቢሆንም ገበያ መዋል እንዲችሉ አድርጋቸዋለች። እናቴ ግን ትደነግጣለች...

"ያቺ ቻይና ነች፣ ቀልብሽ ይገፈፍ!" ትልና ለአባቴ ስሞታ ታቀርባለች። አባቴ ከደፈረ...

"እኔም ባገኘሁት ጣ! የጠንቋይ ልጅ ከሚያደግበት ጠጅ በጠጣሁበት ነበር ጣ! ለሩፋኤል አትሰጪም? የስንት ዲያቆን ደሞዝ በሆነ ነበር ጣ!" ለጠጁ የጓጓ ይመስል አፉን በምላሱ ያባብሳል።

"የበረሃ ጅኒዎችን አስከትለው ደግ፣ ደጉን አያናግርዎትም..." አይኗን ለነገር ሰቃጨነቁርበት ነገሩን በክንብንብ እያጀበ ጣል ያደርጋል።

"ዶሮሽን እያዞርሽ ከመጣል ሰርተሽ ብታበይን ደግ ነበርጣ! ቹቹ ጅሉ ያደገው አንቺ እያዞርሽ የጣልሽውን ዶሮ እናቱ ሰርታ እያበላችው ነውጣ! በዚህ ወገን የጠንቋይ ልጅ፣ በዚያ ደሞ የደፋሯን ልጅ ሰንቶን አሳድጋለሁ እኔ? ጣ!"

ቹቹ ጅሉና እናቱ ከእኛ ቤት ባሻገር፣ እግር ከሳጨት መንገድ ዳር ይኖራሉ። ከጥቁር ጣውላ የተቀረፀች የምትመስለው እናት ጉጥ አይኗን እያጉረጠረጠች ቀስ እያለ አቀርቅሮ የሚሄድ ልጇን በሯ ላይ እስክታስቀምጥ ብቻ ረጋ የምትል ቀዠቃዣ ሴት ናት። ስትናገር አፏ ያነፋራቸው ነጭ ማሽላ የመሰሉ ምራቆች ይፈነጣጠራሉ። ቹቹ የእናቱ ተቃራኒ በሽታ ለክፎታል። ሲያወራ፣ ብዙ "ደሞ"ዎች ይጠቀማል።

"ደሞ፣ ደሞ፣ ደሞ... ዶሮ በልቻለሁ" ይላል። እናቴ በመንቀዥቀዥ አይን እንዳትገባ እጅግ የሚዘገይ ልጅ የሰጣት ይመስለኛል።

"ደሞ፣ ደሞ፣ ደሞ... ዶሮው የእናንተ ነው"

እናቴ የሰው ዶሮ በላሁ ብላ ሀፍረትም ይሉኝታም አታውቅም። እንደውም ከፊንዲሻ የተበጁ ስድቦቿን እናቱ ላይ ታንጣጣለች። ከፍጥነቷ የተነሳ

ቃላቶቿ እየተንገበገቡ ስለሚፈናጠሩ የምትለው በቀጡ አይሰማኝም። እንደውም እናቴ ናት የእሷን ዶሮ የበላች የምትመስለው። ዝም ብላ ወደ ጉልቷ፣ ዝም ብላ ወደቤቷ...

እናቴ እኔን ታስጠነቅቀኛለች።

"እዚች ጠሰኛ ደጅ ትርው እንዳትል..." ትለኛለች "ትርው" ስትለኝ ወፍ የሆንኩ ይመስለኛል። በውሻ "ቤት" በኩል የሰንሰል ቅጠል ገልጩ ስመለከት ቹቹ እንዳቀረቀረ ቢሆንም ያየኛል። ቀስ ብሎ እናቴ ካስቀመጠችው ወንበር ላይ ተነስቶ ቀስ እያለ ይመጣል። ሱሪው የትልቅ ሰው ሆኖ ከጡቱ ጀምሮ እስኪሽበሽብ ጠብቆ ይታጠቀዋል።

"ደሞ፣ ደሞ፣ ደሞ... እናቴ ደሞ፣ እንኳን ዶሮዋን፣ ደሞ ልጇንም እበላዋለሁ ብላለች ደሞ"

የእናቴ ማስጠንቀቂያ ከንቱ ስጋቷ የፈጠረው ይመስለኝ ነበር። ውሸት የማያውቀው ቹቹ ሲነግረኝ አንድ ቀን እንደዶሮው የገባሁበት ጠፍቶ በማፋጭ ወጥነት አካባቢውን የማጥነው ሆኖ ተሰማኝ። የቹቹን እናት ፈራኋት። በጥቁር ጣውላ ፊቷ ላይ የሚያጉረጠርጠው ጉጥ መሰል አይኗ እንደ ረጅም እጅ እንቀ ወደሷ የሚጎትተኝ መሰሎ ተሰማኝ። ትልቅነት እየተሰማኝ የመጣ ቢሆንም ይሄን አስፈሪ ትእይንት መቋቋም ተሳነኝ።

እናቴ ጠየቀችኝ፣ ነገርኳት፣ ለመጀመሪያ ጊዜ እኔን ተቆጣች።

"እሷ ደጅ ትርው እንዳትል አላልኩም ወይ?"

"እኔ አልሄድኩም"

"እ-ሀ-ሳ?"

"ቹቹ መጥቶ ነው"

ባልጠበኩት ሁኔታ እናቴ ዝም አለች፤ ባልጠበኩት ሁኔታ ተረጋግታ አየኋት። አርኩሰና ቅዱስ ደጃፍ ሙጥኝ ያለችው ቹቹና እናቴ አርደው እስኪበሉኝ እንዳልሞትባት ነበር?

ዝምብላ ቤት ገባች፣ ዝም ብላ ረከቦቷን አወጣች፣ ሳንቲሞች ቢጎድሉም ቻይናን አልተራገመችም፣ ዝም ብላ ጀበናዋን አወጣች፣ ዝም ብላ እሳት አቀጣጠለች፣ ዝም ብላ...

... ለምን?

"ይሄን ለእህቶችህ አትንገር"

ዝም ብለህ የመበላት ዕዳህን ገፍግፍ ማለቷ ይሆን?

## ፱

## እኔ፣ ሁኔታዬና ወጥ የመሆን ሽሽት

ውጭውን ፈራሁ፤ ቹቹን ባየሁት ቁጥር በሩ ላይ ቁጭ ብሎ በመጎምጀት አፉን የሚያጣጥም ይመስለኛል። የአባቴ ብሂል ወደቹቹ ተጋብቶ ሲያወራ፡-

“ደሞ፤ ጣ፤ ደሞ፤ ጣ፤ ደሞ...” ሳይል አይቀርም እያልኩ አሰባስሁ። እናቴ እንደ ዶሮ አፍና ክሽን ያለ ወጥ ሰርታኝ ይሄን የተሽበሸበ ሱሪውን የምወጥርበት ጊዜ እሩቅ መስሎ አልታይህ ይለኛል። በተለይ ቤት ማንም በሌለ ሰዓት ሰጋቴ ያይልና ወደ እናቴ ጉልት አፈገፍጋለሁ።

“ቤቱን ጥለህ መጣህ?... ለመሆኑ መለስ አድርገኸዋል?... ሄድ'ክ ዘጋው? ያቺ ሉጢ ገብታ ታንጎዳጉድ? በል ሂድ!...”

ወጥ ተሰርቼ እንድበላ ነገሮችን የምታመቻች መስሎ ይታየኛል። እናቴ ምን ነክቷታል?

“አፈራለሁ”

“አሁን'ኮ ትልቅ ነህ፤ አስራ አራት አመት ሆኖሃል”

ለእርድ ደርሰሃል እንደምትል ሆኖ ይተረጎምልኛል። እየቀፈፈኝ በሩን መለስ ሳደርግ እሄዳለሁ። ዓለምን የሚያጠባት ጠርነትም ሆነ ፍቅር አይደለም፤ ፍርሃት ነው። ከለላ የሌለበት አውላላ ላይ በጅቦች የተከበብኩ መስሎ ይሰማኛል። መኩብለያ ቦታ ሳያስተርፉ ጅቦች ተቸምችመው...

...ህልሜ ሁሉ በቹቹና በእናቴ ተሞላ። ደሞ ምራቅ፤ ደሞ ምራቅ... በላብ ተዘፍቄ እነቃለሁ። ቀን ከቤት ይልቅ ውጭ-ውጭውን እላለሁ። ከጡረታ ድልድይ ወጥቼ በእናቴ ጉልት ጀርባ አድርጌ ወደለመድኩት ትምህርት ቤት እሄዳለሁ። አባቴ ሁነኛው ጠጅ ቤት አይጠፋምና እንዳያገኘኝ እየተጠነቀቅኩ እልፋለሁ። ጠጪዎቹ እ-ም-ም-ም የሚል የንብ ድምፅ ያወጣሉ። በሩ ላይ የማር ሰፈፍ ተሰጥቷል። ጠጪዎቹ

ድምፃቸውን እና ማራቸውን የቀሟቸው ንቦች በፀጥታ ስፈፉ ላይ ያንገብባሉ።

"አባቴ ማሩ አፉን እያጣበቀበት ለማላቀቅ ሲሞክር ይሆን ጣ የሚልበት?" የሚል ሀሳብ መጣብኝና ፈገግ አልኩ።

ሩፋኤል እንደኛ ቤት ጭር አይልም። የሰው ያለህ ብሎ አያዛጋም፤ የተከፈተ አፉ ቹቹንና አናቱን አይጋብዝም። መንገደኞቹ ባብዛኛው ያውቁኛል።

"የእንጓች ልጅ፣ የት ትሄድ? ዛሬስ አናትህ ለቀቀችህ?" ይላሉ እናቶች።

"የቢዘን ጎረምሳ፣ በተሲአት ቤትህ ቁጭ አትልም?" አባቶች

እናቶች የአባቶችን፣ አባቶች የእናቶችን አውቀና የሚነፍግ መሰሎ ታየኝ። አጠጭ ሳለሁ ትንሽም ፍርሃት የተሰማኝ የብሩ ወንዝን ጥግ ይዤ ስጓዝ ነው። እዚህ ሆኜ የሼህ ሆጀሌ መስኪድ ቁልጭ ብሎ ይታየኛል። ቀሰም አምባ ትምህርት ቤት ከመስኪዱ ብዙም አይርቅ። ትምህርት ቤታችን ባለአንድ ደርብ የጭቃ መርከብ ይመስላል። ሼህ ሆጀሌ እንጨት ከአገራቸው ከቤንሻንጉል አስጭነው፣ እንቁላል እየጨመሩ ጭቃውን አስቦክተው የሰሩት ቤተመንግሥታቸው እንደሆነ የህብረተሰብ ሳይንስ መምህራችን ነግረውናል።

"ፈተና ላይ ይመጣል፣ ልብ አርጉ፣ እዚህ የትምህርት ቤታችሁ ጓሮ የሚኖሩት ፓስቱ የሚሸጡላችሁ የሼህ ሆጀሌ ዘመዶችና አገልጋዮች ናቸው። ምንድን ናቸው?"

"ዘመዶችና አገልጋዮች"

"ጥሩ፣ ሼህ ሆጀሌ በምዕራብ ኢትዮጵያ በኩል የኢምፔሪያሊስቷን እንግሊዝ ጨና ተቋቁመው ቤኒሻንጉልን ለአፄ ምኒልክ ያስረከቡ ጀግና ኢትዮጵያዊ ናቸው፣ ምንድን ናቸው?"

"ጀግና ኢትዮጵያዊ"

"ማን?"

"ሼህ ሆጀሌ"

"ጥሩ፣ ሽጎሌ ብትይ..." ብለው ጠቋሚ ጣታቸውን አየር ላይ እያሽከረከሩ ክብ ይሰራሉ "ምን ታገኛለሽ?"

"ዜሮ"

"ጥሩ፣ በአብዮታዊት ኢትዮጵያ ብሔርን ማንቋሸሺያ ቃላት ቦታ የላቸውም፤ ምን የላቸውም?"

"ቦታ!"

"ጥሩ..."

የህብረተሰብ ሳይንስ መምህራችን ለሼህ ሆጀሌ በእጅጉ ስለሚቀረቀሩ የቅርብ ዘመዳቸው ይመስሉኝ ነበር። የቤተሰብ ታሪክ እንዳይጠፋ በህብረተሰብ ሳይንስ በኩል የሚያስጨንቁን፤ እኔም ትምህርቴን ጨርሼ መምህር ስሆን የአባቴን ታሪክ ህብረተሰብ ሳይንስ ውስጥ አስገብቼ አስተምራለሁ ስል የረጅም ጊዜ ዕቅድ እይዛለሁ።

"ጥሩ፣ ወታደር ብዜን አርባ አመት አገልግሎ፣ ሃያ አመት ተዋግቶ ምን አገኘ?"

"ምንም!"

"ጥሩ፣ ከዚህ ሁሉ በኋላ ጡረታ ሲወጣ ምን ማዕረግ ነበረው?"

"ምንም!"

"ጥሩ፣ ወታደር ብዜን በሰሜን ኢትዮጵያ በኩል የገንጣይና አስገንጣይ ጪና ተቋቁሞ ኤርትራን ለጓድ መንግሥቱ ያስረከበ ተራ ኢትዮጵያዊ ነው። ምንድን ነው?"

"ተራ ኢትዮጵያዊ"

"ማን?"

"ወታደር ብዜን"

"ጥሩ፣ ቢዘን ብትይ..." ብዬ ጠቋሚ ጣቴን አየር ላይ ዜሮ እሰራታለሁ። "ምን ታገኛለሽ?"

"ዜሮ"

"ጥሩ"

"ቲቸር፤ ቢዘን ካልሆነ ምን ብለን እንመልስ?"

"ብዜን፤ ደብረ-ብዜን ስለተወሰደ ነው፤ የት ተወሰደ?"

"ደብረ ብዜን"

"ጥሩ፤ ቢዘን ሲባል ይናደድ ነበር፤ ስልችቶት ቢተውም ውስጥ ውስጡን መከፋቱ አይቀርም፤ ምን ማለቱን?"

"መከፋቱ"

"ጥሩ..."

ቀለም አምባ ትምህርት ቤት የደከመው ይመስላል። የአለም ምስጦች የገነቡት ግዙፍ ኩይሳ። በሮቹ የግድግዳውን ጠባይ ተጋርተው ውስጠ ድፍን አስመስለውታል፤ መስኮቶቹ በጣውላ ፍርግርግ ታሽገዋል። እሽጋው ውስጥ ሆነው የተዘጋባቸው ሰው በላ ወንበዴዎች መስኮቶቹን ከፍተው እንዳይወጡ እንጂ ተማሪዎች እንዳይከፍቱት አይመስልም። ክፍል ውስጥ ሆነው የተዘጋባቸው ሰዎች እንዳሉ ባሰብ ነፍሴን ጨነቃት። ጭርታው የቹቹንና የእናቱን ፍርሃት ቀሰቀሰብኝ። ወደ ሩፋኤል፡-

"የጽርሃም አርያም ቅዱስ ሩፋኤል ቤተ-ክርስቲያን" የሚል ፅሁፍ በቀለት ብረት ተሰቅሏል። ፊደል የቆጠርኩት እዚህ አፀድ ውስጥ ነው። ቁጡው መምህር ሰረገላ እኔ በሽተኛ መሆኔ በእናቴ ስለተነገራቸው ባይመቱኝም ጭካኔያቸው በሌሎች ልጆች ላይ ሲፈፀም ማየቴ ብቻ መጥፎ ቅጣት ይሆንብኝ ነበር። አንዳንዴ አለቅሳለሁ።

"አንተ ደሞ ምን ሆንህ? አለቀስክ? ቅብጠት መሆኑ ነው? የማይመቱት ልጅ አሉ..." ትኩስ አይናቸው ገላዬን ሲልሰኝ ይታወቀኝ ነበር።

መምህር ሰረገላ የሚያስተምሩበት ታዛ ባዶ ነበር። ልጆቹ ለምሳ ወደየቤታቸው መሄዳቸውን ማሰቤ ረሃብ ቢቀሰቅስብኝም የእነቹቹ ፍርሃት እንድችለው አስገደደኝ።

ቤተክርስቲያኑ አፀድ ውስጥ አንዳንድ ሰዎች ብቻ በፀሎት ተጠምደው ይታያሉ። ጧፍ የያዙ ሴቶች የመስኮቱ ደፍ ላይ አስቀምጠው እዚያው ለፀሎት ይንበረከካሉ። ፀጥታው እንደበፊቱ

የመረጋጋት ምንጭ አልሆንልህ አለኝ። ፍርሃት፤ የቹቹ እናት መጥለፊያ ሽምቀቅ መሂጃዬን ሁሉ ሞልቶት እግር ማሳረፊያ ሳጣ ይታሰበኛል። ከሙብላት በላይ፤ የመበላት ሥጋት እንዲከፋ ገባኝ።

ወደ እናቴ ጉልት አመራሁ...

...ጡረታ ድልድይ ላይ ቢተሰብ ያልፈለጋቸው ሁለት አረጋውያን ብቻ ተቀምጠዋል። የጡረታ ሰፈር ኪሳ በጡረተኞች ሲጠበቅ ይመስላል። ጡረታ ሰፈርን ጠላት ሲጠር ቢመጣ የሚያጋጥመው መከላከል "በህግ አምላክ!" ብቻ ይሆናል እያልኩ አስባለሁ።

እናቴ ጉልት ስደርስ እንደጠተርው ድስት ጥዳ ሲንተከተክ አየሁ። ነመንም ሆነ ድንች፣ ሽሮም ሆነ ምስር እዚያው ጉልቷ ጀርባ ትሠራለች። የአደባባይ ወጧ መንገደኛውን ሁሉ እንደቻይና ቢያምስም ለማንም አታቀምስም። "የልጆች ነው" ትላለች።

"የአንጓች ወጥ አወደ" ይባልላታል።

ስደርስ በትዝብት አየችኝ። ትዝብቷ "እስካሁን አልተበላህም? ቀው አንተ ልጅ አታብዛው" የሚል ሆኖ ተተረጎመልኝ። እናቴ ትልቅ ፍርሃት እያሳደረችብኝ ስትመጣ ታወቀኝ።

"የት ሄደህ ነው? በተሲአት እህቶችህን ታንከራትታቸው?" አለችኝ።

ዝም ብለህ በእነቹቹ ብትበላ ምን አለ ልትለኝ ይሆን?

"ዝም ብለህ አቤት ብትቀመጥ ምናለ?"

ያው ነው፤ ያሰብኩትና እናቴ የተጠቀመችበት ቃል ሲገጣጠም ደነገጥኩ።

"በእነቹቹ እንድበላልሽ ፈልገሻል?" አልኳት።

ክው ብላ ቀረች። አባቴ ላይ ለዐብ የምታጨነቁርበትን አይኗን ጠበኩ። አጨንቁራለች፤ ግን ሌላ አይነት ማጨንቁር ነው። ዐብ የለበትም፤ ታዲያ ምን?

"ሊበሉኝ ነው ስል ደስ ብሎሻል" ብዬ እንባዬ ተዘረገፈ። እፈፍ ብላ አቀፈችኝ። ዐሐይ፤ ዐሐይ ትሽታለች።

## ፮

## እኔ፣ ቹቹና የጡሩንባው ምትሃት

እናቴ ሬጋ ብላ እንደትልቅ ሰው ለመጀመሪያ ጊዜ አናገረችኝ።

"አሁን እነዚህ ተቀጥር ትጥሬው ትፈራቸው? ዶሮውንም ይዘው የሚበሉት በሽተኛ ስለሆነ እራሱን ስላልጠበቀ ነው። ለማንኛውም የእነሱ መሳው ቀላል ነው።"

በነጋታው እማማ አጀቡሽ የማነፋትን ጡሩንባ ይዛ መጣች። እንጀራ በሉስ ቀን ስትገዛ እንደምታደርገው በቀሚሷ ከለል አድርጋው ስለነበር ብቅ ሲል ደነገጥኩ። የዐበኛ በሬ ቀንድ ይመስላል። ከቅርብ አይቼው አላውቅም፣ ጉርብርብ መዳብ ነው። የፈንጣጣ ውግ የመሰሉ ጉድጓዶቹ በእድፍ ጠቁረዋል። አፉ በክርና በፕላስተር ተጠቅልሎ ወፍሯል። ለቻይና የተመኘሁት የእድር ነፊነት ውርስ እኔ ላይ አረፈ?

"እድር ነፊ ልሆን?" ስላት እናቴ ከት ብላ ሳቀች። እናቴን እሚልቹ አላውቃትም? ጥርሷ ጉራማይሌ የተነቀሰ ነው። ይሄንን እኔ ብቻ ሳልሆን አባቴም የሚያውቀው አይመስለኝም። እንዲህ ስትስቅ አይቼአትም አላውቅም።

"ለጠላትህም አልመኘው፤ ዝም ብለህ እንደ ጠበንጃ አንግተህ ቹቹን ታየው።"

ግር አለኝ። የቅዱስ ወይም የእርኩስ መንፈስ ምስጢር እዚህ ጡሩንባ ውስጥ አለ? ምን ጉድ ነው? እያመነታሁ እናቴ ትከሻዬ ላይ አነገተችልኝ። ወጣሁ። ቹቹ በሩ ላይ አቀርቅሮ ተቀምጧል። በሰንሰሉ ላይ ተንጠራርቼ አየሁት። ቀና ሳይል አየኝ፤ መንፈሳዊ ማይክሮስኮፕ አለው እንዴ?

ቹቹ ድንገት መረጋጋቱና ቀስስተኛ እንቅስቃሴው ተለወጠ፤ በኃይል ተንቀጠቀጠ። "እ-እ-እ-እ..." በብዙ ውሾች የተከበበ ይመስል መግቢያ ጠፋው። ድምፁ እየጨመረ ሄዶ ጆሮዎቼን በሁለት መዳፎቼ ደፈኜ እየተርበተበተ ሬጥኩ።

የተሳገች እናቱ ወጣች። ጥቁር ጣውላ መሰላ ልጇን ለማረጋጋት ሞከረች። እኔንም ሳያይ እናቱንም ሳይሰማ ዝም ብሎ ይጮህ ጀመር። ይሄ ጡሩንባ ምን ድግምት ቢኖረው ይሄን ሁሉ ተአምር እንደሠራ እንጃ። የቹቹ እናት ልጇን ተወት አድርጋ ዙሪያዋን ቃኘች። እሷም በጡሩንባው ምትሃት እንድትመታ ከሰንሰሉ ብቅ ብዬ ታየኋት። ጥቁሯ ጣውላ እንደቹቹ በጡሩንባው ምትሃት አልተንዘፈዘፈችም፤ ዝም ብላ አየችኝ። ባታየው ነው በሚል ክንገትኩበት አውርጄ ከፍ አደረኩት። እኔን ትታ ቹቹን በቀሚሷ ጋረደችው።

ቁጭ ብዬ ሁኔታውን አከታተል ጀመር። ውሻችን ገልጾ እንቅልፍ ላይ ነው። እንደሰው ያንኮራፋል። የጡሩንባው ምትሃት እሱንም እንዳያርበተብተው ሰጋሁ። እንደቹቹ እናት አይነቱን ቀዠቃገ አረጋግቶ እንደገልጾ ያለውን ድብርታም የሚያነቃቃ ምትሃት እዚህ ጡሩንባ ውስጥ ሳይኖር አይቀርም። የቹቹ እናት ልጇን እየጮኸና ለመደገፍ እያዳገታት ወደቤት ይዛው ገባች።

ከመርበትበት ወደ ማርበትበት፣ ከማፈግፈግ ወደ ማስፈግፈግ፣ ከተሰፋ መቁረጥ ወደ ተስፋ ማስቆረጥ... ተሸጋግሬአለሁ። በእናቱ የጡሩንባ ምትሃት ገና ቻይናን አንበረክኳለሁ ስል አሰብኩ "ሴታ ሴት" ማለቷን አስትቼ "ወንዳወንድ" አሰኘታለሁ።

እናቱ የእነቹቹን ወደቤት መግባት ጠብቃ ወደ ጉልቷ እቀርቅራ ሄደች።

እኔ የቤቱን ህልውና በጡሩንባ ማንገት አረጋግጬ በኩራት ወደ ውስጥ ዘለቅሁ። ለመጀመሪያ ጊዜ እህቶቼ ቀን-ቀን የት እንደሚጠፉ ግራ በመጋባት አሰብኩ። ሌሊት ማደሪያቸው ብቻ ሳይሆን ቀን እናቴን በጉልት ዕቃ ማጋዝ ካገዙ በኋላ ይሰወራሉ፤ የት?

ወጣሁ፤ ቹቹና እናቱ ምሽጋቸውን አለቀቁም። የቹቹ መርበትበት እንደተጠለ መሆኑን የሚያረጋግጥ ድምፅ ይሰማል። ሲታይ ያርበተበተው የጡሩንባ ምትሃት ቢነፋ ደሞ እንደከባድ መሳሪያ ምሽጋቸው ድረስ ዘልቶ ያደባያቸው ይሆናል። ለመንፋት ሞከርኩ። እንደ ፊሽካ ቀላል የመሰለኝ ጡሩንባ መንፋት አዳገተኝ። የጠጠረ አየር የጡሩንባው ጫፍ ላይ ተወትሮ አልገፋ አለኝ። የጉንጬን ጡንቻ ገትሬ በኃይል ስገፋው ፈስ የመሰለች ድምፅ አመለጠው።

የቹቹ የጭንቀት ድምፅ ጨመረ። ጣውላ እናቱ ወጥታ የአንጬት ጉጥ በመሰለ አይኗ አየችኝ። ጡሩንባው ቹቹን ሲያፈጥን እሷን አረጋግቷታል።

ወደ ቤት፤ ጡሩንባው ውስጥ ምን ተጨምሮ ይሆን? በቀጭኑ የተተበለውን ድምፅ እያባዛ፣ እያሰባሰበና እያራባ ትልቅ ድምፅ የሚያወጣው ከጠባብ ወደ ሰፊ ስለሚጓዝ ብቻ ነው?... እሺ. ይሄ ይሁን እንዴት የፈጠነ ማዘግየት፣ የዘገየ ማፍጠን ቻለ? ገና ሳይነፋ፤ ስለታየ ብቻ? እንዴት? ...ቻይና ላይ ሰምክረው ምን ያደርጋት ይሆን? ሴታ ቤት ትሆንና እኔን "ወንድዬ፤ ወንዳወንድዬ፤ ወንዴ...." ያሰብላታል?...

እናቴ ግን የማትችለው ምንድን ነው? "መሲው ቀላል ነው?" ካለች ትችላለች። ጡሩንባውን ኦፋ አቡኮ አሻሽቶና ምራቁን እንትፍትፍ ብሎ ከሰጣት ለየትኛውም ተአምር ይሆናል። ኦፋ አቡኮስ ይሄን ችሎታ ከየት አምጥቶት ይሆን? ከመጋረጃ ጀርባ ሆኖ እንደፈረስ እሀሀሀሀ... ይላል እንጂ ምን እንደሚያደርግ አይታይም። እሱ እንደፈረስ እያጀባቸው እነ እናቴ ይዘፍናሉ። ዘፈኑ ሆድ የሚያስብስ ዜማ አለው። አልቅስ-አልቅስ የሚያሰኝ። ማጥመ ግን ትርጉም የለውም። ሎሚ፤ ትርንጎ፤ ፈረስ፤ ሽቶ፤ ጨፌ፤ ጨሌ... የበባበት ነው።

እሱ የሚወደው ሎሚ፤

እሱ የሚወደው ሎሚ፤

ከወዲያ የመጣው በብዙ አጃቢ፤

(እሀሀሀሀሀሀሀሀ...)

ደማቅ ቀለም ይበዛል፣ ከባድ ሽታ ይናኛል፣ ኃይለኛ ሥሜት ሰውን ሁሉ ያደክመዋል። የሚካሄደው ነገር ባይገባኝም አንዳንዴ ደስታ፣ ሌላ ጊዜ ፍርሃት እየተፈራረቀ ይጎበኘኛል። እዚያ ያሉትን ያሀል ሰዎች ሲተባበሩ አይቼ አላውቅም። ኦፋ አቡኮ ድምፁን ልክ እንደጎን ሴት ሲጠይቅ ተቆጥቶ ከሆነ ሁሉም ይለማመጡታል።

"አባቴ ተው፣ ተው ማራት አባቴ" ይላሉ።

ኦፋ አቡኮ ቃል ገብቶላት ከሆነ ደግሞ ሁሉም በአንድ ላይ "እልልልልል... እሰይ፣ እሰይ..." ይላሉ። እንዲሁ ይታደራል። ጠዋት አቤት ስንደርስ ገላችንን በግራዋ ታጥበን ውኃው ቀጭኑ የእግር መንገድ ላይ ይደፋል።

"ለምን ቻይናም ከእኛ ጋር አትመጣም?" ስል ጠየኳት።

"በሰለት ያገኘሁህ ልጄ አንተ፤ ታማሚው ልጄ አንተ፤ እሷ ምን ቤት ናት የሴት ወጠምሻ..."

"ምኑን ያመኛል?" የሚሰማኝ የለም።

"ስንት ፋጭሬ፣ ፋጭሬ ዳንክ መሰለህ። ገና ጨቅላ ሳለህ ዞር ብሎብህ አትናገር አትጋገር፣ አትሰማ አትለማ፣ እንዲሁ ፍዝዝ... ብቻ። በኋላ..."

ስድስት አመት ሳይሆነኝ አይቀርም። አንድ ቀን የማላውቀው ጨለማ ውስጥ እንደቆየሁ ሁሉ ድንገት ተግ ያለ ብርሃን ታየኝ፤ ፀጥታ ውስጥ እንደኖርኩ ሁሉ በድምፅ ተጥለቀለቅሁ። ቀለሙ ሁሉ ደማቅ ሆነብኝ። ከቤት መሰስ ብዬ ወጥቼ የሰንሰሉን አረንጓዴነት፣ የሰማዩን ድምቀት በእንግዳ ስሜት አጤንኩ። ቀን ታውሬ አይኔ እንደበራ፤ ደንቁሬ እንደተከፈተ ሆንኩ። እናቴ ተከታትላ ያዘችኝ።

"ታስ፣ ምነው? ምነው?..."

እናቴን አስጠቀኋት። የጨለማ ውስጥ ህይወቴን ትጋራኝ እንደነበር ልቡናዬ ነገረኝ። አቅፌ ሳምኳት መሰለኝ። ድንጋጤዋ እስካሁን ትውስታዬ ውስጥ ደምቆ ይታየኛል። ዝም አለች።

"ያ-ምንድን ነው?" አልኳት።

"ሰንሰል"

"ያኛውስ?"

"ሰማይ እልልልልል..." እያለች ነጠላ እንኳን ሳትለብስ ወደ ኦፋ አቡኮ ቤት። ተንከባለለች፣ ተንደባለለች፣ አለቀሰች... እዛ ያሉት ሁሉ እሷን ከመገላገል ይልቅ አብረዋት እንደሆነችው ሆኑ። አካባቢው ተሰጠ። ሁሉም ያውቁኛል። እኔ ግን እንዳቸውንም አላስታውስ። ከሶስት ቀን በኋላ ወደ ቤት ስንመጣ እህቶቼን እንደአዲስ ተዋወቅሁ። እንደተዘጋ ሬዲዮ ሆኜ ነበር። ለምን?...

ቹቹ ጅሉን ሆኜ ልቀር ነበር?

ደክመው የተጠቱን ፊደል ስለይ ሳምንት አልሞላኝም። ከዚያ ወዲህ ከአእምሮዬ እርዬ እንደተነሳ ተጓዥ ጉልበተኛ ሆንኩ። ሲነግሩኝ ሳይሆን ሊነግሩኝ ያሰቡት ይገባኝ ጀመር።

ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ? የእኔ ብቻ ሳይሆን የዓለም ሁሉ ምሥጢር ይመስለኛል።

# ፮

## እኔ፣ ቻይና እና የጡሩንባ ጦር ዕቃ

አህቴ (አቴቴ) አንደኛ ክፍል ስታስመዘግበኝ ስሜን ቀየረችው፦

“አልአባር ቢዘን” ተባልኩ።

አባቴ ተንጨረበበ፤ “ታሲሰሙ ምን ሆኖ አላባር አልሽው? ጣ! የእኔ ስም ብዙን ነው አላልኩም? ጣ! እናንተ ልጆች ከእናታችሁ ጋር ሆናችሁ ብትችሉ ከህይወት መዝገብ ታስፍቁኛላችሁ ጣ!” ነገሩን አጣጥሞ እራቱን ሳያጣጥም ተከናንቦ ተኛ።

ደመኛዬ ቻይና ማንነቷን በስሜ ጀመረች።

“አስባሪት” አለችኝ። ቀይዳ፣ ቀይዳ ስሜን የቤት ማድረጓ እንደሆነ ገባኝ።

እህቶቼ ብቻ፣ ብቻ ሲሉ መምሸቱ ታወቀኝ። ልክ እቤት እንደዋሉ ሁሉ ገባ ብለው አንድ ዕቃ አንስተው፣ ሌላው ላይ ገልብጠው ወጣ ይላሉ። ጠባይ ቤት ትህትናን አስተምራቸዋለች። ታናሽ ታላቁን ያስልፋል። የዕድሜያቸው ስልፍ ብቻ ሳይሆን የሥራ ክፍፍላቸውም አይዛነፍም።

“ፋይናንስ” ስምረት

“ነገር” አቴቴ

“የቤት ውስጥ ሥራ ሚኒስቴር” አበባ…

አልጋ ላይ ሆኜ ሲወጡ-ሲገቡ አያቸዋለሁ። የቀዘቀዘው ቤት መሟሟቅ ይጀምራል። እንደንብ ሳያወሩ ሥራውን ሁሉ ያከናውናሉ። ለአይን መያዝ ሲጀምር ተጋግዘው የእናቴን የጉልት ዕቃ ያመጣሉ። እናቴ ስትገባ ቡናው ሲጨጨስ ትደርሳለች።

"ጎሽ! ኑሮአችሁ ይሙላ" እግዚአብሔር የእናት ምርቃትና እርግማን ቢሰማ ኖሮ ነገሮች መረጋጋት ያቅታቸው ነበር ስል አሰባለሁ። የያዘችውን የአደባባይ ድስት ታቀብልና እንዲያሞቁት ትነግራለች። አራት እንበላለን። ብዙ ጊዜ ቻይና እና አባቴ አይኖሩም። አበባም ብቻዋን ትበላለች። ምግባችንን በኢየሱስ ስም እየባረከች ስላስቸገረች እናቴ ለብቻዋ እንድትበላ ወስነችባት። አበባ የምትበላው በዝግር ሰሃን በተሰጣት ቁጥር እናቴ በቅሬታ ትተርታለች።

"አመል ያወጣል ከመሃል።"

አበባ ዝም ብላ ትበላለች። የእናቴ ተቃራኒ እምነት እንዳላት አውቃለሁ። እምላኳ አይን አፋር ሳይሆን አይቀርም። ስትፀልይ ዓይኗን ካልጨፈነች አይን አፋሩ አምላኳ አይቀርባትም። አልፎ አልፎ የቹቹን ጭንቅላት ይዛ ዓይኖቿን ስትጨፍን አያታለሁ። ቹቹ ግን እንደእኔ ከጨለማው ህይወቱ ወጥቶ ወደ ቀለማማው ህይወት አልመጣም።

እምነቷን በጀመረች ሰሞን ከእናቴ ጋር በቡና፣ ከአባቴ ጋር በጠጅ ጉዳይ ትነታረክ ነበር። አይናፋር እምላኳ ቡና እና ጠጅ አይወድም ማለት ነው። መጽሐፍ ቅዱሷም የተለየ ሳይሆን አይቀርም። ቤተሰቡ ሁሉ የእሷን መጽሐፍ ቅዱስ አያከብረውም።

ቡና ሲጠጣ ጡሩንባዬን ካስቀመጥኩበት አንስቼ አነገትኩ። ሁሉም ግራ ተጋቡ። ሲነገራቸው እያውካኩ ሳቁ። ያንን ቁራጭ ፊስ የመሰለ መንፋቴን ደገምኩላቸው። ሳቁ። እናቴ ብቻ ሳትስቅም ሳትኮሳተር ታደምጣለች።

ቻይና ድንገት በር ሳታንኳኳ ገብታ ተገተረች። እኔ ላይ አፍጥጣለች። እንዲህ የምትሆነው ውሻችንን ገልጀን ስመታው ነው።

"ሂሽ! ምን አደረገህ? ሂሽ!" አለችኝ።

ሴቶቹ ሁሉ ለዐቡ እስኪወሰኑ ፀጥ አሉ።

"እኔ አልመታሁትም" አልኳት ወደ እቴቴ እየተጠጋሁ።

"ሂሽ! ኧረ ቹቹን፣ ለምን በጡሩንባ አስፈራራኸው?"

ራቷ ያስፈራል። ያስቀሰችም ትመስላለች። እቴቴ አፈፍ ብላ ትነሳች። ቀደም-ቀደም የማለቷ ውጤት መክሰተሪያዋን የሚያጠናክር ጠባሳ ትቶላታል።

"ምን አገባሽ? እነሱ ያደረጉትን ታውቂያለሽ?"

"ምንም አያደርገውም፤ እሱ ለራሱ በሽተኛ"

"ምናገባሽ" እቴቴ ስትጠጋት ቓይና ትሸሻለች ብለን ጠብቀን ነበር። ግትር ብላለች። በቹቹ ላይ የተደረገውን በእራሷ ለመክፈል የፈለገች ትመስላለች። እቴቴ አስመሸሿ ግር አስኘቷት መምታቷን ትታ ራቷ ተገተረች። ካልተፈራች መማታት እንዳለባት የተረዳችው ዘግይታ ነው። በጥፊ አለቻት፤

ቓይና ግትር ብላ ዝም፣ ደገመቻት። ዝም! አይኗ እቴቴን ትቶ እኔ ላይ እንደተተከለ እንባዋ ዝርግፍ፣ ዝርግፍ አለ። ቓይና እንዲህ ሆና አታውቅም። የምሆነው አጣሁ። ከእቴቴ ጀርባ ሄጄ ቆምኩ። የምሆነው ግራ ገባኝ። ጥፋቴ ጎልቶ የታየኝ መሰለኝ።

"በሽተኛ አይደል? በስንት ነገር ይበደል?..." አሁንም እኔ ላይ።

እቴቴ "ዝም በይ!" ጮኸችባት።

አመመኝ፤ አለቀስኩ "እሺ ምቹኝ" አልኳት።

በሴቶቹ መካከል ሰንጥቃ አልጋዋ ላይ ወጣች። ሳታወልቅ፣ ሳትለብስ ራቷን ወደግድግዳ መልሳ ተኛች።

ፀጥ!!

# ፯

## እኔ፣ አባቴና ሴቶች

ጥፋት ኮተኮተኝ፣ ፀበት አሳደገኝ።

ቹቹ ገና ሲያየኝ ይንዘፈዘፋል። ሀመሚ ሆነ። ቢበሉኝ በተሻለ ነበር። ቻይና ሆነ ብላ አምሽታ፣ በሌሊት መኝታዋን ትለቃለች። ዓይናችን አልገጣጠምም ብሎኝ ተቸገርኩ። እቴቴም ቻይናን መቶጣት ቀርቶ መቆጣጠር የተሳናት ይመስላል። የቢዘን ፋርጎ ወደ ኬላ ሲተምም እኔና አባቴ ብቻ አቢት ውስጥ እንቀራለን።

የተለያዩ ጨዋታዎች አሉት። ስለ ልጅነቱ ብዙ የሚያውቀ ላይመስልም። "እናቴ እንደሀልም ትዝ ትለኛለች፣ ጣ! ልክ የእኩለሊት ጨለማ የመሰለች። ግን ቆንጆ፣ ጣ! ይቺ አሸሻን ቀጭ! አይ ዘር! ጣ! እኔ በትጡ የማላውቃት እናቴ በልጄ..."

ማደጌ የእኔ ስሜት ብቻ አይደለም። አባቴም ማደጌ ሳይሰማው አልቀረም። ከዚህ በፊት ያልሞከረውን አይነት ቁምነገር ያወጋኛል። የነገረኝንም ቢሆን ሲደግመው ክረር ያለ እውነት እየጨመረበት ሆነ።

"የአባቴ አገር ነፋሲት ነው ጣ! አላደኩበትም እንጂ አንድ ሁለቴ ለትንሽ ጊዜ ቀይቼበታለሁ ጣ! እውራጃችን የደብረ ብዜን ገዳም አጥቢያ ስመሆኑ ብዙ ጥንቃቄ አለበት ጣ! ነዋሪው እንደገደመ ቁጠረው ጣ! የወንድ ገዳም ነውና ሴት ፍየል እንኳን የለበትም። ያሉት ጥቂት ሴቶች እንደወንድ ለብሰው ይኖራሉ ጣ! መነኩሴዎቹን ላለማሳት ጣ!" ቀድሞ ይስትና ያሳቀውን ይነግረኛል።

"ደብረ ቢዘን በጨቅላነቱ የገባ ልጅ ዕድሜው አንዳንት ሲሆን ከገዳም ያወጡና ሁሉን እንዲያይ ወደ ገበያ ይዘውት ይገባሉ። ከገዳም የሌለውን እየጠቆሙ ያሳዩታል።"

አባዬ "ጣ"ውን አረሳ ብዬ ስደነቅ "ጣ" ብሎ ይጀምራል።

"ጣ! ታዲያ ይሄ እንትን ይባላል፣ ያደም ሰው እንዲህ ነው ሲሉት ይሡሉና በመጨረሻ ሴት ያሳዩታል። ሴት ናት አይሉትም "ሴጣን ነው" ይሉታል። ልጁ ወደ ገዳም ከተመለሰ በኋላ አበምኔቶቹ ይጠይቁታል።

"ካየኸው የቱን ጠላህ? ጣ!"

"ልጁ ይናገራል "የወደድኸውስ?" ቢሉት "ሴጣኑን!" አለ አሉ። ጣ! ሴቶች ወንዱን ሁሉ በተፈጥሮው ደካማነት ቁራኛ አደረጉት እንጂ እነሱስ ሴጣኖች ናቸው። ጣ!"

አባቴ ነገር ሲያስረዝም "ጣ" ይቀንሳል ማለት ነው። አባቴ በጠላው ሴት መውረሱ የልቡ መደፍረስ ውጤት ሳይሆን አይቀርም እያልኩ ማዘንም መሳቅም ይቸግረኛል።

እዚች የጭቃ አሙቶቡስ ውስጥ እኔና አባቴ ስንቀር የማሊዳ ወጉን ይቀድዳል። እናቴ ካለች ግን የማንተዋወቅ ይመስላል። እንደውም አንዳንዴ የማስመሰል ጠብ ይሞክረዋል።

"አሁን ምን አሎት? እንደው አይኑን ለምን አየሁ? ለነገሩ የትኛው አቀበት ፋችረው እንደዋጋ ይቀጥሩታል?..."

ብቻችንን ስንሆን ሴቶችን ያማልኛል...

"የሴት ጠባይ የሴት ነው ጣ! የሴት ውሎ የሴት ነው ጣ!" ሲጋት ይገባውና አምስት ጊዜ በሩን ይገላመጣል።

"የሴት ጠባይ ለወንድ ነዉሩ ነው፣ ጣ! የሴት ውሎ ለወንድ ውርደቱ ነው ጣ!" በቀድሞ መገላመጥ ላይ አንድ ሁለት ይጨምርበታል። "እነሱም እራሳቸው ቢሆኑ ወንድ ልጅ ጠባያቸውን ሲወርስ ይንቃሉ። ...አይምሰልህ ጣ! ቆፍጠን ሲል ነው እንጂ..."

አባቴ የውስጥ ለውስጥ ሥራ የጀመረው እኔን ከእናቴ ለመገንጠል እንደሆነ ይገባኛል። ጉዳዩን በቀልድ አየዋለሁ።

"ጥቂማችንን የምናውቅ እኔ፣ ጠቢቡ ሰሎሞንና አባቱ ንጉስ ዳዊት ነን። የማንም ገንጣይ፣ አስገንጣይ..." ብዬ በሆዴ እስቃለሁ።

"አትሳት ጣ!" ይላል ሆዴ ውስጥ ያለ ይመስል። ሽምቅ ውጊያውን የጀመረው ሆዴ ውስጥ ሸምቆ ነው እንዴ?

"አትሳቅ ጣ! ሴት የተረገመች ነች ጣ! የመጀመሪያዋ ሴት ምን አደረገች? ጣ! አዳምን የሀጢያን ፍሬ አበላች። ጣ!..."

እዚህ ላይ አባቴ ሁለት ቢዘን ይሆንብኛል። አንዱ ጠያቂ ሌላው መላሽ። አይኔን ጨፍኜ ሳዳምጠው እንደመስታወት አየሩ ላይ ተንፀባርቆ ከራሱ ጋር አፍ ለአፍ ገጥሞ የሚመላለስ ይመስለኛል።

"ደሊላ ሶምሶምን ምን አደረገች? ጣ!" አንዱ አባዬ ይጠይቃል።

"ፀጉሩን ቆረጠች ጣ!" ሌላው አባዬ ይመልሳል።

"ለምን ቆረጠች? ጣ!"

"ኃይሉ ፀጉሩ ላይ እንዳለ ስላወቀች ጣ!"

"ቄስ ቀለመ ምን አሉ? ጣ!"

"ሴት ለወንድ መፈተኛ ናት አሉ ጣ!"

"ማንን ምሳሌ ጠቀሱ? ጣ!"

"መጥምቁ ዮሐንስን ጠቀሱ ጣ!"

"ምን ሆነ አሉ? ጣ!"

"አንገቱን ተቆረጠ አሉ ጣ!"

"በማን አሉ? ጣ!"

"በሴት አሉ ጣ!"

እንደቀሸም ባለቅኔ ግጥሙን በ"አሉ" ከፍቶ በ"አሉ" ይደፋል። ቤተ-ክርስቲያን የሚሄደው ሴቶችን መወንጀያ መረጃ ሊያሰባስብ ነው እንዴ? ዓይኔን ከፈትኩ። በድንግዝግዙ ብርሃን ውስጥ የአባቴ ካኒቴራ አጥበርባሪ ብርሃን ጠግቦ ነፀብራቅ ይተፋል። ካኒቴራው በደመነፍስ አባቴ ላይ ሲመሰክር መሰለኝ። በአባቴ ቁም ነገር ማልገጥ ያዝኩ፦

"የአባቴ ካኒቴራ ምንድነው አሉ ጣ!"

"ንፁህ ነው አሉ ጣ!

"እንዴት ንፁህ ሆነ አሉ? ጣ!"

"ሚስቱና ልጆቹ ስላጠቡለት አሉ ጣ!"

"እሱ ግን ምን አደረገ አሉ? ጣ!"

"ውለታ እረሳ አሉ ጣ!"

በራሴ ድብቅ ቀልድ እራሴ ሳቅሁ።

"አትሳቅ ጣ! አትሳቅ ጣ! እኔ ተውነቱ ነኝ።" አለ አባቴ። ፊቱ በተፎካካሪ የካኒቴራው ብርሃን ተበልጦ ከአንገቱ በላይ የተደመሰሰ ይመስላል።

"አትሳቅ ጣ! ሴቶች ስታስቀምጣቸው ደንቃራጣ! ስትልካቸው ቁራ ጣ!"

አሁን ግጥሙ ያዘለት ስል አሰብኩ። ሳግዘው በሚል መንፈስ በ"ራ" የሚጨርስ ስንኝ አከልኩለት።

"ሲያኮርፉ ተራራ፣ ሲስቁ ብራ፣ ዕውቀታቸው ያልተብራራ፣ አራዳ ሲዷቸው ፋራ..." ሳላስበው ከት ብዬ ሳቅሁ።

"ተውነቴ ነኝ ጣ!" በእሱ ንግግር ስለመሰለው አብሮኝ እየሳቀ...

"ንግሥት ሣባ ወዴት ሄደች? ጣ!

"ወደ ኢየሩሳሌም ሄደች ጣ!

"ለምን ሄደች? ጣ!

"ጥበብ ልታመጣ ጣ!

"ታዲያ ምን አመጣች? ጣ!

"ዲቃላ አመጣች ጣ!

አባቴ ለሦስተኛ ዓለም ጦርነት ምክንያት የሚሆን የፆታ ጠብ አጫሪነት ላይ እንዳለ ሆኖ ተሰማኝ። ከጦርነቱ ከተረፍን ታሪክ ውስጥ መግባቱ ነው። አንደኛ ዓለም ጦርነት ዩጎዝላቪያ፣ ሁለተኛ ዓለም ጦርነት ጀርመን፣ ሦስተኛ ዓለም ጦርነት ቢዘን። አባቴ በፆታ ማጥፋት ወንጀል ተከሰሶ አለማቀፍ ጦር ፍርድ ቤት መቅረቡ ነው። ፈገግ አልኩ።

"አንተ ሳቅ! እኔ ተውነቴ ነኝ ጣ! ሴት የወለደ ጉድ የወለደ ነው። ጣ!" በምላሱ አፉ ዳር የቀረ ወሬ እንዳለ ለማረጋገጥ ይመስል አጥርቶ ቀጠለ።

"አጤ ምኒልክ የልጅ ልጃቸውን ወይዘሮ ዘነበወርቅን ለራስ በዛብህ ድረዋት ሳለ ጣ! አንድ ጊዜ እየተነፋረቀች ከንጉስ መምጣት ጣ!

"ምን ሆንሽ?" አጤ ምኒልክ ማለት ጣ!

"ስደበኝ" እሷ ማለት ጣ!

"ማን?" ማለት ጣ!

"ባል ተብዬው ማለት ጣ!

"ምን ብሎ? ማለት

"ምናባሽ ብሎ ማለት ጣ!

"ታዲያ ለዚህ ነው? እኔ እንደሁ የተሰደብኩት ቀድሞውኑ ሴት ስወልድ ነው ጣ! ቤትሽን ሂጂ አርፈሽ። ማለት... እሃሃሃ ... እኔም ሰባት ስድብ ወለድኩ...ጣ!"

የአባቴ ማምረር ቸግሮኝ ፀጥ አልኩ።

"ምንድን ነው ጉዱ?" እናቴ ሳትታሰብ መጥታ ለፀብ አጪነቀረችበት። መግቢያ ሲጠፋው ታወቀኝ። ሦስተኛ የዓለም የጾታ ጦርነት ቢነሳ አባቴ እራሱ ከቀሰቀሰው ጦርነት እራሱ ቀድሞ እጅ ይሰጣል ስል አሰብኩ።

እናቴ ከቤቱ ድንግዝግዝ ጋር አይኗን እያፈጣጠመች "ደርሶ ወግ እንደሚያውቅ ሰው! እንዲህም አርጎ ወግ የለ፣ እራስ አውግቶ እራስ ማውካት?"

"ተይ እንጂ አንጓቼ ጣ!" አለ ወደማድፌጡ እያፈገፈገ። "የት ቦታ ወግ ሳላውቅ ቀርቼ አሳጣሁሽ? ጣ!"

"እይ ወግ እቴ!"

"ጣ! በሆዱ ያወራውን በአፉ አጣጣመ።

• • •

አባቴ በእናቴ አስኪንቃበት በሽምቅ ውጊያው ገፋበት። ትኩስ የማለዳ ወግ ያግተለትልልኛል።

"እስኪ እንደው በሞቴ ጣ!"

"ምን?"

"ታሪክ የሚያውቅ ጠይቅ ጣ!"

"ምን?"

"በጠላት ጊዜ ጣ!..."

"እ?"

"አንድ ኢትዮጵያዊ ወንድ ከጣሊያን ሴት ወልዶ እንደሁ ጣ!.... ለአመል አይገኝም! ጣ! ሴቶቻችን ናቸው ከሰልዳቶ የቀፈቀፉ ጣ!"

እኔን ከእናቴ ለመገንጠል ሲል የሚጠቀምበት ቃል እየጠነከረ ሲሄድና ማነጠፉ ሲገር ተሰማኝ። እናቴን በሌለችበት የመከላከል ሀላፊነት ለራሴ ወሰድኩ።

"እማዬን ትፈራታለህ?"

ሳይዘገያጅ የጠላት ጦር የመጣበት መሰለ። በሀሳብ ተንጎዳጎደ። መልስ የሚሆን ቅራቅንቦ እያነሳ ሲጥል ይታወቀኛል።

"እ ጣ! እና ጣ! ስለዚህ ጣ! ቢሆንም ጣ!" ካለ በኋላ ጥቂት ዐጥታ ለራሱ ሰጠ። እራሱን እየጠየቀ እንደሆን ተሰማኝ። ሚስቴን፣ እንጓችን፣ የልጆቼን እናት እፈራታለሁ? ነገር ግን ያገኘው ምላሽ "ሁሉም ነው ጣ!" የሚል ሆነ።

"ምኑ ነው ሁሉም?" እናቴን ወክዬ አስጨነኩት። በግራ ክንዱ ተመርኩዞ ከወገቡ ቀና አለና በድንግዝግዙ ብርሃን አጨነቀረብኝ።

"ሁሉም ነው ማለቴ ጣ! አየህ ጀግና ቤቱ ዱር ነው ጣ!"

ምን አገናኘው? አልኩ ለራሴ፤ የሚያስፈልገውን እና የማያስፈልገውን ኩታንኩት ሁሉ እንደሚያጋፍፍ ሰው ተመሰለብኝ።

"ወንድ ሁሉ ይሄው ነው ጣ! ጀግና ሆነ ጣ! መኳንንት ሆነ ጣ! ንጉስ ሆነ ጣ! አጤ ንጉሠ ነገሥት... ወንድ ሁሉ ቤት ውስጥ የሚስቱ

ተናቂና ተጠቂ ነው። ደጃፍ ከተዘጋ በላይ በምሽቱ ላይ የሚፎከር በወንዶቹ ቦታ ያልተሳካለት ፈሪ ብቻ ነው። ጣ! ‹የምትችለውን ምታ ቢባል ገብቶ ምሽቱን መታ› ሲባል አልሰማህም? ጣ!"

አባቴ አዘሉኝ የነገር ምድረበዳ ላይ ተንከራተተ። ምንም አልገባኝም።

መንፈሱን ገስጾ አስታገሰና ባሲታወሰው ፈገግ ብሎ እንዲህ አጫወተኝ፦

ከአጼ ቴዎድሮስ በላይ ወንድ ጣ! ከሳቸው በላይ ጀግና ጣ! ተየት መጥቶ? ግና ቤታቸው ከገቡ በኋላ የሚሽታቸው ተናቂና ተጠቂ ከመሆን አላመለጡም፤ ጣ!

"እንዲህ እንዳንተና እንደኔ ከአባቴ ጋር ስናወጋ የነገሩኝ ነው ጣ! አጼ ቴዎድሮስ ወታደሮቻቸውን ሰብስበው ጠየቁ፤

"ሴቶቻችሁ እንዴት ትይዛላችሁ? ጣ!

"አንዱ ወታደር ተነስቶ "እኔ ያንተ አሽከር እንደገባሁ በጥፊ እመርግባታለሁ" አይልም?

"ቁጭ በል አሉት ጣ!

"ሌላው ተነሳ "ከእሷ ጋር አትካራም አልገጥም ዝም፣ ዝም።" አለ። እሱንም "ቁጭ በል" አሉት ጣ!

"አንድ ቀፍጣና ግን ብድግ ብሎ "እኔ'ኳን ሚስቴን እንዳልሽ፣ ይሁን እላታለሁ" አለ።

"አጼ ቴዎድሮስ አፈፍ ብለው ተነስተው አንተ ነህ የምሽትህ ጌታ ጣ! አሉት። እሳቸውም በቤታቸው እንዳልሽ እያሉ ነዋሪ ናቸው፤ አሃሃሃሃ...

የሚንቃትን ሴት መፍራት የጀግና ገድል ሲያደርግብኝ ኪሳራ ተሰማኝ።

"ሁለተኛዋ ምሽታቸውማ በጥፊም ትደረግምባቸው ነበር አሉ። ሴት መቼም ደፋር ነናት ጣ! ገብርዬ ይሄን አይቶ ‹እንደ ጌታዬን!› ጣ! አለ አሉ ጣ! ጎራዴውን ሲመዝ አጼ ቴዎድሮስ "ተው" አሉጣ! አንተ የምታውቀኝ ታጥቂ፣ እሷ የምታውቀኝ አውልቂ..." አሉት።

ቢቸግረኝ በ"ቂ" የሚያልቁ አንዳንድ የሰንኝ መድፊያ ቃላት በአእምሮዬ ውስጥ እየደረደርኩ እጫወት ጀመር። አፍልቂ፣ መንጥቂ፣ ሰንጥቂ፣ ደቅቂ፣ ወድቂ፣ አጨልቂ. . .

## ፰

## እኔ፤ ገልጆና ውርሱ

ገልጆ ሞተ፤ ከአንድ አደገኛ የሌሊት ዝናብ በኋላ ሞቶ ተገኘ። ከሁላችንም በላይ ያዘነችው ቻይና ነበረች። አባቴ፦

"በህይወት እያለ ነበር እንጂ ጣ!" አለ።

ብሩ ወንዝ ይጣል ሲባል፤ ቻይና አምቢ ብላ እዚያው አንድ ጥግ ላይ ቆፍራ ቀበረችው። ቀብሩ ላይ ከእንጨት መስቀል ስታደርግ እናቴና እቴቴ ተቃወሙ።

"ቢዩ ደሞ እንደውም እንደው ነኝ በቤተክርስቲያን አስወግዢኝ" አለች።

ለጥቂት ቀን ገልጆ አለመኖሩ ግቢውን ጭር አደረገው። ይንቀዠቀዥ ይመስል። ፊዘ መቀመጥም ለካ ማድመቅ አለበት? ካልሆነ ለምን ጭር አለ? ወደ ቹቹ መቀመጫ አይኔን ወረወርኩ። አይን ለአይን ከተገጣጠምን (አቀርቅሮም ቢሆን) ስለሚንዘፈዘፍ ላለማየት እጠነቀቃለሁ። ጋዝ የተቀባ ጣውላ የመሰለች እናቱ በጉጥ ዓይኖቿ አተኩራ ትመለከታለች። እፍንጫዋም ከእንጨት ጥራቢ የተበጀ የገና ዱላ ጫፍ ይመስላል። ወደ ቤት፤

ገልጆ ከሞተ ከጥቂት ሳምንት በኋላ የአባቴን ሽምቅ ውጊያ እናቴ ደረሰችበት። አይኗን አላጨነቆረችበትም፣ በዐጥታ ተመልክታው ወጣች። የዛኑ ቀን ጋሽ ሩፌን ጠርታ ጭቃ ማስቦካት ጀመረች። እንደሼህ ሆጂሌ ቤት እንቁላል ታስጨምርበታለች ብዬ ስጠብቅ ቆየሁ። በሳምንቱ ጋሽ ጠሌን በአናጢነት ቀጥራ እንደ አሳንሰር ቁመት እንጂ ስፋት የሌላት ቤት ሰንሰሉ ስር አጥቀረች። ጭቃው ተለጠፈ።

ልታከራይ መሰሎኝ ነበር። አንድ ቀን ወጣ ብዬ ስመለስ እልጋዬ አዲሱ ቤት ተዘርግቷል።

"በክረምት፣ ጭቃ ቤት" እያልኩ ገባሁ። ቤቱ ሞቅ እንዲል እናቴ እንጨቱንና ወይራውን እሳት ውስጥ አጋፍጣ ትታዋለች። ከጭሱ በላይ ገንኖ የሚሸተው የገልጃ ጠረን ነበር። ልብ ብዬ ስመለከት የረገፈ የገልጃ ፀጉር ወለሉ ላይ ተረምርሞ ታየኝ።

አልጋው ወደእነቴቼ ቤት አቀጣጫ መዘርጋቱ ሳላስብበት ዝግንን እንዲለኝ አደረገ። የቹቹ እናት ነጣጣ ጣውላ መሰላ በመነምጀት አፍንጫዊን ግድግዳዬ ስር ለትለጥፍ ታይቶኝ ዝግንናው ገነነብኝ።

የመጀመሪያውን ሳምንት እቴቴ አልጋዬ ሥር አንጥፋ ተኛች። የእንንስር ወርድ እና ስፋት ያለው ቤት ወደ ሰማየ ሰማያት ይዞኝ የሚመነጠቅ እየመሰለኝ መባተቴ አልቀረም። ንቅቄም የሰማየ ሰማያቱ ጉዞ የቀጠለ ይመስለኝና በር ከፍቼ እያለሁ። እቴቴ ብትት ብላ፦

"ምነው? ታለ?...." ትለኛለች።

"ሽንቴን ሽንቼ" እላታለሁ።

ቤቷ ግን ሰዘጋት ያው ናት። ሰባቱን ሰማየ ሰማያት እንደባለ ሰባት ደርብ ሕንፃ ቆጥራ የምትመነጠቅ... አንደኛ ሰማይ (ክፍት ዝግት) ሁለተኛ ሰማይ (ክፍት ዝግት) አልፋ ኮከብ ደርሰናል (ክፍት ዝግት)... እንዲሁ ልቤ አልረጋልህ እንዳለኝ ይነጋልኝ ነበር።

ያን ሰሞን አባቴ እናቴን ውጭ እየጠበቀ በነገር ይወጋጋት ያዘ፦

"ሴቶቹንም ጎጆ አውጪ እንጂ ጣ! እነሱ እንደሁ አያገቡ ጣ! ግሥላ እያረባሽ ወይ አንድ ወንድ ዝር ያለ እንደሁ..."

በሴት የመከበብን ጥትም የምናውቀው ሁለቱ ንጉሶችና እኔ ነን። አባቴም ልብሱ ሳያድፍ፣ ኪሱ ሳይነጥፍ የሚኖረው በሴት ልጆቹ ነው። እሱ ግን አይዋጥለትም። በጡረታው ይመስለዋል።

"ተገኜን በወንድ ልጅ ያጥለከለከ አምላክ፣ ጣ!"

የጋሽ ተገኜን በወንድ ልጅ የመከበብ ጉዳት የማውቀው እኔ ነኝ። ዘወትር ልብሳቸው ያድፋል፣ ኪሳቸው ይነጥፋል፣ ሆዳቸው ይጎድላል።

“ውይ ዛሬ፣ ቴ! ቴ! ቴ!....” ትላለች እቴቴ።

“ምነው? ምነው? ምነው...”

“እኚህ ጋሽ ተገኔ፣ ቴ! ቴ! ቴ!...”

“ምን ሆኑ? አፈር በበላሁ!” እናቴ ደረቷን ትደቃለች።

“ልብሳቸው ጭቃ መስሎ፣ ያንን ጠበንጃ ተሸክመው ጉትት ጉትት ሲሉ... ቴ! ቴ! ቴ!....”

“እኔ ጭቃ ልምሰል!” እናቴ ደረቷን ትደግማለች።

“ልጆቻቸው እንጂ፣ ያ ሁሉ መንጋ ገረምላ እየተንጋጋ፣ ጭቃ ይልበሱ እነሱ። ዝም ብለው ጫት መብላት ብቻ...”

“ምናለ ይዝሺቸው ብትመጪ ኖሮ? አጥብጥብ ብናደርጋቸው” እየሁፋጓ፣ የእቴቴ ታናሽ

“አ! አ! በምን ገመታችሁኝ ቢሉስ?” እቴቴ

“ያቺ ክረምት ክረምት የምትመጣዋ የሠራተኛቸው ልጅ...” አለች አቃቤ ንዋይ ሰምረት።

“ሲፈን” አልኩ በልቤ፤ ለካ በአፌ ኖሯል።

እህቶቼ ሁሉ ተጠቃቀሱብኝ።

“እሷ ለክረምት ትመጣ አልነበረም ወይ?”

“ያየኋት መሰሎኛል” እናቴ፣ ይሄኔ አግኝታት ነው።

ልቤ ድንግጥ አለ። ክረምት ሆኖ እንዴት ሳላስታውሳት ቀረሁ? ጋሽ ተገኔን ብቻ ሳይሆን እኔንም ታነፃኝ የለም? በንጽህናዋ!

“እንዲህ ነው ማደግ” አለች የእቴቴ ታናሽ ሁሉም አንድ ላይ ሳቁ። ወደ ቤቴ ሄድኩ። ሽግግግግግ... አለኝ።

## ፱

## እኔ፣ ሲፈንና የናዝሬት አዙሪት

"አፋበትን ያላየ፣ መች ወንድነቱ ለየ?"

"ክረንን ያላየ፣ መች ጉዱ ለየ?"

"ተሰነይን ያላየ... መንደፈራን ያላየ፣ አዲቀይህን ያላየ፣ ቀሐይቶን ያላየ፣ ናቅፋን ያላየ፣ ቃሮራን ያላየ፣ ባርካን ያላየ፣ አቆርደትን ያላየ... ወንድነቱ ያልለየ..."

የአባቱ ሞክሼ አዲሱን ቤት ለማርገፍገፍ ግድግዳው ስር ቆሞ ጮኸ።

"ሲፈንን ያላየ፣ መች ወንድነቱ ለየ" ለራሴ፤ በራሴ ሳቅሁ። እህቶቼን ሆኜ እራሴን አሽሟጠጥኩ።

ሲፈን ሦስት ክረምት ከናዝሬት መጥታለች። እኛ ቤት የታናሼ የአበባሽ ጓደኛ ሆና ብትመጣም ስለፈዘዘችባት ይሆናል እሷን ትታ የእናቴ ባልንጀራ ሆነች።

"የእናቴ ጓደኛ ደህና ኖት" እያልኩ አሾፍባታለሁ።

"አንጓች፣ ይሄ ልጅሽ ሲሳደብ ዝም አልሺው?"

"ምን አለሽ? የእናቴ ጓደኛ አይደለሽም እንዴ? ይሄ ስድብ ነው?" ብላ ከንፈሯ ላይ የተንጠለጠለ ሳቅ ታሳያለች።

ሲፈንን ያላየ... አሉ

ያለፈው ክረምት ልዩ ጠረን፣ ልዩ መአዛ፣ ልዩ ለዛ... ይዛ መጣች። እኔና እናቴ እየተጨቃጨቅን ደረሰች።

"አንተ ውለታ ቢስ! አልሄድም? እፋ አቡኮኮ ለአንተ ከአባትም በላይ ነው፤ እንዴት ያለ ጉድ ነው..."

"ተይው ከእኔ ጋር እንሄዳለን" አለች ሲፈን።

የሲፈን ድምጽ ምን ተቀመመበት? የሆነ ነገሬን የአገኘኝ ይመስለኛል። ሰውነቴን መቆጣጠር ተስኖኝ ዝርግፍ ያልኩ፤ እንደጥሬ ተበትኜ መሰብሰቢያ ዘዴው ጠፋኝ። ምን ነካኝ? ምን ጥሬ አደረገኝ? ምን በተነኝ? አሺ... ልበተን፤ እንዴት ወዲያው አልሰበሰብም...?

"ሲፈን ማለት ትርጉሙ ምንድነው?" አልኳት ቤት ገባ ወጣ ስትል።

"እኔ እንጃ!"

"ናዝሬትስ?"

"እኔ እንጃ፣ ግን መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አለ"

የሲፈንን ናዝሬት ለማግኘት የአበባን መጽሐፍ ቅዱስ ገለጥኩ። ለረጅም ጊዜ አላገኘሁትም። ናዝሬትን ስፈልግ ብዙ ቦታዎች አገኘሁ፡ ፡ ዞዓር፣ ሴዊ ሽለቶ፣ ሰናዖር፣ ካራን፣ ከነዓን፣ ሴኬም፣ ሞሬ፣ ቤቴል፣ ጋይ፣ አዳም...

"አጣሁት" አልኳት።

"ምኑን?" ከድምጿ አይኗ...

"ናዝሬትን"

"ሄደህ?"

"አይ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ..."

እንደ እናቴ ሳቋ ከንፈሯ ላይ ተንጠልጥሎ አየችኝ።

እንደጥሬ መበተኑን ደጋግሜ ለምጄዋለሁ።

"ጠይቂ አሳይሃለሁ"

የቶምኩበት ጥላኝ ሄደች። ቀጭን ነች፤ እያየኋት ህዋ ውስጥ ገብታ ጠፋች። የሩፋኤልን ቁስ ገበዝ ጢይቃ መሰለኝ እዚያው እንደቆምኩ መጣች።

"የኢየሱስ አገር ነው፤ አዲስ ኪዳን ላይ አለ ብለዋል፤ ታድዬ" ብላ የጥሬ ክምሯ ሲፈርስ ሳታይ ተመልሳ ሄደች።

የናዝሬቱ ኢየሱስና የናዝሬቷ ሲፋን የአንድ ሰፈር ልጆች ናቸው? ሲገርም፤ ናዝሬትን ፈለኩት እንኳን ናዝሬት ኢየሱስንም አላገኘሁት። በመጨረሻ የአገሌጋይ መልክ ያላትን አበባን ጠየኳት። እንደቀልድ ገለጥ-ገለጥ አድርጋ "እነዚህ አራቱ ወንጌሎች የኢየሱስ ታሪኮች ናቸው። ማቴዎስ ማርቆስ፣ ሉቃስ፣ ዮሐንስ።" አለችኝ። ሲላ ሰበካ ልትቀጥል አሰባ ነበር።

መልሶ እንዳይጠፋኝ ጣቴን ከትቼ ወደ ክፍሌ አመራሁ። አነበብኩ፣ ኢየሱስን ወዲያው አገኘሁት። ሲፋን የተወለደችው አዲስ አበባ፣ ጉለሌ ሲሆን በተመሳሳይ ኢየሱስ ደግሞ የተወለደው ቤተልሔም ነው። ሁለቱም የናዝሬት ልጅ የሆኑት እዚያ በማደጋቸው መሆኑን ተረዳሁ። ናዝሬትን ደብረዘይት እንደሚያዋስናት ቀደም ሲል ሰምቻለሁ። ወንጌል የሚነግረን ሌሎች ከተሞች አሉ ገሊላ፣ ዛብሎን፣ ንፍታሌም፣ ቅፍርናሆም… ይባላሉ።

እንግዲህ ሲፋን 'ከናዝሬት የምትመጣው በገሊላ አልፋ፣ ዛብሎን ላይ አርፋ፣ ንፍታሌም ምሳ በልታ፣ ቅፍርናሆም ላይ ከአውቶቢስ ወርዳው ተናፍሰው መሆን አለበት። ደብረዘይት ከእነዚህ ከተሞች ወዲህ ነው ወዲያ?

ከናዝሬት ተጥሎ ሲፋን የሚል ስም ተጠቅሶ እንደሆን አሰስኩ። ሲፋንን ስፈልግ የኢየሱስን ታሪክ መላልሼ አነበብኩ።

በሲፋንና በኢየሱስ ጉዳዩ ተጠምጄ እያለሁ በሩ ሳይንኳኳ አንድ ሰው ዘው አለ። እጅግ አድርጌ ደነገጥኩ። ጋሽ ሩፌ ነበሩ። የለጠፉትን ጭቃ ሊመረምሩ ነው፤ እናደዱኝ። እራሳቸው ከጭቃ ውስጥ የተመዘዘ መጥረጊያ እንጨት ይመስላሉ። ሲሄዱ በጭቃ ማቡካት ተዕዕኖ ነው፡ ፡ ቀስ እያሉ እ-ር-ግ-ጥ ያደርጉና ከግራና ከቀኝ ጭቃውን ወደመሃል ያስገቡ ይመስል ሸፈፍ አድርገው ይንትቱታል። ከዛ እ-ር-ግ-ጥ።

እሳቸው ሲራመዱ ደረቁ መንገድ፡ ጨቅ፣ ጨቅ፣ ጨቅ... የሚል ድምጽ የሰጠ ይመስለኛል።

እኔን አላዩኝም፤

"ጥሩ ይዟል፣ አይ አቦካክ፤ ትንሽ ጭድ ቅር ብሎታል። ይሄም የባለቤቷ እንጂ የእኔ ጥፋት አይደለም። በዚህ ሶስት ቀን መለሰን አለበት፤ አይጭቃ፤ አይ አቦካክ" እያሉ ወለሉን በማቡካት ወጡ። እንዳስደነገጡኝ ሳላስደነግጣቸው መቅረቴ ቆይቶ ቆጨኝ።

በናዝሬቷ ሲፈን ላይ የነበረኝን ተመስጦ ለማምጣት ጥቂት ጊዜ ወሰደብኝ። ዝም ብዬ ሳነብ ደስ የሚል ነገር ለልቦናዬ የደረሰኝ መሰለኝ።, በእርግጥ ትርጉሙ የማይገባ ብዙ ቃላት አሉበት። ባይገባም ደስ ይላል።

"በመንፈስ ድሆች የሆኑ ብፁዓን ናቸው። መንግሥተ ሰማያት የእነሱ ናትና።

"የሚያዝኑ ብፁዓን ናቸው፤ መፅናናትን ያገኛሉና

"የዋሆች ብፁዓን ናቸው፤ ምድርን ይወርሳሉና..." ብፁዓን ምንድን ነው? ትርጉሙ ባይገባም ብፁዓን ለመሆን በመንፈስ መደህየትን የሚያስመኝ ቃል ነው። ማዘንና የዋህ መሆን... ሲፈን ላይ ስለሚታይ ብፁዓን ናት ስል አሰብኩ።

የሲፈን ፊት ሀዘን የረበበበት ነው። ዓይኖቿ ግን እጥፋት ባለው ቆብ ተጠልፎ ውስጡን የተኳሰ ይመስላል፤ ዘወትር ከንፈሯ ላይ የምታንጠለጥለው የሳቅ ፈርጥ አላት።

እራሴን እስክታዘብ ድረስ ሲፈን፣ ሲፈን፣ ሲፈን... ስል ዋልኩ።

# 10

## እኔ፣ ፍቅር ወደፊትና ፍቅር ወደኋላ

ከቤት ስወጣ "ትልቁ ቤት" መለስ ተደርጓል። ወደ ሩፋኤል ቤተክርስቲያን ለመሄድ መንገድ ስጀምር ሙሉ በሙሉ ሳልዞር አይኔን ወደ ቹቹ መቀመጫ ላኩኝ። አበባ የቹቹን ጭንቅላት በመዳፏ ይዛ አይኖቿን ለአይናፋሩ አምላኳ ጨፍናለች። የቹቹ እናት የለችም። አበባ ይሄንን ሰዓት ጠብቃ ቹቹን ለማንቃት ሙከራ ታደርጋለች።

መንገዴን ቀጠልኩ...

...ለመሆኑ ኦፋ አቡኮም ወንጌል ይኖረው ይሆን? የሚል ሀሳብ መጣብኝ። የት ይሆን የተወለደው? የት ይሆን ያደገው? ብቻ እሱም ናዝሬት እንዳይሆን። የናዝሬቱ ኦፋ አቡኮ።

ኦፋ አቡኮ ወንጌል ከኖረው እንዲህ ብሎ የተጻፈ ይመስለኛል።

ኦፋ አቡኮ አፉን ከፍቶ "እህህህ..." አለ።

"እንቱፍቱፍታ የሚቀበሉ ብፁአን ናቸው፤ የፈለጉት ይሳካልና።

"የጨት ምርቃት የሚቀበሉ ብፁአን ናቸው፤ ከብርሃን አልባ ህይወት ወደ ብርሃን ይገባሉና።

"ዶሮ አዙረው የሚጥሉ ብፁዓን ናቸው፤ ርሚጦ የሚጥሉ ብፁዓን ናቸው፤ ሳንቲም አሻሽተው ረከቦት ላይ የሚያደርጉ ብፁዓን ናቸው።"

ብፁዓን ግን ምን ማለት ነው?

እናቴ የጡረታ ድልድይ አድባር መስላ ጉልቷ ላይ ትታያለች። በዚህ የመጣሁበት ውስጣዊ ምኞች አሁን ተገለፀልኝ። ሩፋኤል ለመሄድ ሳይሆን ሲፈን እናቴ ጋ ትገኝ እንደሆን ለማግኘት ነበር። በሲፈን ፋንታ የእናቴ ወጥ አካባቢውን ናኝቶታል። ውስጤ ሽምቅቅ ሲል ታወቀኝ።

ሲፈን፣ ሲፈን፣ ሲፈን...

...አበዛሁት ይሆን? አስር እና አስራ አንድ ወር ሳላስባት ቆይቼ የለም? እና? እህቶቼ እስኪያስታውሱኝ ድረስ መች አስታወስኳት?...

እናቱ ተንደርድራ እፍንጫዬ ስር ደርሳ ኖሯል።

"የት ትሄድ?"

"ሩፋኤል"

"ምን ታደርግ? አንተ እንደሆን ከዕድሜህ በላይ ተንቀዋለሃል፤ ቢያገኙህ ያፍሱህ የለም? እሬሳ ተጀምሯል ነው የምልህ፤ ወደ ቤት ተመለስ..."

ልብ አላልኩም እንጂ አካባቢው በፍርሃት ውስጥ እንዳለ ያስታውቃል። ሁኔታዎች ሁሉ ደንግጠዋል። የእናቴ ፍርሃትና ድንጋጤ ሲታከልበት ብርጋጋ ገንኖ ታየኝ።

"አባክህ ሂድ... እንኳን አንተን እኒያን ቀጭታጮ አባትህን ቢያገኟቸው የሚምሯቸው አይመስለኝም። በል ና ወደ ቤት..." ቁመት በልጫታለሁ።

አፈሳው ሲፈንን አያሳየ አጥምዶ የሚጠብቀኝ መሰለኝ። ለማቀፍ የተዘረጋ እጇን አዬቹ እቅፏ ውስጥ ለመውደቅ ለንደረደር "ቀብ!" ወጥመድ። ከዚያስ ሲፈን በተጌጠ ዓይኗ ክልል ያለ ብር የመሰለ አንባ እያንከባለለች ወታደር መኪና ላይ ስጫን ባይ፣ ባይ... ከንፈሯ ላይ የተንጠለጠለው የሳቅ ሁብል ፍልቅ-ፍልቅ እያለ ማሰልጠኛ ካምፕ ድረስ ይሸኘኛል። ሸኝቶኝ ይመለሳል? አይመለሰም። ክክብ ሆኖ ከበላዬ ሲያበራ ይኖራል።

አባቴን የእናቴ የሳቅ ሁብል እንዲህ ተከትሎት ይሆን? እንዲህ አብሮት ኖሮ ይሆን?...

አንዳንድ ጊዜ እህቶቼ አባቴን ይጠይቁት ነበር። ከእማዬ ጋር እንዴት ተገናኛችሁ? እንዴት አፈቀርካት?... አባቴ ሁለት አይነት ምላሽ አለው። እናቴ ካለች የአባቴ መልስ ማብሸቂያ ይሆናል።

"ገና ከኮሪያ ዘመቻ መምጣቴ ነው። ጣ! ፈቃድ ሲሰጠኝ ጎንደር ሄድኩ። የሬዲዮኔን አንቴና ሰቢ እያናገርኩ፣ ሰዓቴን አስር ጊዜ እያየሁ መቼም የቁመቴ ነገር ሌላ ነው ጣ! በዚህ ላይ የክቡር ዘበኛ የደንብ ልብሴ ልክክ ብሎ አላዬ ላይ የተሰፋ ይመስላል ጣ!..."

"አንቱኮ ሀፍረት የልዎትም፣ አሁን እራስን እንዲህ መካብ፣ ሰው ይናገርልዎት እንጂ፣ ምንስ ልጆችዎ ቢሆኑ ይታዘባሉ'ኮ..."

"ተይው፣ ተይው፣ ይናገር..." ይላሉ እህቶቼ።

"እንጓቼ እክስቷ ዘንድ መጥታ ኑሯል ጣ! ገና ምንም የማታውቅ ቢሆንም ለካ ብዜን ብዜን፣ ብዜን... እያለ ከተማው ሁሉ ሲያነሳሳ ሰምታ ይሄ ብዜን ማነው? ብላ ኖሯል ጣ! ሬዲዮኔን እያንኮራኮርኩ ሰዓቴን እያየሁ እክስቷ ቤት ጥልቅ ስል 'ያውልሽ ብዜን መጣ' አይሏትም?" ጠጪው ሁሉ አውካካ። ጣ!

"ለማነው? ሴት የለ..." ስላቸውስ

"ጓዳ የእህቴ ልጅ አለች፣ ወትውታ ልትሞት!

"እምልዎታለሁ፣ እኔ እንጓች መች ቀና ብዬ? የሰው መልኩ ጥቁርና ቀይ እንዳለው ያወኩት አዲስ አበባ ከገባሁ ነው። ደሞ..."

"ተይው፣ ተይው ይናገር..."

"ያን ቀን ውጪና ብዜንን እይው ብትባል በእንገቱ ካራ አለች። ተዋት ብዬ ሄድኩ። ያኔ እኔ ሴቶቹ ሁሉ ውኃ ይሆኑልኛል፤ መች ቁምነገር ጥፈው፤ በሁለተኛውም ቀን ያው፣ ውጪ ብትባል ኧረ ወዴት? ተዋት ብዬ ሄድኩ። በሦስተኛው ቀን ይመስለኛል እክስቷ የማዋይህ አለኝ፣ ጠጪ ሲወጣ ና አሉኝ።

"እሷ? ሥራም አላጣች..."

"ተይው፣ ተይው ይናገር..."

"ታዲያ እውነቱን ትተው ቀጥፈው ሲናገሩ..."

"ተይው፣ በኋላ አንቺ በተራሽ..."

"ሥራም አላጣሁ..."

"በኋላ ማታ ቤታቸው መሄድ ጣ! እክስቷ ተነስተው እጃቸውን እያርገበገቡ፣ ብዜን ከጉድ አውጣኝ፣ አይሉም ጣ!

"ምነው? ስላቸውስ

"የእህቴ ልጅ

"ምን ሆነች? ጣ!

"ምን ትሆናለች? አንተን ወድዳ እንደተለከፈ፣ ስለነብስ ብዜን፣ እርግጥ ቁመተ ጎማዳ፣ አፍንጫ ጎራዳ ናት ጣ! በዚህ ዘመን ቆንጆ ማስቶ ምን ያደርግልሃል? ቆንጆ ከጂ ነው ጣ! ብዜን - ጣ! ሾፌር ነህ አሉ፣ አውታንቲ ትወልድልሃለች ጣ"

"አንቱ ጥሽ፣ አከስቴን ካላጋባሽኝ ብለው እንዴ በሹጉጥ፣ እንዴ በልምምጥ እንዴት ደጅ እንደጠኑ ያውቁታል።"

"ተይው፣ ተይው፣ ከዚያስ?..."

"ከዚያማ ጣ! ለነፍስ ትሆነኛለች ብዬ..."

"ነፍሶት ይጥፋ፣ እኚህ ቀጣፊ!! ለልጅ እንዲህ ተብሎ ይነገራል? ምንም ልጆችዎ ቢሆኑ ይታዘባሉ'ኮ..."

"ተይው፣ ተይው..."

"እስኪ ክጓዳ ትውጣ፣ ጣ! ሰል ብትመጣ አቀርቅራ ኧረ ወዴት፣ ብቻ እንባዋ፣ አቤት እንባ ጣ!..."

"በመካከላችን እግዜር አለ፤ ያለቀሰውንማ... እኔ ግን እንደርሶ አይደለሁም።"

"እንባ ጡር አለው ጣ! ይሁን አልኩ። ጣ! እሷ እንኳን ካገቡኝ ሌላም አልፈልግ ብላ ነበር፣ እኔ ግን ልብሷን አልብሼ ጣ! ወርቋን አንቆጥቁጬ ጣ! ደሞ ጫማ... ጫማውን እንዴት ትልመደው? እንደልጅ ታቅፈው በእግሯ ስትሄድ አደርሳለሁ ጣ!..."

ክሳቅ የበሰጠ ሁካታ ይሆናል

"ወግማ ያውቃሉ፣ ውሽቲቱን ጨመር፣ ጨመር ለማድረጉ የበረሃው ጅኒ ረዳትዎ አለ..."

አባቴ ለእሷ አይመልስም፣ ዝም ብሎ ይቀጥላል።

"ወይኔ ብዜን፤ ጣ! የማንንም ቀርፋፋ ባላገር አግብቼ እንጀቴ ይረር? ጣ! ብቻ አመሏ ጥሩ ነበር፤ ቢርባት፣ ቢጠማት፣ ቢከፋት... ምንም፤ ጣ! ስጠይቃት፣ 'እርሶን ያህል የባህር ቂጠማ አግኝቼ ሌላ ምን አሻኝ?' ትልና አቀርቅራ ዝም! ጣ። መልኬን እንኳን በትጡ ማየት የጀመረችው አፍሪካዋን አሸቫን ከወለደች ወዲህ ነው፤ 'መልክዎ እንዲህ ቆንጆ ነው እንዴ? እኔ የማውቀው ቁመትዎን ነው' ትል ነበር።"

"እግዜ! እርስዎን መስማቱም ትልቅ ሀጢያት ነው" ብላ በመነሳት ዕቃ ታንጎዳጉዳለች።

እናቴ ከሌሎች ግን ልቡን ሞቅ እያለው...

"እፁኗ በብር ማርዳ የተጠለፈ ጣ! ፈገግ ያለች እንደሁ ተመሬት የምትደባልቅ ነበረች፤ ጣ! ምሽቱ ከቁመቷ ማጠር በላይ ምን ይጠጣላታል? ሁክተኛ የሚል ቅጥል ተሰጥቶኝ ጣ!"

እንደመተከዝ ብሎ...

"...አሁን ኑሮ አበላሻት፤ ጣ! አንድ ሲናገሯት ሺህ የምትመልስ ሆነች ጣ! ምን ታድርግ? እኔ አጠገቧ አልነበርኩ። ልጆቿ የሴት ልጅ ሆነች ጣ! እንዳይባሉ፤ አ-የሴት ልጅ ያለ እንዳያጠቃቸው ተናቻፊ ሆነች። ጣ! አሁን እፏ አያልች እናንተን የሚናገር አለ?..."

ይሄን የአባቱን ሚዛናዊነት እኔጋ፣ በእኔ ጉዳይ ሲሆን አጣጥለሁ። ለምን?

• • •

አፈሳ ሸሸት ወደቤት ስንመለስ መንገድ ላይ አበባን አግኝታ በግልምጫ አነሳቻት።

"አሸሻ ተመለሽ! አልበዛም? ኢየሩሴ ለማለት የቤቱ መች አንሶ ትንከረፈፊያለሽ?...."

ሦስት ሆነን እቤት ስንደርስ እህቶቼ ሲርበተበቱ ደረስኩ። "ምንድነው? ምን ሆናችኋል?..." እናቴ

"የጋሽ ሩፌን ልጅ ወስዱት፤ ኪታብ በዕድሜ አይበልጥም፤ እንደጡም ባያንስ?... አለህ ታስ? የት ሄድክ?" አቴቴ።

"ጋሽ ተገኔ ከቤት አይውጣ ብለዋል" ሰምረት እኔ ተይዤ ለጉቦ ብር አውጪ እንዳትባል የሰጋች ትመስላለች።

ሲፈንን ቢያመጧት የቆምኩበት ሣር እስኪበቅልብኝ ሳልንቀሳቀስ ቃል ለምድር፣ ቃል ለሰማይ።

"በቃ የጉልቱን እቃ አስገቡት፣ ጠጡ እንደማይደፋ ተጠንቅቃችሁ። ደሞ ከእሳቱ ላይ አውርዳችሁ..."

አፈሳውን በመቃወም የሥራ ማቆም አድማ እንዳይባል ሰጋሁ። እናቴ የሥራ ማቆሙ መሪ... ያቺ ቻይናስ? ወንድ ሲጠፋ ወንድ መሰል ወንዳወንዶችን ማፈሳቸው ይቀራል?

"ቻይናስ?" ስል ጠየኩ።

"እዛው እርግጫዋጋ ትሆናለች፣ እንዳያፍሷት ፈራህ? እውነትህን ነው፤ ከሚያውቋት አካባቢ ከራቀች ማፈሳቸው አይቀርም። እስኪጣራ... ኦሆሆሆይ... የጨነቀው መንግሥት" አለች እናቴ።

የአካባቢው ፍርሃትና ድንጋጤ እኛም ቤት ገብቷል። የጉልት ዕቃዎች ተጠቃለው ከገቡ በኋላ በፀጥታ አሳት ተቀጣጥሎ በፀጥታ እራት ተበላ። እበባ የብቻዋን ማዕድ አስከትባርክ እኔ እጠግባለሁ። እናቴ በማሽሟጠጥ ቃያቃለች። ቡናው ተቆልቶ እንዳለቀ እናቴ ፊቴ ላይ እንዲያንዣብብ ይደረጋል። እንደወትሮው ምርቃት አላዥጎደጎደችም። "ለወለደችው አድልታ ምርቃት ቃበዛለች" መባሏን ተቀብላው ይሆን?

"ኦሆሆሆሆይ" አለች እናቴ "ልጆቹን በክረምት የሚያፍሷቸው ለወንዝ ጋኔን ሊገብሯቸው ነው?..."

እዚህ ቤት እንኳን ሊታፈስ የሚችል ልጅ ተገኝቶ እንዲሁም የአፈሳ ወሬ አይበርድም።

አፈሳ፣ አፈሳ እያሉ የፍቅር ሀሳቤን አቀዘቀዙብኝ። መውደድን ሲያገኙት የሚያስቡትን ያህል ይጥማል? ሲፈን መጥታ ብታቅፈኝ የመታቀፍ ምኞቴ ያበቃ የለም? ያንን የመታቀፍ ምኞት ምን ይተካዋል?...

የሚያስፈራ ፀጥታ፤ እናቴ ቡና ከስኒ ስበት ለማላቀቅ በአየር ስትጎትተው የሚሰጠው ድምፅ ይሰማል። እቴቴ የራሷን ቡና እረከቦት ላይ ትታ ለሁለተኛ ዙሩ ጀበናውን ውኃ ትሞላለች። ስምረት ኢኮኖሚያዊ ስጋቷ ቡናዋን አስረስቷታል። ስኒውን እጇ ላይ እያሽከረከረች ዝም!

እንዴት ያስፈራል...

...በራችን ተንኳኳ፤ የእኛ ቤተሰብ አባል የማንኳኳት ልምድ ያለው የለም። እናታችን ቀልባችሁ ይገፈፍ እያለች አስትታናለች። ታዲያ ማን? ሴቶቹ ተያይተው እቴቴ እየተጎተተች ተነሳች። በሩ ባይቀረቀርም ባለመክፈት የምታስቀረው ነገር ያለ ሳይመስላት አልቀረም።

ጋሽ ተገኔ ነበሩ። ጋቢ፣ ካፖርት፣ በክንብንብ ላይ ከፍያ አድርገው ሲታዩ ጠበንጃ አንግቶ የቆመ ነጭ ድብ ይመስላሉ። ሲፈን ተከትላቸው እንደሆን በጉጉት ከኋላቸው አየሁ። እናቴ በድንጋጤ አየቻቸው።

"ምነው?" እናቴ ስኒዋን መሬት አኖረች

"ደህና ነኝ" ሳይጋበዙ ተቀመጡ "አንድ ወሬ ሰምቼ፣ መቼም ጠጅ ቤት ነገር በሬ ወለደ ነው።"

"ምን ሰሙ? እስኪ ቡናውን ሰጪያቸው፤ አቦሉ አለቀ? አንቺ ይቅርብሽ..." እናቴ ሆን ብላ ወሬ አቋረፈደች። የፈራችው ነገር አለ።

"እናንተ ካልሰማችሁማ ወሬ ነው... ተጡት" አሉ።

እኔ ሲፈንን ስለማፍቀሬ ሰምተው ሊያጣሩ የመጡ መስሎኝ ደነገጥኩ።

"ምንድነው እሱ?"

"እ-ይ ብዜን..." አባቴን በሚወደው አኳኋን ስሙን የሚጠሩት ጋሽ ተገኔ ብቻ ናቸው።

"ምን ሆነ?" ተነሳች እናቴ፣ እቴቴ ደረቀች፣ ሰምረት ውኃ ሆነች።

"እንደው ወሬ ነው፤ ዛሬ ጡረታ ሊቀበል ሲሄድ ዳግም እንዲዘምት ወረቀት ሰጡት..."

እ? እ? እ?... "እ"ዎቹን መቁጠር ተሳነኝ። ከጀርባ አበበና አበዛሽ "ከእቃ ቤት" ወጡ። ነገሩ መልኩን ለውጦ መርዶ መሰለ።

"እረ ተዉ፣ ገና መች ተጣራ? ሳይጣራ?..." ጋሽ ተገኔ እንደእኔ ጥሬ ሆነው ተበተኑ። መሰብሰብ ተሳናቸው።

"አይ ብዜን" አለች እናቴ። ስሙን ስትጠራ ሰምቼ አላውቅም። ነገሩ የከበደኝ ይሄኔ ነበር። "አይ ብዜን፣ በስተርጅናም አትረፋ ያለህ ከርታታ፣ እኔን ጓደ፣ እኔን እኔን በረሃ ይብላኝ፣ እኔን... አሁንስ አትመለስም!! ሞት ነው የፈረዱብህ ጓዴ..." ስድስት ልጆቿ ተጠመጠሙባት፤ እኔ እና ጋሽ ተገኔ ፈዝዘን ከተበተንበት መሰብሰብ አቃተን። እማዬ ቁርጡ ሲመጣ አባቴን አንተ አለችው።

"እግዚአብሔር የት ነው? የኦፋ አቡኮ ከራማ ምን ይሰራል? አንድ ሰው እንዲህ ሲጠቃ ምን ያደርጋሉ?... አውጪልኝ ይሄን ሲኒ፣ ውሰጂና ደጅ ላይ ስበሪው ይሄን ጀበና፤ ማነው የሚዘከረው? ማንን ነው የምለማመነው?... ሆዴ ነግሮኛል። ፈርቻለሁ፤ ይሄ ልጅ መሰለኝ እንጂ ብዜንን መች ጠርጥሬ?... አውጪ ይሄንን ሁሉ ድፊው!!"

ቁና ቁና እየተነፈሰች ቻይና አልጋ ላይ ተዘረረች።

## Ⅷ

## እኔ ስፈንና የመንገድ ማሚቶ

"እኔ ብዜን ጣ! ዕጣ-ክፍሌ ጠር ሜዳ ነው፤ ጣ! እመች!! ዕንጓጜ እኔ ልሙት!!"

"ጠላትህ!" እራሷን ታማ የተኛችበት የቃሪና አልጋ ላይ ሆና።

"አላየሽም እንዴት እንደ ወበራሁ? ጣ! ሬዜን ልጭትጭት ስልጣ... ጥንትም ያለ ዕድሜዬ በአምባጓሮ ነው ጡረታ ያወጡኝ!!"

"እሱን ተወው..."

"እመች፣ ጣ! ሰነግርሽ? አወንዶቹ ቦታ ከሆንኩ ገና መቶ ዕድሜ ይቀረኛል፣ ታያለሽ፤ የተነገረኝ አለ።"

"አንተ ውቃቤ ቤት ሄደህ?"

"አገሬ'ኮ ገዳም ነው፤ ጣ! ደብረ ብዜን ብዙ የበቁ መነኮሳት ነበሩ፤ ጣ! በመንገድ ከአባቴ ጋር ስንሄድ አንድ ሁለት መቶ አመት የኖሩ መነኩሴ አገኙንና እራሳቸው ጠሩን። ‹ስሙን ማን አልከው?› ጣ! አሉ

"ዮሐንስ" አለ አባቴ

"ዮሐንስ ጥሩ ስም ነው። ጣ! ግን ብዜን በለው። ጣ! የዕድሜው ጫፍ ተዚህ አይታየኝም። እንደኔ ያህላል። ጣ! ታዲያ ዕድሉ ትሰላም ለሁከት ያጋድላልና መንፈሳዊውን ትምህርት አያጥብቅ ጣ! አሰኳሳ አስገባው ጣ! አሉት። አለቱን አሰኳላ ገባሁ ጣ! ምን ያደርጋል ገና አራተኛ ክፍል ሳለሁ ዘግይተን ትምህርት የጀመርነው ላይ ጃንሆይ አይናቸውን ጣሉብን። አጭሩን ለጠር ሰራዊት፣ ረጅሙን ለክቡር ዘበኛ መለመሉት፤ ያኔ ተበሳጭቼ ነበር ጣ! አሁን ግን ሳስበው፣ ዕድሜዬ የረዘመው ወታደር በመሆኔ ነው። ጣ! አንጓቼ ሙቾ ወንዶቼ ቦታ ከሄድኩ ገና መቶ እድሜ ይቀረኛል ጣ!"

"ለስብከት ያልከው ነው" እናቴ

እህቶቼ ሆን ብለው ቤት እንደለቀቁ ያወኩት እቴቴ ስትጠራኝ ነው።

"አንተ ክፍል ሁን። ሲፈንን አግዛት፤ ባታግዛት እንኳን ብቻዋን እንዳትሆን..."

ብትን እንደ ጥሬ፤

እቴቴ ሁኔታዬን አይታ እንደእናቴ "ሆሆሆሆይ" አለች። ድምፅ ግን አልወጣትም። አፏ ሲያሞጠሙጥ ገባኝ። ሆፍረት፤ ወደ ውጭ ስሄድ፣

"ወዴት ነው? አርፈህ ተቀመጥ፣ አፈላ አለ እየተባልክ?"

ሳልወድ በግድ ወደ እሳንስሯ ክፍሌ ገባሁ። ጨልሟል፤ ጋሽ ሩፌ እና ጋሽ ወሌ መስኮት አረስተዋል። ሲፈን እዚህ ክፍል ውስጥ አለች፤ እዚያ ክፍል ውስጥ ደግሞ እኔ አለሁ። የሳቅ ሁብዒ ከንፈሯ ላይ ተወስውሶ ብርሃን ይፈልቃል።

"ታለ?" አለችኝ። ድምፅዋ ገና አላገገመም። እንደደከመ ነው፡ ፡ ከናዝሬት ተነስታ ገሲላን፣ ዛብሎንን፣ ንፍታሌምን፣ ቅፍርናሆምን፣ ደብረዘይትን... አልፋ እዚህ የደረሰችበት ድካም ድምጿ ላይ ተጠራቅሟል። ሙትት ያለው ገላዋ አረንጓዴም ቀሚስ ውስጥ ተከትቶ የሰውነት ለውጧን ሽፋፍኖታል።

"አ-ቤ-ት፣ እንዴት ትልቅ ሆንክ?" አለች።

አባባሏን አልወደድኩትም። ትላልቅ ሰዎች ለትናንሽ ልጆች የሚሰጡት አስተያየት ነው።

"አትስመኝም?" ተጣጥፋ ከተቀመጠችበት ወለል ላይ ተነሳች። ወለሉ የጆንያ ቅርድድ ተነጥፎበታል። ዳቦ ቆሎ እየቆረጠች ነበር። ጉንጩን አስጠጋሁላት። አልሳምኩትም ሳለማለት ያህል ሳመችኝ። እልፊያት አልጋ ላይ ቁጭ አልኩ። ቁልጭ ብላ ትታየኝ ጀመር።

የሲጥ ገመዱን አንስታ እያዟዟረች በመቀስ ትቆርጠዋለች። ጥቃቅን ጆንያዎች እህል የተሞሉ መስለው ዱቄት የተነሰነሰበት ሰፌድ ላይ ያርፋሉ። ኣፅኖቿ ፈዝዘው የዳቦ ቆሎ ቆረጣው የሚካሄደው ወደ ደመነፍስ በተሸጋገረ ልምድ ይመስላል።

"መቼ መጣሽ?" አልኳት የሞት ሞቴን።

ዓይኖቿ እንደፈዘዙ ለደመነፍስ በቀረበ ልምድ፡ ምላሽ ሰጠችኝ። “ሦስት ቀኔ”

እኔ ሁለት ቀን ናፈኳት፤ አስር ወር እንደ ጨንራዬ፣ ጣፊያዬ፣ ኩላሊቴና ጉበቴ ምልክት ሳታሳይ ውስጤ የምታክናውነውን ታከናውን ነበር። እንደ ደም ዝውውሬ ሳይታወቀኝ መላ ሰውነቴን ታዳርሰው ነበር። ሲፈን፣ ምን ይባላል። ማደጌን እንኳን ያወኩት በእሷ አቀማጠር አስልቼ ነው። ምን እኔ ብቻ? እህቶቼም መጎርመሴን የለዩባት… ምንድን ነው የማስበው? ጭንቅላት እንደወፍጮ ይሄን አሰብ ብለው ጥሬ ሀሳብ ቢከቱበት ደግ ነበር።

ሲፈን አቀርቅራለች። ሉጫ ፀጉሯ ጀርባዋን ትቶ በግራ ጎን ማጅራቷ በኩል ወደ ጡቷ ወርዷል። ረጅም አንገት፣ ወይም አንገትጌው ወደ ጀርባዋ ወርዶ የተሰፋ ቀሚስ አንገቷን ከተገቢው በላይ የረዘመ አስመስሎታል።

“ሲፈን?”

“እ?”

ዝም!! ምን ልላት ጠራኋት?

“ሲፈን?”

“እ?” ቀና

ዝም!!

“ምን ሆነሃል?” ትዝብት አተረፍኩ፤ ምን ነግጄ?

ፀጥ!!

“ሲፈን?”

ሰሬዱን አስቀምጣ ወደውጭ ወጣች።

“ምን ሆንሽ?” እቴቴ፣

“ምንም!” ተመልሳ ገባች። ይሄ ምንን ያመለክታል? የእኔስ ነገር ምን አመለከታት? እንጃ! ጫማዬን አውልቄ አልጋ ላይ ወጣሁ።

"ሲፈን?"

"አቤት!" ድርቅርቅ ያለ ምላሽ

"ላግዝሽ?"

"የወንዶች ሥራ ካለ አግዠ፤ ይሄ የሴቶች ሥራ ነው።" አቅረቀረች። መናገሯን እንጂ የንግግሯን ፍቺ ሳላጤን ቀጠልኩ።

"ሲጡን መሸብለል አይደል? ከዚያ መለስ ቀለስ እያደረጉ መቀረጥ..." ሲፈንን በአካል መቅረቢያ ምክንያት እንዲሆነኝ ነበር። የሲፈን ጥቂት ቃላት በቋማዬ ዙሪያ አንዣበው ብርሃኔን ያወደሙት ያህል ሆኑብኝ።

"እምን ወንድ ለመሆን አትደፍርም? ለምን እነሱ የሚያደርጉትን አታደርግም? ለምን እነሱ የሚውሉበት አትውልም?..."

በእናቴ ምልጃ ከጭለማ ወደ ብርሃን አልመጣሁም። በቀለማት ሊተከበብኩም። አሁንም ጨለማ ውስጥ ነኝ። አእምሮዬ አልሰላም፤ እናቴን፣ አባቴን፣ እህቶቼን አላወኩም።

ምንድን ነው? ቃይና በኋላም አባቴ ምንድን ነው እኔ ላይ ያዩ የነበረው? አሁን ደግሞ ሲፈንን... እራሴን ሴታ ሴት አድርጌ አይቼው አላውቅም፤ ስለዚህ እራሴን አላውቀውም ማለት ነው? እንዴት ከራሴ ጋር ተጣጣሁ? እኔ ሳላውቀው እነሲፈን እንዴት ተረዱት?...

...ተነሳሁ፣ ተቀመጥኩ። ስነሳ ሲፈን ቀና ብላ አየችኝ፤ ስቀመጥ ተወችኝ... አይታዋ ውስጥ ንቀት፣ ንግግሯ ውስጥ መቆርቆር አለ። ወደት አቅጣጫ መሄድ እንዳለብኝ ሳይነግሩኝ አውላላ ላይ ተዉኝ። እራሴን ወዴት? እራሴን እንዴት? እራሴን ከየት? እራሴን ከማን?... ሲፈን እንዲህ ከምትገምተኝ ቹቹና እናቴ ጦጥ ሰርተው ቢያጣጥሙኝ እንዴት በቀለለኝ።

እራሴን ተፀየፍኩት፤ የት እንዳለ በማላውቀው ምንነቴ ላይ ጥላቻ አደረብኝ። እንደ ዛር ተፈናጥጦ፣ እንደ እደከበሬ በእኔ ላይ ገዝፎ ለሌሎች ሲያሳጣኝ የኖረው እኔነቴን የመፀቀል ብርቱ ፍላጎት አደረብኝ። ሲፈን ሰፌዷ ሞልቶ ልትገለብጥ ወይም ለምትቆላው ልትሰጥ ስትወጣ ተከተልኳት። ወደውጭ።

እየሩ እንደከበደ ነው። ፍርሃት ይነፍሳል፤ ጭርታው የሚለፍፈው አንዳች ድንጋጤ በግልፅ ይታያል። የእናቴ ጉልት ከጡረታ ድልድይ መኖሪያዎች ሁሉ ከፍ ብሎ ይታያል። ከምን እንደተዋቀረ መለየት ያዳግታል። ቆርቆሮ፣ ጆንያ፣ ማዳበሪያ፣ እንደግድግዳ የተሰሩ የድንጋይ ካብ፤

አንዳንድ ሰዎች በሲጋራ ያዩኛል። ወንድነቴን በመታፈስ፣ ከዚያም ወታደር በመሆንና በመሞት የማገኘው ክሆነ ግድ አልነበረኝም። በተዘጋ በርና መስኮት በኩል ስሜን የሚጠሩ ድምፆች ይሰሙኛል።

"ታለ?" ካሉ የሚያውቁኝ በእናቴ ነው።

"አሌ፣ አሳዛር፣ አልፎ..." ካሉ የሚያውቁኝ በትምህርት ቤት ነው። ምላሽ ሳልሰጥ ነጠቅ-ነጠቅ እያልኩ እራመዳለሁ።

ጡረታ ድልድይ ላይ የማይጠፉት ጡረተኞች እንኳ የሉም። እንዳይታፈሱ ፈርተው ይሆን? ወደ ሩፋኤል አደባባይ አቀናሁ። መንገዱ የሁለት ቀበሌዎች ድንበር ነው። ሎብዮች ጥበቃዎቹ አደባባዩን ትተው መንደር መንደሩን ያሰሳሉ። በለዚህ ጭር ብሏል። በተለይ የወንድ በር አይታይም። አንዳንድ የተከናነቡ እናቶች ሩፋኤልን በፍጥነት ተሳልመው መንገዳቸውን ይቀጥላሉ። እንኳን ለመሳለም ጊዜ የሚሰጡትን፣ እንኳን ወታደር ለመሆን ጊዜ የሚጠሉትን ጨርቅ አሁን እዚህ ብሞት ስለ ምንም አልነበረም። ሲፈን ብርሃኔን አጥፍታዋለች፤ ጭለማ ውስጥ ነኝ፤

"ቁም!" መንገድ ባዶ ሲሆን ማስተጋባቱን ለመጀመሪያ ጊዜ አወቅሁ።

ጠበንጃ ተቀባበለ፤ ልቤ በጣም መታ። አሁን ሳስበው ድብቅ እኔነቴን መበቀል የምችለው በመቆም ሳይሆን በመሮጥ ነበር።

"ደ!" ያበቃ ነበር።

የጠበንጃች መቀባበሉ በራሱ እንዲህ ያለ ከባድ ድምፅ እንዳለው አላውቅም ነበር። ቀኩስ ሆኖ ተሰማኝ።

"ማነህ?"

"ወዴት ነው?"

ይሄ ሁሉ ጥያቄ ምን ያስፈልጋል? እኔ ሲፈንን ሳይ እንደተርበተበትኩትና ቃላት አላግባብ እንዳወጣሁት መሆኑ ይሆን?

ወዲያው ስሜ ሲጠራ ሰማሁ።

ሁሉም አብዮት ጠባቂዎች ያፌሱት እንዳያውቃቸው ተመሳስለዋል። ጋቢያቸውና ካፖርታቸው እንደዳክዬዎች አንድ አድርጓቸዋል።

"ታስ" በቤቴ ወይም በሰፈሬ የሚያውቀኝ እንደሆነ አወቅሁ።

"የብዜን ልጅ እኮ ነው" የአባቴን ስም በትክክል የሚጠሩ...

"እኔ ታስ፣ ጦርሜዳ ዕጣ-ክፍሌ ነው" ለማለት አሰኘኝ፤ በግዴለሽነት አብዮት ጠባቂዎቹ ሲከራከሩ ሰማሁ።

"የማንም ልጅ ይሁን!"

"ብዜን'ኮ ዳግም እንዲዘምት..."

"አባቶቻቸው ጦር ሜዳ ያሉትን ልጆች አልላክንም?"

"ተው እንጂ ጓድ ተገኜ"

"ሥም አትጥራ! ጓድ!"

"ልጁ'ኮ ገና ልጅ ነው!"

"ለአድሚና ለክብደት የተመደበ ኮሚቴ አለ፤ እኛ የተሰጠንን ኮታ..."

የአንዱ አብዮት ጠባቂ ድምፅ ሰገደል ማሚቶ የአስር አብዮት ጠባቂ ድምፅ ይሆናል። ምኑን የገደል ማሚቶ ተባለ የመንገድ ማሚቶ እንጂ...

"ቀጥል!"

አስር "ቀጥል!"ዎች።

# 12

## እኔ፣ ገልጀና የስሜት አዙሪት

"መዝመት አፈልጋለሁ" አልኩ።

"ታዲያስ? ይኸው? ጓደኛ..." እኔን ለመውሰድ የቋመጠውን ድምፅ እያለየሁት መጣሁ።

"አባቱ ነገ ሲዘምት ልጁንማ ዛሬ አላሳፍስም። ጓደኛ ግፍ እንፍራ እንጂ"

"ዛሬ ነው ግፍ መሆኑ የታየህ፣ ጓድ?"

በመካከል ጠበንጃ ተቀባበለ። በፊት የተቀባበለውስ? ጊዜው ሲያልፍ ወይነበረበት ይመለሳል?

"በል አሬሳዬን ተራመድና ያን ጊዜ ይሆናል!"

በዚህ መካከል ፀጥተኛውን አየር የመተረ ኡኡታ ተሰማ። የእናቴ እራሱ እንደሆን ወዲያው ለየሁት።

"በሽተኛው ልጄን፤ እንድፍሬው ልጄን፣ የዓይኔን ማረፊያ ልጄን... ኡ! ኡ! ኡ!..."

የሆነው ሁሉ ተዘበራረቀብኝ። እናቴ ዶሮ እንቁላሏን እንደምታቅፍ ውስጧ ከተተችኝ። እንዲህ መርዘሟንና መግዘፏን አላውቅም። ሁሉም እህቶቼ አሉ። በድምፃቸው ለየኋቸው። ጫጫታ ውስጥ "ጓደኛ!" የሚል ቃልና የጠበንጃ ማቀባበል ድምፅ እየጎላ ይሰማል። መንገዱ ገደል ማሚቶውን በእናቴ ተነጥቋል። "በጨኸት መች ይሆናል? ይዘነው እንሂድ"

"ውሰደው!" አለች እናቴ ድንገት ተረጋግታ፤ እንኳን ጠላቱን አወቅሁት እንጂ ውሰደው። እህህህህ..."

ከእፋ አቡኮ የቀዳችው የፈረሰ ድምፅ።

"ውሰደው፣ በሰባት ዘርህ ለውጠኝ! ከተወለዱት እስካልተወለዱት፣ ካልተወለዱት እስከታሰቡት፣ ከታሰቡት እስከአልታሰቡት... በዘርህ እመጣለሁ። ለውጠኝ፣ ውሰደው!!"

ፀጥ!

"ኑ እንሂድ" አለች ልጆቿን "እኮ እንሂድ!"

እረኛው "ጓድ!" የለ፤ ጠበንጃ ማቀባበል የለ።

"ጥርስ አስገባሽን ጓድ ተገኜ፤ ከማንጋፋው ባሻጋራ ጋር፤ ሂድ ወደ እናትህ..."

"መዝመት አፈልጋለሁ!"

"ምን ያለው ጠሰኛ ነው እባካችሁ"

ከኋላዬ ቀጭን ለቅሶና የቀጭን እጅ ማቀፍ ተሰማኝ። ሲፈን፣ ሲፈን፣ ሲፈን...

• • •

አቤት እስክንደርስ ቤተሰቦቼ ለሲፈን ተጨነቁ። ሲፈን ወገቤን በግራ እጇ ይዛ ታለቅሳለች።

"ይቅርታ፣ ይቅርታ፣ ታለ? ይቅርታ" ትላለች እልፎ እልፎ። እኔ ፀቤ፣ ከራሴ ከትሸሸገው እኔ ጋር እንደሆን እንደምን ላስረዳት? እባቴ፣ ቻይናና እሷ ካዩት የእኔ ወካይ ጋር የተፈጠረ የላጥፉህ አጥፋኝ ፀብ እንደሆነ እንዴት ልንገራት? የት እምኔ ውስጥ ተሸሸገ? እንዴት እንደምን አጮልቶ ለእነሱ ታየ?

ከፍሌ ገባሁ፤ አባቴ ከቤትም አልወጣም። ምን አልባት የእኔን ጉዳይ የተረዳው እሱ ብቻ ሊሆን ይችላል። ለካ ዘንቧል? መበስበሴ አሁን ታወቀኝ። ጫማዬን ብቻ አውልቄ አልጋ ላይ በጀርባዬ ተኛሁ። እራሴን ፈራሁት። በየትኛው ድርጊቴ ውስጥ ተቀጥላው እኔነቴ ብቅ እንደሚል አልተገለጸልኝም። ስተኛ? ሳወራ? ስበላ? ስለብስ?.... የቱ ድርጊቴን ትንተርሶ ሲታሲትንት ብቅ አለ? ለእኔ ግልፅ አይደለም።

አንድ ጊዜ አባቴ ገልጆ ውሻችንን በሀዘኔታ ሲመለከተው ቆይቶ፣ ሴት ውሻ አሳስሮ ይዞለት መጣ። መላው ሩፋኤል ሳይስቅ አይቀርም።

ገልጀ የተፈጥሮ ግዴታውን ይወጣል ብሎ ሲጠብቅ በአባዬ ግምት ያልተገባ ነገር ፈፀመ። ከውሻዋ ኋላ ሆኖ ጭራዋ ሰር ይድፎነፎንና ያሸት ጀመር። አባቴ ተበሳጨ። "ወንድ አስዳቢ" ብሎ ገልጀን ቀጠቀጠው።

በገልጀ ቦታ ሲላ ወንድ አስዳቢ ቤቱን ቀልሶ አረፈው።

የመረረ ቢሆንም ለመሳቅ ዳር ዳር አለኝ።

አራሴ ስራሴ ውሻ ውሻ ሸተተኝ። የት ልሸሸው?

በሩ ክፈት ብሎ አቴቴ ብቅ አለች።

"አራት ይምጣልህ?" አለች በቀጨ መንፈስ ሳይሆን በተቀጨ ልምምጥ።

"በቃኝ" አልኳት፣ ሄደች። ብዙም ሳትቆይ ሲፈን መጣች። ተሸማቃ አየችኝ።

"ታስ?"

"እ?"

ዝም! እንደ እኔ ሰም ጠርቶ የሚያወሩት ማጣት እሷም ላይ ሰፈረ? ቆይታ፡-

"ለምን አራት አልበላም አልክ?"

"በቃኝ" እንደ ጥሬ መበተኔ የት ጠፋ?

ገባች፣ ወደ አልጋዬ ተጠጋች። አይኔን ጨፈንኩ፤ ውስጤ ምንም ነገር እንደሌለ ገባኝ። ፊቷን መልሳ አልጋው ጫፍ ላይ ተቀመጠች።

"ፈራሁ"

"ምን?"

"አንተን ፈራሁ"

"ለምን?"

"ተደብቀህ የምትሄድ፣ የምትሄድ ይመስለኛል።"

ማልቀስ ጀመረች። ዝም አልኳት። እንዴት እንደሆነ ባላውቅም ጫማዋን ስታወልቅ ይታወቀኛል። አውልቃ አልጋው ላይ ወጣች። ከጎኔ ተጋደመች።

ፀጥታ!!

ፊቷን ወደኔ መለሰች። እንደተንጋለልኩ እጆቼን የጭንቅላቴ ጀርባ ላይ አጣምሬአለሁ። አራሴን ፈተሽኩ፤ ከጥቂት ሰዓታት በፊት የጥሬ ክምር እንደነበርኩ የሚመሰክር አንድም ፍንጭ የለም። ጠላኋት?

ደረቴ ላይ ጉንጯን አድርጋ ተኛች።

ፀጥ!!

"እዚህ ልደር?"

"ለምን?"

"እንዳትሄድ፣ እንዳችን እንዳታሳዝናት"

"አልሄድም፣ አንቺ ወደ ቤትሽ ሂጂ..."

"እውነትህን ነው?"

"አዎ" አላዬ ላይ እንዳለች በአህቶቼ መታየት አልፈለኩም፤ እስክትነሳ ጊዜው ረዘመብኝ።

"እሺ፣ አምንሃለሁ። ነገ ጠዋት እመጣለሁ"

ውስጤ እንደ ሩፋኤል መንገድ ያለ የገደል ማሚቶ ፈጠረ። እንደቹቹ አንድ ቃል አስር ጊዜ ደጋገመ።

ሲፈን ተነስታ ወጣች፣ በሩን ከውስጥ ቀለፍኩ። እቴቴ እዚህ የማደር ፍላጎት እንደሌላት ገብቶኛል።

ያን ቀን ማታ ሲፈን ተራቁታ እኔን አልጋ ላይ ስትጠብቅ በህልሜ አየኋት። እኔን ለማደፋፈር ሳይሆን አይቀርም እንቅልፍ የወሰዳት መሰላለች። እንደ ጥሬ መበተን ከጠፋበት ተገኝቶ ከእውኑ ባሰ። ቤቱን ሞላሁት። ከየተበታተንኩበት እንደምንም ተሰባስቤ ተጠጋኋት። አይኗ ሲንቀሳቀስ በተፈጥሮ የተጌጠው የዓይኗ ቆብ እንደ ነፍስ ጡር ሆድ ይላወሳል። አጎንብሼ ግንባሯን ሳምኳት። ጠይም ጭኗ ቀልቶ በከፊል

ተራቅቃለሁ። እጇን አስረክባለች። በእንቅልፍ ልብ እንደመገላበጥ ብላ ተመቻቸችልኝ። ልቧ ያናጥራል፤ ላቱ የተሰበሰበበት ከንፈሯ እንደ አዩና ማቅረፊያ ይለምናል።

እነዚህ ሁሉ ስሜት የመስጢታቸው ተአምር ከየት መጣ? ያረቷን ደረቴ ላይ ለማስጠም ታገልኩ። እግዚአብሔር ነፍሷን ሳይነጥቅ ገድሎ የሰጠኝ መሰለኝ። ከንፈሯን ሳምኩ፣ ከዚያም በላይ ለመሄድ የሱሪዬን ቁልፍ ፈታሁ። ሊፍሯና ከንፈሯ እንደተገጠመው መልመላቸውን አላቀመሙም። ሁለቱ ግን ይጠብቃሉ። ዚፔን አውርጄ ወደ ቢሯን ግፋ ለመጠጋት ስሞክር ቀድሞ መድረስ ያለበት የተወጣጠረ አካሌ ሳይነካት ቀርቶ ጭኗ ጭኗ ላይ ደረሰ። እጎንብሼ ስመለከት በብልቷ ፋንታ መብቀያው ላይ ሳንቲም መሳይ ብረት ተከድኖ አየሁ።

አልደነገጥኩም፤ ግን ከፍተኛ ተስፋ መቁረጥ ወረደብኝ። ሰዎች ሳይሆኑ ተፈጥሮ ከዳችኝ። ተፈጥሮ የከዳችው ወንድነት ምን ተረፈው? ስል አሰብኩ። ሳንቲም ከተደፈነችው ቀዳዳ የተነሳ ለዚሬት መሰል ስሜት በአካሌ ላይ ሀያውነትን አጥቦ ሲወስድ ታወቀኝ። ከእንቅልፌ ስነቃ አካሌ ሀያውነት እንደሌለው በሚያሳምን መልኩ ድንዛዜ ውስጥ እንደተዘፈቀ ነበር።

## ፲፫

## እኔ፣ ሲፈንና የቀን ቅዠት

የሚያስጠላ ቅዠት ይደጋግመኛል። ገልጀን ሆኜ ስንሰል ሆድ ውስጥ ተጣጥፌ ተኝቼ... ቹቹን ሆኜ መፍጠን ሲሳነኝ... አንዳንድ ጊዜ ደግሞ በቹቹና እናቴ አንገር አቢታቸው ተቀምጬ...

...ሲፈን ከእኔ ፍቅር የያዛት መስሎኝ ነበር። ግን ዐፀት ነው። ከተናገረችው በላይ በአንገባ ከፊለች። ጎዳሁት ብላ ካሰበችው በላይ እራሷን በዐፀት ጎዳች። እኔ ውስጥ ግን ማንንም፣ ምንንም መፈለግ የለም። እናቴ ለናፍቆቷ፣ እህቶቼ ለጥርጣሬያቸው ስክፍታ አይተውኝ ይሄዳሉ። ሲፈን ታስተናግደኛለች።

"ታስ? ታስ? ታስ?..."

እንደ ሩፋኤል ጎዳና ጭር ሲል ጡብቃ የገደልማሚቶ ታስተናግዳለች።

"እ?" ለደጋገመችው ስሜ የተደጋገመ ምላሽ ያስፈልጋት ይሆን?

ዝም!!

በዓይኖቿ ለመናገር ትሞክራለች። እነዚያ በጥልፍ ሽፋሽፍት የተጌጡ ዓይኖች ከውስጤ ጋር የፈጠሩትን የሥጋ ዝምድና ገድለው ሸፍተዋል። ዛሬ መለፍለፋቸው እንጂ ምን እንደሚሉ አይታወቀኝም። ከሀሳቤ ጋር ብቻዬን እንድትተወኝ እመኛለሁ።

"እሺ ብላ፣ እሺ ጠጣ፣ እሺ..."

ቹቹ ከሲፈን አጿጓን ተነስቶ አሁን ያለበት ደረጃ እንደደረሰ ይሰማኛል።

ዝም!!

ትሄዳለች።

ከሴት ቅዠት የሰፋና የጠቀረ ሀሳብ ውስጥ እዘፈቃለሁ። እዚያ ጭለማ ባህረ-ሀሳብ ውስጥ የጨዋታ ዓሳ እጠምዳለሁ።

አሞራ ሴታሴት ይኖረው ይሆን? የአንበሳስ? የፍየልስ ሴት እውል ሞልቷል፤ ሴታሴትስ? ወንዱ ኤሊ, ያን ሁሉ መቶ አመታት በወንዳወንድ ባህርይ ብቻ ይዘልቀዋል? ...ለመሆኑ ወንዱ ወፍ እንቁላል ታቅፎ ሲቀመጥ ሴታሴት እያሰበለው ይሆን? አውራ ዶሮም በሰባት ሴቶች መካከል ውሎ ያድራል፤ የእነሱ መራመድና ማውራት አይጋባበት ይሆን?

ንጉስ ሰሎሞንስ በሰባት መቶ እቁባቶች መካከል ሲኖር ሴታሴትነት አልሞካከረው ይሆን? ወይስ እንደ ፍየል ሴታእውራነትን ከሴታሴትነት የሚጠብቅ ተፈጥሮ ነበረው። መቼም "ንጉስ ሰሎሞን" የተባለው ከሴቷ ንግሥት የሚለይ መጠሪያው ስሆነ ነው። ሴታሴት ቢሆን ኖሮ ማን ብለው ይጠሩት ኖሯል? ንጉሲት? ንጉሲት ሰሎሞን!!"

ከትብዬ እስቃለሁ። ቤቴ አትራቢያ ካሉ ሴቶች አንዷ ብቅ ብላ ታየኛለች። ለመሳቅ የተዘጋጀ ፊቷ ማንም፣ ምንም እንደሌለ ሲያውቅ ጭው ብሎበት ይመስላል። "ለመሆኑ በሀበሻ ምድር ሴታሴት ንጉስ ገዝቶ ያውቅ ይሆን? አባቴ እንደነገረኝ ከሆነ ከልጅ ኢያሱ ሴታሴት የነበረ ሳይሆን አይቀርም። አባ መላ የተባሉት ብልግብልጥ ሽማግሌ፤ ልጅ ኢያሱን መናቅ የጀመሩት ለዚያ ነው። "እያያዙ ሁሉ የሴት ነው፤ ሲያወራ፣ ሲራመድ... ኢትዮጵያ ምኑን ሴታሴት ማለባት? እንግዲህ ንጉሲት እስኪሆን ‹ልጅ ልጂት› በሉት" ብለዋል፤ ወይም ያሉ ይመስለኛል። "ልጂት ኢያሱ"

አሁንም እስቃለሁ፤ አሁንም ሴቶቹ ያዩኛል። ለመሳቅ የተዘጋጀ ፊታቸው ጭው ብሎበት የበረሃ መሬት ይመስላል።

ወንድ እዚያ... ሴት እዚህ... በሀበሻ ምድር የዖታ አጋፋሪው ማነው? ለቅሶ ከሆነ ድንኳን መትከል፣ ድንኳን መንቀል የወንድ... ዕቃ ማጠብ የሴት፤ በቀጡ ሀዘንን መግለፅ የወንድ... ደረት መደቃት የሴት፤ የሬሳ ሳጥን መግዛት የወንድ... ንፍሮ መቀቀል የሴት፤ እንጨት መፍለጥ የወንድ... ቡና ማፍላት የሴት፤ ጋቢ መደረብ ለወንድ... ደረት መጣል ለሴት፤ ጉድጓድ መቆፈር የወንድ... ወጥ መቀቀል ለሴት፤ ደልዳዩ ማነው? የመጀመሪያ ጠንሳሹ? በምን አሳምኗቸው ተቀበሉትና ወጥ የሰራን ወንድ ዓይንህ ለአፈር አሉት?...

አንድ ጉዳይ ትዝ ብሎኝ አሁንም ከጣሪያ በላይ ሳቅሁ። እናቴ አልፎ-አልፎ አባቴን በብሽሽቅ አፏን ታሲዘዋለች። እሱ አጭርነቷን፣ ፉንጋነቷን እየጠቀሰ በእኛ ፊት እንደሚያበሽቃት ማለት ነው።

"አባታችሁ ሆዴ ገብተው የቀሩበት አንድ ዘዴ ነበራቸው"

"ምን? ምን? ምን?..." እንላለን።

"ያኔ እጠገቤ ሰው ባልኖረ ጊዜ የሽንት ጨርቂቱን አጥብ፣ አጥሚቱን ስርት፣ ገንፎውን ላግ ላግ ያደርጉና..."

"አባዬ?" እንላለን ባለማመን።

አባዬ ይቁነጠነጣል።

"ታዲያስ? ወጡ ሲጣፍጥላቸው ያያችሁ እንደሆን፤ ሽንኩርቱን ድቅቅ አድርገው ይከትፉና፣ ድስታቸውን እጥብጥብ አድርገው ጣድ ያደርጉና፣ ሽንኩርቱ እጋም እስኪመስል አቁላልተው በላዩ ላይ የታጠበ ምስራቸውን ከትተው እንደገና ያቁላሉ። ያንን ውኃ ከልሰው ሲበስል አካባቢው ይታወዳል። የእንጓች ወጥ ፍላል፤ ያስጠቅ ሁሉ። የሳቸውን ያህል ሙያ እኔ ተየት አምጥቼ?..."

"ወሬ ባፈጠልኝ ብስሽ፣ ጣ!..."

"ተዋት ታውሪ፣ ተዋት ታውራ..." ይላሉ እህቶቼ፦

"እንጀራቸውን አልቀመስኩም እንጂ ቂጣ የጋገሩ እንደሆን ኪክ፣ ኪክ ይልላቸዋል። የሳቸውን ያህል ሙያ በድፍን ጎንደር የለችም..."

አባቴ ራት ላይ ሀፍረትና ንዴት ተቀላቅለው ምስቅልቅል ያደርጉታል። ቶሎ አልጋው ላይ፣ ቶሎ ክንብንብ።

እናቴ በደስታ አፏን ሽብሽብ አድርጋ ጠቀስ ታደርገናለች።

አባቴ ወጥ ሲሰራ ማሰብ ወሬው እንጂ ግብሩ ለአዝነ ልቡናዬ አይመጠንልኝም ነበር። እናቴና እኔ ብቻችንን ስንሆን ለማረጋገጥ እጠይቃታለሁ።

"አሳቸው እቴ! የፈለሰም ውኃ አያቀኑ። ለጠግ ያልኩት ነው" ትላለች። የአባቴ አኳኋን ግን... እውነት ባይሆን ኖሮ "እምልሻለሁ! ጣ!" ይል ነበር።

እኔም እንደ አባዬ የወጥ መስራት ታሪኬን በሽለላ እና በፉከራ መጋረድ አለብኝ? አጥሚት መቀቀሌን በጦር ሜዳ ገድል ማላስ አለብኝ?

አባቴ ደስ ብሎት ነው የዘመተው...

"ይሄ የኔ ልጅ ትንሹ ጣ! ካልዘመትኩ፣ አባቴ ሄዶ አልቀርም ብሎ ጣ! በሰንት ምልጃ ተመለሰ አሉ!... ወንድነት ይዘገያል እንጂ አይቀርም ጣ! ተገኜ ሲነግረኝ አብዮት ጠባቂዎቹ በእሱ የተነሳ እርስ በእርስ ሲጋደሉ ጣ! እሱ መች ፍንክች ብሎ ጣ! እዘምታለሁ ይላል እሱ - ጣ!..."

"የበረሃ ጅኒህ ልጄንም ሲያስከትል..." አለች እናቴ። ከእንግዲህ አባቴን እንቱ ላትለው ነው?

"ይሄን አይቼ ብሞትም አይቆጨኝ ጣ!"

የዘመተ ምሽት ድፍን የጡረታ ድልድዩ ሴት ተሰብስባ ዘፈነች።

"ጉሮ ወሸባዬ

ጉሮ ወሸባ

ጉሮ ወሸባዬ

ጉሮ ወሸባ

ጉሮ ወሸባዬ ወሸባ

ዘማች ድል አርጎ ሲገባ"

ምድረ አሰመሳይ ሁሉ፤ ልጆቻቸውንና ባሎቻቸውን ደብቀው ማድቤት እያሳደሩ... እናቴ ሲታለቅስ፣

"አረ ወዲያ፤ ያንቺ ከራማ እንኳን ላንቺ ለኛም የሚተርፍ ነው። የምን ቀሊ ማስራት ነው? በመለማመኑ በርቺ ይልቅ፤" ትላለች እንደ።

"ይሄን ጅሉን ልቡና ይስጥልሽ እስቲ፤ ሰው ሁሉ ተደብቆ ሽንቱን በላዩ ላይ በሚለቅበት ሰዓት እዘምታለሁ ይበል?..." ሴላኛዋ ትጨመራለች።

አባቴ በወንዶች ተከብቦ ከጠጁም ካረቄውም ካቀላቀለ በኋላ እንደመፎከር ቃጣው።

"እናንተዬ፣ ቢዘን መልሶ ጎረምሳ ይሁን?" ይላል አንዱ።

"ጉድኮ ነው" ያደንቃል ሌላው።

በዚህ መካከል አባቴ ድምጹን ከፍ አድርጎ ጠየቀ፡-

"ምነው ብዜንን አላየሁትም? ተቀይሞ መቅረቱ ነው?"

"አዬ፣ የሱ ነገር እንዳይታፈስ ፈርቶ ከቤቱ መች ይወጣል?"

ሁሉም ወንዶች ሳቁ።

ወንዱ ሁሉ ተደብቆ አዝማች ሆኗል። ለራሱ እየፈራ ሰው የሚያደፋፍር። አባቴ ጋ የመጡት ወንዶች ሁሉ የጡረታ ድልድይ ያበቃላቸው ጡረተኞች ናቸው። ታይተው አታስፈልጉም የተባሉ።

ሲፈን ወደ ጆሮዬ እየተጠጋች።

"ጠጅ ላምጣልህ?" ትለኛለች።

"አልፈልግም" እላታለሁ።

"አረቄስ?"

"ይቅርብኝ"

"ለስላሳ ይምጣልህ?"

መቼም ሴት ነህ ለስላሳ ጠጣ ያለችኝ ይመስለኝና አኮሳተርባታለሁ።

"ተይኝ""

የሰማ ሰው እንዳለ ታረጋግጥና ዞር ትላለች።

የአባቴ መዝመት የጡረታ ድልድይ እና የመላው ሩፋኤል ጉዳይ መሆኑ አብቅቶ የእኛ የቤተሰቡ ብቻ ሆነ። ሲዘምት ጉዳይ የተኛሁበት ግንባሬን ስሞኝ ሄደ።

በቃ!

ወንድ ይሄው ነው? በር ዘግቶ የሰራውን በአደባባይ ጀብዱ የሚሸር? ጉዳዩ ከቤቱና ከቤተሰቡ ውጭ የሆነ? አባቴ አርባ ዓመት ሙሉ ለማን ወታደር ሆነ? ሃያ ዓመት ሙሉ ለማን ተዋጋ? ለኛ ለቤተሰቡ? ለጡረታ ድልድዩ? ለሩፋኤል? ለሸጎሌ? ለጉለሌ? ለአዲስ አበባ?... ለነዚህ ሁሉ አይደለም!! ታዲያ ለማን? ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያውያን ከሆነ ምነው እዚህ ጋ መቆሙ? ለምን ሱማሌን፣ ሱዳንና ኬንያን አልጨመረም? ሳያያቸው፣ ሳያውቃቸው የተዋጋላቸው ወገኖች አሉት አይደል? ሌሎቹንስ ወገን ካሉዋቸው ወገን አይሆኑም? ወገን ካደረጉዋቸው ወገን ይሆኑ የለም?...

የያኔውን የአባቴን ዳግም መዝመት ተመርኩዤ አሁንም ብዙ በጣም ብዙ ነገሮች አስባለሁ። በእርግጥም የወንድና የሴት ልዩነት ይሄው ነው። ወንድ ሕልሙ ከራሱና ከቤቱ ውጭ የሚያድር ነው። ከአካባቢው ርቆ የሚሄድ። ያንን ህልሙን በሁከት ላይ መሰርቶ የሚያዋቅር። በጉልበትና በኃይል በልጦ መገኘትን የህልሙናው መሰረት የሚያደርግ። ሴቶች ግን እንዲያ አይደሉም። ጉልበታቸው ለቅሷቸው መሸነፋቸው ነው። የቅርቡን በሥጋ ዝምድና ድል ያደርጋሉ፤ የሩቁን በጋብቻ ዝምድና ይረታሉ። ሁለቱም ጋ ፍቅር አለ። የወንዶች ግዛት ሲፈርስ የሴቶች የሚጸናው ለዚያ ነው። አባቴ ሰሜን ዘምቶ ስንቴ ድል አደረገ? ምን ያህልስ ወደፊት ገፋ? ስንቴን አሰደገደገ?... በመጨረሻ ሽንፈት ወደሱ አልዞረችም? ድል አልተደረገም? አላደገደገም?... ይህ የወንዶች ዓለም መደምደሚያው ይሄ አይደለም። ተሸናፊ ጉልበት ሲሰማው ይነሳል፤ የአባቴን ድል ይደግማል፤ እንደ አባቴ ወደፊት ይገፋል፤ ያሰደግድጋል... የወንዶች ዓለም ማብቂያ፣ ድምዳሚ የለውም። ይቀጥላል።

እናቴም እንደ አባቴ ሁሉ ለአርባ ዓመት "ወታደር" ነበረች። የእሱዋ ውጊያ ግን ከቤቷ ደጃፍ አላለፈም። ድሏም የማይነቃነቅ መሰረት ላይ የተተከለና ባላጋራ የሌለበት ነው። እናቴ ባትኖር አባቴ የቆጡን ሲያወርድ የብብቱን ጥሎ መግቢያ ቤትና ቤተሰብ አይኖረውም ነበር። ቆይቼ፣ ቆይቼ ሳስበው ወንድና ሴት ይሄው ነው። ያኔ ገና በአሥራ አራት ዓመቴ ላይ ግን የማደርገው ሲጠፋኝ ቻይና እግር ላይ ወደቅሁ።

"ምንድነ ነው? ምንድን ነው? ሂሽ!" አለች ወንዳወንድነቷ ከሴትነቷ ጋር እየተባረዘ፤

"ወንድ አድርጊኝ" አልኳት "በእናትሽ ቻይና ወንድ አድርጊኝ..."

ዝም አለች።

"እራሴን ጠላሁት፤ በእናትሽ፤ አለዚያ እራሴን እገላለሁ።" ደግሞ እውነቴን ነበር።

ደነገጠች። ትወደኝ ኖሯል?

"እሺ. በቃ! እሺ. ተነሰ..." እንስታ አቀፈችኝ። ቻይና የምታዝነው ላነሱትና ለተጎዱት ነው። ቹቹ፣ ገልጆ፣ አበዛሽ... እኔ።

"መጀመሪያ እዚህ ቤት ውስጥ ከሴቶቹ ጋር ተወሽቀህ ማውራትህን ተው፤ ቀላል ነው። ከእኔ ጋር እንጫወታለን፤ ስፖርት ትጀምራለህ... የሚደብር ነገር እኮ የለብህም። ግን በቃ..."

ወንድ ለመሆን መዋጋት ካለብኝ እዋጋለሁ፤ መሞት ካለብኝ እሞታለሁ።

"ትምህርት ቤትም ሴቶቹን ጓደኞችህን አባር። ምናባታቸው እኔ ነኝ የማባርራቸው...ሂሽ!"

በጥቂት ጊዜ ውስጥ ብዙ ነገር ተረዳሁ። ቻይና እኔን እየሰደበች መፍትሄ ስታፈላልግ ኖራለች። አንዳንድ አስተያየቷ ሙያዊም ነው። በትምህርት እኮ የምትበልጠኝ በሁለት ክፍል ነው። ግን...

መጀመሪያ ከእናቴና ከእህቶቼ ጋር ተጋፈጠች። ክፍሌ ሆኜ እሰማታለሁ። እቴቴ "ምን ይሁን ነው የምትይው?" አለች። "እንዳንቺ ዱርዬ ይሁን?..."

እናቴ "ለስንቱ ታምሚ፣ ማንንም ካድሚ ያገኘሁትን ልጅ ምን ሳደርገው ነው የምትለው?"

በመጨረሻ ቻይና አንዲት ቃል ጣለች። ፀጥ! ቤተሰቦቼ የተነኑና የበነኑ መሰለኝ። ከረጅም ፀጥታ በኋላ እናቴ እኔ ክፍል መጣች "ይቺ ፈረሳ፣ ይቺ ፈረሳ የምትለው ምንድነው?..."

"እውነቷን ነው" አልኩ።

"እኔ ይሄንን አላውቅም፤ ለእኔስ አታዝንም? ምን ሆንክ? ምን ጎደለህ? ዱርዬ ካልሆንክ መሞት?..." በሩን ዘግታብኝ ሄደች።

## ፲፬

## እኔ፣ ቻይናና ተፈላጊው ወንድነት

አሁን ሳስታውሰው እንደ አዲስ የሚያስቀኝ የመጀመሪያው የስፖርት ገጠመኜ ነው። የቻይናን አሮጌ ቱታ ለብሼ አካል ስናሟሙቅ ድንገት ቀጥ ብላ ቆመች...

"አስቲ፣ አስቲ፣ እንዴት ነው የምትሮጠው? እጅህን ጡትህ ላይ የምታደርገው ለምንድን ነው? ጡት መያዣ አላደረክም እንዴ? ምናባቱ!! ሂስ!!"

"አላደረኩም" ስላት ክት ብላ ሳቀች። "ስፖርት ሲሰራ ጡት መያዣ ይደረጋል እንዴ?" ለራሴ ያቀረብኩት ጥያቄ ነበር። የየትኛዋ አህቱ ጡት መያዣ እንደሚበቃኝ አሰብኩ።

"ስማ! የምትሮጠው ጡቷ ትልቅ ሆኖ እንደሚያስቸግራቸው ሴት ነው። ሂስ! እጅህን አውርድ! ደሞ ስትራመድ እግርህን ወደፊት እንጂ ወደጎን አትሰደድ ጉልበትህን ገጥመህ ወደጎን የምትራመደው ድንግልህ እንዳይጠፋ ነው?... ሂስ!"

ያኔ ያስቀሰኩ ይመስለኛል። አሁን ሳስታውሰው ግን የሚያስቀኝ ሆኗ። ከቻይና ኋላ ኋላ መሮጥ ብቻ ሳይሆን ስንሄድም እርምጃዋን እንድቀዳ አስከትላኝ ነው።

ይሄ አካሄድና እርምጃ ምኔ ውስጥ ተደብቆ ነበር? ግራ ያጋባል። ትምህርት ቤት ስፖርት ክፍለ ጊዜ ይስቁብኝ የነበረው ለዚህ ኖሯል? ይሄን ለማረም ከወር በላይ ወሰደብኝ።

በጥንት ጊዜ የሰው ልጅን እንደ ቻይና አሯሯጥና አካሄድ ያስለጠነ አንድ ጀማሪ ሰው ሳይኖር አይቀርም።

"አሁን የሮጥከው የሴቶች ነው"

"አንቺ አዛጋ አረማመድሽ የወንድ ነው። አሳይቼሽ አልነበረም?" ያለ አሉ። ሰው ያልደነገገው ተፈጥሯዊ ቢሆንማኖሮ እንደጡት እና ጢም አካሄድና አሯሯጣችን የፆታ ጉዳይ በሆነ ነበር። ነገር ግን

ቻይና የወንድ አካሄድ ሲሰፍርባት ያበረታታትና እኔ ላይ የሴት ሩጫ ሲሰለጥንብኝ የነቀፈው ማህበረሰቡ ነው።

ለአንድ ሰሞን ወንዳዊ አካሄድና አራሯጥ ብርቅ ሆኖብኝ ሰነበተ። እኔን ለሚያውቅ እንጂ ለማያውቅ ልዩነቱ የማይታይ ተራ ጉዳይ መሆኑ እንደተገለጠልን ስሄድ መርሳት ጀመርኩ።

ቻይና ሩጫዬ ሲስተካከል ከአራት ስፖርተኛ ጓደኞቿ ጋር ቀላቀለችኝ። ወሬያቸው ሁሉ የቻይና ፊልም፣ ካራቴ፣ ምግብ፣ ማስተር፣ ቤልት… የሆኑ ናቸው። ዝም ማለት ሰልችቶኝ ለማውራት ስሞክር ሁሉም ይስቃሉ።

ቻይና "ሂሽ! ምናባታችሁ" ትላቸዋለች።

ጓደኞቿ ቻይና አይሏትም "ቺ" ነው።

"ቺ አንቺ እኮ ነሽ፤ ከጀማሪዎቹ ጋር ቢውል…" ይሏታል።

"አንተም ጀማሪ ነህ፣ ምናባቱ ሂሽ!" ትላቸዋለች። እኔ እንዳወራ አትፈቅድልኝም። ዝም ብለህ አዳምጥ። ዝም! ዝም! አንድ ቀን የትኛው ሲያወራ ደስ አለህ?

"ሊ ይሻላል…" አልኳት።

በቃ እንደሱ ለማውራት ሞክር። ወንድነት ማለት እሱ ነው።

"ሊ" የሚሉት ብሩስ ሊ የተባለ የካራቴ ፊልም አክተር ስለሚወድ ነው። እንደ አክተሩ አፍንጫውን በአውራ ጣቱ ጠረግ የማድረግ ልምድ አለው።

"ሻዩሊን" የተባለው ፊልም ላይ (አፍንጫ ጠረግ ያደርግና) ብሩስሊን የሚገጥመው የእሱን ሁለት የሚያክል (ጠረግ) ሸሸት ሸሸት ይልና… (ጠረግ)…"

ሊን የወደድኩት ንግግሩን ሳይሆን በእኔ ላይ አስተያየት ስለማይሰጥ ነበር። በተለይ ሳኮ የሚሉት የሸጎሌ ሜዳ ብረት አንሺ ልጅ እኔ ላይ አስተያየት ለመስጠት የቻይናን ዞር ማለት በናፍቆት የሚጠብቅ ነበር።

"ሄይ፣ ጆ! ወንድነትህን በምስር ወጥ ለቺ ሸጠሀላት ነው?" ይላል። ሳኮ የተባለው እንደሳኮ ቢደበደብ፣ ቢደበደብ ስለማያመው ነው ይላሉ። እጁ ያስፈራል። የእጁ መርዘም ገመሬ ዝንጀሮ

አስመስሎታል። እናደዳለሁ፤ ምን ተሰፋ አለኝ? ደብድቤ ደብድቤ ሰጨርስ እንደ ገመሬውን ጭኖብኝ ይጥለኛል።

"አንተ ደሞ ታበዛጥለህ፤ ወንድ ከሆንክ ቺ እያለች አትናገርም?" ይላል ሲ።

ካራቴ ከምንሰለጥንበት ከፍተኛ 8 አዳራሽ ስንወጣ ቀጥታ ወደ አትክልት ተራ እናመራለን። የሩፋኤልን ቁልቁለት ፊልም እያወራን ፋት እንለውና በአለም ጸሐይ ድልድይ በኩል ሰባራ ባቡር እንደርሳለን። ሳኮ ሲሄድ በብረት አንሺ ደንብ ሁለት እጆቹን አንክርፍፎና እግሮቹን እንፈርክኮ ነው። ዋናው መንገድ ትተን ወደ መንደር ገብተን ጥቂት ከሄድን በኋላ ሻሚታ የሚሸጥበት ቤት እንገባለን። የቀለም ቆርቆሮ በመሰለ ትልቅ ጣሳ ይቀርብልናል። ልድልድ ያለ የገብስ ሲሾ ነው።

ሳኮ "ጃ" ይለኛል። ስለማልጨርሰው እንድሰጠው ነው። ሲን ስመለከተው። "ጨርሰህ ጠጣ" ይለኛል። ቻይና ጠጣም አትጠጣም አትልም። የራሷን ትጋተራለች።

ሳኮ ሻሚታውን ሲያነሳ እጁ ከመርዘሙ የተነሳ ፊት ለፊት ላለሰው ሊያጠጣ ይመስላል። ሁለት ሽልጠ ጨምሮ ወደ ሆዱ ይከትና ምንም እንዳልተመሰ ሁሉ እኛን በጉጉት ያያል። አንድ ቀን ማንም ሳያይ ምራቁን ሻሚታ ውስጥ ክትቶ ለሳኮ ልሰጠው ስል በቀብብላችን መካከል ቻይና እጁን ዘርግታ አፈጠጠች።

"ይሄን የቤት ተንኮልህን ሂሽ!" ጣቷን ጠዘወዘችብኝ።

የወንድና የቤት ተንኮል አለ?

ከሲ እና ከሳኮ ሌላ ሎሎች ሁለት ልጆች አሉ። አንዱ "ቴሱ" ይሉታል። አባቱ የሩፋኤል ቁሰ-ገበዝ ናቸው። ካራቴ የሚሰለጥነው ታቦቱን ለመጠበቅ ነው ይሉታል። ሌላኛው የሀኑኛው ጠጅ ቤት ልጅ ነው። ጥቁር ጭንቅላታም። ብዙ ጊዜ የሻሚታውን ዋጋ የሚከፍለው እሱ ነው" ከስፖርተኛ ይልቅ ሰካር የተጠናወተው ጠጪ ይመስላል። አይኑ ዘወትር ቀይ ነው።

ከሻሚታ በኋላ ሻገር ብለን ከአትክልት ተራ የቻልነውን ያህል ሙዝ ገዝተን በእግር ወደ ሩፋኤል እንመለሳለን። ሳኮ ሙዙን ከሦስት ሽልጠ ጋር ያጣጥምና ያገኘውን ልጅ ኪስ እየፈተሸ ይሄዳል። ካራቴ ስለማይሠራ ስነምግባር አልተማረም። አንዳንድ ጊዜ የደደረ እጁ ልጆቹ ኪስ ውስጥ መግባት ሲያቅተው ልጁን ብድግ አድርጎ በመዘቅዘቅ

ሳንቲሙን ወደመሬት ያራግፋል። ሳንቲሞቹ አስፓልት ላይ ስለሚለጠፉ ማንሳትም ሌላ ችግር ይሆንበታል። "ሲ፣ ቂስ በናታችሁ አንሱልኝ" ይላል።

"ስንት ትሰጠናለህ?"

ላለመስጠት በቆረፈደ እጁ ይሞክራል። በኋላ መንገደኛ ልጅ ፈልጎ ያስለቅምና ፈትሾ ይለቀዋል።

ሳኮ ሌላ የሚያስገርም ነገር አለው። እንደ እኔ ሲትነት ስራሱ የማያውቀው የአካሄድ ስልት አለው። እጆቹን ከፍቶ፣ እግሮቹን እንፈርክክ በማጥ ውስጥ የሚሄድ ይመስላል። ታዲያ ሌላ ሰው እንደእሱ ሲሄድ ካየ ብው ብሎ ይነዳል። የአካሄዱ ሞክሼ ፊት ግትር ይልና አይን አይኑን በቁጣ እያየ፦

"ጭገርህን አበጥረሃል እግርህን ከፍተህ የምትሄደው?" ይለዋል።

የሳኮ ፀብ ከተመታ በኋላ የሚካሄድ በመሆኑ ሰውዬው እጁን እስኪያሳርፍበት ይጠብቃል።

እኔ ቻይና ለዚህ የተፈጠሩ ማሽኖች ናቸው። ሌሊት ተነስቶ ስፖርት መስራት፣ ትምህርት ከሌለ ወደስባራ ባቡርና አትክልት ተራ ደርሶ መመለስ፣ ለክስአት በኋላ ስፖርት አረፍት መውሰድ። ትምህርት ካለ የጌህ ሆጀሌ ዘመዶች ጋ ፓስቲ ገዝቶ ወደ ክፍል መግባት።

እኔና ቻይና ወደቤት ስንመለስ የጓደኞቹን ሁኔታ እየተወንኩ እንዳሳያት ትጠይቀኛለች። ሁሉንም ልብ ብዬ ስለምመለከት ቀድቻቸዋለሁ። ትስቃለች።

"ሲ እንዲህ ነው የሚያወራው? ካካካካ..." ጀርባዬ ትደልቀኛለች።

"ሳኮ እንዲህ ነው የሚሄደው? ካካካካ..." ጀርባዬን ደልቃ ሳቋን ትቀጥላለች።

"ቂስ?... ካካካ..."

አንድ ቀን ሌሊት ለስፖርት ነቅቼ ለመጀመሪያ ጊዜ ቻይናን ልቀሰቅስ በሬን ከፈትኩ። እኛ በር ላይ ብዙ ነጠላ የለበሱ ሴቶች ቆመው ነበር። እፍታም ሳይቆይ እናቴ ጮኸች።

"ጓዴ፣ ጓዴ፣ ጓዴ..."

## ፲፭

## እኔ፣ ቀንና፣ ኪሎ ሜትሮች

"የልጆቼ ተገልማጭ አደረኩህ!!"

እናቱ እንደእብድ ደረቅ ለቅሶ ከደረቅ ሳቅ ጋር ታካሂዳለች።

"የልጆቼ ተለማማጭ አደረኩህ!! መሬቱ! መሬቱ! ቤቱ! ቤቱ! ጓዳዬ፣ ጓዳዬ!..."

የእናቱ ሀዘን ያማል፤ ሥጋትም ይፈጥራል። እጇን ጨብጣ ደረቷን ትደቃለች። የእኔ ታናሽ ይሄን እያየች "ልቤን!" ትላለች።

ቻይና እንደ ጎረምሳ ሳል ቅልቅል ለቅሶ አላት።

"አባዬ፣ ኡሁ! ኡሁ! ኡሁ! አባዬ፣ አባዬ ኡሁ! ኡሁ! ኡሁ!..." ሳሏን አቀጥራለሁ፤ በአማካኝ ለአንድ አባዬ ሁለት ሳል ይካፈላል።

እቴቱ እንደቹቹ እናት የተጣደፈ የለቅሶ ስልት አላት። መሀል ላይ ብቻ "አባዬ" ስትል ይሰማል።

"ትርርርርርር.... አባዬ ብርርርርርርር.... አባዬ ጭርርርርር አባዬ!" ከሁሉም የገረመኝ የሳኩ ነው።

"የቺ አባት! የቺ አባት!" እያለ እጁን እንዳንከረፈፈ አግሩን ከፍቶ በዝነጣ ድንኳኑን ይዞራል። "የቺ አባት! ወይኔ የቺ አባት!!"

አንድ ሌላ አልቃሽ በሱ ስልት እየተራመደ ቢያገኘው እስቴም ያፈጥበት ነበር ይሆን?

"ጭገርህን አበጥረሃል?..."

ለ. እና ቄሱ ክስሰው ተቀምጠዋል።

ስምረት አባዬን የከለከለችው ሳንቲም ትዝ እያላት ሳይሆን አይቀርም እየተትከነከነች እምርራ ታለቅሳለች። የገረመኝ የእንባዋ

መስመር ከፊቷ ላይ ለአንድ ሳምንት አልጠፋም። ያለቀሰችው አሲድ ነው እንዴ? ፊቷን ስትታጠብ አያለሁ፤ የእንባዋ ቅሪት ግን አይጠፋም። የአሲድ ማጥፊያ ፈልጋ ፊቷን መታጠብ ሳይኖርባት አይቀርም።

እናቴ ደረቅ ለቅሶዋን እያካሄደች ወደኔ ቀረበችና "አንተ-አረንዛ ሆድ፣ አባትህ አይደል የሞተው? ጥርኝ እንባ እንኳን ብትፈነጥቅለት ምናለ?..."ብላኝ ወደ ደረቅ ለቅሶዋ ተመለሰች።

የአባቴን ሞት አላመንኩም። እንዳው መቶ አመት እንደቀረው ከእሱ በላይ አምኛለሁ። እንደውም ፀሐይና ምድር ያልፋሉ፤ አባዬ ግን አያልፍም። ቆሞ ያሳልፋቸዋል።

"ምን አይነት ዘበን ጣ! የግታ ሙብራት፣ ማረፊያ መሬት የሌለበት ጣ!" ይላል።

በሳምንቱ ሲፈን መጥታ ለቅሶው አገረሸ። እናቴ ለቅሶዋ መድረቁን ትቶ ከዜማ ጋር ረጠበ። ሆድ የሚያንሰፈስፍ ዜማ ብቻ የሆነ ለቅሶ። አልፎ አልፎ ግጥም ጣል ታደርጋለች።

ጋሽ ተገኔ ጋቢያቸውን ተከናንበው ካፖርታቸውን እንደደረቡ "ወንዱ! ወንዱ!" ይላሉ። የአባቴ መርዶ ከመጣ ጀምሮ ለቅሷቸው ስፋክራ ያደላ ሆኖ ከርሟል። የአባቴ የፋክራ ዛር እሳቸው ላይ ሳይሰፍር አልቀረም።

"ወንዱ!" የሚሉት አባዬን ነው እራሳቸውን? ያምታታል። "ወንዱ!" የሚሉት ደሞ ሳያስቡት እንደተጎነተሉ ሁሉ ድንግጥ እያሉ ነው። እሳቸው "ወንዱ!" ሲሉ ታናሽ እህቴ አበባሽ "ልቤን" ትላለች። "ወንዱ!"፣ "ልቤን!"፣ "ወንዱ!"፣ "ልቤን!"

ሲፈን ማንኛውም ባልንጀራ እንደሚያደርገው እናቴን አቅፋ አለቀሰች። ቁመትና ሰውነት ጨምራለች። ትራ ምኞት ገረፍ አድርጎኝ አለፈ። ወዲያው ብልቴን ያጣሁበት ህልሜ ታውሶኝ እራሴን ቀጥቼ ምኞቴን ገታሁ።

የለቅሶውን መሟሟት የሰሙ የአካባቢው የለቅሶ ቤት ሱሰኞች ተሰባሰቡ። በገዛ እጃቸው መቀመጫ የሚሆን ነገር ከቤት እያወጡ ደረደሩ። ሳምንቱን ሙሉ እንዲሁ ነበር። ከበው ካርታ የሚጨወቱ አሉ። የጠጅ ታርቲመኞች ደግሞ እርቦ ይዘው መዋጩ ይጠይቃሉ፤ የቡና ሱሰኞቹ ቀልብ የሌለው ቡና (እናቴ እንደምትለው) በትልቅ ድስት

ይጥዳሉ፡፡ እማማ አጀቡሽ ደግሞ የእድር ተረኛ ወጠ-ሠሪዎችን ያስተባብራሉ፡፡ ድምፃቸውም እንደጡሩንባቸው "ጏሬያም" ነው፡፡ ጡሩንባው በጡሩንባ ስለሚነፋ ነው ቤት የሚንቀንቀው ስል አሰብኩ፡፡ አለበለዚያማ እንደእኔ የመንፋት ሙከራ አፍራም ፈስ ሆኖ ይቀርም አልነበር? ጡሩንባው እስታውሶኝ ብድግ ብዬ ቹቹን እየሁት፡፡ እኔን ሲያይ መደንገጡን ትቷል፡፡ ቀስ ብሎ ብድግ ሲል እኔን ለማናገር እንደሆነ ገብቶኝ ከእኔ ቤት ቀጥሎ ወዳለው ስንስል ጠጋ አልኩለት፡፡ ቀይቶ ደረሰ፡፡ ፊቱ ላይ ሪዝ ማንዣበብ ጀምሯል፡፡

"ደሞ፣ ደሞ፣ ደሞ አባትህ ከሚሞቱ ደሞ እናትህ ደሞ ድፍት ቢሉ ይሻላል ደሞ" ብሎኝ ለመመለስ ቀስ ብሎ ዞረ፡፡

ንዴት ለእፍታ ሸው አሰብኝ፡፡ ፊቴ ቅይም ሲል መቼ እንደወጣች ያላየኋት እናቴ ደጃፍ ቆማ በጣሙልኛ እየችኝ፡፡ በጉጥ ዓይኖቿ ልቤን ፋቀችው፡፡ ቃር የሚለቅ እይታ...

ወዲያው ቹቹ መንገዱን አቋርጦ ወደእኔ ተመለሰና....

"ደሞ፣ ደሞ ማን ደሮ ይገዛልናል? ደሞ..."

መለስ ስል ከቻይና ጋር አይን ለአይን ተገጣጠምን፡፡ በሰፈር ልጆች ተከባ ነጠላ ጋቢ ትከሻዋ ላይ ጣል አድርጋለች፡፡ የሆነ ነገር ገብቷታል፡፡ ለሷ ስል ቹቹን የማዳመጥ ዕዳ በላዬ ላይ ጥያለሁ፡፡ ሆድ የሚቀትረው የጅል በትር ሳይሆን የጅል ንግግር ነው፡፡ የጅል ንግግር ሆድ ይቀትር መባል አለበት ስል አሰብኩ፡፡

ሲፈንና እናቴ አፍ ለአፍ ገጥመው ያወራሉ፡፡ ስለየትኛው ቃል ቻ ይሆን? ስምረት የእንባ ቅረቷ ፊቷ ላይ መልስ እየደመቀ መጣ፡፡ ሌላ የአሲድ መንገድ አተመች፡፡ የቻይና ታላቅ (ረቂቅ) ከእናቴ ጀርባ ዱካ ላይ ቁጭ ብላ በከለላ ሰዎችን ታያለች፡፡ ረቂቅ ያላት አባቴ ነው፡፡ እውነትም ረቂቅ መልክ አላት፡፡ አንዳንዴ ከሰፈን ጋር ትነፃፀርብኛለች፡፡ ረቂቅ ግን ሆን ብላ ያጠፋችው መብራት እውስጧ አለ፡፡ ደብዛዛ ናት፡፡ አትታይም፣ እኔ እንኳን የማስታውሳት አንዳንዴ ነው፡፡ ልክ እንደዱር አበባ ማንም ሳያያት የምታልፍበትን ጫካ በዙሪያዋ የፈጠረች ይመስለኛል፡፡ ከእሷ ይልቅ እቴቴ ብትኮሳተርም ውስጧ ብርሃን አለ፡፡

አበዛሽ እንደእናት የምታያት እቴቴ ስር ተወሽቃለች፡፡ ትኩረት ፈልጋ ግጣቷ ሆድ ሆደን ይበላኛል፡፡ ትንሽ ከፍት ቦታ አይቼ ልቀላቀላቸው

ስል ቻይና በክፉ ዓይኗ አየችኝ። እንደእሷ ከእናቴና ከእህቶቼ ጨዋታ (ወሬ ላለማለት) ተነጥዬ እንድቀር ትፈልጋለች። በጣም ቅር እያለኝ ተመልሼ ወደ ክፍሌ ገባሁ። የዕቃ መአት ወለሉን ሞልቶታል። ኩባያ፣ ሰሃን፣ ማንቀራቀሪያ፣ ጭልፋ፣ ድስት... በግርጌ በኩል አልጋ ላይ ቁጭ ብዬ የጫማዬን ክር ሳልፈታ አወለኩት።

በተለይ የእህቶቼ ሞቅ ያለ ወሬ ሳይናፍቀኝ አልቀረም። ቁንጥንጥ የሚያደርግ ስሜት ይሰጣል። እህቶቼ ፍቅርን ሆነ ፀብን ተጋግዘው አንድ ሰው የማይችላቸው ሆነዋል። አንዳንዴ ብቻ ግራ የሚያጋባ ንግግር አላቸው። በወንድ ላይ ሲያሴሩ አንዷን በጋራ ይመክራሉ።

"እንግባ ቢልሽ አትግቢ"

"እሺ"

"እንውጣ ቢልሽ አትውጪ"

"እሺ"

እኔ ግራ እጋባለሁ። አትግቢ ካሉ ውጪ አይደለም እንዴ? አትውጪ ካሉስ ግቢ አይደለም? ተመካሪዋ እህቴ "አትግቢ" ስትባል እውጭ ቆማ ትታየኝና "አትውጪ" ሲሏት ደግሞ ቤት ውስጥ ሳጥን ላይ ቁጭ ብላ ከቤት ላለመውጣት ስትታገል። ምንድን ነው ውጪ፣ አትውጪ? እንዴት አይመክሯትም? እላለሁ።

ከክንውኑ በኋላ ተመካሪዋ የምትሰጠው ማብራሪያ ሌላ ግራ አጋቢ ይሆንብኛል።

"እንግባ ሲለኝ እንቢ አልኩት"

"ጎሽ!"

"እንውጣ ሲለኝ እንቢ አልኩት"

"የታባቱ!"

እህቶቼ በጋራ ያበዱ ይመስለኛል። ወንዱ በግቢና በውጪ ተሰንጥቆ ቤት ውስጥና ውጭ ሲንገዋለል ይታየኛል። በመጥፎ ምክር የሰው ሰው ሰንጥቀው እረፉት እላለሁ።

አንዷ እህቴ ይዛ የመጣችውን ወረ እንደጨፈጨፈት ከእሷ ለንሻማ...

"እ...ድ!"

"አትይኝም!"

"እኔ አላምንም?"

"እስቲ" አንዷ እጇን ትዘረጋለች

"ታስ ይሙት" ሲላዋ ትምላለች፡፡ ይሄኔ እናቴ ከውጭ እየገባች "ምንድን ነው?" ትላለች፡፡ እሷ የማትሰማው ከሆነ በአንድ ቃል፡፡

"ምንም!" እንላለን፡፡

"ምንማችሁ ይጥፋ! ታስ ይሙት ስትሉ አልሰማሁም? ቂጣችሁን ስትገጥሙ መከራ፣ ስትባሉ መከራ..."

እውነቷን ነው፡፡ እህቶቼ ወደሊሎች ሲያዩ ትከሻቸው ይገጥማል፡፡ እርስ በርስ ሲሆን አይተዛዘኑም፡፡ ጉልበት አይተባበሉም "የምኝ ጉልበት ማድረግሽ ነው?" በማለት አንዷ ለአንዷ እንድታጥብላት ያስቀመጠችውን ልብስ ታሽቀነጥራለች፡፡ ትባት፣ ሽቶ፣ ላሙና፣ ጥፍር ቀለም፣ የፀጉር ጌጥ፣ ኩል፣ የእጅ ጌጥ፣ የእግር አምባር... የየግላቸውን አደራጅተዋል፡፡ እናቴ ይሄን ስታይ...

"የነጋዴ ሲሳይ መሆኙ፤ ምናለ አንድ እቃ ለድስታችሁም ከምትገዙ ብትዋዋሱ? አመል እቴ..." ትላለች፡፡

እህቶቼ ግን አይሰሟትም፡፡ አንዷ የሌላኛዋን ከነካች "የቢዘን ፋርጎ" ነውጥ ይበታትነዋል፡፡ እስከመደባደብ ይደርሳሉ፡፡ እናቴ እንኳን የአንዷን ሽቶ አንስታ ከተርከፈከፈች፣

. "ምነው የሰምረትን አትነኪም? ረቂቅም አታቀምሰሽም፡፡ እኔ ላይ ትበረቺያለሽ"

"ጥ! ቀልቤ መጥሮ ነው፤ እኔ የወደድኩት መዘዙ ብዙ ነው፡፡ ላንቺው ብዬ ነው፤ሙች" ትላለች እናቴ፡፡

እህቶቼ ለእኔ ሲሆን ብቻ የማቶጥቡትም የሚሰስቱትም የለም፡፡ መነጠል፣ ብቸኝነት ተሰማኝ፡፡ በእኔ ክፍልና በትልቁ ቤት መካከል ብዙ

ኪ.ሎ ሜትሮች የተዘረጋ ያህል ናፍቆት አፍትልቶብኝ። ወንድነት መነጠል ነው? አደን ሄዶ መነጠል? ጦር ሜዳ ሄዶ መነጠል? ሲራራ ነጋዴ ሆኖ መነጠል? አብሮ እያሉ መነጠል?

ሰትቶ ብዬ ወደ ክፍሌ ስገባ ሴቶቹ ቀንጋሚታው ይመጣሉ ብዬ ነበር። ባይሆን አንድ በአንድ አቴቴና ሲፈን ብቻ ብለው የሚያዩኝ መስሎኝ ነበር። ማንም የለም። እኔን ችላ ማለት ጀምረዋል ማለት ነው?... በረደኝ።

እኔም እንደ አባቴ ግማሽ እድሜዬን በበረሃ አሳልፌ ከበረሃ ጅኒዬ ጋር ባዕድ የሆንኩበትን ቤተሰብ መቀላቀል። የጠጅ ለማግኘት ተስማምጭ፣ ተሸቀጥቋጭ ሆኜ እንዳላሳጣቸው ፀዳዳ እየሰበሰብኩ... ይሄ ነው ወንድነት?...

እንጀት ይበላል፣ ወንድነት። የማን እንደሆን የማላውቀው ዑዑ በጦርነት እያስተናገድኩ፣ ማን እንደሚበላው የማላውቀውን እያደንኩ፣ ማን እንዳተረፈ ባልገባኝ ንግድ እየኳተንኩ ማርጀት...

...ከቤት ውጭ እየርከርኩ ለመኝታ ስገባ እየተለማመጥኩ "ቶይ እንጂ ሲፌኔ፣ አሁን እኔ ያልኩትን ተቀም ነገር ፅፈሽው?"

"ዝም በሉ አንቱ መልቲ!..." እየተባልኩ።

ማን አልኩ? ሲፌኔ? ሲፈንን ለማግባት የሆድ ውስጥ ክቅድ አስኘ ማለት ነው? ለምን ተከትላኝ ሳትመጣ ቀረች? ንብታ በፊምዎጥ እያየች "ቃሰ?" ለምን ሳትል ቀረች? እንዴት ያለጉዳይ ሰሚን ደጋግሞ ቹፉን ሳትሆን ቀረች?

ሙሰጤ አንዳች በገና መሰል ነገር ተደረደረ። ሕንጹ እናቴ ለቅሶ ብዙም ቃል፣ ብዙም ግጥም የሌለው ራሮት። የቀዳፊን ዚማ ድግግሞ ገለጥ-ገለጥ እንዳደረጉት ሁሉ ብልጭ አለ። "ሲፈን" በእኔ ጨክና ትያለቅሳትም። ግን በእኔና በእህቶቹ መካከል የተዘረጋውን ብዙ ኪሎ ሜትር ጫካ፣ ጅረት፣ ሜዳ፣ ዳገት... አቀራርጧ አስከትዶርበ ነው። ከናዝሬት እንደምትመጣው ዘብሎንን፣ ንፍታሌምን፣ ገሌ.ሳን፣ ቶፍርናሆምን፣ ደብረዘይትን... እንደምታቀራርጥ። እንዲሁ...

...ጥበቃ፣ ኮሽታን አገዘፍኩ፣ ሴኮንድ ለጠጥኩ፣ አይኔን ተክልኩ፣ የልቤን ምት አዘገየሁ፣ ኢምንት ውስጥ ዋኘሁ...

እቴቴ ሰው ሰራሽ መኮሳተር አስቀድማ ገባች። እንደ ዓይን ስውር በትር ሁሌም የሚቀድማት መኮሳተሯ ነው።

"ምን ሆነሃል? አሞሃል? ምንድን ነው?..."

እቴቴ የሲፈን መምጣት ትንቢት ናት። እኔ በውሃ... እሷ ግን በእሳት የምትል መሪ ኮከብ።

"ስማ እንጂ..." ያስቀሰችበት ዓይኗ አብጧል።

"እ?..."

"እስኪ ቀረብ በል"

ወደ ግርጌ ተጠጋሁላት። ግንባሬ ላይ መዳፏን አሳርፋ ሙቀቴን ለካችና "ኦ ሆሆሆሆይ" አለች።

በሲፈን ከጠረጠረችኝ ጀምሮ ይሄ ትርጉም አልባ ቃል ከአፏ እየተዝለገለገ እንደወጣ ነው። ቃሉ ትርጉም ከሌለው እንዴት ስሜት ሊፈጥር ቻለ? "ትሽማቀቅ" የሚል መልእክት እንዴት ኖረው?

"ኦሆሆሆሆይ" ደግማ ጠጣች።

አሁን ሲፈን ደመናውን ገለጥ ገለጥ አድርጋ ቤቴን ታፀዳየዋለች። የእኔ እህቶች ጉዶች ናቸው መቼም፤ ሲፈንንም ይመክሯት ይሆናል፦

"ቃለ እንውጣ ካለሽ እንቢ በይው"

"እሺ" (ሲፈን)

"ቃለ እንግባ ካለሽ እንቢ በይው"

"እሺ" (ሲፈን)

ከዚያ እንደዚያ ሰው በእህቶቼ ምክር "በውጪ" እና "በግቢ" ተሰንጥቄ ለአንዱም ሳልሆን መቅረት።

ሲፈንን ስጠብቅ ቻይና መጣች።

"ጠጥተህ ከወንዶቹ ጋር አትጫወትም? ሂሽ!"

"እሺ" አልኳት እሷን ደግሞ እንዴት ወደሴትነት መቀየር እንደሚቻል እያሰብኩ። የእኔን ያህል የእሷ ወንድነት አልተነጠረም። እንደውም የየሰዉ አስተያየት ላይ መደነቅ አለ። አባታችን ለቅሶ ላይ እኔን ለማፅናናት የመጡት የትምህርት ቤት ጓደኞቼ ሴቶች ብቻ ናቸው። በተለይ እምቢቱ ሰብለ፣ ሰአዳ፣ ወይኗ፣ ሂሩትና ፍሬ ደጋግመው ስለመጡ ቻይና መንገድ ላይ ጠብቃ አስፈራራቻቸው።

"ሂሽ! ሁለተኛ ከእሱ ጋር ባያችሁ" አለቻቸው አሉ።

እንደተለመደው ብዙ ኪሎ ሜትሮች ሸሹኝ። ሌሎቹንም አሸሹ። ይሄን የነገረችኝ ሰአዳ ናት።

"ወይኔ በአላህ፣ ምን አይነት ሸይጣን ናት?" አለችና ግራቀኝ እየተገላመጠች "ደሞ እንዳትመጣብኝ" ወደ ገኸ መሬቷ ብዙ ኪሎ ሜትር አፈገፈገች። ሴቶችን መራቅ ወንድ ያደርጋል? ከእነ ሰአዳ ጋር ጥሩ የጓደኝነት ጊዜ አሳልፈናል። ወንዶች የላኩላቸውን የፍቅር ደብዳቤ በጋራ እስከማንበብና ጃስ ብሎ በጋራ እስከመሳቅ።

"ካ ካ ካ ካ ካ ካ..."

"እ ሃ ሃ ሃ ሃ ሃ..."

ወንዱ በ"ካ" እና በ"ሃ" አሩምታ እየተመታ ላለመውደቅ ሲንደፋደፍ በአፍጢሙ የሚደፋው ሌላ ሳቅ ይላክበታል። ከእነ ሰአዳ ጋር አልለይም ነበር። እንደውም ስድስተኛ ክፍል ይመስለኛል፤ ስፖርት ክፍለ ጊዜ ወጥተን እካላችንን በሩጫ አሟሟቅን። በመቀጠል መምህሩ ወንድና ሴት ተከፋፍላችሁ ሩጫ ተወዳደሩ ሲል እኔ ከእነ ሰአዳ ጋር ቀረሁ። ትርጉሙ አልተገለፀልኝም ነበር። ተማሪው ሁሉ ሳቀ። መምህሩ:-

"አላዛር ለዛሬ እንኳ ወንድ ሁን" አለኝ።

ተሳቀ፤ እኔም አብሬ ሳቅሁ። ታዲያ ሲፈን ከዚህ በላይ ምን ተናግራኝ ቀጠቀጠኝ? አስነጠሰኝ? እንባ በእንባ አደረገኝ?....

...እየተንቀራፈፍኩ ከአልጋ ብነሳም፣ እየተንቀራፈፍኩ ጨማ ባሰርም ሲፈን አልመጣችም። እየቀፈፈኝ ወጣሁ። ደጃችን ገበያ መስሏል። ካርታ፣ ጠጅ፣ ቡና፣ ነገር...

## ፲፮

## እኔ፣ ለቅሶና ቀልድ

ካርታ፣ ጠጅ፣ ቡና፣ ነገር....

...የጡረታ ድልድይ ሰዎች ሀዘንተኛ በከፍተኛ ደረጃ የሚያፅናኑ ይመስላሉ እንጂ ተፅናኝዎቹ እራሳቸው ናቸው። በቋሚ ሀዘንተኝነት ተመዝግበው ሳለ ጊዜአዊ ሀዘንተኛን ለማፅናናት ይሰባሰባሉ። ፊታቸው ይሄን ይመሰክራል። ሽማግሌ የመሰሉኝ የእኔ እኩዮች ሆነው ያገኘኋቸው አሉ። በተለይ ከጠጅ ታርመቲኞች መካከል።

ፊታቸውን ጠጅ እንደ-ብል በልቶ ካነተበው መካከል አንድ በሰዎች የተከበበ ተናዳፊ ይታየኛል። አብዛኛዎቹ ወጣቶች ጠጅ ያስቀዱ ቢሆንም ወደአሱ ኩባያ ይገለብጣሉ እንጂ አይጠጡትም። አይጥ የቀደደው ብርድ ልበስ በመሰለ አፉ አንዱን ሲነችፍ ሌሎቹ ይስቃሉ። እናቴንና እህቶቼን "የ-ብዜን ፋርጎ" ሲል ቅፅል ሰም ያወጣላቸው እሱ ሳይሆን አይቀርም።

"ትናንት ጉድ አየሁ" አለ

"የምን ጉድ?" አሉ እማማ አጀቡሽ በጡሩንባ ድምፅ "የምን ጉድ ነው ያየኸው፣ ሽክና"

ቅፅል ሰሙ ጠፍቶኝ ነበር፣ አዎ ሽክና።

"እናቴም ያለቀሰችበት አይናን አጨንቁራ ለመሳቅ ተዘጋጅታለች። ሲፈን እንድታዳምጥ በክርኗ፣ ጎሸም አደረገቻት።

"ይሄ የእኔ ጓደኛ" ብሎ አጠገቡ የተቀመጠ ልጅ መሰል አዋቂ ላይ ጠቆመ። ፊቱ ካልታየ የሰባት ዓመት ልጅ ቢመስል ነው፤

"በጠዋት መጥቶ ሁሌ ጠጅ መጠጣት አይደብርህም ሽክና?" አለኝ።

"ወድጄ ጠጅ አልጠጣ፣ አጥቼ እንጂ ስለው።

"በልና፣ ዛሬ ይለፍልን ብር ይገኘለሁ ማስተምስ ሆቴል እንጠጣለን እጋብዝሃለሁ" አለኝ።

"ጥሩ፣ ብዬ ተከተልኩት። ሄድንና ሁለተኛ ፎቅ ላይ ይዞኝ ወጣ። ግማሽ ጠርሙስ ውስኪ አዘዘ። ከሁለት ብርጭቆ ጋር በረዶ መጣልን። እንዴ ቀድቶን እንደጠጣን፣ ሽንት ቤት ጠየቀ እስተናጋጇ በምልክት ሲጠቁመው አሳየኝ ብሎ ደነፋ። ሲቀድምለት ወደእኔ ጆሮ ጠጋ ብሎ፦

"ዘላለም በጠጅ ከመኖር በውስኪ ታጅቦ መሞት ይሻላል። አይሰኝም። ምን ማለቱ ነው? ከማለቴ በቅልጥፍና ተንደርድሮ ከሁለተኛ ፎቅ ዘለለ። እየተጯጯህን መሬት ስንወርድ አጣነው። የበለጠ ተደነጋገጥን። በኋላ ‹እዚህ ነኝ› የሚል ድምጽ ተሰምቶ ቀና ብንል አራተኛ ፎቅ ላይ ነው። ለካ ሲወድቅ እንደፌስታል ንፋስ ተቀብሎ ወደላይ ወሰደታል ጓደኛዬ ወደላይ ወደቀ።"

ሁሉም ሳቁ። የእጀቡሽ ባስ።

"በሉ እናንተ አውርዱት ብዬ ወደቤቴ"

"አይ ሽክና!" እንደበት ያለው ጡሩንባ።

"እትዬ እጀቡሽ?" አለ።

ወደሳቸው ሊዞር እንደሆን ሲገባቸው ቆጣ ብለው

"ምናባክ?" አሉት። ቀልድ ፊላጊነታቸው ከፊታቸው ሳይጠፋ

"አሰከሬን ሲወጣ ሲል ሴቶች ከፊት ከፊት፣ ወንዶች ገቡ-ገባ ይላሉ አሉ"

"ታዲያ አስከሬን ሴት አይሸከም" አሉና ሌላ ትርጉም ሲመጣላቸው እሳቸው ብቻው ሳቁ።

"አይ ሽክና ፣ ያንቶ ነገር..."

"ሽክና በመሀል የማይጎድል ኩባያውን አይዋ ወደቀደደው አፉ ያመላልሳል።

መለሰ ብዬ ሲፈን ወዳለችበት አይኔን ላኩ። ከእህቶቼ በልጣ የእናቴ የቅርብ ሰው ሆናለች። በቅርብ ቀን "ታለ ፀሙት" እያለች መማል ትጀምራለች የሚል ስጋት ያዘኝ። አይኔን ወደሴቶቹ በላኩ ቁጥር ቻይና ትታወሰኛለች፣ እየኋት እያየችኝ ነው። በአይኗ "ሂሽ!" አለችኝ። የምታስለጥነኝ ሰድንግላዊነት ነው እንዴ? ስል አሰቤ ውስጤ ተነጫነጨ።

"አንዱ ሩፋኤል ማር ነጋዴ ደሞ ቻይናን አፍቅሮ አኛጋ አይመጣም? ኸ ከ ክ ከ..." ሰው ሁሉ ሳቀ። አንዳንድ ቀልድ ገና ሲጀመር የሚያልቅ አለ። ቢሆንም ቻይና ቆጠች።

"ሂሽ! ሽክና ዋ! ምናባቱ!"

ሽክና ቀልዱን ቢያቋርጥም ገና ሲጀመር ስላለቀ ሰው ሁሉ በጣም ሳቀ። ያልሳቁት ቻይና እና ሳኮ ብቻ ናቸው። እናቴ ብሳለች፤ ቢፈን ስወረት ፍቅሯ እናቴን እየታከከች ትስቃለች። በዚህ ፀባዩዋ አንድ ቀን እናቴም ከወደደቻት በኋላ እንደእኔ መስለ ብላ ሲታያት ትቀርጣለች።

ሳኮ ብድግ ብሎ ሽክናን ተጠጋው። ሲሄድ እንድስ በሚያክል እጁ የሚራመድ ይመስላል። እግሩን እንዳንፈረከከ፦

"ጆ! በሌላ የለመድክውን፣ ከቺ ጋር ቀልድ... እ? ገብቶሃል?... ስምንት ቦታ አጣጥፌ እ-ገብቶሃል?..."

ቢመታውና የሚገላግለው እንኳን ያስ አልመሰለኝም። ቻይና በገዛ ፀሏ መልሳ ሳኮን ተቆጣችው

"ሂሽ! ይሄ ደሞ... ሂሽ!" እያለች ወደውጭ ገፋፋችው፤ እፍታም ሳይቆይ ሳኮ ደንግጦ እየሮጠ፣ በረጅም እጁ መሬት እየጠረገ ተመለሰ።

"አብዮት ጠባቂ!!" አለ።

"ዎ-አፈሳ ነው?" አለች እናቴ

"አዎ!" አሉ ጋሽ ተገኔ ሳያስቡ እንደተናነቱ ሁሉ በፋክራ። "እረስቼው ሳልነግራችሁ፤ ዛሬ ነው..."

ወንዶቹ ተንጋግተን እኔ ቤት ገባን። ሴቶቹ በእግዶ መረነት የመጣውን ለመጋረጥ ወደ ሰንስሉ መተሳሰሪያ ተጨን። ቀይቼ ቀይቼ ቢፈን ትዝ አለችኝ። እንዴት ሰሸሸ፤ እንዴት ሰንደፋደፍ ይሆን ያየችኝ? አሳንሰር ቤቴ በፊሪ ኀረምሳ ተጠቀጠቀች። ሽክና እና ነፋስ የወሰደው አዘውንት መሳይ ጓደኛውም ሽተው እኔ ስር ቁና ቁና ይተነፍሳሉ። ሳኮ ቀድሞ ገብቶ እንዴት በር ላይ እንደቀረ ገረመኝ። መለሰ ባደረገው ደጃፍ ወደውጭ በፍርሃት ያያል።

አፈሳን በመድፈር የተጀመረው ወንድነት አፈሳን በመፍራት ይረጋገጥልኝ ይሆን? ለመሆኑ ቢፈን ምን ታዘበች? አፈሳን ብደፍር በቀጭን ድምጿ ጮሃ፣ በቀጭን እጆቿ ከኋላዬ ታቅፈኝ ኖሯል? "ታላ?" ትለኝ ኖሯል? "እዚህ ልደር?" ትለኝ ኖሯል?... ከዚህ ሁሉ በኋላ ብዘምት እንኳ አትጎዳ ኖሯል?...

# ፲፯

## እኔ፣ ሽክናና ቅኝ ግዛት

“ወታደሩን በምን ያህል መጠን እናጠናክረው? ለእናት አገራችን በአስቸኳይ እንድንደርስ፣ ይሄ ቀዳዳ ሳይከፈት... ነገር ግን በሕግ እንበይናለን፤ እናስፈፅማለን እንላለን... ገና ጦር ሜዳ ሄዶ ጠላቱን አይቶ መግደሉን ወይም መሞቱን ሳያውቅ ከመኪና ላይ በራሱ እየወረደ የሚሞት ወጣት ነው ያለው። ምንድን ነው ይሄ? ከኢትዮጵያ ነው እንዴ የበቀለው?...”

አሉ አሉ ጓድ ፕሬዝዳንት መንግሥቱ ኃ/ማርያም።

ከፍርሃታችን አለማፈራችን።

ከእሳቸው በላይ እኔ እርሬአለሁ። “ምንድን ነው ይሄ ታለ? ከኢትዮጵያ ነው እንዴ የበቀለው?” ብያለሁ። እሳቸው አጣለሁ ብለው ከሰጉት በላይ እኔ ሰግቻለሁ። “ፍቅራችንን በምን ያህል መጠን እናጠናክረው? ለሲፈን በአስቸኳይ እንድንደርስ፣ ይሄ ቀዳዳ ሳይከፈት...” ብያለሁ።

የቱ ቀዳዳ? መንግሥቱ እኛን የሚፈልጉን እንደ ጋሽ ሩፌ ጭቃ፣ ቀዳዳ ለመድፈን ነው እንዴ? እያነሱ ሊመርጉን፤ ትንሽ ሽንቁር ላይ ልክክ ስንል “ለእናት ሀገሩ አኩሪ መስዋዕትነት ከፍሎ...” እንባላለን እንደ አባቴ፤ አይ ወንድ!

እነ ሽክና እኔ ቤት ሦስት ቀን አደሩ። ሽክና በእናት ሀገሩ እጅግ አድርጎ ተበሳጨ፤ በተለይ የጠጅ አቅርቦት ከተቋረጠ የኢትዮጵያን የሶስት ሺህ አመት ነፃነት ይገፍፋል።

“ተገዝተናል!” ይላል ቀበኛ ያኘከው ጨርቅ በመሰለ ፊቱ ላይ ብስጭት እያስነበበ።

ፈርተን የተሸሸግን ቢሆንም አንዳንዶች ይሄንን ሀሳብ በጀግንነት ይዋጋሉ።

"እሲዙ፣ እኔ አረታችኋለሁ" ይላል ሽክና።

ጨዋታ ሞቅ ሲል ሴቶቹ አብዮት ጠባቂ ከሚጠብቁበት ከዋርድያ ነቅለው ይመጣሉ።

"አንተ ምን ታሲዛለህ?" ምንም እንደሌለው ያወቀ።

"አስክሞት ቀጥቅጡኝ" ይላል።

ሽክናን ለመምታት ሰበብ የሚፈልገው ላኮ የመጀመሪያዋን ሃያ አምስት ሳንቲም ይጥላል።

"ይኸው፣ እዩ ደሞ!"

"እንምርሀም ግን"

"አትማሩኝ"

"ከሁለተኛ ፎቅ እንደመዝለል ይቆጠራል"

"ንሩስ ይወስደዋል"

ሳቅ!!

ሽክና ለውርርድ የቀረበውን ፍራንክ አይቶ "ለዚችማ ብዬ ውርርዱን አላበላሽም" አለ።

እልህ የያዛቸው ጨመሩ።

"አሁን ይቻላል! ለምንት ብርሌ ጠጅ በቂ ነው።"

"በውርርዱ ካላሸነፍክ ተመላሽ ነው አትጠጣ"

"ለሱ ግድ የለም።" አለና ቀጠለ። "እዚህ ስፈር ያሉትን ሰሞች ስነግራችሁ መዝግቡ"

"እሺ," መዝጋቢ ተመደበ

"ፋፊ" አለ

"ፋፊ" ተመዘገበ

"ዎሌ፣ መዝገቦችሁ? ቾሩ፣ ዶሪን ሳኒ፣ መዝገቦችሁ! ድገሙልኝ፤"

"ሩፌ" ሲሉ

"ሩፍ ከሚለው እንግሊዘኛ ነው የተገኘው። ጣሪያዬ ማለት ነው"

"ዎሌ"

"ዎል ከሚለው እንግሊዝ ቃል የተገኘ ነው ወለሌ"

"ቾሩ"

"ቾር ወንበር ነው። ወንበሬ"

"ዶሪ"

"ዶር፤ በሪሁን ማለት ነው"

"ሳኒ"

"ሰን፣ ፀሐይ አይደል ፀሐዬ ማለት ነው። ለነዚህ ኢትዮጵያ የእንግሊዝ ቅኝ ተገዢ እንደነበረች በዚህ ይታወቃል።"

የሚስቀው ሳቀ፤ የሚናደደው ተከራከረ።

"በእንግሊዝ ቀኝ አልተገዛንም ካለች እንዴ እኔ በማስረጃ ተከራከሪ"

"ነው እንዴ? አንተ? እንግሊዝ ገዝታናለች?" እሱ ሳቀ። "ወይኔ ቀመውዜን አሰበሉኝ፣ ምን አስቀኛችው? ወይኔ የሻሚታዬን..."

ሽክና ጠጁን በሴቶቹ አስላኩ።

በሁካታ መካከል እናቴ ትመጣና እንዴ በማልምጫ ታነሳናለች። "እኔ እዚህ ነፍስና ስጋዬ ይቦጨቃል እናንተ ታወካላችሁ? እንዴት ያለ ሀሳብ የለሾች!"

ቻይና ስለአፏ የተጀመረው ወሬ እንዳይቀጥል ብቻ ለጥበቃ የተቀመጠች ይመስላል። ለመሳቅ ትሞክርና ሽክና ሲያያት ትክሳተራለች። ያ ማር ነጋዴ ማን ይሆን? ከእኔ የባሰ ሲፏፈርድበት አልቀረም። ማር የነካካ እጁን ወደኋላ አድርጎ ይሄኔ...

ፈገግ አልኩ። ለካ ቻይናን እያየሁ ኖሯል በአይኗ "ሂሽ!" አለችኝ፤ ገብቷታል።

በዚህ መካከል በር ተንኳኳ፤ እንኳን መንኳኳት ከሸታም መጋኛ ከጀመረ ቆይቷል። ሁሉም ተመሳሳይ ማሰብ እጣ ፈንታው ሆኗል፦

"አብዮት ጠባቂ! እኔ እናቴ የትሄደው?"

አልነበረም። ከጥቁር ማውሊ የተቀረፀችው የቹቹ እናት ብቅ ብላ አሩር የመሰለ የጉጥ እንጨት ኳሰ አይኗን አቅለበለበች። በጣም አድርጌ ደነገጥኩ። የቹቹን እናት እንኳን እኔ ቤት ደጃፍ ላይ የምታዋስነን የአሲፈ መንገድ ተሻግራ አይቻት አላውቅም። ሁሉም ጋጥ ብሏል። እንደእኔ እሱም ይረዳታል?

በጥንቃቄ ተናገረች፦

"ቹቹን እንዳያፍሉት ከእናንተ ጋር ይደበቅ"

ሁሉም አንድ ላይ ሳቁ፤ እኔም ሳቅሁ። የተገረመው አብዮት ጠባቂ ቹቹን ሲያምረው ይችላል፤ የጨነቀው ጤና መርማሪ ያስልፈው ይሆናል፤ እጥረት ያጋጠመው አሰልጣኝ "ባይሆን እንኳን ስለሚያቀረቅር ፈንጂ አምካኝ ይሆናል" ይል ይሆናል። እና? የቹቹ እናት የማውላ ድንጋጤ ብታሳይ ይገርማል።

"ሂሽ!" አለችኝ ቻይና። ወደ ቹቹ እናት ዞራ "እምጨዉ ከኛ ጋር ይሁን" አለቻት።

"ይኸው መጥታል፤ ቹቹ ቀስ ይላል እንጂ ምንም አልሆነም፤ ቢያፍሱብኝስ? ሰው ሁሉ ልጁን ሲደብቅ..." ዘወር ስትልስት ቹቹ አቀርቅሮ ወደ ውስጥ ገባ። በቻይና ግልምጫ መሬት የተነጠፈው ፍራሽ ላይ ቦታ ከፈት ከፈት ተደረገለት።

"ደኅና፣ ደኅም፣ ደሞ... ሲወስዱኝ ደሞ ደሞ ሲያፍሱኝ" አለ።

በአልዘፃምንም ፍርሃት ውስጥ ያለው ወንድነት ዓይነቱ ብዙ ሆኖ ታየኝ። ጓድ ፕሬዝዳንቱ መንግሥቱ እንዳሉት ኢትዮጵያ በትዳዳ ብዙ ወንፊት መስላለች፤ መለሰኛዎቹ ወጣቶች እዚህ (ምንድን ነው የማስበው?)

ቹቹ የቤቱን የጨዋታ ስልት አዛብቶት ኖሮ ፀጥታ ሰፈነ፤ ፀጥ-እረጭ።

ቹቹን ፊት ለፊት አስቀምጦ መመልከት ህይወትን የማዘግየት ምላሽ አለው። ቹቹ በዐጥታና በቀስታ ፕላኔትንና ቅንብሯን ያዘገያል። አንድ ደቂቃ በቹቹ ዘንድ አስር ደቂቃ ሳይሆን አይቀርም።

ጨነቀኝ፤ ጭንቀቱ ያባባሰው ቹቹ እኔ ቤት ለማደር ቢወስንስ? የሚለው ሀሳብ ነው። እናቱ እኔ በር ላይ ቁጭ ብላ አስር ጊዜ ከፊት እያደረገች በጉጥ ዓይኗ ትቃኘዋለች።

በቹቹ አቆጣጠር አንድ ሌሊት አስር ሌሊት ነው። ታዲያ? ምን? ሽክና እንኳን ቹቹን መዘንጋት አልቻለም። ዐጥታ ሲሰፍን ሌሊቱ በመቶ በሚቆጠሩ ሌሊቶች ሊመነዘር ይችላል።

ወደ "ትልቁ ቤት" አፈገፈኩ።

እናቴ በማንደጃ አሳት እንተርክካ የግቢውን መውጫያና መግቢያ ከነልጆቿ ዘግታለች። ልጆቹና ጥቂት የሰቅሶ ቤት ሱሰኞች ከበዋት ያወጋሉ። ሲፈንን በአይኔ ፈልጌ አጣኋት።

"ትልቁ ቤት" ጨላልሟል። ይሻላል። እዚህ በዐጥታና በቀስታ የፕላኔት ቅንብር አልተነተተም። አባቴ አልጋ ላይ ወጣሁ አባቴ ከትዝታው ውጭ እዚህ አልጋ ላይ ጠረኑ እንኳን አልቀረም። አንድ ወደ ልጅነት ያደላ ፎቶው ጥቁር ጨርቅ አዘቅዝቆ ግድግዳውን ሙጥኝ ብሏል። ከአባቴ መርዶ ይልቅ የአባቴ ፎቶ ሞቱን የሚያረጋግጥ ይመስላል። ለመጀመሪያ ጊዜ ለአባቴ ሀዘን ተሰማኝ። በቹቹ የዘገየ ፕላኔት ህግ መሰረት ከመርዶው አስር ቀን በኋላ ላለቅስ?...

ቤቱ የበለጠ ጨለሞ ቻይና ገባች። "ሂሽ!" ትላለች ብዬ ስጠብቅ በዐጥታ ወደ እኔ መጣች። አልጋው ጫፍ ላይ ተቀምጣ አቀረቀረች። ድንገት የደከማትና የታከታት ትመስላለች። የሆነ ጥፋቷ የተገለጠባት። ትከሻዋ ሲንቀጠቀጥ እያለቀሰች መሆኑ ገብቶኝ ማመን አቃተኝ።

እንደእኔ ዘግይቶ የአባቴ ሞት ተሰማት?

"ምን ሆንሽ? እ? ቻይና..."

ዝም

"ንገሪኝ በእናትሽ፣ ምን አጠፋሁ?"

"አንተ አይደለህም"

"እ?"

"ቹቹ ነው"

"ምን አለሽ?"

"ምን ይለኛል? እሱን ሳየው ያመኛል..."

"ለምን?" እንዴም "ሂሽ" አላለችም።

"እናታችን ናት እንዲህ ያደረገችው"

ልቤ ላይ ፍልጥ ገባ። "እንዴት? ለምን? መቼ?"

"እኔ ብቻ ነኝ የማውቀው፤ አባታችን የለም፤ ሌሎቹ ወደ ኬላ ሄደዋል፤ እኔ እምኝ አልጋ ላይ ነበርኩ። እናቴ ገርበብ ያለውን በር ከፍታ ገባች። አንተን አዝላለች፤ አንድ እንግዳ ሰው አብሯት አለ። ሰውየው እዚያ ተቀመጠ፣ እናታችን አንተን አውርዳ አስቀመጠችህ፤

"ሂጂ ልጁን አምጪው" አላት ሰውየው። ሄዳ ቹቹን ይዛው መጣች። ሰውየው ምን እንዳደረገ አላውቅም፤ እኔ ፈርቼ ተኸናነብኩ። በቅርብ ቀን ውስጥ አንተ ዳንክ ቹቹ ታመመ።"

"እና? እኔ? ቹቹ? እ... እ-ኔ?..."

• • •

የማይታመኑ ነገሮች ለሳቅ እንጂ ለሀዘንና ለፍርሃት ይፈጠራሉ ብዬ አስቤ አላውቅም ነበር። ሽክና አምስት ዓመት ወንዝ ውስጥ የተዘፈዘፈ ጨርቅ የመሰለ ፊቱን አኮሳትሮ የሚናገራቸው የማይታመኑ ነገሮች ፍፃሚያቸው በሳቅ መታጀብ ነው። ቻይና የነገረችኝ የማይታመን ነገር ግን አስደንጋጭነቱ የከፋ ነው። የተፈጥሮ አደጋ ይመስል የሥሩን ወደላይ ከሚገለባብጥ ኃይልና ሁሉን ከሚውጥ ሰፊ አፍ ጋር ተጋፈጥኩ።

አሁን ሳስበው ያንን መጥፎ እውነት እንዴት እንደተጋፈጥኩት ግራ ይገባኛል። አንዳንዴ ከአቻነት የበታችነት ከከፋ አደጋ የማምለጫ ቀዳዳ አለው እላለሁ። ነገሮች ጉዳት ከማድረሳቸው በፊት መውደቅ፣ ወይም የነገሩን ክብደት በቅጡ አለመረዳት ከማምለጫ መንገዶቹ ውስጥ ናቸው።

መጀመሪያ ይሄን ስሰማ እንደሸክና ጓደኛ ወደ ላይ የወደቅሁ መሰለኝ፡፡ ከሁለተኛው ሰማይ ወደ አራተኛው ሰማይ ኸው ብዬ ኮርኒሱ ላይ ተፈጠፈጥኩ፡፡ ቻይና እየቀለደች እንዳልሆነ ገብቶኛል፡፡ ብዙ አመታትን የተውሰኩትን ጉድ ውስጥ ከትታ ያስደገችውን ፍርሃት እኔ ላይ እንደገለበጠች አውቄአለሁ፡፡

"እንዴት እንዲህ ሊሆን ይችላል?" አልኳት፡፡

"ሆስፒታል ቁሉን ጠየኩት፡፡ አጣርቶ ነገረኝ፡፡ እንዲህ አይነት አለ፤ ግን በመንታዎች መካከል ነው አለኝ፡፡"

"እና? ቹቹ ከ..."

"ዘመዳችን ነው፡፡ የቹቹ እናት እናታችንን ተከትላ የመጣች ዘመዳችን ናት፡፡"

ምስትና በሌለው እውነታ ውስጥ በተጠራጣሪነት ከመኖር ውጭ ሌላ ምን አለ? የስንዱን ዕጣ-ፈንታ ወደሌላ ከማዘዟር የበለጠ የእውነታ መፈለስ የትኛው ነው? የመሬት መስመጥ? የሰማይ መደርመስ? የአድማስ እንደተራብ አፍ መከፈት? የከዋክብት መርገፍ? የፀሐይ መንጠፍ? የሆነው ነገር ሁሉ ያለመሆን?... ሌላ ምን?

ወደላይ መውደቅን ልምድ አደረኩ፡፡ አንዳንዴ ከእነ አሳንሰር ቤቱ ሰማየ-ሰማያት መቀመጫ ሆነው ሲውጡኝ ያድራሉ፡፡ ኸው ብዬ ሰወድቅ ውስጤ ይገለባበጥብኛል፡፡ የቀመስኩት ሁሉ ይወጣል፡፡ ወደታች መውደቅ ስለንት ጣዕሙ፤ በወገቱ በሆድ መፈጥፈጥ መፅናኛው ብዙ ነው፡፡ የዚያን ሰኖን ሁኔታዬ ለወግ የማይበቃ ትብጥርጥር ሆነብኝ፡፡

ለመሆኑ እናቴ ባታለዋውጠኝ እኔ ማን ነበርኩ? ቹቹስ? የቹቹ እናት እኔን ይሆን የምታሳድገው? እናቴስ? ማን ማን ላይ ጡሩንባ ነፋ? ማን ተጨንቶ? ማንኛው አስጨነቀ? እዚያ ቀለም አልባ፣ ድምፅ የተራቆተበት፣ እንቅስቃሴ የነጠፈበት ዓለም ውስጥ የነበርኩት እኔ ነኝ፣ እንዴ? እኔ የምለው ማንን ነው? እሱስ?...

...አንዳንዴ ነገሮች ይገለባበጣሉ፤ ወደላይ መውደቁ ግን አይዘነጋኝም፡፡ ይሄን ትርጉም የምሰጠው አሁን ይሆናል፡፡ ነገር ግን ያን የነበርኩበት ዓለምና የሚሰማኝ እንዲህ ለመሆኑ እርግጠኛ ነኝ፡፡

፲፱

## እኔ፣ እናቴና ያልተማሸው ገደል

የኛቹ እናት የሚጠላ ዓለሲሽራ መሳላ ወደእኔ ቤት ትመለከታለች። ብቻዬን መሆኔን ስታረጋግጥ ልጇን ከቤት እየጎተተች ትወጣና በር ላይ የተቀከለ ይመስለኝ የነበረውን ሰገርር በሌላኛው እጇ እንዘልቆየለ ታዘግማለች፣ ታዘግማለች… የለበሰውን ሾገር መነፂር አቋርጣ ወገበሩን እኔ ደጃፍ ላይ ታስቀምጥና ልጇን ታሳርፋያለች። ግና እሷኝን እኔ ላይ እንድታከለኝ ነበለማን ትዘናጋለች። ከልጇ ቀስር ከሚያዩዋ ቀለታ በትስቀቅ የበለጠ ትፈጥራለች። አፀኗ የእንቢኤት እልትቅ ነው። እንደተለመደብኝ ያሚን ይመጠያሚማል። እንዳንዴ ሆዷ ተገልብጦ ይታየኛል። እንጭ፣ እፍ፣ እፍንጫ፣ እፀን፣ ግንባር፣ ክንብንብ።

ማልብጥ ፊቷን መልሳ ትሄዳለች። እኔና ቹቹ እንፋጠጣለን፣ ከማንባሩ ስር አይኖች አይታዩም፤ ግን ያያሉ። እምንት የሚያነሳ ፀፀት እንደሸውሬ ጉብ ይልብኛል። ቹቹን መስጠጥ የሚያስኝ ስጠም እስተናግዳለሁ። በእሱ ውስጥ እኔን ለመመልከት እሞክራለሁ። በማይታዩ ዓይኖች እራሴን መመልከት። በእኔና በቹቹ መካከል ትልቅ መስተጠት እንደተጋረጠ ሁሉ እኔ እራሴን፣ እሱም እራሱን እንመለከታለን ብሎ ማመን። እሱ የእኔ ነፀብራቅ ነው። እኔ የእሱ። እውነታ እንዲህ ተገላብጦ ተቀናብሯል።

አበባ ከሮጣች አደነጋገጧ የጠደቀ ወርቅ ያገኘች ያስመስላታል። የሚያዋክቧት አሁቶቿና እናቷ እንደሌሉ ስታውቅ ወደቹቹ ትቀርብና ሄራ እጇን ሒና አይን ስሚፈራው እምላኳ ትጨፍናለች። ለረቂቅ የአምላኳ ጆሮዎች ድምፅ ሳታወጣ ከንፈሯን ታንቀሳቅሳለች። አምላኳ እንደእናቷ ውቃቢ በሽታን ከአንዱ ወደሌላው ማስተላለፍ ቢችል ቢያደርግብኝ የሚል ምኞት ያድርብኛል።

እቴቴ ከመጣች እግሯን ሰርቅታ ይዩዟታል። “ነጭ” ቁርጭምጭሚቷ ይታነቃል። እኔን ሲታይ ወደ ትልቁ ቤት ታመራለች። እፍታ ሳትቆይ ዝርግ ሳህን ላይ እንጀራ አጥፋ ትመጣለች። አሁንም እግሯን ሰርቅታ ያንቀዋል። ከጊቢ ወጥታ ወደ እናቱ መደብ ትሄዳለች። በስሎ ያልጠጣለት ወጥ አፍስሳ ትመለሳለች።

አንድ ሁለቴ አግሯን ስርቅ ይለውና ቹቹን ተጠግታ ትሰጠዋለች። እንዳንዱ አይቀበላትም። ጭኑ ላይ አስቀምጣለት ትሄዳለች። እቴቴ ሁኔታ ላይ የወትሮ ባህሪዋን የለመጠ ዐዐት ያነበብኩ ይመስለኛል።

"ታውቅ ይሆን?"

ቻይና ከመጣች በቃልኪዳን ትንጠልጥሎ በቀረ ወንዳወንድ አካሄድ ቀጥታ ወደእኔ ታመራለች። እንዳቀረቀረች ኩርፊያ ቅልቅል ሰላምታ ታቀርብልኛለች።

"ሰላም ነው?"

"ሠላም ነው" እላታለሁ።

"ክሳህ?" ስትል "ጠፋህ" ያለች ይመስለኛል።

"አለሁ"

"ሂሽ! ክሳህ ነው ያልኩህ፤ አላበዛኸውም?"

ቀና ብዬ አያታለሁ። ከእኔ የበለጠ የእሷ ፊት ጭር ያለ ነው። ለሀዘን የተላጨችው አራሷ ላይ ጥቁር ክፍያ ደፍታለች። አህቶቼ ከጥቁር ጨርቅ ቀሚስ ሲያስፉ ቻይናንም ሞክረዋት ነበር። እንቢ አለች። እህቶቼ ከመቼውም የበለጠ አለባበሰ አህታማኞች አድርጓቸዋል። እናቴ ውቃቢዬ አይፈቅድም ብላ ጥቁር አለበሰችም።

እናቴን እየፈራኋት መጥቻለሁ። ዓይኔ ግን የበለጠ እንደደፈራት ይሰማኛል። ምናልባትም እንደቹቹ እናት ዓይኔ የእንጨት አልቅት ሆኖ ሳይሰጠፍባት አልቀረም። ቀልቧን ስርቅ ሲለው ይታወቀኛል። ፊቷን መልሳ ወደምትሄድበት ትሄዳለች። አንድ ቀን ግን፦

"አስኪ ዓይንህን መለሰ አድርገው ልጄ፣ ደግ አይደለም፣ እንዳትወጋ።"

ከእዚያች ቀን አንስቶ በእኔና በእናቴ መካከል የማይለካ ገደል መፈጠሩ ተሰማኝ። አንድ ቀን ጠሴን ሁሉ ሰብስባ ከእነወለዱ እንደምትጭንብኝ አሰቤ በተስፋ መጠባበቅ ጀመርኩ። ቹቹን ከማየትና ከማሰብ ቹቹን መሆን በስንት ጣዕሙ። አንድ ቀን አልአዛርን ሆኜ ተኝቼ፣ ሰነቃ ቹቹን ሆኜ ወንበሩ ላይ እገኛለሁ። አልፈራሁም፤

የተዋቡትን መመስለ፤ የተበደሩትን መክፈል አረፍት እንጂ ጭንቀት የለበትም። እስከዚያው ነፍሴ አርፎታ ተነስታ በቅስፈት እንደታበትኩ መኖር የማይሰጠኝ ስሜት ይመስለኛል።

ይሄን ሳልነግራት የምትረዳልኝ ቻይና ብቻ ነች። ከፍያዋን ለመንዳወንድ ሀፍረት ወደ ግንባሯ እየጎተተች፦

"ሠላም ነው?" ትለኛለች

"ሠላም ነው" እላታለሁ

"ከማህ" ጠፋህ ያለችኝ ይመስለኛል፤ ረድፋም እንደዚያው ስለሆነ።

"እሰይ"

"ሂ.ሽ! ከላህ ነው ያልኩህ፤ አበሻኸው!!"

ወንዳወንድ እንባ ይተናነቃታል። እድርጋ የሚታውቀውን እጇን ትከሻዬ ላይ ጣል አድርጋ ካለሁበት ቦታ ገለል እንድል ትጋብዘኛለች፡፡ እኔና ቻይና ስንሄድ እናቴ በድንችና ሽንኩርት መካብና መናድ ትጠመዳለች። በእኔና በእሷ መካከል ያለው ገደል እንዳልተሟሸ እንስራ ቀይና የተሰጠለጠ ግድግዳ ያለው ነው ስል እሰባለሁ። የተማደው ድሎት መድኃኒት እየተብላላበት ይመስለኛል።

ቻይና ምንም ሳትል ያለሁበትን ሁኔታ ለመለወጥ ትሞክራለች። ስፖርት ቤት ሄደን እነሳኩን እስከትሰን እንመጣለን። የካራቴ "ውዝዋዜዎችን" እያሳዩና እየተመካከቱ ፊልም ላይ ያዩትን ይደግማሉ። ሲ. እፍንጫውን ጠረግ እያደረገ ሳኮ ላይ ይሰነዝራል። ሳኮ ከመመክት መጠቃት እንደሚያስወድሰው ስለሚያስብ ሆዱንና ደረቱን እያጋፈጠ ወደፊት ይገፋል። ቁሱ እሱጋ ሲመጡ ብቻ እየተከላከለ ይሄዳል። ቻይና እጇን እኔ ትከሻ ላይ ጣል እንዳደረገች ፍርድና አስተያየት ትሰጣለች።

"ሳኮ፣ ብረት ትተህ ካራቴውን በደንብ ብትሰራ ሰውነትህ ይላቀቅ ነበር።"

በመሰኪድ አድርገን ወደ ግራ በመታጠፍ አባ ሳሙኤል ወንዝ እንደርሳለን። አባ-ሳሙኤል ከሉፋ እቡኮ ያላነሰ የሚያምኑበት አሉ። የሰው ግብር አለው ይላሉ። እውነትም ቢያንስ በአመት አንድ ልጅ በአባ-ሳሙኤል ይዋጣል። አስከሬኑ የሚገኘው የመለማመኛ ሥነ-ሥርዓት

ሲካሄድ እንደሆነ የሚያምኑ እዛው ሄደው ቡና አፍልተው፣ በንደልና እጣን አጨሱለት፡ ዶሮ ወይም በግ ሲያርዱ አስከሬኑ ከዘቀጠበት ወጥቶ ይንሳፈፋል። እልልታ...

...ይሄን በሰሚ እንጂ በዓይኔ አላረጋገጥኩም። የማይቀኝ ስፍራ የመሰከሩበት በመሆኑ ያየሁ ያህል እየተሰማኝ መጥቷል። ልጆች ለጥቂት ጊዜ አባ ሳሙኤልን ፈርተው ይቆዩና ሲረሱት መጥተው ይዋኛሉ። አባ ስንደርስ ሳክ እንደአብዮት ጠባቂዎች "ቁም!" ብሎ ይጮሃል። ጉዳዩን አፈሳ የሚያስመስለው ኪሳቸውን ለመፈተሽ ነው።

"እስቲ ኪስህ፣ ገልብጠው፣ ይሄ ምንድን ነው? ተወርዋሪው።" አንተ ደግሞ ና፤ እስቲ ፈትሸው፣ እዎ አምጣ፣ ሊ. ይሄን ስንቲም እንጃው... እንደውም ተወው አንተኛው ና፣ አንሳ... አንተ ኪስህን ሳልፈትሸው ከመኝክ ብትወጣ አዘጋሃለሁ..."

እኔ ከአፋፉ ላይ አልወርድም። ፍተሻው ሊጠናቀቅ ተያይዘን ወደ ሰገነ አሙትሩብ ማሳደሪያ እንሄዳለን። በአጥር በኩል የወዳደቁ ኳሶችን በመቋመጥ ያያሉ።

"ያናው፣ ለዳንኤል የሚሆን ብረት..." ይላል ሳክ ሥጋ እንደዋ ሥጋ በለ በንጉት። "ያናው ዳንዲ ብረት ደግሞ ተቆራርጦ ለዳምፒል ያደርጋ... እ...ወይኔ!"

"ቸርኬው ደግሞ ለክብደቱ..." ሊ.

"ቀላል እኮ ነው በዚች ጫቁ እንሰቃለሁ..." ሳክ

ፋሉ እስኪጠይቁት ዝም ይላል...

የእናቴን ጉዳይ ጠይቁ ሁሉም ነገር ወደነበረበት የሚመለስበትን መንገድ በጠቆመኝ ስል አሰባለሁ ቀሉን እያየሁ።

ከብረት ጉብኝት በኋላ ጨካ እንገባና የደረቀ ችግኝ የመስሉ ልጆችን ሳኩ ያሰባስባል።

"ሽሮ ብቻሉን ፈትሸው፤ ባክ ደጣም አባቡን..." በእኔ እድሜ ያሉ ልጆች እንደትንሽ ልጅ ሳክ ያለውን ይፈፅማሉ። እሌስ ቃይና እስቱ ባትሆን ኪሴ ተገልብጦ መፈተሹ ይቀራል?... ጭራሮ ሰብሳቢዎች ልጆች በጭራሮ የተፋፋቀ እጃቸው የሰምረትን የእንግ

መስመር ያስተሙባል፤ በመፍራታቸው አብረው በማያኗኑር አኳኋን ይፈታተኻሉ። በእንጨጬት ዘርንታቸው የቁቼ እናት ዝምድና ይኖራቸው ይሆናል ስል አሰብኩ።

"ወንት ሴት ቀርቀር ብሆኑ እየው" ይባላል ሳኩ።

ከሸርጣ ከብችልና ከባኩ እና ከእባቡ ጋር አንድ ላይ እንማራለን። አንድ በማን "የቢዘን ፉርጎ" እያሉ ያበሽቁኝ ነበር። ማየት እንኳን አትቶኝ በደናበር ብዙ ቆየሁ። በኋላ ብችልን ስመለከተው ሌሎቹን ጠቆመ፤ እኔን ሳይሆን ቻይናን ፈርተው እንደተርበተበቱ አሁን ታሰውኝ። ዛሬም እኔን ባለማናቸው ያሸበብሻሉ። እኔን እንቅ የያዘኝ በእኛ መካከል ያለው መበላለጥና መለያየት እንዴት እንደተፈጠረ ማሰብ ነበር።

ሴላ ሌላ ቁሉ፣ ቻይና፣ ሸክና፣ ሸርጣ ብችል፣ ባኩ፣ አባቱ... ብዙም በማይበላለጥ ዕድሜ ውስጥ ሆነን ይሄ የማበፈራራትና የመፍራትን የሚዘዝና የመታዘዝ... ልዩነት እንዴት መጣ? ከራቱ ከሆነ ሌሎቹም መበልጠን ይችሉ የለም? እና? እንደ እኔና እንደቹቹ መንፈስ የማቀያየር ቁማር እናቶቻቸው ሳይጫወቱ አይቀርም። ልጆቻቸውን ካርታ አድርገው እየጠወዙና እየተከፋፈሉ በመሸናነፊያ መንፈስ ዳኝነት እንደ ተበሊታ የነፈዘ ሌላዋ በሊታ የነቃና የበላይ የሆነ ልጅ ይዘው የቀሩ ሳይሆን አይቀርም።

ባተገኘው ኳሜታ፣ ሽለጠ፣ ሙዝ፣... ወይም የሺህ ሮጀሉ ዘመዶችጋ ሄደን ፓስቲ... አንዳንድ ጊዜ ገንዘብ ከእህቶቼ ተቀብዬ ለቹቹ ፓስቲ ይዤለት አመጣለሁ።

"ደሞ፣ ደሞ፣ ደሞ... ዱርዬ ሊታደርገኝ" ይላል። መብላቱ ግን አይቀርም።

አንድ ቀን እናቱ እኔ ደጅ አስቀምጣው እንደሄደች ሳትመለስ ቀረች።

# 19

## እኔ፣ እናቴና ስርቅታ

"ናቅፋን ያላያችሁ ... ወንድ ነኝ አላችሁ?

"አፋበትን ያላያችሁ... ወንድ ነኝ አላችሁ?

"አቁርዳትን ያላያችሁ... ወንድ ነኝ አላችሁ?..."

የአባቴ ሞክሼ ትልቁን ቤት አርገፈገፈው። መርገፍገፉ ሳቅ ይመስላል። እንደቁሶቹ ብዜንም "የሚለውን እንጂ የሚያደርገውን አትዩ" የሚባልለት ጀግና ቀስቃሽ ነው። አፈሳ መናሩ የሚታወቀው የብዜን ድምፅ ሲጠፋ ነው።

ከእናቴ ጋር ዓይን እንደ ድንጋይ እንወራወራለን። የሚፈነክት ዓይኔ ሁለት ጊዜ ዓይኗን አግኝቷል። የዓይን ማቀፊያዋ ዘጉኖ ውስጡ መቅለጥ ነበረበት። ምሽጓ የድንችና ሽንኩርት መደብ ስለሴሊ ወሬ ውስጥ ትደበቃለች።

"የዚህ ልጅ እናት የት ገባች ይባላል?" ቀልቧን ስርቅ ሲሰው ያስታውቃል።

ዝም... ቤቱ ያደመባት ይመስላል።

"ትናንትና በአለም ፀሐይ ድልድይ አድርጋ ወደ ሰባራ ባቡር ሾተው ብላ ስትሄድ ያያት ሰው ነገረኝ።" ስርቅ።

ዝም

"ልጁን ቤቱ ማመላለሱም ገደለን። ጠዋት ማምጣት፣ ምሽት መመለሱ። በዚህ ላይ ተዘግቶ የዋለ ቤት ሲገባ..." ቢለክፍስ ትላለች ብለው የጠበቁት እህቶቼ ተያይተው ተጠቃቀሱ። ቻይና ለሁሉም ሳትናገር አልቀረችም። የቤታችን መንፈስ ተበርዟል።

"ባይሆን ከቀልቧ ሆና እስክትመለስ ልጁ ታለ ቤት ይቶኛ። ታለ አድሮ መተኛው እዚሁ..." ስርቅ፣ ስርቅ፣ ስርቅ...

"ለምን?..." አልኩ።

ዝም፣ እህቶቼ።

"ለምን እኔ እዚህ አመጣለሁ! እዛው እተኛለሁ"

"ከእሱ ጋር?"

"አዎ!"

"አይዘገንሽም!" ሰርቅ፣ ሰርቅ፣ ሰርቂ..

"የማይዘገነው ከሆነ ቶሎ አግቢሽ" አለች እቴቴ።

የእናቴ ልብ ለባሏ ያስተሰኘችውን ለራሷ ሳይደግምላት አልቀረም።

"የልጆችሽ ተግልግሎቱ አይደርስብሽ፣ የልጆችሽ ቁስማማው አይደርስብሽ..."

እናቴ ለታዳዟኛ ምክክራቱ። የአልሞት ባይ ተጋዳይ የመሰለ ደካማ ድምፅ ለቀቀች።

"ይሁን ካሰኘሁ! መሬት ለልጁ ይነጠቁና..."

"አ-ይ፣ እኔ ነኝ መሬት የምትኛው" አልኩ ምን ነካኝ?

ዝም! እንደ አባዬ አንኳን የምትሸፋፈነው ያጣች መሰለች። ዓይኗ እንባ አቀረረ? እንጃ ብቻ የዓይኖቿ ኳሶች አብረቀረቁ...

"ምን ይሁን ነው የምትሉትን?" አለች እንግሊዚ ስምረት ተመቸቸ።

"ምንድን ነው አፍ አፏን የምትሏት?"

"እንቺ ምን ታውቂያለሽ?" እቴቴ በሚጋረጥ በባይዋ ምላሷ አለቻት። ሁሉም ጥቁር ለብሰው የእንጉድ ቡድን አባል የሚያስመስለው አስመሰሏቸው። ፈቂት ትነስታ መካከል ቀመችኝ።

"አጡታለሁ! ማግኛቱም እናት የምታደርገውን ነው ያደረገችው ቤቴ!"

"ሲጣን የተገሰዐ ይሁን!" አለች አበባ።

"ዝም በይ፣ ዝጊ፤ አፍሽን ያገር..." ሁሉም ጨኸቡባት።

ከዚህ በላይ መቀየት አልቻልኩም። ወደ አሳንስር ክፍሌ አመራሁ። ከነገ ጀምሮ እዚች ክፍል ውስጥ ፕላኔት ትዘገያለችን በሐይ ትንቀራፈፋለች፣ ልጓሞች ይጠብቃሉ፣ ሰዓቶች አንዷ ገደል ማሚቱ አራሳቸውን ይደግማሉ... አንድ ደቂቃ በስድስት መቶ ሰከንድ ይመነዘራል፣ አንድ ሰዓት ስድስት መቶ ደቂቃ ይሆናል። ወደ ሰዐ የሚወደቱ መምዘግዘግ በአንድ አስረኛ ይዘገያል። ፀሀይ ይጋሽባል፣ ገል እና ፀዳ ተሽራርሮ ለማለት ይሞክራል...

# 20

## እኔ፣ የተቀደደው ሰማይ እና የረጋው አየር

በአብረተኛ ነፋስ እንደተመታ ደመና ጊዜ በተለዋዋጭ ነገሮች ተሞላ። ለትረካ እንኳን ማዘግየት አዳገተ። ግንቦት 13 እናቴ ራፋኤልን በአንባበሮ ስትዘክር ብዙ እንግዳ ሰዎች በአስፈሪ ፊት ታጅበው ጠበል ጣዲቁን ተሻሙት። ልብሳቸው አሳያቸው ላይ አልቶ የየኔ ብጤ ሠራዊት ይመስሉ ነበር።

የዛኑ ቀን አመሻሽ ላይ መንግስቱ ኃይለማርያም መሸሻቸው ተለፈፈ። የበለጠ ለውጡ ፈጠነ። ሁሉም ነገር ቀጥ ብሎ የቆመው ግንቦት 22 ከቀኑ አምስት ሰዓት ገደማ ነበር።

ያን ቀን ረፋድ ላይ ፍራሽ ላይ ሆኜ መጽሐፍ ቅዱስ እያነበብኩ ነበር። ቹቹም ካልጋ አልወረደም። ወዲያው አንድ ጎላ ያለ ድምፅ ተሰማ።

"ቹ! ቹ! ቹ!..."

ላኮ ነበር። ተነስቼ ስወጣ ቹቹ ተከትሎ ቀስ እያለ ወጣ። ቻይና ቀድማው ነበር። በስስ የስፖርት ጃጉኒ ነበረች።

"ለዳምጌል የሚሆን ብረት እናምጣ! ሰው ሁሉ እየሄደ ነው" ላኮ ነበር። ከኋላው ሊ. እና ቁሉ አሉ። ቻይና ልብስ ልትደርብ ስትገባ እኔም አብሬ ለመሄድ እንዳቀበቀብኩ ቹቹ ተረድቶ ኖሮ እንዳቀረቀረ፦

"ደሞ፣ ደሞ እኔም፣ እኔም እሄዳለሁ" አለ።

"የት?" አልኩት።

"ደሞ፣ ደሞ አንጃ! እኔ እናት የለኝም ደሞ"

"አትቀልድ" አልኩት በዚህ መካከል ቻይና መጣች።

"እረግምሃለሁ ደሞ፣ ደሞ..." አለ።

ቻይና ሰቃ "ምንድን ነው?" አለች።

"ልሂድ እያለ..."

"ይምጣ..." ብላ ሳቁን ዋጠች።

"እንዴ፣ ኧ! እሱን ስንሳቀቅ ዳምጧል ያልነበረን ነ" ቀስ እያለ ይምጣ"

ቻይና እጄን እየጎተተች፡ ቀስ እያልክ ይዘሽው ነ ስግብግብ ለንደል ገባን። እሱን ይዤ ሩፋኤል ስንደርስ እነሱ ሶስቱ ደርሰው ይጠብቁ ነበር። ነየሳቅሁ እየሁት። ትቅርቅሮ በራሱ ጉዳይ የምናወራ አይመስልም።

"እሺ" አልኩ።

"ደሞ፣ ደሞ፣ ደሞ አጠፋርትሃለሁ" አለ።

አዘጋጆቹ፤ እነ ቻይና ክዳዩን ጠሩ። ጉልት ስንደርስ እናት ልብሳቸው ያለቀውን ወታደሮች አስቁማ ትጠይቃለች። ስለእቱ እንደሆነ ጠርጥሬአለሁ። ፋንታዋን አልቅሶ በእምነት ያላበቀሉትን ድርሻ ትሻማለች። እኔና ቹቹን ብታየንም እንዳላየ ዝም አለች።

ነገሮች ሁሉ ተቀያይረዋል! እኛና ቹቹ ብቻ በዘገየች ፐላኔት ላይ ሰርገ በዘገየ ልብ ምት፣ የልጅነት ላይ ጉዞ እናካሂዳለን። በመጨረሻ አለ ሳሙኤል ለመድረስ ጥቂት ሲቀረን ጊዜን ያቆመ ክስተት ተፈጠረ። ባዶ በርሜል በያዙ ሰዎች እየተገፋን ስንጓዝ ድንገት ብሩሁ ሰማይ በአፍታ ጨልሞ ተሙሉ የሚያፏጭ ንፋስ በጭንቅላታችን ላይ አለፈ። ተከታትሎ እንደ ጋሻ ተገኔ ሰማዩ ደንግጦ ያልተረገዘ እሳት አስወረደው። ፍምጌ ዓለም መሰለ። ከሰሜን ፍንዳታ ተሰማምቶ ብናኝ እንባቢውን ጉም ሠራበት። ጠዷምሙኑ በጥንስ ተቃጥለው ደም የሚያበራቸው ሰዎች የብናኙን ጠለቀ እየጣሱ አለፈውን ሲሄዱ የጀሶ ምስል ይመስሉ ነበር።

የተጨባጭ ዓለም ውል ማፍረስ ተካሄደ፤ ድንገት ተዝቃዛው አየር እሳት ሆነ፤ እቶን ሲወልድ ትሰበታች በቁኝ። ትጋሽ መሬት በቁጣንቶ አረፋ ደፈቀች። ለወትሮው በስው ጉዳዩ ሲገቡ የማይታዩቱ ግዳለሽ ትክሎች የሚሸሸውን እንቀው ያስተፋት ጀመር? የተፈጥሮ ቃል ኪዳን

ፈርሶ የማይሆነው ነገር ሁሉ ሆነ። የእናቴ የድግምት ጥሪ፤ ቁጣ ሆኖ ዓለምን አንቀጠቀጠ? ኡብዮት ጥበቃዎች የፈሩት ይሄን ነበር?

ብናኙ የማይንቀሳቀስ ከመሆኑ አንጻር አርጎ ውስጥ የተቀመጥኩ መሰለኝ። የአርጎ ውስጥ ድምፅ ዘገምተኛ ሆኖ እንደ ባለቴፕ እየተሳበ ማለፍ ጀመረ። የታላቁ ፍንዳታ ቅሪት ደግሞ ጭንቅላቴ ውስጥ ተቀብሮ ቀርቷል። "ተፈጥሮ" እንደ እናቴ ቀልቧን ሰርቅ አስሙ፤ ረጅም ሰርቅታ፤ በፈጣሪ ልጓም አልዳኝ ብላ አመፀች።

አእምሮዬ ወደኋላ የተረጋገጠ ነገር ለማሰብ የቻለው ዘግይቶ ነበር። የት ነኝ? ከየት መጣሁ? እንዴት መጣሁ? አርጎ ውስጥ ምን ከተተኝ?... አጠገቤ ቹቹ አልነበር? የት ሄደ?... መጣራት ተሳነኝ፤ አባ ሳሙኤል ጋ ደርሰን አልነበር? ከቤት ተነስተን አልነበር? እነ ቻይናን አነጋግሬ አልነበር?...

...ከታላቁ ፍንዳታ ጋር የሚነፃፀር ድንጋጤ። ቻይና፣ ቻይና፣ ቻይና...

"ቻይና!!"



# ክፍል ፪

## ልውጥውጡ

“ምድር ከአንተ የተነሳ የተረገመች ትሁን…
እሾህና አሜኬላን ታበቅልብሃለች…”

ዘፍጥረት 3፡ 17

## ፵፱ ኅዳር

## ዘ ጳጉሜን

"የጽርሐ አርያም ቅዱስ ሩፋኤል ቤተክርስቲያን" ቀበቶ ደጋና በመስለ ብረት ላይ ተፅፎ ይታያል። የረጅም ዘመን ጥያቄ ሆነው አብረው የኖሩ ሁለት ቃላት ጽርሐ ምንድን ነው? አርያምስ?...

...ስፈሬን ተረትኩ እኛን ደግሞ የተረት ስፍር ውስጥ ተረት ለማድረግ እነዚህ ሁለት ቃላት ጠቅመውኛል። ከእስቀያሚ እውነት ገላግለውኛል። እውነታ እኔ እናቴና ቹቹ መካከል ያለውና አለዉዲን ከንውን ይመክላል፤ ምን ያምራል? እውነት ከተረት የባሰ የሚታመን ነገር የሌለው ክስተት ነው። ቻይና ከቤት ወጣችና የሚዘዋ እምና ጥይት ፋብሪካ ደረሰች። አይሆንም ያለችው ሆነ፤ ጠጣሩም፤ እየፋ፤ ፈሳሹም ፈነዳ። ሞቶች ከማለት ጠፋች ማለት ይቀላል። እና እኔ ላይ ያለው እውነት የቻይና ከቤት መውጣት እና አለመመለስ ብቻ ነው። ሌላው ግምት ነው። ያ-ግምት እውነት ተደርጎ እንዲወሰድ እውነታ ግድ ይላል። አባቴም...

...ነገ ጳጉሜን ሦስት ነው። ጠበል ከሰማይ ይወርዳል፤ ልጆች ይጠመቃሉ። ከፈውስና ከትድስና በላይ እርቃናቸውን አደባባይ የመውጣት ነፃነታቸውን በፈቃድ ያገኛሉ። ግን ለምን እርቃን መሆን ክልክል ሆነ? ከጨርቅና ከገላ የትኛው ነው እውነት? ገላ አይደለምን? ታዲያ እውነትን መጋረድ እንዴት እውነታ ሆነ?

ሩፋኤል አጥር ስር ብዙ ሴቶች ተቀምጠው ጧፍ፤ እጣን፤ ዘቢብ፤ ሻማ፤ ዣምጃ፤ ጃንጥላ... ይሸጣሉ። ወንዶቹ ግን ማተብ፤ የመዝሙር ካሴትና የፀሎት መጻህፍት ብቻ ይዘዋል። ይሄን ድልድል ያደረገው ማነው? ወንድ ይሄን ይሽጥ! ይሄን ሳይሸጥ ቀርቶ ይሄኛውን ከቀረበ ሴታሴት ይባል የሚለው ስምምነት ከየት መጣ?

ሲፈን በሰበብ የትውስታ ደጃፌን ቀረቶረች። ከረምትን እዚሁ አሳለፈች።

"ደስ ሲል" አለችኝ አንድ ቀን።

"ምኑ?" አልኳት።

"መንግስት ያለውን አልሰማህም?"

አራሴን በአሉታ ወዘወዝኩላት። ጥልፍ አይኗን በቁንጥ ጨፈን ገለጥ አድርጋ፦

"በአሁኑ ዓመት ተማሪዎች ሁሉ አልፈዋል፤ መውደቅ የለም ተብሏል። ከማትሪክ በስተቀር። ደስ አይልም?"

ድንቅ አልሆንልህ እንዳለኝ ገብቷታል።

"ቡና ላፍላልህ? አንተ ክፍል?"

ሰሞኑን ደጋግማ እንዲህ ያለ ግብዣ እያቀረበችልኝ ነው። ፍላጎቷ አልተጨበጠልኝም።

"እንጓች አይኑ ይጠጋል፣ ትከሻው ይከብዳል፣ አደብ ገዝቶ ክፍሉ ቢቀመጥ ጥሩ ነው ብላለች። ለምን ክፍልህ ቡና እያፈላሁልህ..."

የመጀመሪያ ቀን ግብዣዋን በፍርሃት አስተናገድኩት። የሁለተኛ ቀን ግብዣዋን ግን ተንኮል ደግሼ ጠበቅሁት። ቼቼን ከእኔ ክፍል አውጥቼ ትልቁ ቤት በር ላይ አስቀመጥኩት። የእናቴን ረከቦት፣ ስኒ፣ ጀበና፣ ብረት ምጣድ፣ ሙቀጫ፣ መቁያ፣ ዘነዘና... ስታመላልስ ደነገጥኩ። የእናቴን የቡና ዕቃ ማንም አይደፍርም። እህቶቼ'ኳ የሚያፈሉበት ሳንቲም የሌለው ሌላ ረከቦት አላቸው። እንዴት ተፈቀደላት? ረከቦቱን ትቼ ሲፈንን በጉጉት አየኋት፤ ምኔ እንደጎመጃት፣ ምኗ እንዳስጎመጀኝ አልተገለጠልኝም።

አልጋ ላይ ሆኜ ስጠራት መጣች። ጫፍ ላይ እንድትቀመጥ ስጋብዛት ተቀመጠች። አግሯን እንድታወጣ ስጠይቃት ታዘዘች። በህልሜ እንዳየኋት ሆነች። እግዚአብሔር ነፍሷን ሳይነጥቅ ገድሎ የሰጠኝ መሰለኝ። እንዲህ ያሉ እውነቶች ተረትና ሕልም ይመስላሉ። በፈራ ተባ ከንፈሯን ሳምኳት-ዝም።

ሕልምና እውነት ተጣረሱ። የዓይኗ ኳስ ሲንቀሳቀስ የዓይኗ ቀብ እንደነፍስ ጡር ሆድ ተገላበጠ። ይሄንንም በሕልሜ አይቻለሁ። ከዚህ ቀጥሎ በሳንቲም ተደፈነ የብልት መብቀያ ይከተላል። ፈራሁ።

"ቡናውን አፍይልኝና..."

"እሺ" ከሞቷ ነቃች፣ ተነሳች፣ ወደ ቡና ማፍላቷ ገባች።

ቀይቼ፣ ቀይቼ ጠየኳት። ልክ አይደለሁም ግን ለምን እንደታዘዘችኝ ቀስ አድርጌ ጠየኳት።

"ለአንተ'ኮ አይደለም"

"እህስ?"

"ለውቃቢህ ነው። ውቃቢህ ካረፈብኝ..."

እንደሲታሲትነቴ ሁሉ አንዳች የታያት ነገር ሳይኖር እንደማይቀር ሳስብ ፈራኋት። እራሴንም ፈራሁት። ከዚያች ቀን አንስቶ እሸሻት ጀመር።

ከሩፋኤል "ድረሳነ ሩፋኤል" ገዝቼ ተመለስኩ። መንገዱ ሁሉ በሰዎች መጥለቅለቅ ጀምሯል። ማን እንደጎዘጎዘው የማይታወቅ ቄጠማ፣ ጎዳናውን በውስጥ እግር የሚሳም ለሰላሳ ገላ አድርጎታል። ገለጥ ገለጥ አድርጌ መጽሐፉን አየሁት። አምላክ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ሩፋኤል፣ እግዚአብሔር... የሚሉት ቃላት በቀይ ተፅፈው ዓይን ውስጥ ጥልቅ ይላሉ። ገፁ ለሁለት ተከፍሎ በስተግራ ግዕዝ በስተቀኝ የግዕዙ ትርጓሜ አማርኛ ቀርቧል። ክፍሌ ገብቼ ለማንበብ ቸኮልኩ።

የእናቴ ወጥ መላው ጡረታ ድልድይን ማርኮታል፤ ብዙ ያደገደጉ እፍንጫዎች ተሰቅለው የናኘውን የእናቴን ወጥ ይምጋሉ። የእናቴ ዓይኖች ከእኔ እንዳፈገፈጉ ናቸው። ማኩረፍና መጥላት ሳይሆን መፍራትና ማክበር ይነበብባታል። ምን እያለችኝ ነው? የልጇ ተገልማጭና የልጇ ተለማማጭ ለመሆን ለምን ፈለገች? በሲፈን በኩል ምን እያለችና ምን እያደረገች ነው?

ወደቤት ስሄድ ቹቹ እኔ በር ላይ ተቀምጧል። እንደ ሁሌውም ያየኝ አልመሰለኝም ነበር። "ደሞ ደሞ..." ሲል ቀም ብዬ አዳመጥኩት።

"ደሞ ደሞ ደሞ ልትደግምብኝ ነው ደሞ ደሞ ወደ ቤቴ እሄዳለሁ ደሞ..." የጉንጩ ላይ ሪዝ እየደመቀ መጥቷል።

ቹቹ ስለራሱ ጤነኛነት ይስማማል ማለት ነው? ማነው እራሱን የሚያውቅ? ሲታሰቡን ታችንና አውሲያዎሚታችን ከራሳችን ከተደበቀ ስለራሳችን እፉችንን ምሉቀን መናገር እንዴት እንችላለን? በሌሎች ሳይረጋገጥ በራሳችን በስራሳችን የምናውቀው ምንድን ነው?… ዥው እያሉ ወደኋላ መውደቅ ሲያምካክረኝ በፍጥነት ገብቼ አልጋ ላይ አረፍ አልኩ።

ለሽንት ድርሳነ ሩፋኤልን ማንበብ ጀመርኩ።

"በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አመ ሠለሱ ለጽጉሜን ተዘከረ በዓሉ ለመልአክ ክቡር ሩፋኤል ሊቀ መላእክት ዘውእቱ ሣልሳይ እምሊቃነ መላእክት ትጉሃን ቅዱሳን ስማያውያን በከመ ሐተነ አመ በምሩ ወሰኑዩ ሰጋዳር።"

ግዕዝ ትርጉሙ ሳይገባ የሚያፀናና ቋንቋ ነው። ቃል ከዳን ቃልኪዳን ይላሉ። እንክን የለሽነቱ እንዳለ ሆኖ የማያዳግም ድምዳሜ ስጪ ይመስለኛል። ቁሶች በአከራካሪ ጉዳይ ላይ ግዕዝን ከጠቀሱ ጉዳዩ እንዳበቃለት ሲቆጠር ብዙ ጊዜ ተመልክቻለሁ። ሲናገሩት ሆነ ሲያነቡት የለደለደ ደርባባ ነው። እንደ አንዳንድ ቋንቋ ነጠላ፤ ክውካዋ አይደለም። የቹቹ እናት በግዕዝ ብትናገር ኖሮ ደርባባ እመቤት ትሆን ነበር እያልኩ አሰብኩ። እቴቴም ሲታሰቅስ በግዕዝ ቢሆን እንደቴሶች ወረብ እነሳሱና እወዳደቁ ባማረለት ነበር። ትንሽም ጥሩ የሚይሆነው ስረገ በግዕዝ ብታወራ ነው። መስሕቢ ሪግር እስፈሪ መንፈስ ደበኛርባት ይመስለኛል። ከግዕዝ በኋላ እንዴት አጠገቤ ትኚ ትባላለች?

የግዕዝን ትርጉም አንድ ቀን እንኳ አላውቅም። ሌላ ትልዕኮ ያለው ሰው ሆኖ ብሎ ያቀለለውኔ ወይም ግዕዝ የማያውቅ ሰው በግብር ይውጣ እንደህ ይባል ብሎ የተረጎመው ይመስለኛል። ድርሳነ ሩፋኤልን እንደ አለንገጅር ቂሱ ሰዎቶኝ ሌላ ጊዜ ገዘቼ እንብቤዋለሁ። አሁን ስደግመውም የግዕዙ ክብደት ተቀንሶ፣ ሚስጥሩ ተጓድሎ በአጠቃላይ በአማርኛ ተጎሳቆሎ ይታየኛል። ቢሆንም የሩፋኤል ቤተክርስቲያን እንነባብና አጠፋፍ የሚቀርብበተ መንገድ ታሪኩ ብቻውን ግርማ ሞገስ እንዳለው መካድ አይቻልም። አንዳንዴ ያነበብኩትን ዓይኔን ጨፍኜ ከምናባዊ እንቅስቃሴ ጋር እደግመዋለሁ።

አለክንድርያ ትባል የነበረው አጠቃላይ ጉስሴ እንደሆነች አሰባለሁ። "ድርሳነ ሩፋኤል" ላይ "የዳርቻዋ ደሴት" በሚል የምትጠቀሰው አሁን የሩፋኤል ቤተክርስቲያን ያለበት የሸህ ሆጀሌ አፋፍ ነው።

እንዲት ሁብታም ሮማዊት የሩፋኤልን ልዕልና ልጆቹን ይዛ ሜሮ ባለ ሊሊት፤ ጎዳናው ለገደል ማሚቶነት ሰበብ ፈልጎ እንዳሚጠሞጠ ያለፈችው ከእንቁላል ፋብሪካ ተነስታ በጡረታ ድልድይ በኩል ነው። እዚያ ስትደርስ ሊቀ ጳጳሱ አባ ቴዎፍሎስን አግኝታለች። ከዚያ ትያይዘው ከረብታማውን ሉሉልታ በማስቆፈር ወርቅ የተሞላው ሳጥን አውጥተዋል። በወርቅ ካሠሩት ቤተክርስቲያን አንዱ ሩፋኤል ሆነ።

ከዚህ በኋላ ያለው የሚያም ታሪክ ነው።

ብዙ ሕዝብና ምዕመናን በአዲሷ ቤተክርስቲያን ውስጥ ተሰባስበው ሲፀልዩ የመሬት መንቀጥቀጥ የመሰለ መርገፍገፍ ተከሰተ። መታወክና መናወጥ ሆነ። ለካ ቤተክርስቲያኒቱ የታነፀችው እንደታሰበው በደሴቱ ላይ ሳይሆን ውሀው ውስጥ ፀንቶ የሚኖር እጅግ ግዙፍ አሣነባሪ ጀርባ ላይ ኖሯል። ዓሣ ነባሪው ከሰዎች ብዛት የተነሳ ክብደት ስለተሰማው ያቺን ቤተክርስቲያን ይገለብጣት ዘንድ ሰይጣን አነሳስቶት ኖሯል። ሰዎቹ ከሊቀ ጳጳሱ ጋር በመሆን ያድናቸው ዘንድ ጮኹ። እግዚአብሔርም ቅዱስ ሩፋኤልን ላካላቸውና ከጭንቀታቸው አዳናቸው። ከሀዘናቸውም አረጋጋቸው። ዓሣ ነባሪውንም ባለበት ቦታ በያዘው ጦር ወግቶ እንዳይንቀሳቀስ ፀጥ አደረገው። ቅይቶ ግን አልቀረም። ዓሳ ነባሪው አዘናግቶ በመወራጨት በማዕበልና በሞገድ ቤተክርስቲያኒቷ ፈራረሰች። ብዙ ሰዎች ባህሩ አሰመጣቸው።

እነዚያ የሰመጡ ሰዎች እነማን ናቸው? የማንን ፍቅር አነደሉ? የእነማን መከታዎች ነበሩ? ለእነማንስ ደቅረቶሩ ነበር? እቅዳቸውስ ምን ነበር?... የደረሱት ግድ አልነበረም። የሰው እውነታ ይሄው ነው። የበጎነው ፍንዳታ ሲዘንብ እንዲሁ ያለችግር ነበረበት። ሦስት መቶ አስራ ሰባት ሰዎች ሞቱ ብለው አበቃ። ሦስት መቶ አሥራ ሁለት ቢሆኑ ኖሮ ቻይና አትካተትም ነበር? ያቺ በአንድ ነጠላ ቁጥር የተጠቀለለችው ልጅ ለእኔና ለቤተሰቦችን ምን እንደነበረች ማንም ልብ ያለው አይመስለኝም። ምናልባትም በዘገባው ቁጥር ላይ የተነሳው ክርክር ይሄን ያመለክታል። የሟቾች ቁጥር ከእዚህ በእጅጉ ይልቃል ያሉ ወገኖች ነበሩ። የአንድ ሰው ዋጋ የትናሌኔት ያልገባቸው ናቸው...

...ከእውነትና እውነታ ማምለጫ ቦታ አጣሁ። መንገዳገድ ሲበዛ እህቶቼ ከየተበተኑበት እንደተመለሱ አወቅሁ። ዕቃ ከዕቃ ካላጋጩ ነገሮች አይሰልጡላቸውም። በፊት እወደው የነበረው ይሄን የሲቶች ሁካታ ነበር???

## ዛፉ ሁለቱ

## ተእምራት

ጳጉሜን ሣሰት...

...ብዙ ተአምራትን ሰሴ ይጠብቁሉ። ምናልባትም ላጃቸ ሰዉን እፊቀቃቸንን የሷረቀንበት የገናብ ጠበል! ትድፍ የበዛበት ውኃ መውረጃ ሰይተር በጠበሌ መሞላቱን በማየት ጉንቅላቱ ላይ የተተረበው የተጋነነ አደሜሩ ይሆናል፡ በማታጠቢል የተፈጠረው የልጆች ጠላት ላማ ሰይተር በቤቱ ቱን ሰሞይ ቤት መላእክታት ያሸበሸቡበትንና ትዲሰን የተደሰበትን ጠበል ይጠማል፡ ውሻችን ገልጆ እንዲጌን የተጠለሰበት የበገበል ጎጆ ድረስ በሬት ያሬበርበው ነበር፤ ቹቹ ብቻ ጠበሉን ይቃጠማስ፡ ሰኦ ጠፉንባ እንደሰማ ውሉ እየተረበሸ ሰመከላከል ይሞክራል፤ የሚከላከለው የያዘችውን እናቱን ሳይሆን ጠበሉ ጭንቅላቱ ላይ እንዳይዘንብ ነው፤ ድንጋጤው ለሶስት ቀን የሚቆየው አይመስለኝም፡፡ ዝናብ ሲጀምር

"ደሞ ደሞ ወጣብኝ ደሞ" እያለ ያጉረመርማል፡

በጳጉሜን ሣብት እና በማግቦት እስራ ምስት ከቤቱ መውጣት አልወድም፡፡ የሰው ብዛት እራስ ያዞራል፡ የሰው ብዛት ብቻ ሳይሆን የአካሄድ ስልቱ መዘበራረቁ እንደቹቹ ፈር ባልያዘ ትቃውሞ እንዲጮሁ ያስገድዳል፡፡ በተለይ የሽቃጮና የለማኙ ብዛት የበዓሉን ትልቅነት ቀይሮ የነፍስ ጉዳይ ሳይሆን የኑሮ ዘዴ ያስመስለዋል፡፡ የተንሰራፋው ጎግድና ልመና ከዞና ጎዳና ግንፍሎ እስከአኛ አጥር ድረስ ይናኛል፡፡

"ሽንኮራ፣ ሽንኮራ"

"ስለመልአኩ ፋፋአል"

"በረዶ፣ በረዶ"

"ስሴፈታሄ ማሕፀኑ!"

"ቆሎ፣ ቆሎ..."

"ስለሲቃን መልአክቱ ስለሩፋኤል"

ከተሰመደው ልመና ውጭ አንድ ጎላ ያለ ድምፅ ጆሮዬ ውስጥ ጥልቅ አለ፡፡ እንደ መጋዝ ክርክር ያለው ድምፅ ወደፊትና ወደኋላ እያለ ድድሩን እየር ለመቁረጥ ይታገላል፡፡ ወጥቼ ፈለኩት፡፡ ድምፁ ውፍረትና ርዝመት ሰላለው ፈልጌ ለማግኘት አልተቸገርኩም - አየሁት፡፡ የነተበ የጠታደር ልብስ ለብሶ እጁን ከነከፍያው ወደኋላ ያደረገ፤ አካሉ እንጂ ድምፁ ትህትና የሌለው፤ የጠረጠርኩትን ልመና ደገመው፤

"ስለቆራጡ መሪ፣ ስለመንግሥቱ ኃይለማርያም!"

መንግሥቱም እንደ እኔ አውሊያም ነበረ ማለት ነው? ሳያውቅ ነው የሄደው? ወይስ አውቆ?

"ስለኢብዮታዊ መሪው፣ ስለመንግስቱ ኃይለማርያም!"

እኔም ሰጥች ሲፈን በስሜ እንዲህ ሳትለምን አትቀርም "ስለሲታሴቱ፣ ስለ..." እናቱ ታቋርጣት ይሆናል፡፡

"ምነው እንዲህ ይባላል?"

"እንጓች ደሞ፤ ታዲያ ምን ልበል?"

"ዓይኑ ስለሚወጋው ታለ፣ ትከሻው ስለሚከብደው ታለ፤ አትይም?"

ወታደርነት ያልቀናው ወታደር ልመናው ይዞለታል፡፡ ከደረደራቸው ፎቶዎች ስር ብዙ ሳንቲምና ብር ተኮልኩሏል፡፡ የመንግሥቱ ኃይለማርያም ሥም ሲነሳ የደነገጡ ሰዎች የሰጡት ነው፡፡ ይሄ ሁሉ ሰው የመንግስቱን ባለአውሊያነት ያውቁ ነበር? ወይስ ምንድን ነው? "ስለመልአኩ ሩፋኤል" እያለ የሚማፀነው ለማኝ የእሱን ያህል

አላገኘም። እንደ ኦፊ. አቡኮ መንግሥቱም ሩፋኤልን እየተገዳደረው ነው?..."

ይሄን እያሰብኩ መስስ ብዬ ወደ ጎዳናው ወጣሁ። የስጦ ብዛት ዳግም አሳንባረውን እንዳያርገፈግፈው ሰጋሁ። የየኔ ብጤዎቹ ሚዛን ዓይኖቼ ላይ አሉ። ማለቱ ቁጥራቸው ሲያንስ ዓይኔን ይቆለዋል፤ ሲበዛ ደግሞ አይኔን ይከብደዋል። ይሄንን ያወቅሁት ዛሬ ነው ዓይኔን ሲከብደው። ብዙ ተባራሪ ወታደሮች በቡድንና በነጠላ ለልመና ተኮልኩለው ዓይን ይይዛሉ። አንዳንዶቹ ክሮቶ በተጨማሪ የጀግንነት ሜዳያቸውን እንደ እናቱ ድንች መድበው አስቀምጠዋል። ሌሎቹ ደግሞ ከአነቤተሰባቸው አንገታቸውን ሰብረው፣ ጭንቅላታቸውን ቀብረው ቆመዋል። አባትየው ብቻ የልመና ስልት ባልተረዳ ድምፅ የክልል "ቻርት" የሚያነብ መስሎ ማብራሪያ ይሰጣል።

"ሃያ ዓመታት ሙሉ፣ በረሃ በላኝ፣ ጥይት አስፈራኝ ሳልል አገሬን በዱር በገደሉ..."

አባቱ ቢመጣ የእኛም ቤተሰብ እንዲህ ወጥቶ ያቀረቅር ነበር? የወታደሩ ሁኔታ ስለወቅታዊ ሁኔታ ማብራራት እንጂ ልመና አይመስልማ።

"...ለነዚህ ቤተሰቦቼ፣ ከባለቤትና ከአባት እናት አገራቸውን በማስቀደም፣ ሀገር ከሌለ ሁሉም የለም በማለት ሃያ ዓመት ሙሉ ዛሬ ነገ መርዶ መጣ በሚል..."

ሁሉም ወታደሮች ላይ እኔ "ሴታሴት" ሰባል የሰፈረብኝ በሚት ተጭኗቸዋል። የእውነታ ተረትነት እዚህ ላይ ነው። ይሄ ሁሉ ወታደር ዘምቶ መንግስቱ ያሉት "ቀዳዳ" እንዴት ሳይደፈን ቀረ? እነዚህ ሁሉ ወታደሮች ካሉ ለየትኛው "ቀዳዳ" አፈሳ አካሄዱ? ...በመጨረሻ ከሚዞርብኝ በላይ በዚህ ኃሳብ ተጭበረበርኩ። ወደክፍል ተመልሼ ተረት መሰል ነገሮች ላይ ማተኮር እንዳለብኝ ገባኝ። ብዙም አልራኩም። የሰንሰል አጥራችን በየኔቢጤ ሽምጥ ታጥሯል። ይሄኔ ቹቹ በሩ ላይ የነበረ ቢሆን "ደም፣ ደም... ሂዱ! ሂዱ ከዚህ ደም" ይላቸው ነበር። በየኔቢጤዎቹ ላይ የበላይነት ተሰምቶታል እንጂ

ፊርቷቸው ቢሆን ኖሮ በሁለት እጁ ሁለት ጆሮዎቹን ደፍኖ ይጮኽል እንጂ "ሂዱ!" አይልም ነበር።

ይሄን እያሰብኩ አጥራችንን አልፌ ቆምኩ። ሦስት ወታደሮች (ከፊተና በኋላ ይመነለሱ) በራችንን አንቀው ቆመዋል። አንዱ የሲላኛው ቅጂ ያስመስላቸው ችግር አሳያቸው ላይ ተለክቶ ይታያል። በተለይ ጫማቸው አላያቸው ላይ ተበታትኖ ሲታይ የድንጋይ ኳስ ለዓመታት ሲያጎኑና ሲያንቀረቅቡ የኖሩ ይመስላሉ። "የደርግ ወታደሮች እነድንጋይ ኳሱ፣ ከመቼው ተበትነው ከመቼው ደረሱ?" ድርቅ ብዬ እንደቆምኩ ከበስተኋላዬ እናቴ ገፍትራ በአፍጢሜ ልትደፋኝ ነበር። ከተልቢ ሆኜ ስመለከት አንዱ ወታደር አንገት ላይ ተንጠለጠለች።

"መሬቴ! መሬቴ! ቤቴ! ቤቴ! ጓዳዬ! ጓዳዬ!" አለች።

ወዲያውኑ ግቢያችን በስሙ ጎርፍ ተሞላ። አህቶቼ በሰሙ ባዘር ላይ እየቀዘፉ ወታደሩ ፊት ደርሰው ጥስስ ይላሉ። እቴቴ በለቅሶዋ ስልት "ትርርርር አባዬ ብርርርር አባዬ!" ትል ጀመር። የእኔ ታናሽ የእቴቴን አባዬ እየተከተለች "አቢን!" ትላለች።

አባቴ ከሙታን እንደተነሳ ቆይቶ ገባኝ፤ ከመልአክ ሞት የጸቀርታ ደብዳቤ እስኪሰጠው ቢያንስ ለሦስት ወር ያህል በመቃብር ቆይቷል። አኳኋኑ የሚገልፀው እንደነገሩ ስበሰ-ስበስ የተደረገውን መቃብር ፈንቅሎ እንደወጣ ነው። ልብሱን ሳያራግፍ እንኳን ወደኛ... ዛብሉን ውኃ የለም? ንፍታሌም ወንዝ አይፈስም? ገሊላ ኩሬ አያቁርም? ቅፍርናሆም ጅረት አይገኝም? ደብረዘይት ፏፏቴ አይንደሰደልም?...

...ሲፈንስ?

# ሻይ ሦስቱ

## ድርድር

...ሲፈን እንደመጣች እናቴን በባልንጀርነት ኩራት ጎተት አድርጋ በጆሮዋ አንዳች ነገር ነገረቻት። እናቴ በእሺታ እራሷን ነቀነቀች። እህቶቼን ሁሉ እየዞረች እንዲሁ አስማምታ ወደ እኔ መጣች።

ሲፈንን ሳያትና ስትቀርበኝ እንደመጀመሪያው ጊዜ ሁሉ የጥሬ ክምር ሆኜ መፍረስ ጀምሬአለሁ።

"አባትህ የቻይናን መሞት እንዳያውቁ፣ ሌሊት በወኑ ይረዳሉ" አለችኝ። እንደእናቴና እህቶቼ መስማማቴን ለመግለፅ ምን ማድረግ እንዳለብኝ አላወኩም። ጭንቅላቴን ስነቀንቅ "እንደሴት ጭንቅላትህን..." ብትለኝስ?

"እሺ?" ስትል ማረጋገጫ ከእኔ ጠየቀች።

"እሺ" አልኳት ከየተበተንኩበት ለመሰባሰብ እየሞከርኩ። ሲፈን ወደእናቴ ተመለሰች። ወታደሮቹን ይዛ ወደቤት ለመግባት እንግዳ መስሎ የተኮለኮለው ሰው እንዳላስቻላት ገባኝ። ለመጀመሪያ ጊዜ ከአባቴ ጋር ዓይን-ለዓይን ተገጣጠምን። ግንባሩ ላይ ብይ መሰል እብጠት ይታያል እንጂ አሱው ነው። አባቴ መንፈሴን ያነበበ መሰለኝ። ፊቱን በኩራት ሞልቶ ግራ ቀኝ ቁጭ ያሉት ጓደኞቹ ጆሮ ላይ ተለግቶ አንዳች ነገር ነገራቸው። ወታደሮቹ በዓይናቸው ፈለጉኝ። የሽንፈት ማላሻ ሊያደርጉኝ የሚመካከሩብኝ መሰለኝ። ወደ ክፍሌ ስገባ ቹቹ እኔ በር ላይ ቁጭ ብሎ ያልጎመጉማል።

"ውጡ፣ ደሞ ደሞ ከጊቢያችን"

አባቴ የእኔን ገመና ለማያውቁ ወታደሮች አንዳንድ የኩራት ታሪክ ያወራላቸው ይሆናል።

"ካልዘመትኩ ያለው ልጄ ያ ነው ጣ! አይ ጀግና ጣ! እናቱ አልቅሳ ባትመልሰው ኖሮ ጣ! ይሄኔ እኛም አንሸነፍም ነበር።" ይሄን ሲል አጠገቡ ብሆን የሲፈንን ጆሮ እንዳታዳምጥ እደፍን ነበር። ብትን ካለው አካሌ አንድ ጥሬ ጆሮዋ ውስጥ ተወትፋ ትቀርና ዘልአለም (አንድ አይና እንደሚባለው) እንደ "ጆሬ" ሆና ትቀር ነበር። ሌላ የተፈናጠረ ጥሬ በአባቴ አፍንጫ ገብታ በሰርን አልፋ ግንባሩ ላይ ሁለተኛ ብይ ሆና ትቋጠር ነበር...

ከሌጋ ላይ መውጣቴን ትቼ መሬት አረፍ አልኩ። ጥቂት እንደቆየሁ "ወንዱ!" የሚል ድንጋጤ ሰማሁ። ጋሽ ተገኔ እንደሆኑ አልተጠራጠርኩም። በአብዮት ጠባቂነት የሚፈለጉ መሰሏቸው ከዓይን ለመሰወር ለሦስት ወር ከቤታቸው አልወጡም። እኛ ላይ የደረሰው ሁሉ እሳቸው ላይ መድረሱ ገርሞኝ ብድራቸውን ለመመለስ አደባባይ ወጥቼ መሮከር አማረኝ።

"ጓዶች፣ ጋሽ ተገኔን የምትወስዱቸው እሬሳዬን ተረማምዳችሁ ነው።"

አሳዳጃቸው ደግሞ ተሳዳጅ የነበረው የአባቴ ሞክሼ ብዜን ሰላምና መረጋጋት ሆኖ፣ የራሳቸውን ጠበንጃ ይዞ፣ በራሳቸው ስልት ተክናንቦና ኀፖርት ደርቦ ነው። "የተሸነፍነውም እኛ፣ ያሸነፍነውም እኛ" ማለት ይሄኔ ነው። ለሩፋኤል ተሸናፊ የሩፋኤል አሸናፊ ተመደበለት።

"ወንዱ! ወንዱ!" ሲሉ ከለትሰው ትንሽ ጠየም ባለ ሰሜት፤ ከሁንም አሻሚ ነው። "ወንዱ" ያሉት እራሳቸውን ከሆነ ተሸንፈው ተደብቀዋል፤ አባቴ ሁለት ወታደር ማርኮ የመጣ መሰሏቸው ይሆን እንዴ?

"ወንዱ ብዜን! ይኸዋ! ማነው እጁን የሚይዝ? ወንዱ!... ወንዱ!" የመጣ ይምጣ ያሉ ይመስላል፤ እኔ ተሰፋ እንደፋረጥኩት ሁሉ ውሽማቸው "ሴታሴት" ብላቸው ይሆን?...

"አንተ ዐረ ህዝብ! ተሸናፊ የደርግ ወታደር ታሞግሳለህ?" የሚል ጽምፅ ተከተላቸው። እናቴ የእኔን ፊንታ ተጋፈጠችልኝ።

"አንት የጓሮ ወንድ! አፋበት ምናምን እያልክ ተሸሽገህ የሰውን ልጅ ሁሉ ስታዘምት ቆይተህ ዛሬ... ጠበንጃ ተያዘና... እከክክ ልቀቁኝ እኔ አበቃጥለሁ፣ ይሄ ፈሳም! ጠበንጃ ቢሸክም አትኳኩሱን የት አውቆት፣ ልቀቁኝ!!"

ወዲያው ብዙ ሰው ሳቀ። ብዜን እናቴን ፈርቶ ከነጠበንጃው ሮጠ? በስንት ድብቃ ከአፈሳ ያተረፍኩትን ነፍስ ጠበንጃ ሰጥተው ሊያስገድሉኝ? ይላል ሮጦ ሲጨርስ በቹቹ ስልት። መቼም በዚች ሰዓት የአህቶቼ ጨጣ ትዝ ሳይለው አይቀርም። አውልቀው የጠፈጠፏት።

እንግዶቹ ወታደሮች ምን ይሉ ይሆን? በብዙ ተአምራት ተኩለክልከው፣ የአባቴን ጨርቅ ይዘው ከመልአክ ሞትና ከአጋፋሪዎቹ የማምለጣቸው ተአምር ተረስቷቸው "ወይ ተአምር" ይሉ ይሆናል። አንደኛ ተሸናፊን ወታደር በአሸናፊ ወታደር ደንብ "ወንዱ!" እያለ የሚቀበል ማህበረሰብ፤ ሁለተኛ እነሱን ያሸነፋቸው ወገን እዚህ ግቢ በሴት ተሸንፎ መሮጡ ሦስተኛ...

ሲፈን ገባች። አልጋ ላይ ስታጣኝ ድንግርግር አላት። መሬት እንደሆንኩ ተበትኜ ከየአልጋ ስሩ እንደምንም ተጠረቃቀምኩና፡-

"እዚህ ነኝ" አልኳት።

ገረማት፤ አገራረሟ ከመቼው ተበትነህ ከመቼው ከየተበተንክበት ተሰበሰብክ ይመስላል። እንደጥልፍ የተወሰወሰ ውበት ያለው ዓይኗን እኔ ላይ እንደጣለች አጠገቤ ቁጭ አለች።

ብትን!! ዳግም።

"ምነው ብቻህን?"

አሁንስ መሰብሰቤን እንጃ! የዛሬው ሩፋኤል፣ ወይም የትናንቱ ኦፋ አቡኮ ከረዱኝ (ኦፋ አቡኮ የሚነግሰው ትናንት ነበር እንዴ?)

"ለምን አባትህን አልሰምካቸውም?"

ለመመለስም ቢሆን ከየተበተኑበት መሰብሰብ ያስፈልጋል። ሲፈን አጠገቤ ተቀምጣ ብሰበሰብም ወዲያው ብትን!!

"የአባትህ መምጣት የገረመህ አትመስልም፤ አይደል?"

አፏ ቢጠይቀኝ ምን ያደርጋል? ዓይኗ እየበተነኝ።

"አይደል?"

"አዎ" አልኳት። ከተሞከረ የማይቻል የለ።

"ለምን?"

"እንዳልሞተ አውቅ ነ..."

"ይኸዋ!" አለች አጠገባችን ሌላ ሰው ያለ ይመስል። "መርደቻው የመጣ ቀን ያላለቀስከው ለዚህ ነው። እኔ መች አጣሁት! አንተ ግድ አልሰጥህ አለ እንጂ እንጓች..."

"እንጓች የወለደችውን ለማምለክ ሰበብ እየፈለገች ነው" ለማለት አሰቤ ተውኩት።

"...አይንህ ይወጋል፣ ትከሻህ ይከብዳል፣ ቀልብህ መጪውን ይናገራል..."

‹ሰውነትህ ይበተናል› ብትል ኖሮ ያለጥርጥር እራሴን ማምለክ እጀምር ነበር። እኔና መንግሥቱ ኃይለማሪያም አቀያችንን ሳንቀበል ህዝብ ጥሎ መኮብለል ዕጣ-ፈንታችን ሳይሆን አልቀረም።

"ምናለ አደብ ገዝተህ፣ እኔ ቡና እያፈላሁልህ..."

አፏን በአፌ ከደንኩት። እውነትም አዋቂ መሆን ለሰበት እንጂ ለኔ አላደረኩትም። ለመገፍተር ደረቷ ላይ ጠበቅ አድርጋ ያስቀመጠችውን እጄን አላላችው። ከንፈሬን በውስጥ ከንፈሯ አጥብቃ ይዛ የጥርሷ ድርድር እየተሰማኝ ስትስመኝ ነፍሴ ተበተነች። የአካል መበተን በስንት ጣዕሙ። እራሴ በጀመርኩት ጦርነት ተሸንፌ "ማሪኝ" ማለት አሰኘኝ። መሳሳም ውስጥ ያለው ተአምር ምንድን ነው? ነፍስ እንደአካል የጥሬ ክምር ናት እንዴ? ካልሆነች ምን በተናት?...

..ወደ ጓዳዬ ፍንግል ብዬ ሲፈንን ለበስኳት። የመልካም ሴብ ሰፊ ሰፊት ይመስል ለአካሊም ለነፍሲም ልክ ሆነች። ከከንፈሬ ከንፈሯን ሳታሸሽ "በሩ አልተዘጋም" አለች።

"ልዘጋው?"

"ደጁ ያሉት ምን ይላሉ?"

"ደጁ ማን አለ?"

ከት ብላ አፌ ላይ ሳቀች። የነፍሴን መበተን ሲፈጣሪ ትቼ አካሌን ስለቃቅም አንድ ነገር ትዝ አለኝ። በእኔና በሲፈን መካከል አንዳች ባዕድ ነገር ገላችን እንዳይነካካ የፈለገ ይመስል ፍርፍር እያለ ሲገፈታትረን። በስንቱም የተደፈነ ትዳሳ ተፈንቅሎና የአፍታ ተክል አድጎ አየሁ። የህልም ልክፍቷን በእውን ሥራ ሥር ተፈወስኩ?

"ሌሊት እመጣለሁ፣ በሩን እንዳትዘጋው"

"ቹቹስ?"

"እሱን ተወው" ካለች በኋላ ፊቷን አጽታ "እሱ እስከዚያ አይቆይማ፣ ይተኛል"

ይኼን ጊዜ ለአብርሃም ቃል የተገባው ዘርህን በምድር አሞላዋለሁ ሲፈን ከሰጠችው ተስፋ ጋር እንደማይነፃፀር ገባኝ። የሙሴ የተስፋይቱ ምድር የአርባ ዓመታት ፍለጋ ከሲፈን መምጫያ ቃልኪዳን ጋር አይኳኳንም። ምናልባት የተኮነነው አዳም ለመዳን ከሚጠብቀው የልጅ ልጅ ጋር በጊዜ እርዝመት ይኳኳን ይሆናል። ሲፈን እስክትመጣ ጊዜ እኝኮ ጨርሶ ለሞት ሲያቀብለኝ፣ ሞት ከሰውነት ወደ አፈርነት፣ ከአፈርነት ወደ ትቢያነት፣ ከትቢያነት ወደብናኝነት ቀይሮኝ አየር ሲ እየተነሳፈፍኩ እንኳን ብጠብቃት ሲፈን ትትመጣም። ጊዜዋ ገና ነው።

ሲፈን ቀሚሷን ወደታች እየሞዠቀች ከዚህ ቤት ከወጣች ስንት ዓመታት ተቆጠሩ፣ ነገር ግን ያለችው ሌሊት ገና አልደረሰም። እናቴ ከቹቹ ወደእኔ ያስተላለፈችው ፈጣን መንፈስ ይሄን የሲፈንን ተስፋ መቋቋም ተሳናት

ቀንሸራቶ ወደ ዘግምተኛው ዓለም ገብቶ ይሆናል። ቹቹ እናቱን የረሳው ከእናቱ የተለየበት ጊዜ በቹቹ አቆጣጠር በምዕተ-ዓመት መስፈር ስለጀመረ ይሆናል። እኔና ቹቹ በአሁኑ ሰዓት አንድ ነን። እናቴ በክንቱ ሀጢያት ገባች፤ በልጆቿ ተናቀች እንጂ አሁን ብትመጣ እኔና ቹቹን መለየት ይሳናት ይሆናል። ምናልባትም፦ "ደሞ፣ ደሞ፣ ደሞ..." ስላት ጠብታ፣ ጠብታ... እናት ናትና ተስፋ ባለመቁረጥ ስትጠብቅ ሰማይና ምድር ያልፉ ይሆናል። የእናቴ ጥበቃ ግን አያልፍም።

ምድር "እልልልልል..." አለች። የሩፋኤል ታቦት ገባ ማለት ነው።

የአጡንት ቤቱን ጠላሁት። የቹቹ መንፈስ በቤቱ ላይ ረብቧል። ሁሉም ነገር ይዘገያል። በይበልጥ የተፈለገ ነገር ያዘግማል። ማዝገም ውስጥ የእንቅስቃሴ ስሙጡ ቢዘገይም አለ። ኖ ኖ ኖ ኖ ኖ እዚህ ቤት የተፈለገ ነገር ይቆማል... ቹቹ ከተደረገበት በላይ በእኔ ላይ ተደረገ። ቹቹ ከተበደለው በላይ ተበደልኩ።

ክክፍል ሰጠጣ አባቴ ገፈቱን በምላሱ እያፈናጠረ ያወራል። እንደተረት አባት አሰሩ የተኮለኮለው ሰው ከአፉ የሚዘንበውን በእንክር ያደምጣል። አብረውት የመጡት ጠቃደሮች እንኳን አብሮን የኖረውን ሰው ምን ነብይ አደረገው በሚል ድንቅ ሀሳብ ያደምጡታል።

"ጥይት ሰንል እንዲህ ቢፈጥኑ ጣ! ሬሽን ሰንል እንደሀ ቢፈጥኑ ጣ! ጥሩ ነበር ጣ! ሰው ሞተ ብሎ ለማርዳት እንዲህ መቻኮል ጣ! የሚገርመው የእንቺ አምኖ እንዲህ መጎሳቆል..."

አባቴ ጥሩ ተናጋሪ አይደለም። ብዙ ሰው እያዳመጠው እንደሆን አረስቶ ለሚሰቱ ብቻ ያወራል። ሰው ሁሉ ጠላ ይፀል። ሲጠመቅ ያልታየ ጠላ ከጉድጓድ ተደነበቀ?

"መቼም ያለሻጥር ጣ! ጥይት ሰንል ሬሽን ጣ!፣ ሬሽን ሰንል ጥይት ይላክልናል ጣ! አረፍ በሉ ከተባልን የሚጠጋን ይመጣል ጣ! ተዋጉ ከተባልን ምናምኒት የለም ጣ! መሄጃችንን የሚያውቀው ጠላት ነው ጣ! እንደ ባቢሎን ዘመን ቋንቋችን ተዛንቶ ፈረሰን ጣ! የእግዚሐር ቁጣ ነው ጣ!..."

የአባቴን ፊት ለማየት ስሞክር የግንባሩ ላይ ዕጢ ትቀድማለች፤ ሲያወራ እንደመንጋጭላ አጥንት ትንቀሳቀሳለች።

"አንደኛ ብርታት ቢሆን ጣ! አፍሪካን ጠቅልለን ነበር ጣ! አንደኛ መስዋዕት ቢሆን እንኳን ኢትዮጵያን አፍሪካን አንድ ባደረግን ጣ! ታዲያ የእግዚሐር ፍቃዱ ያልሆነ ሁኖ..."

አባቴ ሲያወራ የሚንቀሳቀስ የማንባሩ ላይ ብዩን እያለሁ። አንዳንዴ የአባቴ አፍንጫ፣ ዓይንና አገጭ ጠፍቶ ቶዳ የለበሰ ብይ ብቻ ይሆናል።

"ወገኖቼ! የእኔን ጀብዱ ማውራት አይሁንብኝ እንጂ ጣ! እዚች ግንባሬ ላይ ካለችው የተዘቀዘች ጥይት በተጨማሪ ሰባት ቦታ ቆስያለሁ! ሦስቱ ጥይቶች አሁንም አሉ ጣ! እሱ ጓድ (በስተግራው አመለከተ) ጫርሶ ገላው ወንፊት ሆኗል። ጓድ ሻምበልም የኔን ያህል ጥይት አያጣም ጣ! ታዲያ ፍየሚያችን ምን ሆነ?..."

የአባቴ የግንባሩ ላይ ብይ ጥይት ናት ተባለ፣ ጉድ! ጥይቷን እንደ ቀቢ በአፍንጫው ሳባት? ጥይቷ ክሰርኑ አልፋ ግንባሩ ላይ ተወተፈች? ጥይት በአፍንጫው የጠጣላት ኢትዮጵያ ይሄን አይታ ምን መዘገበች? ምን ታሪክ አስቀረች?... ነው ተሸናፊ ታሪክ የለውም ብላ ተወች?

የት እንደተሠራ ያልታወቀ ምስር ወጥ፣ የት እንደተጋገረ በማይታወቅ እንጀራ ላይ እየፈሰሰ ለተኮለኮለው ሰው ሁሉ መታደል ጀመረ። አባቴ እንደተቀበለ ጠቅልሎ ለእናቴ አጎረሰ። አባቴ ምናልባትም ከበላ ሦስት፣ አራት፣ አምስት.. ቀናት አልፈውት ይሆናል። ዝርግ ሳህኑን ሲቀበል እናቴን ማጉረስ አልዘነጋም። እናቴም በመርደው ቀን የገባችለት ቃል አለ። ካልሸፈጠችው የልጆቹ ተገልማጭና የልጆቹ ተለማማጭ አይሆንም።

ሲፈን ዝርግ ሰሀን እያደለች ስትመጣ ሰርቃ ተመለከተችኝ። የነገር ደርዜ ተበትኖ ምን ሳስብ እንደነበር ጠፋኝ። እንኳንም እኔ አልተበተንኩ እያልኩ ሰሀኑን ከእጇ ተቀበልኩ። ከኋላዋ ያለችው ረቂቅ እንጀራ ስታደርግልኝ ሰሀኑን በወጉ አልያዝኩት ኖሮ ሚዛኑን ስቶ ሊወድቅ ነበር። እንደምንም ሳተርፈው ረቂቅ "ኦሆሆሆይ" አለች እንደ እቴቴ።

"ኦሆሆሆይ ይብላሽ!" አልኳት። ረቂቅ ከፊቷ ያለችውን ሲፈን ጎሽም አደረገቻት...

...በዚህ መካከል ወጥ የያዘችው እቴቴ የእንጎቴ እና የዝርግ ሰሀኔ አንድ ቦታ አለመገኘት አሰገርሟት፣

"ታለ?" አለችኝ።

ጭራሽ ተደነባበርኩ። ወጡን አድርጋልኝ ስትሄድ "ኦሆሆሆሆይ" አለች።

ይሄን ዱዳ፣ ይሄን መካን፣ ይሄን አጦር ቃል የማልሰማበት የት ልሂድ?

## ዓፆ ክሎቱ

## ፈጣን ዓለም

የሲፈን መምጫዋ ሲሊት እንደ አዳም ጠዳኛ ቃልኪዳን አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ቆጥሮ መጣ። "ነቅታችሁ ጠብቁ" የሚለውን ትዕዛዝ ለአምስት ሺህ አራት መቶ ዘጠና ዘጠኝ ዓመታት ፈፅሜ አንድ ዓመት ሲቀረኝ እንቅልፍ ወሰደኝ። ሲፈን መጥታ አጠገቤ ስትቆም አየች! እንዴት አፈርኩ!! ሁኖረቱን ያባሰው ደግሞ የቹቹ በንቃት ውስጥ መገኘት ነው። አልጋ ላይ እንደተኛ፦

"ደሞ ደሞ ደሞ ሲፈንን አመጻታለሁ ደሞ" አለ።

ሲፈን እንደቀልድ አይታው ሳቀች። እኔ ግን ደነገጥኩ። ይሄ ልጅ አሁንም እኔ ነው? ተሽፋፍሮ ያባለቀ የጋራ ስሜት ይኖረን ይሆን? ሰል አሰብኩ። ጥበቃዬ የእሱ ነው የእኔ?... የእኔ ከሆነ እንዴት ይሄን ያህል ረዘመ? እኔና ጊዜዬ እጅግ ፈጣኖች አልነበርን? ሲፈንን ችላ ያልኩበት ዘመን የእኔ ነው የእሱ? የእሱ መውደድ የእኔ ይሆን እንዴ?... የእኔና የቹቹ ግንኙነት ቤት ከመጋራት ደባልነት ልቆ የነፍስ ቁርኝነት እንዳለበት ጠረጠርኩ። እናቱን እኔ ከመጥላቴ በፊት እሱ ጠልቷት ነበር፤ ምናልባትም ሲፈንን እኔ ከመውደዴ በፊት እሱ ወዷታል ይሆናል። መንገዳችን ቅደም ተከተል ይሆን? እሱ የረገጠውን እኔ እንድደግም ተፅዕኖ እንደሆነስ? እውነትን በሚታጠቀው እውነታ ውስጥ ምንም ነገር ላይሆን አይችልም።

"ደሞ ደሞ ሲፈን እዚህ ትምጣ ደሞ እኔጋ ትተኛ ደሞ"

"እሺ አመጣልሀ፤ ተኝተህ እንቅልፍ ከወሰደህ አመጣለሁ"

የእኔን ጃርባ በመዳፎቿ በቀኝዋ አያሻሸች። ቹቹ ባይረብሸኝ ምን እሆን፤ ምን ይወጣኝ ነበር? ቀስ በቀስ ወደ ሲፈን ዓለም ገባሁ። ፈጣን የጊዜ አቆጣጠር አላት። ልብ በፍጥነት ይደልቃል። በስሜት ችኩላ ነፍስ ይራወጣል። ሁሉም ነገር ይጣደፋል። የቹቹ የዘገየ ዓለም በሲፈን ፈጣን ዓለም ሙሉ በሙሉ ድል ተመታ። ያንን አሳሳቧን

ኢመጣችው። ምን ብለው ይገልጡታል? ከሳመችኝ፣ መሳሳሙ እኔ እጅ ከገባ እንዴት መግለፅ ይሳነኛል? ነው ሳመችኝ እንጂ አልሰጠችኝ ይሆን? ልክ የሲጠሩና አረፋ እንደመቀባበል፤ ከንፈሩ አለ፤ እጅ ላይ የሚቀር ግን የለም። ልክክ ያለ ሙቀት ከፊቴ ላይ ይሰማኛል፤ ልክክ ያለ ደስታ... እሷም እንዲህ ይሰማት ይሆን? ነው ወይስ አገልግሎት ተቀባይና ሰጪ እንሆን? አንዳንዴ መኪናውን ከፍቶ ለሻይ እንደሚጠጣ ፊልም አሳይ ሰው።

ምንድነው የማስበው? ደስታን ብቻ ሳይሆን ጊዜንና እድሜን የሚሰርቅ ሀሳብ። ጎኔ ተኝታ የመሳሚን ስልት ቀየረች። እሷ ከላይ ሆነች። ይለያል። መሳሚያ አፍ አልተለወጠ እንዴት ተለየ? ከንፈሮቿ የበሰለ ነፃ ሆነው ወደታች በመጫን ይስማሉ፤ እና መሳሚያው ሳይቀየር አሳሳሙ ይለወጣል።

ድንገት እንደተለከፈ ሰው በደረቅ ሌሊት ወጥቼ "ዓለም እንዴት ፈጣንና ውብ ነች!" ብዬ መመስከር አሰኘኝ። "ይሄንን ደረቅ ሌሊት ውብ ያደረገ አምላክ ይመስገን"

አበባ የተኛችበት ሆና "አሜን!" ትላለች።

"እሽሽ" ትላለች እናቴ "እንቺ ልክፍታም!"

"እናቴ፤ አታንገላብጭኝ እረርኩልሽ" አላታለሁ። ሲፈን በሌሊቱ ትራዳሊነት ሳይሆን እንቅፋም ስትስቅ ይዛ ከስር ግባኝ እየተገለበጠ ማረፉ ቀጠለ። ከላይ ስሆን የመሳም ኃላፊነቱ እኔ እጅ የገባ መሰለኝ ነበር። ግን እንደ አረፋው ጓል ተቀባበል፤ ትብብሩ ትክክለኛ እንጂ ነገሩ እጅ ላይ የለም። ከስር ሆና ስትስም ከላይ ሆና መሳሚን ታስንቃለች። በአፏ ብቻ ሳይሆን በእግሯም መዋጥ ትችላለች። ቀጭን የነበረ ገላዋ ውስጥ ትሰገሰ አጠፋችኝ።

አለበቃችም፤ ያ ድንገት የሳንቲም ክዳኑን በርቅቶ የወጣ ወንድነት መግቢያ ሳይኝ አልቀረም። አዲስ የሆነብኝ መሳም አዲስነቱ ሳያረጅ ሳያፈጅ ሌላ ነገር ፈለኩ። እሱ እንደቀጠለ ሆኖ ሌላ ከፍ ያለ ነገር ይመስለኛል።

"ቀይ እሁን አይደለም" አለችኝ አፌ ላይ። "እንደዚህ ደስ ይላል የለ?..."

እውቷን ነው፤ ደስ ይላል። ግን ፈጣን ዓለሟ እንደእንዝርት እራስ ሲጠዝ ሌላ ያስኛል። አሽከርክሪቱ የዕይታ አቅጣጫው በፍጥነት እየቀያየረው ይሆን? እጇ መሰርሰሩን አላቆመም።

"እንቢ አላልኩምኮ" ቱቱ እንዳይሰማ የተሳቀቀች ይመስላል። እንኳን የሱ የእኔም ዓለም የእሷን ፈጣን ፕላኔት አትኩሮ መመልከት አልቻለም። ዘመናት አፍታ ሲሆኑ አፍታዎችን ማን ጠንቅቆ ይከታተላል?

"በባዶ ገላሽ ብቻ አቀፊኝ" አልኩ።

"እሺ ቀይ" ብላ ቀሚሷን ወደ ላይ ሰብስባ በራቁት ጭኖቿ ራቁት ታፋዬን ዋጠችው። አ-ቤ-ት! ግን አይበቃም። ሆዱ ሆዷን እንዲነካ አሁንም ቀሚሷን የበለጠ ከፍ አደረገችልኝ። እነሆ ገላ የአንድ ሰው አካላት ይሁን እንጂ አንድ አይነት መልእክት እንደሌለው ተረዳሁ። እጅ ሲዳስስ፣ ከንፈር ሲዳብስ፣ ጭን ሲውጥ፣ ሆድ ሆድን ሲያላምጥ… የተለያየ ጥፍጥና አለው። ያላየሁት አለ፤ አ-ሱ-ን

"ቀይ" አለች ድምጿን ዝቅ አድርጋ። "እንደ አዲስ እንጀምር፤ አልሳምከኝም አሉ"

"እንዴት?"

"እንዳልሳምከኝ አስብና ለመሳም ለምነኝ"

"በእናትሽ" እየኗት፤ ብርሃን አለ? የለም?

"እንቢ! አታፍርም? ዘለህ ልሳምሽ ስትለኝ?"

እውነተኛ የመሳም ጉጉት አፍተለተለኝ።

"በእግዚአብሔር"

"እሺ እግሬን ሳም"

"እሺ" ወደታች እየተንሸራተትኩ ስወርድ ስወርድ ጉንጩቼን በሁለት እጆቿ ደግፋ ሳበችኝና አፌ ላይ ሳመችኝ። ልጅ ሳለሁ እህቶቼ እያስጨሁ ጉንጩን እንደሚስሙት ያለ፤ ይሄ ግን አያምም፤ ካመመም ደስታን ካለመቋቋም የተነሳ የሚደርስ ጉዳት ሳይሆን አይቀርም። እንደ አዲስ ተንገብገቢ ሳምኳት። ዝም ብላ ተቀበለችኝ።

ገርበብ ያሉ ከንፈሮቿ እንደአሷ በከንፈሬ ገበር ጥርሴን እያስታከኩ ሳምኳት።

"እ-ህ" የሚል ድምፅ አሰማች። እንዳደረገችብኝ እያረኩባት ማለት ነው? ከንፈሬ እንደ መርፌ ዓይን የጥርሶቿን ቀጭን ቀዳዳ አልፎ ወደ ውስጥ ለመግባት እስኪጨንቅ ድረስ ምጥጥ አድርጋ ሳመችኝ።

"ደ!" ፊንዳ፤ ምን? እንጃ!

እቅፍ አድርጋ ጭንቅላቴን አንገቷ ውስጥ ኀሰኀሰችው።

"ልጅ አወድልሃለሁ፤ ያንተን የመጀመሪያ ልጅ፣ የእንዳችን የመጀመሪያ የልጅ ልጅ..."

የሆነ ብርሃን ጨለመ፤ ወይም በፊትም ብርሃን አልነበረም። ሲፈንን ፈራኋት። ሴት እስክትወልድ የሰማየ ሰማያት ኗሪ ናት። ስትወልድ ግን ወደ ምድር ትጣላለች። በልጆች ዕጣ-ፈንታ ትገባለች። ሴት ስለልጇ የወደቀች መልአክ ትሆናለች። በእሳት ስንሰለት ብትታሰር የማትገታ ትሆናለች። በልጆች መካከል ማበላለጫ ሚዛን ታኖራለች።

"ጋሼና አባትህ ይዛመዳሉ" ጋሼ የምትለው እናቷ እንደዘመድ የቀጠረቻቸው አሰሪዋን ጋሽ ተገኜን ነው። "ጋሼ አባቴ እንደሆነ ታውቃለህ? አታውቅም አይደል? እናቴ ለእኔ ብቻ ነው የነገረችኝ። እኔ ለአንዳች ነገርኳት። ጋሼ እንኳን አያውቅም፤ ልጆቹም አያውቁም።"

የሴቶች ዓለም በወንዶች ዓለም ውስጥ በገሃድ የሚኖር ምስጢር ነው። የሴቶች ምስጢር የወንዶችን አለማስተዋል ከለላ አድርጎ ዘልዓለም ሳይገለጥ ይኖራል። ያኔ ሲፈን ግራ ክንዴ ላይ ጠውልጋ እንደተኛች ያሰብኩት ይሄንን ይመስለኛል። ሴቶችና ወንዶች አንድ ዓለም ቢጋሩም እንደጨለማና ንጋት ይፈራረቃሉ እንጂ በጋራ አይኖሩም።

ሲፈንን መፍራቴ ከዚያች ሌሊት ያገኘሁት ፀጋ ነው። የሌሊቷን መፈፀም በእናቴ የመርዶ ለቅሶ አወቅሁ።

"ልጄ! ልጄ!" አለች።

# የ፬ ክምሰት

## መንትዮቹ

ሲፈን ያስጥርጥር ሁለት ናት። እኔ ስለምትወልድልኝ የምጠላት፣ ቹቹ የሚጠዳት። ሳያት እንደጥሬ መብትኑ ቀረልኝና እንደ እናቴ በጠላትነት ዓይን ወግቼ አይዛት ጀመር። ስሜቷ ግራ ሲጋባና ስትሽቆጠቆጥ ይሰማኛል። የዕድሌ መጥመመ ደግሞ የአባቷ የጋሽ ተገኔ ሆድ ሰለባ (አታሰራስሁ በሚል) የናዝሬቱን ቤት አከራይታ እዚሁ ሰመጠቃለል ትምህርት ቤት ተመዝግባለች። አባቴ ተነግሮት የጋሽ ተገኔን አባትነት እንዲያረዳቸው (እንዲያበስራቸው) በሴቶቹ ተመስጥሯል። የሴቶች ምስጢር ወንዶች አፍንጫ ስር የሚከናወን ቢሆንም አይገለጥም፤ ምክንያቱም ደግሞ የወንዶቹ ቅርባቸውን ትተው ሩቃቸው ላይ ማነጣጠራቸው ነው።

ሲፈን እኔጋ ያነጋች ጠዋት የአባቴ ለቅሶ ደራሾች እንደተኮለኮሉ ቹቹ አድርጎ በማያውቀው መንገድ አለቀሰ። ሰው ሁሉ ግራ ተጋብቶ ሲጠይቁት በሳግ እየተደናቀፈ መናገር ተሳነው። በመጨረሻ...

“ደሞ ደሞ፣ ይሄ ታለ ደሞ ሲፈንን ቀማኝ ደሞ” አለ። እቤት ለቀብተኛው እንዴት እንደሳቀ።

ሲፈን ስትሽማቀቅ አንጀቴ ቅቤ ጠጣ። ባፍርም የእኔ ከእሷ ሽምቀቅ ማለት ጋር ሲነፃፀር ውኃ የሚያነሳ አልነበረም። የገረመኝ ከዚያ መሽማቀቅ ሳትላቀቅ በአጠገቤ ስታልፍ “ሌሊት እመጣለሁ” ማለቷ።

“እሆሆሆሆይ...” ከእህቶቼ አንዷ.

ሲፈንን “ምን ልታደርጊ?” ብዬ መጠየቅ እየፈለኩ ሳልችል ቀረሁ። ደስታው የሚገፋ ነው? ከሲፈን ጥበብ የሚፈልቀውን እርካታ ገፈሁት ብል የሚያምነኝ ማነው?

የዚያን ቀን ውጭ አመሸሁ። አባቴ የድሮ ልብሱን ቀይሮ የድሮውን ደርባባ አዛውንት ሆኗል። ሁለቱ ወታደሮች የአባዬን ልብስ ለብሰው የሰፋቸውና የረዘማቸው ቢሆንም ቅሉ ቢዘን በተለያየ ቀን ለባበሱን ወክለው ሦስት ቢዘኖች ትደርድረው ተቀምጠዋል። ሻምበሉ ሲያወራ የአባቴ ብዩ እየረዘመች ሻምበሉ እፍ ላይ የተደቀነች ትመስለኛለች። ምን ሲል ይቺን ጥይት በአፍንጫው ሳባት? የአጼ ቴዎድሮስ ጥይት መጠጣት አደናግሮት ይሆን? መቼም በዚህ ዘመን

አጼውን ለመሆን የፎከረው እንደመብዛቱ አንዱ.ም አልተሳካለት። መንግሥቱ እንኳን አዚያው ወንበራቸው ሲፁ ደርቀው ይገኛሉ ሲባል የሽሽት ጥይት ጠጥተው ዚንባቡዌ ገቡ አሉ። እኔ ሃሳቤን ሰደቀድቅ ሻምበሉ ያለውን ሳልሰማ አለፈኝ።

"...እና ይሄ ሰፈር እንዳልኳችሁ የታሪክ ቦታ ነው። ጥሩ! እዚህ ከፍ ብሎ የሼህ ሆጀሌ መስጂድ አለ፣ ጥሩ!..." ሻምበሉ ለካ ለሩፋኤሎች ሩፋኤልን እያስተዋወቀ ኖሯል። የአባቴ ብይ ትገለባበጣለች።

"መች አጣነው? ጣ!"

"ቆይ-አቦይ" አለ ሻምበል። አባዬን አቦይ ይለዋል? ምን የሚሉት ሹመት ይሆን አባቴ ያገኘው? "ወደዚያ ፊት ያላችሁ እንደሆን የራስ ኃይሉ መኖሪያ ይገኛል ጥሩ"

"መች አጣነው ጣ!" አባቴ ከደጁ ሞፈር የተቆረጠ ሞኝ የሆነ ሳይመስለው አልቀረም።

"ቆይ አቦይ" አሁንም አረጋጋውና ቀጠለ "በዚያ ጋ ይመስለኛል.. ጥሩ... የአንድ ትልቅ ሰው ቤት አለ። ማነው ስማቸው?" አቦይ ከሻንበል ይበልጣል? ያንሳል?

"የሊጋባ በየነን ቤት ማለትህ ነው? ጣ!" አባዬ አለወትሮው ተቀለበለበሳ...

"ቆይ አቦይ" እኛ ቤት ሰሳረፈ እንጂ ሌላ ቦታ ቢሆን ሻምበሉ አባቴን አንድ መቶ ወታደራዊ ፑሽአፕ በቀጣው ነበር። "ቆይ-ቆይ" ጠፋው እንጋጠጠ "አምጡልኝ፣ ስማቸው አፌ ላይ አለ"

"እንዴ ቆይ፣ እንዴ አምጡልኝ" አለ አባቴ ብዩን በሀይል እያሽከረከረ፣ ዛሬ ምን ነካው? ለካ በዚህ ሀባዩ ነው ጠጅ ቤት የሚጣላው።

"ቆይ አቦይ! ጥሩ! በስማቸው ወታደራዊ ማዕረግ አለ..."

"ጀኔራል (ማናቸው) ቡሊ? ሙሉጌታ ቡሊ?"

"ቆይ አቦይ!"

ዛሬ ሻምበልና አባቴ ከምክሼው ክቡዘን ጋር እንደሆነው ተናንቀው ሲጠባወሁ ነው። እህቶቼ አናቱን እያማከሩ ለቀስተኛውን (የለትሶ ቤት ሱሰኛውን) ያስተናግዳሉ።

"በል ቀጠሁ ምን ያለው ነው እባካችሁ"

"እስቲ አታዋክበው!" አናቴ ናች። አባዬ "አንተ" እንደተባለ ቀርቷል "አንቱ" እንደወጣች ቀረች።

"አዎ! ብላቴን ማስልጠኛ አይደል፤ አዎ ብላቴን ጌታ ጎሩይ ጥሩ!"

አባቴ በማንኳሰስ ሳቀ። ሲስቅ ብዩ ተንቀጠቀጠች "ጎሩይ ወልደ ስላሴን ነው አንዴ? ጣ! ባላቴን ጌታ ሹመታቸው አንጂ መች ስማቸው ሆነ ጣ! አይ ያንተ ነገር ጣ!..."

"እስቲ ይጫወትበት" አናቴ በፊት ቢሆንም የበረሃ ጅኒው ይጠሳ ነበር።

ሻምበሉ የስማው አይመስልም "ቀይ አቦይ" ብሎ ቀጠለ። "አ-የልጅ ኢያሱ ልጅም አዚሁ አለች ሲሉ ሰምቻለሁ። በስሟ ድልድይ ተሰይሞላታል"

"ዓለም ፀሐይን'ኮ ነው ጣ! ድልድዩ ቀርቶ ጥቂት የተጠረሰባት ቤት ቢመለስና ኑሮዋ ከትቢያ ከፍ ባለ ጣ! የተቀደደ ነጠላ አጣፍታ ጣ! ኮንጎ ጫማዋን እየጎተተች በዚህ ታልፋለች። ጣ! በእሷ ላይ የተሠራ ግፍ ነው እኛን ሁሉ መቅኖ ያሰራቀን ጣ!" አባቴ ሲያዝን ብዩ ቀዝቀዛ አረጋች።

አባቴ በዚህ ፀባዩ እንዴት ታሪክ ሊያውቅ እንደቻለ ገረመኝ። አፍ አፋችውን እያላቸው ታሪክ የሚነግሩት አይኖሩም። ታዲያ እንደነባጅ ታሪክን መሬት ቆፍሮ አወጣ? ይሄ ሰው መቶ ዓመት የመኖር እቅድ ያወጣው ምናልባት ከዚህ በፊት አምስት መቶ አመት ኖሮ ይሆናል። ግማሽ ምዕተ አመት ታሪክ ነጋሪን አፍ አፋን ቢልም የተሸራረፈውን በጊዜ ብዛት እየገጣጠመ አንድ ያደርገዋል። ለዚህ ነው፡-

"ዓለም ፀሐይ ስትወለድ ጣ! ጎጃም የተተኮሰው ጥይት ጣ! የአድዋ ጦርነት ላይ ሩቡ አልተተኮሰም።"

እውነት ሲጣመም ከተረት ይብሳል። ብርቅ ሆኖ መቶ አመት ከተከበረ ብሔራዊ ድል በላይ ለመወለዷ ጥይት የተተኮሰለት ሰው፣ መኖሩ ክንብንቡና መጫሚያው በነተበ ድህነት ይከናወናል። እኚህን ሴት እኔም አይቻቸዋለሁ። የእሳቸው ለነበረው መላው ጉስሌ ባዕድ ሆነው በእንግዳ መልክ ይሹለከለኩ ነበር። ልጆቹ "ዓለም ፀሐይ ድልድይ" ይሏቸዋል። ስማቸው ስለገጠመ መሰሎኝ ነበር። አባቴን ስጠይቀው ዛሬ የተናገራትን ሁሉ ልቅም አድርጎ ነገረኝ... ከዚያም የብላቴን ጌታ ጎሩይ ወልደሥላሴን ጨመረልኝ።

ብላቴን ጌታ ግቢ ብዙ አይነት ፍራፍሬ አለ አሉ። ዓመቱን ሙሉ ፍሬ አይጠፋም። ታዲያ ዘበኛው ክፉ ነው። ልጆቹ የብላቴን ጌታ ልጅ እስኪመጡ ጠብቀው ከዘበኛው ጋር መነታረክና መባረር ይጀምራሉ።

"ምንድን ነው?" የብላቴን ጌታ ልጅ

"ፍራፍሬ ስንለቅም ይመታናል"

"ለልጆች ካልሆነ ታዲያ ለማን ሊሆን ኖሯል? በል አርግፍና ስጣቸው" ሲሉ ዘበኛውን ያዙታል። እዚያ ያለ ውሪ ሁሉ ፍራፍሬ በጨርቁ ታቅፎ-ታቅፎ ይሄዳል። እኔ እንኳን ፍሬ ካመጡ ልጆች ገዝቼ ቀመስኩ እንጂ እዚያ አልሄድኩም። እነ ሸሮ መዋያቸው እዚያ ነበር።

° ° °

እኩለ ሌሊት የጊዜ መግፋትና የመጠጥ መንሰራፋት ሰውን አደከመው። ሁለቱ ወታደሮች እነቹቹ ቤት ገብተው እረፍ እንዲሉ ተነገራቸው። እነአባዬ ትልቁ ቤት ሲገቡ የለቅሶ ቤት ሱሰኞቹም የጠጅና የካርታ ማኅበራችን አፍርሰው ለመበተን ተገደዱ። እኔ ወደ ክፍሌ፤ ጨልሚል። ተንጠራርቼ መብራቱን "ቶግ" ሳደርገው ሲፈን አልጋ ላይ ተኝታለች። አጠገቧ ቹቹ በጀርባው ጓ ብሏል። ዓይኖቹ እንደፈጠጡ ናቸው። ሲፈንን ነቅንቄ ቀሰቀስኳት።

"ለምን እዚሁ እንተኛም በጋሼ ሞት" አለችኝ። ይፋ በሚወጡ አዲስ አባቷ መማል ጀምራለች ማለት ነው?

"አይሆንም ነይ መሬት" ብዬ ወረድኩ። ከቹቹ ጋር ምንም እንደማታደርግ ባውቅም ደስ አላለኝም። ስሜቴ ወደደስታ ሀሰሳ እስኪያቀና ትንሽ ጊዜ ወሰደብኝ። ሲፈን የተቋረጠ እንቅልፏን ለመቀጠል እጅ የመስጠት አዘማሚያ ላይ ነች።

"ለአባትሽ ተነገራቸው?"

"እ-እ..." ዝም

"ለወንድሞችሽስ?"

"እ-እ... እ-እ..."

"እኔ ለትንሹ ወንድምሽ ነገርኩት" ድንግጥ ብላ ቁጭ። ዓይኖቿ ገላዬን የመበተን ኃይላቸውን ማን ገፈፋቸው? እራሴን በየአልጋስሩ እና በየአይጥ ጎሬው ፈልጌ አገኘው አልነበር?

"ውሸቴን ነው"

"ው...ይ" ልቧን በሚያማምሩ ጣቶቿ ደገፈች "ልክ አይደለህም፣ ጋሼ ይሙት"

የእቴቱ መክሳተር "ሰው ሰራሽ"ነቱ ሲፈን ላይ በአባት ደርሶ ቢሆንስ? እንዲት ሴት ከወለደች በኋላ፣ ከሰማየ-ሰማያት ከተወረወረች በኋላ፣ የወደቀ መልአክ ከሆነች በኋላ... ለልጇ የማትቀምረው መላ አለ? ስለልጇ ለምትፈፅመው ሀጢያት የአባዬን መልአክሞትና

ጭፍሮቹን ያስፈራታል? እና የሲፈን እናት የልጃቸውን ብቸኛነት፣ የጋሽ ተገኔን በወንድ ልጅ መጥለቅለቅ መዝነው መከታ ለማብዛት፣ አንድ ቀን የተሳሳቱት ጋሽ ተገኔ ላይ ል-ጥ-ፍ! ጋሼ ተገኔስ ምን አሳሳታቸው?.. እኔስ ይኸው ልሳሳት አይደል?...

"መብራቱን አጥፋው"

ከዚያ...

"ለምነኝ"

ከዚያ...

"እንደ አዲስ መሳሳም፤ እንዳልሳምክ ስሱብና..."

"በቃ እንተኛ..."

"ተው..."

ከዚያ

"እንድለምንህ ነው?"

ከዚያ

"እሺ ለምነኝና ሲክስ አናደርጋለን"

ብድግ "በእናትሽ"

"እንቢ! አ!..."

"በእግዚአብሔር፤ የእኔ እመቤት፣ ሲፈንዬ..."

"እምቢ፣ ለሴክስ ሲሆን ለመንከኝ..."

"የናዝሬቷ ሲፈኑ እንዲህ እንደትዕዛዝ ነው እንጂ እንቅልፌ አልመጣም"

"ምን ብለህ ጠራኸኝ?"

"የናዝሬቷ ሲፈን... አይደለሽ?"

"ኡ! አንተ ልጅ? ልታሰቀስፈኝ ነው? ኢየሱስ በሚጠራበት?..."

"እሱም አንቺም የናዝሬት ልጆች፣ እሱም አንቺም ቆንጆዎች፣ እሱም አንቺም ገበያ ሙሉ ሰው የሚከተላችሁ..."

ክንፈሯን ገልብጣ በውስጡ ሳመችኝ። ቀሎ እጄን ወደ ቀሚሷ ሰሰድ "ቆይ" አለች።

ለካ የራሱ ስልት ኖሮታል (የታባቷ ተማረችው?) የት እርቴፊሻል አባቷ ተማረችው ልበል እንጂ...

...ልመናው ከአፍ ወደግብር ተቀይሮ የአምልኮ ገጽታ ይኖረዋል። ከወገቤ በታች ጠጋ ስላት፣ ሸሸት። ሸሸት ስላት ጠጋ። እጇን ስስድ ያዝ፤ ስተው እሷ በአፍራም መጠን ገለጥ አድርጋ ከትኩሳቱ ማትመስ... እንደገና ሰጣጋ ሸሸት... ሙጥኝ ስል ትውት አድርጋኝ ትኩረቱን ወደመሳሙ ሷጋ እንዳደርግ መርዳት። ሲያፈነዳኝ የደረሰው ትኩሳቷ ትኩረት በማጣት ጋብ ብሎ ሰረጋጋ፤ እሳት ላንቃዋን ከፍታ ቶሎ ጭኗ መሀል ክትት ታደርገኝና በእንዳች ነገሬ እንዳች ነገሯን ሰፈልግ አሁንም ታረጋጋኛለች፡-

"እንደእኔ አድርገህ ሳመኝ፣ አሪፍ ወንድ እንዲህ ነው"

ከራሴ ጋር ፋክክር፤ ከሌለ እኔነቱ ጋር ፋክክር፤ እንደአሪፍ ወንድ ሰሰማት እታች ያለውን ነገር እርስት። እሷ ቀስ በቀስ በመሳሟ የተደሰተች እስመሰላ፤ ቀስ በቀስ እቶኗን ከፍታ ጥጥ ታደርገኛለች። እዛው እንዳለሁ በስሜት ዝብርቅርቁ ሲወጣ መመሰከር ያምረኛል።

"ሲፈን፣ የናዝሬቷ ሲፈን እንዴት ብልህና ውብ ነች!"

"አሜን!" (አበባ)

"አሸሻ፣ አንቺ ልክፍቲያም" (እናቴ)

ይሄን ማሰብ እራሱ የስሜትን እድሜ ማራዘም፤ ፅድቅ ውስጥ መቆየት መሆኑን ቆይቼ ተረዳሁ።

"ሲፈን፣ ሲፈን፣ ሰ.ፈን..."

አፈን በጣቶቿ ጥርቅም አድርጋ ፀዛ እላዬ ላይ ወጣች። ነፍሴ ስሟን ማነብነቧን አላቆመችም።

እሷም

"እ...ህ!" የሚል የእሮጌ ላንቃ ድምፅ አሰማች። እንዳደረገችብኝ አደረኩባት ማለት ነው? ከንፈሬን ወደ ጥርሶቿ ቀጭን ቀዳዳ ምጥጥ አድርጋ ለመበተን ሞከረች። በመቀጠል ጭንቅላቴን አንገቷ ውስጥ ኀሰገሰች።

በአማርኛ የምንፈራው በእንግሊዝኛ የምንደፍረው ሴክስ ይሄ ነው? የማይስፈር እረፍት ተሰማኝ፤ ምን ተሸክሜ ነበር? የማይለካ ጥልቅ ፀጥታ ውስጥ ሰጠምሁ፤ እንዴት ያለ ጫጫታ ተሸክሜ እዞር ኖሯል?

# ፃያ ሶፀሶት

## የተቀመሰው

ነፍሴ ለሲፈን ተአምር ቀንደኛ መሰካሪ ሆነች። እናንት ሽክማችሁ የከበዳችሁ ወደ ናዝሬቷ ሲፈን ሂዱ እርሷ ከሽክማችሁ ትገላግላችኋለች፤ እናንት የዓለም ቱማታ ቀልባችሁን የነሳችሁ ወደ ናዝሬት ሲፈን አቅኑ የሰማይ ፀጥታን ታወርሳችኋለች። እናቴ የናዝሬቷ ሲፈን ተከታይ መሆኔን ብታውቅ ምን ትለኝ ይሆን?

"ታለ፣ አንት ልክፍቲያም"

እንደ አሸሻ ድንገት "በሲፈን ሥም" ሰልስ? እህቶቼ "የብዜን ሴት ልጆች አብዮታዊ ደሞክራሲ ግንባር" (ብሴአዴግ) አቋቁመው ይዘምቱብኝ ነበር። "ዝምበል! ዝምበል!..." ነፍስ መክፍ መሳሪያ "እሆሆሆሆይ!" ከባድ ጦር መሳሪያ...

እሁን ላይ ሆኜ እንደሚገባኝ በዚያ ጊዜ ከሲፈን ያገኘሁት እረፍትና ፀጥታ ሌላኛው የእውነታ ግላጭ ሆኖልኝ ነበር። በተረት አባሮሽ አሽሽ የነበረው የቹቹ እና የቻይና እውነት በሌላ እውነት ካልሆነ በስተቀር ድብብቆሹ እድሜ እንደማይኖረው የገባኝ ይመስለኛል። ልክ እሾህን በእሾህ እንደሚባለው የሲፈን እውነት የቹቹንና የቻይናን እሰካሪ እውነት የሚያስዝብ ማላሻ እንደሚሆን ገብቶኝ ነበር።

ሲፈን ስትመጣ ከመበተን የላቀ መሽኮርመምና ማፈር ነፍሴን ይደቃታል። ደረቴ እሷን ለመዋጥ ያዛጋል፤ እአአአአ... የሚል ድምፅ ይሰማኛል። ከወገቤ በታች እራቁቴን የሆንኩ ያህል እሷን እንደሱሪ እስከታጠቃት ወንድነት እንደምሰጥ ያንከተኛል... የቹቹ ምህዋር ውስጥ ዘገምተኛ ሹረት ያጠዘኛል። ጥቂት የሲፈን ቃላት ሞቀው፣ ግለውና ፈንድተው የኢዮሩ ግዙፍ ዓለማት ሲሆኑ ይሰማኛል። ቆይ፣ እንዳልሳምከኝ ሁን፣ ስምንኝ፣ እንቢ፣ እግሬን ሳምና፣ ሴክስ እናደርጋለን፣ እ-ሀ... የቃላት ፕላኔቶች በሲፈን ዙሪያ ይሽከረከራሉ። እኔ ከፕላኔት ወደ ፕላኔት የምዘል ከቀንጫ ያነሰኩ ፍጡር ሆኛለሁ።

እናቴ ስለወንዶች በፍቅር መነሁለል ስትሰማ "አንዳች ነገር አቅምሳው እንጂ መች በጤናው" ትል ነበር። እኔም ሲፈን አንዳች ነገር አቅምሳኝ እንጂ መች በጤናዬ ከዓለማት ዓለማት እባዝን ነበር?

መቃበዜ እያስፈራኝ ቀደም ሲል የነበረውን ጭምት ፍቅርና እንደጥሬ መበተን እመኝ ጀመር።

ግን፣ ግን ሲፋን ያቀመሰችኝን ሁሉም ሴቶች ለሁሉም ወንዶች ማቅመስ ይችላሉ? ቢሆንስ ማቀመስና መቀመስ እንደሰው አይለያይም? እንደፈተናስ ደረጃ አይወጣለትም? መቼም ከሰባ ስድስት ልጆች አንደኛ እና ሰባ ስድስተኛ የሚወጣ ተማሪ መኖር አለበት።

ሲፋን መንፈሴን ብቻ ሳይሆን ሀሳቤንም በአቀመሰችኝ አንዳች ነገር ተቆጣጠረችው። በቹቹ ምክንያት የሚያነክተኝ ዐዐት በቻይና ሰቡብ የሚቦጠቡጡኝ ሀዘን የህይወት እቅሌን ወደመሳቱ መርቶኝ ነበር። የናዝሬቷ ሲፋን ሽክሚን ስታቀል ቹቹን እያየሁ ዐዐቱ ሳይዳበስው መቅረት ጀምሯል።

ለከባቢ ሁኔታዎች የምሰጠው ትኩረትም ቀንሷል። ዛሬ ቀን ሰንት፣ ምን፣ የት፣ እንዴት... የሚለውን ለማስታወስ እችገራለሁ። አሁን እንኳን የአመቱ በጀት መዝጊያ የሚመስል ኃይለኛ ዝናብ እየዘነበ እንደሆን ቆይቼ ነው የተረዳሁት። መብራቱ እንደበራ ነው። መንጋቱና መምሸቱ አምታታኝ። መብራቱን አጥፍቼ ወጋገን ለማየት ሞከርኩ። እምብዛም ጨረር የለም። ሲመሽ ወይም ሲነጋ እንደሆነ ገባኝ።

ሲፋን ዛሬ እኔጋ አልነበረችም። አባቷ ልጃቸው መሆኗን ሳያውቁ "የሰው ልጅ ልትበላሽብኝ ነው" ሲሉ አጉረመረሙ አሉ።በአፈሳ እንዳላስደበቁ፣ ለአፈሳ እየተደበቁ። ወንድሞቿ መሆናቸውን ባለማወቅ "የሰው ሰው" በማለት እያዩ ያላዩ ሆኑ።

"ትንሽ ቀን፣ እስኪረሱ" ስትል ተማጠነችኝ። "እንዳለሁ አሰብና በግራ ጎንህ ተኛ። እኔም እንዳለህ አሰብና በቀኝ ጎኔ እተኛለሁ"

"እላዬ ላይ እንድትሆኚ ብፈልግስ?"

ሽኩርምሚት እንደሰርቅታ ለአፍታ ትንፋሿ አቋርጠባት ያልፍና "አሰስምንሃለኋ" አለች።

"ልምን አደርጋለኋ"

"እሺ. እግሬን ሳም እልሃለሁ!"

"ሳም አደርጋለኋ!"

"እሺ. እልሃለኋ"

"በያ"

"አሁን አይደለም'ኮ ሌሊት በየቤታችን ስናድር አንተ በጀርባህ ትተኛና እኔ አንተን እያሰብኩ በሆዴ..."

ሰካ ዝናቡ አባርቶ ኖሯል፤ ወጋገኑም በበሩ ስንጥቅ ፍንጥቅ ብሎ ጆንያ የለበሰው ወለል ላይ በፈዛዛ ተሰራጭቷል። ወዲያው ከባድ የእግር ዳና እርጥብ መሬት እያንጬፈጨፈ ተሰማ። ከቀልቢ ሳልሆን አፈሳ መስሎኝ ብትት አልኩ። እናቴ ከሴሰች ሲወስዱኝ ይችላሉ። ወዲያው እስታውሼ ሳቅ አፈነኝ።

የእግር ዳናውን ድምፅ አጀብሁ።

"እንጓች? ጣ! እናቴ? ጣ! መጥተናል ጣ! ያዝ እንኳ ጓድ ባሻ ቦሩ ጣ!"

አዲስ ፍቅር ያመናቅር፤ ትንሽ ሲቆይ "ሰፍተን ሰፍተን..." ሰማለት፤ እሷም የቀድሞ እንቱታዋን ከተሰቀለበት አውርዳ አቧራውን ልታራግፍ "እንቱ፤ የበረሃ ጅኒዎ" ልትል... ሰቅዛ ከያዘኝኝ ሲፈን ፋታ ለመውሰድ ወጣሁ።

ሣስቱ ወታደሮች በአለባበስ ሣሰት ቢዘን ሆነው እየተረዳዱ የተቋጠረ ጆንያ ይፈታሉ። የደርግ ግብአት መሬት ያልተፈፀመው እኛ ቤት ብቻ ይመስለኛል።

"ጓድ ባሻ ቦሩ!"

"ጓድ ሻምበል" ይባባላሉ። በተለይ መጠጥ ቀርቦ ሞቅታ እስኪረብብ ወታደራዊ ሥርዓቱ እንዳለ ይቀጥላል። ለሽንት የሄደው ሲመለስ በተለይ ሻምበሉ ከሆነ ሁለቱ የአሰባበሰ ቢዘኖች ተነስተው እግራቸውን በመግጠም እንደመንጠራራት ያለ ወታደራዊ ሰላምታ ይሰጣሉ። ሻምበሉ መለዮው ባይኖርም የመለዮ ሠላምታ በአፀፋ ያቀርብና እኩል ይቀመጣሉ። ትንሽም እኛ ግቢ ደርግ አዘቅዝቶ መታብሩን የሚያየው ሞቅታ ሲሰፍን ነው። አባዬ ብዩን አሹሎ ሻምበሉ አፍ ውስጥ ሲከት ያነጣጥራል።

ወታደሮቹ ተረዳድተው ከፈቱት ጆንያ ውስጥ ለስላሳ የተጠጠረ ብልጭልጭ ሰልቻ አወጡ። ሰልቻው ሲታይ የሲፈንን የከንፈር ገበር ይመስላል።

"ብረት ምጣድ ጣ! ገበቴ ጣ! ልጆች ጣ! ቢላዋ! እንጓች! ጣ" አባቴ ሮጦ የሚያመልጥ ነገር እንደያዘ ሁሉ ተርበተበተ። ወዲያው እቴቴ ውስጥ ገባች፤ ረቲት ወጥታ ገባች፤ እቴቴ ሳፋ ይዛ ወጣች። መፀየፍ ባስበት ሁኔታ "ጆንያው" አጠገብ አስቀምጣ ይዛ የመጣችውን ቢላዋ ሳትሰጥ ዘወር አለች።

ምን እንደሆን ለማየት ጠጋ አልኩ። አባቴ የካኪ ኮቱን አውልቆ ዝናብ እያገ ለቴቱ ሰጣት። ሸሚዙን ሰብስቦ እቴቱ የያዘችውን ቢላዋ ትቀብሎ እዚያ ሳስቲክ የተሰበጠ የሚመስለው የተፈጥሮ ከረጢት ላይ አሳረፈ። ወዲያው ቀጭን ፈርስ ሳፋው ላይ ተንዠቀዠቀ።

ባሻ ቦሩ ተነጥሎ እቴቱን ያነጋግር ጀመር። እቴቱ ከቤት ትልቅ ድስት አውጥታ ሰጠችው። ሳቷ የመጣ ይመስላል።

አባቴ ከረጢቱን ቀድዶ ሲገለብጠው ወፈር ያለ ፈርስ ዱብ፣ ዱብ ሲል ታየኝ። ከሻምበሉ ጋር እየተረዳዱ ተሸጉጠው የቀሩ ጠፍራም ፈርሶችን እየጠረጉ ማውረድ ጀመሩ። አባቴ እንደወሬው ሁሉ ሥራውንም ይሻማል። ከረጢቱ የጠበኩትን ያህል አልሚሸሽም። ውስጡ ድርብ ድርብርብ ሆኖ እየፀዳ ሲሄድ በግማሽ የተቀረደደ የብራና ኳስ መሰለ።

አባቴ የበሬ ጨጓራ ወጥ ሊሰራ? ለታቦት ተስሎ ይሆን እንዴ? "ከሞት የመለሰከኝ እንደሆን ጣ! በድብቅ ለሚሸቱ የሠራሁትን የጨጓራ ወጥ ጣ! በአደባባይ ሰርቼ እዘክርሃለሁ ጣ!" ብሎ ይሆን?

እናቴ ብቅ ብላ "እናንተ ከገዛችሁ አይበቃም ወይ? ብዜን፣ ለምን ሴቶቹ አንሠራውም?"

"ተይ ጣ! ይሄ የወንድ ሥራ ነው"

"ደሞ ከነእበቱ ተሸክማችሁ መጣችሁ? እዚያው ኬላ አታራግፉትም ኖሯል?" እናቴ በአቃቂር ተውባ።

ያ የወንድና የሴት ተግባር ደልዳይ ሰው ትዝ አለኝ። "የበሬ ጨጓራ ከሆነ ወንድ ወጥ ቢሰራ አያስነውርም" ሲል ደንግጎ ኖሯል? ይሄ ሥራ ፈት። ምክንያቱ ምን ይሆን? የራሴ የሴታሴትነት ውርክብ ትዝ አለኝ። ወንዳወንድ ሆኛለሁ? ወይስ እዚያው እላዬ ላይ የሚያንገብበው ሴታሴት ሥር ነኝ?

"ና ጣ! ያዝ ጣ!" አለኝ ያለስራ መንከርፈፌ ከብዶት። "ሻምበል፣ ሽንኩርት ጎረድ ጎረድ አድርግ"

ሴት ሽንኩርት ትከትፋለች፣ ወንድ ሽንኩርት ጎረድ ጎረድ ያደርጋል።

አባቴ ጨጓራውን በቢላ ሲገዘግዝ እኔ እወዛውዛለሁ። ጨጓራውንም ጎረድ-ጎረድ እያደረገ ትልቁ ድስት ላይ ይወረውራል። አካባቢው በፈርስ ሽታ ተናውጧል። ጨጓራውም አልጠራም። አድቅቆ መክተፍ ብቻ ሳይሆን አፅድቶ ወጥ መስራትም የሴት ሳይሆን አይቀርም። ሙልጭ ሙልጭ እያለ ከሚያስቸግረኝ ፈርስ ጋር የሚሰራ የወንድ ወጥ "አበት ወጥ" መባል አለበት። እቴቴ የሴት ጣልቃ ገብነት ፈፅማ ውኃ በባለ. ለቀብላ እንደተፀየፈች ሸሸች። ሻምበሉ እቴቴን አይቶ ሳቀ። የሚልጠው ሽንኩርት ሊያስለቅሰው እየሞካከረው ነው፤ ገና በመላጥ ካለቀሰ ሲከትፍማ ደረት ይመታል ማለት ነው።

ቁጥር አንድ ቢዘን ጨጓራውን እንደልብስ አጠበ፣ ቁጥር ሁለት ቢዘን እንዳልኩት በደረት መምታት ስልት እየዘለለ ሽንኩርቱን ከተፈ (እቤት ውስጥ ቢከትፍ ኖሮ እንደሀዘንተኛ ፊቱን ሲነጭ ነበር?) ሦስተኛው ቢዘን ሦስት ድንጋዮችን ጎልቶ ቦታውን ለማደራረቅ እመድ ደፋ፤ የፍልጥ እሳት አቀጣጠለ።

ሴቶቹ በወንዶቹ ይስቃሉ። የእቴቴ ሰው ሠራሽ ኩስትሯ የተፈወሰ መሰለ "ቃሪያ ጣ! ቃሪያ ጣ!"

"እይ ሞያ እቴ! ቃሪያው በስሎ ሲወጣ መስሎኝ የሚከተተው" እናቴ እንደአባቴ ወሬ፣ ሥራዋን ስለተነጠቀች ለመንቀፍና ለማጣጣል ያሰፈሰፈች መሰለች።

"ድንቹስ? ጣ!"

"ድንቹ አጋማሽ ላይ ይገባል፤ ሳታውቁ ነው የጀመራችሁት? እይ የወንድ ነገር... ኧረ የታጠበበትን ድስት አለቅልቀው፣ ከነ እበቱ ልትጥደው? ምነው ብዜን?..."

"እሳት ከመታው ምን ይሆናል? ጣ!"

"እኛንም ብሉ ማለታችሁ አይቀር፣ ነይ እቴቴ..."

"አይሆንም ጣ! እኔ አጥበዋለሁ"

ተጣደ፣ ወጠ-ሠሪዎቹ ወታደሮች ድስቱን ከበው ሆዳቸውን በአረቂ ማሟሸት ጀመሩ። ትንሽ ሲፈላ ሽንኩርቱ ተጨመረ። ከዚያ በወንድ ብሂል ጎረድ ጎረድ ያለ ድንች፣ አባዬ እያለፈ እያለፈ በፍልጥ ያማስለዋል። እሳቱ ሳይቀሰቀስ ቀርቶ ጭስ ከበዛ ሻምበሉ ተነስቶ ይሸሻል። አይኑ ድጋሚ እንዳያለቅሰበት። አባቴ ይሞክርና ሲያቅተው፣

"ባሻዬ ጣ! ና እባክህ" ይላል፤ የበረደች ጥይቱ በእሳቱ ሞቃ እንዳትተኮስ ሳይፈራ አልቀረም።

ባሻ ቡሩ የእሳት ማንደድ ተሰጥኦ ሳይኖረው አይቀርም እላለሁ። ተሰጥኦ ሳይሆን የእሳት ግርማሞገስ ያለው ይመስል እሳቱ ገና ሲጠጋው ነደደ።

አባቴ ቃሪያ መጨመር ላይ እየቸኮለ አስቸግሮ እየተከለከለ ቆይቶ በኋላ በእናቴ ተፈቀደለት። በቁመቱ እየሸነተረ ከተተው።

"ተገኙን ጥሩ ጣ!"

ጋሽ ተገኙ ሞያ እንዳይቀዱ የተፈሩ ይመስል ሲበስል እንዲመጡ አበባሽ ተላከች። "ልቢን!" ለማለት እየቃጣት፣ ጉርዱ የሀዘን ቀሚሷ ሰፍቷት ከፍ ከፍ እያደረገች ሄደች። እንግዲህ ሲፈን አባትነታቸው ሲነገራቸው መሰሏት ከተኛችበት በድንጋጤ ተነስታ ቆጭ ትላለች፤ እንዳልሆነ ስታውቅ "ወ...ይ" ልቧን በሚያማምሩ እጆቿ ደግፋ "ልክ አይደላችሁም ጋሼ ይሙት"

ሲፈንን ሳስብ እንደወታደራዊው ሰላምታ ከተረከዝህ ተነስተህ ተወጣጠር፣ ተወጣጠር አለኝ። አንዳች ነገር አቅምሳኝ።

ጋሽ ተገኜ እየተገላመጡ ከጠረጴቻቸው ከአበባሽ እፍታም ሳይቀዩ መጡ። ከእሳቸው ኋላ ያልተጠሩ ጥቁር እንግዶች ተኮለኮሉ። የአባዬ ወታደሮቹ ተረጋግተው መጫወት ጀመሩ። የወንድ ወጥ ሙብሰል ሲጀምር የአባዬ ብይ በካቲካላ ሰሙ-ሠራሽ ሙቀት እየተነቃቃች መንጠራራት ጀመረች። እንግዲህ ሻምበሉ አፍ ካልገባሁ ብላ ትሸላለች።

ሲፈን በሰንሰሉ አጥር በኩል ተንሿካ ብቅ አለች። የእኔ የወሲብ ዐሒይ ወጣች። ብርሃንና ሙቀት ከበበኝ። የተሸማቀቀው ፊቷ ለተቅ እያለ ከንፈሯ ላይ ዋሽ ሳቅ እየተጫወተ ወደ ውስጥ ዘለቀች። እንዳትረተረች እናቴን በጠረኗ ፊልጋ አገኘቻት። በተራ በተራ ጆሮና አፍ ተቀባበሉ። ሲፈን አምሮባታል። ከአምሮት ጋር ይያያዝ ይሆን? እየችኝ፤ እያየኋት ስለነበር የሚያማምሩ ዓይኖቿ የሚለቋቸው የጨረር ቅንጣቶች እየተጠማዘዙ አፍራም መልእክት አስተላለፉልኝ። እንደ ወታደራዊው ሰላምታ ክተረከዝህ ተነስተህ ተወጣጠር፤ ተወጣጠር አሰኙኝ።

ሲፈን ወዲያው ዓይኗን አስደንግጣ ተነሳች። በሰዎች ወንዝ ላይ እየቀዘፈች፤ እንደደራሽ ውሃ እየተገዳደራት ወደእኔ ክፍል ገባች። ወዲያውኑ አንድ ወንበርና ቹቹን ይዛ ብቅ አለች። ዐዐት ተሰማኝ፤ እንዲሁም የማገናዘቢያ ጊዜ ያልሰጠኝ ቅናት አከታለፈኝ። ቀጥሎ ፍራቻ፤ እኔን ስታይ ለምን ቹቹን አስታወሰች? ቹቹ የእኔ ጥላ ነው? ወይስ እኔ ላይ የቹቹ መንፈስ ተቦጭቆ ቀርቷል? ተበዳሪን ሲያዩ አበዳሪን እንደማስታወስ ያለ ይሆን? የሚታወቅበትን መንፈስ ገፍፌ መልበሴ አጋልጦኝ እንደሆነስ? ወታደሮቹ በአለባበሳቸው አባቴን መስለው እደናግረው የለ? እኔስ የቹቹን.. የማልመልሰው ነገር በእናቴ ተሰርቶልኝ በልዓለም በሌብነት መሸማቀቅ ዕጣ ፈንታዬ ሊሆን?...

...እናቴን አየኋት። እያየችኝ ነው። መንፈስ ተናበናል። ቹቹን ስታይ አይዐዕታትም? አይመስልም! እናትነት ውስጥ እንዴት ያለ፤ የልጅ ፍቅር መሰል አርኩስ መንፈስ ነው ያለው? የትኛዋ እናት ደሞ የእኔን መንፈስ ለልጇ እየጎመጀች ይሆን?

በዚህ መካከል ከበድ ያለ ድምፅ ተሰማ። የአባቴ ሞክሼ ብዜን እንደሆነ ወዲያው ለየሁት...

"ሰላምና መረጋጋቱን ለማደፍረስ ፀረ-ህዝብና የደርግ ወታደር ግንባር መፍጠራቸውን ደርሰንበታል። ደርግ ኢሠፓ ሁሉ!!"

ወዲያው ወደ አጥሩ መውጪያ ገደማ ያሉ ሳቁ። ብዜን ጠበንጃውን እንደያዘ እናቴ ሳትመጣበት ቀድሞ እሮጠ ማለት ነው?

## ፃያ ሰባት

## ከወዲያ ወዲህ

በሬ በማለዳ ተቀረቀረ፤ አልዘጋሁትም፣ ለሲፈን መለስ ብሎ ማደር ከጀመረ ቆይቷል። ሲፈን ብትሆን አትቀረቁርም፣ ታዲያ ማን? አዲሱ መንግሥት አፈሳ ጀምሮ የአባቴ ሞክሼ መጥቶ ይሆን?

ስከፍት ሻምበሉ ፊቱን ወደ ትልቁ ቤት መልሶ ቆሟል። የአባቴ ጠረን እሳዩ ላይ ተላኮ አፍንጫዬን ታከከኝ። የቼቼ ጠረን እኔ ላይ ይኖር ይሆን?

"ልጅ፣ ስንት ዓመትህ ነው?" ለዚህ ጥያቄ ሲንደረደር ከእነ ቼቼ ቤት መጣ? እልነጋ ብሎት በሌሊት?

"አስራ ስድስት"

"ጥሩ፣ ስንተኛ ክፍል ነህ?" እኔንም እንደ አባቴ ለወታደራዊ ማደግደግ የሚገፋፋ ደረቅ ድምፀት አለው።

"ዘጠኝ"

"ጥሩ፣ ከሲፈን ጋ አንድ ቦታ እልካችኋለሁ።" እስካሁን ፊቱን ወደእኔ አልመለሰም። ከጀርባ ሉጫ ፀጉሩ እንደ እርግብ አንገት የሚያብለጨልጭ ቀለም ይረጫል። በችግርና በመከራ የተሸፈነ ቆዳው አጨልቆ መታየት ጀምሯል። ቀይ ሳይሆን አይቀርም።

"ልብስህን ልበስ"

ለካ በውስጥ ሱሪ ነበርኩ። ለዚህ ይሆን ፊቱን ወደእኔ ያልመለሰው። ሱሪዬን ታጥቄ ሰወጣ በጥርጣሬ ነበር። የአባቴን ስብከት ሰምቶ እንደጀግና ሳይቆጥረኝ አልቀረም። ‹አንድ ሁለት ወያኔ ማርከህ ይዘህ ና› እንዳይለኝ። ‹ሲፈን ስንቅህን ይዛ ትከተልሃለች› ሲፈን ፊት እንዴት እሸሻለሁ? ያንን የፆታ መጠራጠሪያዋን አውጥታ ከምትለጥፍብኝ በክብር ታንክ ላይ ወጥቼ መሞት ይሻለኛል።

ሻምበሉ ሲፈንን ቀድሞ ቀስቅሷት ኖሯል፤ እርጥብ ፊቷን ይዛ እኔ አጠገብ ቆመች። ወታደራዊ ትዕዛዙን ለመቀበል ዝግጁ ሆንን።

"መርካቶን ታውቂት የለም? ጥሩ! ራጉኤልን? ጥሩ! እዚያ ቴሌብሽዥንና ቴፕ የሚሸጡትን መደዳ ሱቆች? ጥሩ! የሱቅ ቁጥር 169 ገብታችሁ ባለቤቱ ዮሴፍ ሽታዬ ይባላል ይሄን ደብዳቤ ስጡት ጥሩ! ሻምበል ጠናጋሻው ሽታዬ ልኮን ነው በሉ፤ ጥሩ! የሚሰጣችሁን ይዛችሁ ኑ፤ ጥሩ! ስትሄዱ በእግራችሁ ነው ጥሩ! የምሰጣችሁ መሳፈሪያ የለም፣ ጥሩ ዳርዳሩን ሂዱ፣ ጥሩ..."

ከሲፈን ጋር፣ ከኛ ግቢ ውጪ ለመጀመሪያ ጊዜ ጥሩ! አጠገብ ለአጠገብ ስንሄድ ለመጀመሪያ ጊዜ፣ ጥሩ! ትከሻዋ ላይ እጄን ጣል አደርጋለሁ አላደርግም? ጥሩ! ከቤት ውጭ በሲታሴትንቱ ታፍርብኝ ይሆን? ጥሩ!...

ዝም ተባብለን እየሄድን ነው፤ ከቤት ውጭ ላለው አብሮ መሆን እንደ አዲስ መተዋወቅ ይኖርብን ይሆን?

"ሲፈን" እየጨበጠችኝ

"ታለ" እየጨበጥኳት

ሽኩርምም አሏ

"እዚህ አካባቢ አላይሽም"

"ሌላ ቦታ ነው የምኖረው"

"የት?"

"ናዝሬት"

"ኦ! የናዝሬት ልጅ ነሽ?..." ይሄን እያሰብኩ በጎን እያታለሁ። ሲፈን ከእኛ ግቢ ይልቅ አውጭ ሲመለከቷት ታምራለች። ለእኛ እድሜ ቀረብ ያሉ ወንዶች ደጋግመው ሳያዩዋት አይለቋትም፤ አይኗ ከጎን፣ አፍንጫዋ ከጎን፣ ፀጉሯ ከጎን...

ዓለም ፀሐይ ድልድይ ደረስን፤ ለዓለም ፀሐይ ልደት የተተከለው ጥይት የአጀበን መሰለኝ። እንቁላል ፋብሪካ ሼህ ሆጀሌ ቤታቸውን በእንቁላል ሲያንፁ ያቋቋሙት አስኳል ማምረቻ ይሆን? ሰባራ ባቡር ላይ ሀዘን አለ። ቻይናና፣ ሳኮ፣ ሊ፣ ቂሉ፣ ሻሚታ፤

"ጭገርህን አበጥረህ ነው..." ልብ የሚሸነትር ሀዘን ተወነጨፈብኝ።

"ምነው?"

"ምነው?" እያየችኝ ኖሯል? ፊቷ ወደ እኔ አልዞረ።

"ዝም አልክ፤ ደስ ያለህ አትመስልም"

‹እዚህ እንዳልደረስን ቁጠረውና ለምንኝ› ልትለኝ ይሆን?

"ሴቶች እያዩህ ነው" አለችኝ።

"ወንዶች እያዩሽ ነው" አልኳት።

ተሳሳቅን፤ እጇ ትከሻዋ ላይ አረፈ፤ እግሮቼ ቀስ በቀስ መሬት እየለቀቁ መንሳፈፍ የጀመሩ መሰለኝ። አይደለም ልቤነው ክንፍ ያወጣው። ልቤ ክንፎቹን አመጣጥኖ ለመዘርጋት ከግራ ጡቴ ወደ ደረት-አካፋዬ ጠጋ ሳይል አልቀረም። መርካቶ ግርግርና ጫጫታ መካከል እንኳን ወንዶቹ ሲፈንን ደግመው ሳያዩ አይሄዱም። "ዞር ሲፈንን የተመለከተ እርሱ አመነዘረ" የሚል መፈክር ፅፌ አለመምጣቴ ቆጨኝ።

ሱቁን አገኘነው። የሻምበል ወንድም መቶ አለቃ መባል ይኖርበት እንደሆን እያሰብኩ ደብዳቤውን ለዮሴፍ ሰጠሁት። ብስል ቀይ ነው፡ ፡ ምናልባት ሻምበሉም ችግር ሳያጠላበት በፊት እንደወንድሙ ብስል ቀይ የነበረ ይመስለኛል። ደብዳቤውን አይኖቹ እየተንቀራጠጡ አንብቦ ሲጨርስ፤

"ሂዱ እዚያ መኪና ውስጥ ግቡ" አለን።

መኪናው የአትክልት ተራ ሳይሆን አይቀርም፤ ባደውንም ሆኖ ተንጋደል። ሳይጭን ከተንጋደደ ሲሸከም የሚቃና መሆን አለበት። ተጣበን ከሾፌሩ ጎን ተቀመጥን። አንድ ሦስት ካርቶን እንደታሸገ ተጭኖ ዮሴፍን ስንጠብቅ ሌላ ሸማግሌ መሪውን ጨበጡ። ዮሴፍ ከሱቅ ሳይወጣ "ሂዱ!" አለ። የሻምበሉ ወንድምነቱን "ጥሩ" በሚል ያረጋግጣል በሚል ጠበኩ። የለም።

መኪናውን እየመራን ጡረታ ድልድይ ገባን። ሾፌሩ እንደማርሹ፣ እንደመሪው፣ እንደ ፍሬሲዮኑ... የመኪናው አንድ አካል ይመስላሉ።

"ወደግራ"

ወደግራ ይጠመዝዛሉ።

"ወደቀኝ"

ወደቀኝ ይጠመዝዛሉ፤ ሾፌር ሳይሆን መኪናውን እየታዘዘ እያደረሰን ማለት ይቀላል። ከመሪው ጋር የተያያዘ ሁለት "ብረት"፣ አንዳንዴ አንዱ

"ብረት" እየተላቀቀ ማርሹ ላይ ያርፋል። ከነዳጅ መስጫውና ከፍሬኑ ጋር የተያያዘው ሌላ ሁለት "ብረት" እንዲሁ እንዱ ከነዳጅ መስጫው ላይ እየተላቀቀ ፍሪሲዮኑ ላይ ይጣበቃል። ሹፌር ማለት አራት ብረት ነው እንዴ? ምንአይነት በድን ሹፌር።

አንዱን ካርቶን እናቴ ጉልት ላይ አስቀምጠን አንድ አንድ ያዝን። እኔ ክፍል ስናስገባ ቹቹ አልጋው ላይ እንደተንጋለለ አይኑ ፈጦ አየሁት። እኔ እንድፈጥን እሱ ዘገየ፣ እኔ አሳልጬ እንዳስብ እሱ ላይ ቃላት እየተደጋገሙ ናዳ ሆነው ወረዱበት፣ እኔ ቀጥ እንድል እሱ እንዲያቀረቅር ተፈረደበት፤ ዛሬ ደግሞ እኔ ነፃ ሆኜ ወዳሻኝ እንድሄድ አልጋ ላይ ታስሮ ጠበቀኝ። ከዚህ በላይ ስቃላት፣ ከዚህ በላይ ስለ እኔ መቸንከር፣ ከዚህ በላይ አራስን አሳልፎ መስጠት አለ?... አድፍ እንባ ውስጤ ተጠራቅሞ እየተብላላ መተንፈሻ አጣሁ። መሬት የተነጠፈው ፍራሽ ላይ ዝርፍጥ አልኩ። አሳንሰር ቤቴ ወደ ላይ የመምጠቅ ልምዷን ትታ ወደመቀመቅ ወረደች መሰለኝ። የመሬት መሬት፣ የመሬት መሬት፣ የመሬት መሬት መሬት መሬት...

"ምን ሆንክ?" እጠገቤ ተቀመጠች።

ምን ሆንኩ ይባላል? ዝም!

"ታስ? ደክመህ? አመመህ?..."

አራስን ችሎ መድከምና የራስን በሽታ መታመም ፀጋ መሆኑን ማን በነገራት? ዝም!

"ቡና ላፍላልህና..."

"ከቻልሽ ቹቹን አውጪው..."

ከአልጋው ላይ እጁን ይዛ ስታነሳው ወገቡ ላይ ማጠፊያ የገባለት ቀልማማ ዱላ መሰለ። ቀስ እያለ የእጥፋቱ ዲግሪ እየቀነሰ፣ እየቀነሰ ከመቶ ስማኒያ ወርዶ ዘጠና ዲግሪ ገባ። እግሩን ከጉልበቱ ስባ ወደ መሬት አወረደችው። ጫማውን አራሷ አደረገችለት። ስለቸኮለች ለማፋጠን እንጂ እነዚህን ሁሉ አራሱ ያከናውናቸው ነበር።

ሲፈን እኔን እያገለገለችኝ ሆኖ ተሰማኝ። እኔን መካደም ቡና ማፍላት ሳይሆን ቹቹን ማገልገል እንደሆነ ማን በነገራት? ዝም!

ቀኝ እጁን በግራ እጇ ይዛ ሲሄዱ ሙሽሮች መሰሉኝ። በቀኝ እጇ ዳስሳ ወንበሩን አንስታ ወጣች። ሰው ስለምን ለአውሲያ እድሜውን ገብሮ ሲካድም አርጅቶ ይሞታል? ምን ስላደረገለት? ስለምንስ

ድንግላዊ ሆኖ ሥጋውን ቀጥቶ፣ ፍሬ ተነስቶ ለመኖር ይወስናል?... እኔ ከቹቹ ከቀማሁት በላይ ማን ምን አግኝቷል?

ሲፈን ቀሪውን ካርቶን አምጥታ አስቀመጠችው። ለማናገር ያህል፦

"ይሄኛው ካርቶን በጣም ይከብዳል፤ ምን ቢኖርበት ይሆን?"

ዘወር ብዬ አየኋት። አዚች ቤት ከገባን አንስቶ በቹቹ በኩል ያገለገለችኝ ከምስጋና በላይ ሆነብኝ። ዝም! እጇን ይዤ ሳብኳት። አላዬ ያገለገለችኝ ... ላይ የመውደቅ ያህል... ዘወር አድርጌ አፏ ላይ ሳምኳት። መሳም እንደምን ምስጋና እንደሚሆን አልገባኝም፤ ደግሞስ ሲፈንን መሳም መጥቀም ነው መጠቀም? ለእኔ እንዳደረገችው ይቆጠራል ወይስ ለእሷ እንዳደረኩት?...

"አመሰግናለሁ" አልኳት።

"ሲዖጙ" ሚሽን የሳተ መስጠፏን ከእኔ ላይ እያነሳች አጠገቤ ቆሙ።

"ቹቹን..." በፍጥነት እጇን አፌ ላይ ጠረቀመችው። ሳስለቅቃት አፌን ወደእንገቷ ውስጥ ከትታ ዳግም እንዳልናገር ተከላከለችኝ። አንገቷን አፌ ውስጥ አስገብቼ ሳምኩት። እየዘገነናት ቀና አለች። እጇን ጎትቼ ሳምኩት።

"ቀድሞ በእሱ ነው የከፋህ?"

"አ" አይኖቿ እንደታቦት ጥላ በጥልፍ የተሞሉ ሆነው ታዩኝ። አይኔ እንባ አቆረ? መልሳ አንገቷ ውስጥ ከተተችኝ።

"ታለ?"

"እ?" ለትናገር የሆነ እርግብግቢት ግንባሬ ላይ አረፈ።

"ብቹቹ ትቆጫለህ? ማለቴ ትዐዐታለህ? ማለቴ..."

"በ-ጣ-ም..."

"አንተ ምን አደረክ?"

ምን ይባላል? ዝም!

"ቁጭቱም፣ ዐዐቱም፣ ሀጢያቱም የሌላ ሰው ነው" የእናትህ እንዳትል የሌላ ሰው እንዳለች ገብቶኛል።

"የእዳ ማወራረጃ ያለው ግን እኔ ዘንድ ነው። ክፍያውም ቁጭትና ፀፀት ሳይሆን አይቀርም" በረጅሙ ተነፈስኩ። እሷም በረጅሙ ተነፈሰችና

"መጀመሪያ'ኮ፣ ማለቴ አንጓች እንደነገረችኝ እስከ አራት ዓመትህ አንተም ጤነኛ ነበርክ። ድንገት በአንድ ሌሊት ድንጋይ ያደረገህ ጠስ ከየት መጣ?..."

እውነት ከየት መጣ? ዝም!

"...እናትህ የሚቆጨትም የሚጸጽታትም አይመስለኝም። ልጇን ከአውሬ መናጠቅ እናት የተወለደችለት የተፈጥሮ ዓላማ ነው..."

ቀና ብዬ አየኋት፣ ሲፈን መሆኗ አጠራጠረኝ። በእሷ ውስጥ እናቴ የምገትችኝ መሰለኝ። ሙግቷ ከከረሩ ቃላት ባሻገር ጭስ እንደጠጣ ሽመል በማይታጠፍና በማይሰበር ጠንካራ ስሜት የተደገፈ እንደሆነ አየሁ። እንኳን ለእኔ ለሔምንቱ ቀርቶ ለምዕአቱ አቃቢ ፍትህ የማይረታ...

"ማን እንዲህ አድርጊ አለሽ?"

"ማን እናት አድርገኝ አለህ?"

"ያደረግሽውን ታውቂዋለሽ?"

"ያደረከኝንስ ታውቀዋለህ?"

እውነት የት ናት? የፍትህ ምርኩዝ ምንድን ናት? በዳይና ተበዳይን ምን ደባለቃቸው?....

"እወድሃለሁ፣ ታለ"

እናቴ ሄዳ ሲፈን መጣች። ሲፈን እንደ ቹቹ ሁሉ የእናቴ ስለባ መሆኗ ተሰማኝ። እናቴ ሲፈንን ለእኔ አገልጋይነት ፈንግላታለች። ርዕስ-ጉዳያችንን ወደእሷ አዙሮ በእናቴ የእኔ ባሪያ እንድትሆን መገደዷን ብነግራት ፍርዷ በቹቹ እንደታየው ለእናቴ ያደላ ይሆናል?

"እናትህ የሚቆጨትም የሚፀፅታትም አይመስለኝም። ልጇ ያለ አገልጋይ እንዳይቀር ባሪያ መፈንገል እናት የተወለደችለት የተፈጥሮ አላማ ነው።" ትላለች?

ፈገግ አልኩ፤ ሲፈን የተገለጠ ጥርሴ ላይ ሳመችኝ። እኔም የአገልጋዬን ግልጋሎት ለመቀበል ነፍሴን አፍታታ ጀመር። የሲፈን አሳሳም ሁሌ ጊዜም አዲስ ነው። ተለውጦ ሳይሆን እንደሁ አዲስነት

ዕጣ-ፈንታው ስለሆነ ሳይሆን አይቀርም። እንደ ነጠኩት በኋላ ዞሮ ሲመጣ እንደገና አዲስ ትውውቅ ለምን እንዳስፈለገ ለእኔም ይገርመኛል። ምስጢርነቱ እምን ላይ ነው? እስኪ በእንክሮ ላጥናው…

የሲፈን አሳሳም… አሳሳም… ከንፈሮቼን ጎርሳ እንደ ምላሷ ላይ፣ ሌላ ጊዜ ጥርሷ ላይ እያስደገፈች ታመላልሳቸዋለች። ይኼ ብቻ አይደለም እልር እልፎ ከንፈሬን ገልጣ፣ ጥርሴን ፈልቅቃ ውስጤ ገብታ ምላሴን ለማግኘት አፌን ታንጎዳጉዳለች። ይሄ ብቻ እንዴት…

…የዓይኔን ቅድ ታክኪ ሰመለከት አንድ ሰው እንደቆመ ታወቀኝ። እንደአባቱ ከሙታን ተነሥቶ ተነሳሁ። አባቴን በእንዲህ ያለ ጉዳይ ላይ ያየው ይሆን ሞቶ ብሎ ያረዳኝ? አባቴ ይሆን እንዴ? ምንጭቅ!

ሻምበል ነበር። ሲፈን ከእኔ ጀርባ ፊቷን ሸሸገች። እኔ መሸሸጊያ ሆኜ የምሸሸግበት አጣሁ። ሻምበሉ እንደወንድሙ ልጅ በፍቅር የሚመለከተው ካርቶኖቼን ነው። ቁጢጥ ብሎ በመስገብገብ ከፈታቸው። በስርቆሽ አየሁ። ሲፈንን የከበዳት ካርቶን በመጽሐፍ የተሞላ ነው። ሁለተኛው በስቴንስል የተባዙ ወረቀቶችና ደብተሮች፣ ማሲታወሻዎች ናቸው። ሦስተኛውን ካርቶን ከፍቶ አንድ እሽግ ብር አወጣ። ደነገጥኩ። መጽሐፎቼም፣ ወረቀት፣ ብሩም ወረቀት… አንዱን ደንጋጭ ሌላውን አስደንጋጭ የሚያደርገው የወረቀቱ እጣ-ፈንታ ነው?

ሻምበል ብሩን ወደሌላ ካርቱን አስተላልፎ ባል አድርጎ ውስጡ ያሉትን እቃዎች ይፈታትሽ ጀመር። ካሜራ አውጥቶ እንደሥጋ ዘመዱ በናፍቆት አየው። ቃታውን በአውራጣቱ ገፍቶ ካሜራውን ወደኛ በማዞር ተጫኑ አደረገ።

ሲፈን ጎሬዋ ውስጥ እንዳለች "ምንድን ነው?" አለች።

ምን ይባላል? ዝም!

ሻምበል ካሜራውን አስቀምጦ ፎቶዎች አወጣ። አንድ አንዱን እየነጠለ ተመለከተ። ትዝታ ፊቱ ላይ ያንዣብባል። ት-ዝዝዝዝዝ! በሚል ድምፅ የሻምበልን ሁኔታ አጀብኩለት። በእሱም ሕይወት ውስጥ አመላማጣ የምታስመጡና የምታስለምነው ሴት ትኖራለች። ለዚህ ሕይወት መጋለጥ ሳይሆን ከሲፈን አይነቷ ሴት ማምለጥ የሚከብድ ሳይሆን አይቀርም።

ሻምበል ፎቶዎቹን አስቀምጦ አንድ የታሸገ ሽሚዝ፣ አንድ ጅንስ ሱሪ እና ከፋት ሹራብ በተራ በተራ አወጣ። እየመረመረ ካስቀመጠ በኋላ እጁን ሰዶ ጥንድ ጫማዎች አነሳ። እነዚህን ሁሉ ይዘን መምጣታችን ትንግርት ሆነብኝ።

"ጥሩ፣ ጥሩ ሆቴል የት ይገኛል? ሻወር ያለበት?" ሲል ጠየቀ ጫማዎቼ ላይ አይኖቹን እንደተከለ፤ ሩፋኤልን አውቃለሁ ብሎ በሩፋኤሎች ሲያስረዳ አልነበር?

"ማስተምስ ሆቴል" አለች ሲፈን፤ አካሏን ሸሽጋ ቀልቧን እንዳጋለጠች ኖሯል።

"የት አካባቢ ነው? ጥሩ..."

"ብሩ ወንዝ" አሁንም እሷ መለሰች። ድምጿ በጀርባዬ ገብቶ በደረቴ የሚወጣ መሰለኝ።

"ጥሩ፣ ብሩ ወንዝ የት ነው?" ቀና ብሎ አየኝ።

በሙዋው የሴትና የወንድ ድምፅ አይለይም እንዴ?

"ተወው፣"

ጭራሽ?

"ተወው፣ ሰው እጠይቃለሁ፤ ማስተምስ ሆቴል አልከኝ?"

ሲፈን ከት ብላ ስትስቅ የድምፅ አፋምታ ጀርባዬን ቀድዶ በሆዴ በኩል ሻምበሉ ላይ አረፈ። ሻምበሉ ምንም ሳይመስለው ልብሶቹንና ጫማውን ታቅፎ ወጣ። ከአባቴ ጠረን ለመገላገል ሳይቻኩል አልቀረም። ሲፈን ካደፈጠችበት ሳወጣ ስል ተመልሶ መጥቶ ሁለተኛው ክርቶን ውስጥ እንደቀልድ የጠረጠረውን ብር ይዞ ሄደ። የቻቹ ማልጎምጎም ትከተለው።

"ደሞ፣ ደሞ ሁለተኛ ደሞ እዚች እንዳትደርስ ደሞ..."

ሲፈን ትንፋሿን ውጣ እንደተደበቀች ሁሉ በረጅሙ ስቃው "ውይ ቅሌቴ! ውይ ቅሌቴ!" አለች።

በሚያሳፍር አይን አየኋት

"አንተ ነህ ደሞ..." ብላ የዱላ ልፊያ ገጠመችኝ። "አዋረድከኝ፣ አዋረድከኝ" እየተከላከልኩ...

"ማን ነበር የጀመረው?" ስል አሰብኩ። ጠፋኝ። ባይሆን የአሁኑን ድማሬ ለማስታወስ መሞከር ነው እንጂ የቀድሞውስ...

...ሳምኳትን፤ ተከላከለች በግድ ስደግማት....

## ፃያ ስምንት

## እብድ ቀን

እኔና ሲፈን እንደተጋደምን ጥላ በደጃፉ ስንጥቅ ሾልኮ የብርሃን ወረራ ፈፀመ። ልቤ እየመታ አደፈጥኩ። ቼቼ አልጎመጎመ

"ደሞ፣ ደሞ እስካሁን አቆይተሻል ደሞ"

እቴቴ ምሳ እየሰጠችው እንደሆነ ሳውቅ እሷ ደጅ ቆማ ሰው ሠራሽ መኮሳተሯ በሩን ከፍቶ ዓይኔ ሥር ተደቀነ... እንዲህ ነው ትንፋሽ መያዝ...

በሩ ተከፈተ፣ ጥቁር ጥላ መሰላ የሀዘን ጨርቋን እንደ ዓይነ እርግብ ፊቴ ላይ የጣለችው መሰለኝ፣ ጭልም። ቤቱ ሳይሆን ዓለም...

"ኦሆሆሆይ" ይሄን ቃል!!

የእናቴ የአደባባይ ወጥ አወደኝ።

"ተነሱና ብሉ፣ እዛው ደርቃችሁ እንዳትገኙ..." ሄደች።

ሲፈን ጆርባዬ ላይ ጥፍሯን ሰቀሰቀችው። እኔም እንደሲፈን "ውይ ቅሌቴ! ውይ ቅሌቴ!" ማለት አሰኘኝ። የሲፈን ላይ የእኔ ሀፍረት ከተጨመረ ዓለም ሁሉ ሀፍረት በሀፍረት ሆኖ መቅረቱ ነው።

"አልራበሽም? አትበይም?"

"እሺ፣ አጉርሰኝ ግን"

እቴቴ ካርቶኑ ላይ የጣለችውን ዝርግ ሰሀን ጎትቼ በማያስተማምን ቀረሳ ሲፈንን አጎረስኩ፣ እራሴም፤ በዚህ መካከል አንድ ጎረምሳ ድምፅ እንደ እማማ አጀቡሽ ጡሩንባ አናፋ፦

"ሲፈን! ሲፈን! ሲፈን!..."

ሲፈን ትታይ ይመስል ጭንቅላቷን ትከሻዋ ውስጥ ቀበረች።

"ደሞ ደሞ አንተም ልትነጥቀኝ ነው ደሞ ሲፈን የምትለው ደሞ? ሂድ! ሂድ!"

ሲፈን በአፍንጫዋ አጭር ትንፋሽ ለቅቃ የከሸፈ ሳቅ አሰማች።

ፀጥ!

ማጉረስ ጀመርኩ።

"አባዬ ልኮት ይሆን?"

ጋሽ ተገኔ ከጋሼ ወደ አባዬ መቼ ተሸጋገሩ? አባቴ የስዕሉት ጨዋራ የጋበዛቸው ቀን የሲፈንን ልጅነት ነገራቸው። በአረቄ ግፊት አረቄ ቅልቅል እንባ አፈሰሱ።

"ምነው ትንሽ ቀደም ብላ በነገረችኝ፣ በመጨረሻ! ጥሩልኝ ልቀፋት፤ ጥሩልኝ" አሉ፤ ተጠራች፤ እንደ አዲስ አገላብጠው እይዋትና አቀፏት። እኔ እሳቸውን ብሆን ኖሮ እናት ልጄን አያሰበች ያለችውን አላምንም ነበር።

ጋሽ ተገኔ "አባት ኖት" ሲባሉ መጠባበቅ ጀመሩ አ! አብዮቱን ጠብቀው ከምን አስጣሉት? የተደበቁት ለምን ሆነና አሁንም ጥበቃቸውን ቀጠሉ?...

"ታስ?"

ዛሬ ምንድን ነው? ዝርግ ሰሀኑን ወርውሬ ተከናነብኩ። አሸዋ እንደሆነች አውቄአለሁ። በሩን ከፈተች

"ታስ?... አሞህ ነው?... ውይ በኢየሱስ ስም!" ወጣች።

"ወይ ዛሬ" (ሲፈን)

አበባ ድንገት መጽሐፍ ቅዱስ ሳነብ ካጋጠማት ደስ ስለሚላትና ተሰፋ ስለምትጥል ለዚሁ እንደመጣች ገብቶኛል።

"የናዝሬቱ ኢየሱስ..." ብላ ስትጀምር እኔ በልቤ:-

"የናዝሬቷ ሲፈን" እላለሁ።

ከእህቶቿ እንደ መጥታ ታዋክባታለች።

"የራስሽን እምነት ለራስሽ! አዛው"

አበባ ቹቹ ላይ የጣለችው ተስፋ ስለተሟጠጠ ይሆናል እሱን አልፋ ገብታ፤ እሱን አልፋ ሄደች። ቹቹ ላይ ያልሠራ ፀሎት ሆነ ድግምት እንዴት ለሌላ ሙከራ ዳግም ይቀርባል? ተደጋግሞ ተተኩሶ ከከሸፈ ችግሩ ከጥይቶቹ ሳይሆን ከጠበንጃው አይደለምን?

"ልሂድ" (ሲፈን) "ሆዴ ፈራ"

ሆድሽ በእባትሽ ወጥቶ ነው። ይደበቅ (ሳቅሁ) በአንድ ወቅት ሬሳዬን ተራምደህ ይሄንን ልጅ ትወስዳለህ የሚል ቀራጥ ስሙ፣ ጠበንጃ አስር ጊዜ የሚያቀባብል ድንገት እንዴት ፈርቶ ይደበቃል? እውነትና እውነታ መቼ ይሆን የሚገናኙት?

በሩ ተከፈተ

"ወይ ዛሬ" (ሲፈን)

ሻምበል ደጃፉ ላይ ቆመ "ሲፈን"

ምን ሊላት ነው?

"ታስ?"

"እ?"

"ኑ፣ አንድ ነገር ታመጪልኛላችሁ ጥሩ!"

"ምን?" ሳልነሳ

"ጥሩ፣ ጥሩ ጨዋት፣ መጽሐፎቹን ስመለከት ሙሉ አስብኝ ጥሩ! ኑ..."

የጨዋት ገበያ አእምሮዬ ላይ አለመጣ አለ። ሲፈን የቀረዳችኝ ይመስል "እኔ አመጣለታለሁ" አለች።

"ጥሩ"

ሻምበሉ ሁኔታችን ስላላሰደነቀው ሲፈንን አበረታቷታል። ተነሳች፤ ተነሳሁ። ሻምበሉ ዕድሜው አሰቀልቁሎ የእኔ ታናሽ መስሏል፣ ቀላቱ ከወንድሙ ጋር የሚገዳደር ሆኗል። ሂሙን ሙሉጭ አድርጎ ተላጭቶ ጉንጩ እንደባልጩት ለስልሷል። ፀጉሩን አሳጥሯል። ብር አውጥቶ ለሲፈን ሰጣት፦

አባቴ ሻምበሉን እንዲህ ሆኖ ሲመለከት "የእስክዛሬውን ሰላምታዬን ጣ! አንድ በአንድ ቆጥረህ መልስ! ጣ!" ሳይል አይቀርም።

"አይ፣ መንግሥቱ ጣ! ለኩታራ ክፍ-ዝቅ ሲያሰድርገን ጣ! አሁንም ብን ያድርግህ ጣ!"

ሲፈን በችኮላ ስትወጣ ሻምበሉ ወደ ውስጥ ዘለቀ። እኔም እንደሱ የመልበስ አምሮት አደረብኝ። ጂንስ ሱሪ፣ ሸሚዝ፣ ክፍት ጫማ እንዲያምርብኝ አማረኝ። ቁጢጥ ብሎ መፅሐፍቶቹን ሲያገላብጥ አልፌው ፍራሹ ላይ ተቀመጥኩ። ብዙ እንግሊዝኛ ጥቂት አማርኛ መፅሐፍት።

"ታነባለህ?"

መፅሐፍቶቹን ነው የሚጠይቀው?

"እኔን ነው?"

"አዎ"

"አነባለሁ"

"ጥሩ"

ብሂሉን መድገሙ ይሁን ጥሩነቱን መግለፁ ግራ አጋባኝ።

"ይሄን አንብበሃል?" ብሎ አንድ ትንሽ የአማርኛ መፅሐፍ አቀበለኝ። አገላብጬው አየሁት። "ከአድማስ ባሻገር" የሚል ርዕስ አለው። በዓሉ ግርማ እንዴት ያለ ያልተለመደ ሥም ነው? ዝም!

"አንብበኸዋል?"

"ኡ-ፅ እኔ መፅሐፍ ቅዱስ ነው የማነበው?"

"ሌላስ?"

"መልክ ሩፋኤል"

"ጥሩ፣ የህይወት ጥያቄ በእነዚህ መፅሐፍት ከሚሰጠው መልስ በላይ ይበዛል። ጥሩ፤ ድፍረት ይመስላል ግን ባህልህንና ሥነልቦናህን የሚያውቁ ደራሲያች የሚፅፏቸውንም ማንበብ ያስፈልጋል። እሱን አንብብ። ጥሩ!"

ሰው ሁሉ የህይወት ጥያቄ አለበት? እንደእኔ የማይመልሰው? ታዲያ በቀላሉ ህይወት እራሷ ናት ጥያቄ የሆነችብኝ።

"ስንተኛ ክፍል ነኝ አልከኝ? ጥሩ!"

"ዘጠኝ"

"ጥሩ! ለንባብ ዘግይተሃል፣ ቢሆንም ጀምር። መጽሐፍት ለጥያቄዎችህ ቀጥተኛ ምላሽ ባይኖራቸው እንኳ የማሰብ ልምምድህን በማፋጠን የጥያቄህን ምላሽ እራስህ እንድታገኘው ያግዙሃል። " ከሚያነሳው ከእያንዳንዱ መጽሐፍ ጋር እንደፎቶው ሁሉ የትዝታ ቀዘዝታ ያሳያል፤ የጨዋታውን ውል ግን አይስትም።

ለእኔ ጥያቄ ምላሽ የሚገኘው በአንድ መንገድ ብቻ ነው። በድግምት፤ የጥያቄዎቼን ምላሽ እራሴን የማገኘው ደብተራነት ወይም

አውሊያምነት እኔ ላይ ካረፈ ብቻ ነው። "ከአድማስ ባሻገር" የአሰማት ክህሎትን ይጠቁማል? እንዲያ ከሆነ ቹቹን...

"የአንዳንድ ጥያቄዎች መልሳቸው መቶው ብቻ የሚሆንበት ጊዜ አለ። ጥሩ! ከአፀ በሰሉ ጋር ውስጣችን ይግባ፣ አይግባ ባይታወቅም የሰው ልጅ ሁሉ አጣፊንታችን የሚጠቅመንና የማይጠቅመንን፤ የምንደርስበትንና የማንደርሰበትን ማሰብ ሆኗል። ከጠቀመን ጥሩ! ካልጠቀመን መቶው! ከደረስንበት ጥሩ! ካልደረስንበት ለሚደርሰበት ትውልድ መቶው... የሰው ልጅ ውስንና ፍፁምነት የሚጎድለው ፍጡር መሆኑን መገንዘብ። ይሄንን የተማርኩት ከአቦይ (ከአባትህ) የተግባር ውጫ ውረድ ነው። ከእሳቸው ጋር ባልገናኝ ኖሮ ገና ድሮ ራሴን አጥፍቼ ነበር። ገና ድሮ!"

ድንግጥ የሚያደርግ ትውስታ እንደተወረወረ ድንጋይ ጭንቅላቴ ላይ ነጥሮ አለፈ። አባቴ የማይጠቅመውንና የማይደርሰበትን ነገር ነበር በከንብንብ ያልፈው የነበረው? "ተይ እንጂ አንጓቹ፣ አሁን እኔን ከቁም ነገር..." አባቴ ይቺን የመከናነብ ስልት ጦርሜዳ ላይም ተጠቅሞባታል?

"ከእነዚህ መፃህፍት ያቋረጥኩትን ትምህርት ከቀጠልኩ የሚጠቅሙኝ ሁለቱ ብቻ ናቸው። ሌሎቹ ለጥሩ የወጣትነት ዘመን ትዝታዎች የሚበቃኝን ያህል አይቻቸዋለሁ። ጥሩ! ስለዚህ አንተጋ ይሁንና ቀላሎቹን በቀላሉ እንብባቸው፤ ከባዶቹን ደግሞ በከባድ ጥረት መርምራቸው። የያዙትን ሳይሰጡህ አትልቀቃቸው ጥሩ!"

ፀጉሩ በአጭሩ ተደፍቶ ብርሃን እያነጠረ ያብረቀርቃል።

"ትማር ነበር? አቋርጠሃል?" ‹ጥሩ› ልል ብዬ ከአፌ መለስኩት

"አዎ፣ ሦስተኛ ዓመት የፍልስፍና ተማሪ ነበርኩ። ጥሩ! ሰዎች በጥጋብ ይላሉ እኔ ግን ያስሁብት ሰልችቶኝ ወደ መካንኖች ማሰልጠኛ ገባሁ። ወታደር ቤት ከትምህርት ቤት የበለጠ አሰልቺ ቢሆንም ህይወትን ለማጤን ትክክለኛ ቦታ ነበር፤ ጥሩ! ግን ዘግይቼ ነበር።"

ዐጥ!

"አንተም እንደእኔ ካልዘመትኩ ማለትህን ስሰማ አንዳች ነገር የሚያመሳስለን እንዳለ ገባኝ፣ ጥሩ የማንደርስበትን ጥያቄ በደረስንበት መንገድ መልስ ለመስጠት የመፈለግ ሙከራ እንደሆነ ግልፅ ነው።"

ሲፈን በጥድፊያ መጣች። ጫቱን ጠርሙራ አስታቅፋኝ መልሱን ሽምበል ጎን ካርቱን ላይ አስቡተምጣ በዚያው ፍጥነት ሄደች። ግር ብሎኝ እንዳለሁ፤

"አባቷን ወስደዋቸዋል። ጥሩ!" አለ።

## ፲፱ ዘመን

### እናት ተፈጥሮ

የሻምበል የሆነ ነገር ሁሉ እኔን የሚያጓጓኝን ያህል እሱም የእኔን ዕድሜና ወደፊት የተዘረጋ ህይወት አጥብቶ እንደሚመኘው ገባኝ። በእርሱ ልምድና ማገናዘብ የእኔ አማራጩ-ሰፊ ህይወት ቢገኝ...

...ግን አይሆንም። የሰው ልጅ ሁሉ ከራሱ ስህተት እስካልተማረ ድረስ የሌላው መውደቅ የሌላው እንጂ የእርሱ የማይመስለው ፍጡር ነው። ይህን ዘግይቼ መረዳቴ በራሱ፤ የሰው ልጅ ሁሉ ወደአንድ የስህተት "ገደል" ገብቶ የመጥፋት ማረጋገጫ አይሆንም?

ሻምበል እኔ ፍራሽ ላይ ሆኖ ጫቱን እየቃመ መፅሐፍቶቹን እያነሳ ይጥላል። እንደመርካቶ ህዝብ ትትክር ቢመለከተው አዙሮ ይደፋው ይመስል መጽሐፉን በዓይኑ ሥር ያሳልፈዋል። አልፎ አልፎ "ጥሩ!" ይላል።

"ምኑ?" ማለት ከጀለኝ።

"ቅመህ ታውቃለህ? ጫት?"

"አዎ"

"ጥሩ"

እንዴት ልቅም እንደቻልኩ ለማስረዳት እድል ሳይሰጠኝ አለፈው። እኔና ሲፈንን ከተመለከተ በኋላ አዲስ እንዳልሆነበት ሁሉ። ትኛቹ ከእንቃሁ ወይም ከጨለማ ወደ ብርሃን ከወጣሁበት ቅፅበት አንስቶ ለአምልኮ ጫት ሲቃም አይቻለሁ። አንዳንዴ ምርቃት የተርከፈከፈበት ጫት በስኳር እንድጎርስ ይደረግ ነበር።

"ታዲያ ትቅማለህ? ጫት?"

"አዎ" ለጊዜው ከሻምበል ጋር ልጋራ የምችለው ማዕድ ጫት ነው። ክብር እንዲሰማኝ ይሆን? እኔንጃ! ግን እኔ የምፈልገው፣ እኔ ያጣሁት አንዳች ነገር እርሱ ዘንድ እንዳለ ገብቶኛል።

የሚያንቀራብጠውን መፅሐፍ ጭኑ ላይ አስቀምጦ አንድ ቀንበጥ ጨት አነሳ፤ አናቷ ላይ አጁን አሾሎ ያዛት፣ በግራ እጁ ቅጠሏን ተጠግቶ በመያዝ በቀኝ እጁ ቀነጠሰ። ወደ አፉ ከማለቱ በፊት ወደዓይኑ አስጠግቶ ቅጠሏን የሚመረምር መሰለ። እንደመፅሐፍ ጭንቅላቱ ነገር እያንቀራበጠ እንደሆነ ገባኝ።

"እንተን ሳክል የአመፅ ሥራዎች የመኖሬ ማረጋገጫዎቼ ይመስሉኝ ነበር። ጥሩ! ጨት የጀመርኩት ያኔ ነው። አባቴ ምርጫዎቼን ሁሉ ተጭኖ በፈቃዱ እያስገደደ ሰላሳደገኝ ይሆናል። ስጎረምስ አባቴ የሚጠላቸውን ሁሉ ለራሴ መፍቀድ የነፃነት ምልክቶች ሆኑ።"

ቅጠሏን ምላሱ ላይ አስተኛት።

"እስከ ቅርብ ጊዜ ከአባቴ የትዕዛዝ አዙሪት ሳልወጣኖርኩ። አባቴ ለውትድርና ሲያዘጋጀኝ ነበር ይሆን? ጥሩ፣ ውትድርና ሌላ ሳይሆን የመታዘዝ አዙሪት ነው። የአለቃህ አለቃ ያዘዋል- እሱም ታዞ ነው። እሱ እንተን ያዝሀል ጥሩ፤ አንተ ደግሞ ያንን ትዕዛዝ ለሚፈፅሙ ሰዎች ታደርሳለህ። ትዕዛዙ በትዕዛዙ መሰረት መፈፀሙን ትቆጣጠራለህ። እየህ ከማዘዝ መታዘዝ መሻሉን ያወቅሁት ያኔ ነው። ጥሩ!"

ሌላ ቅጠል ቀንጥሶ ወደአፉ አድርጎ አንኳለወሳት። እኔን ለመታዘብ ጨት ጋብዞ ዝም አለኝ።

"መታዘዝ በስንት ጣዕሙ፤ ጥሩ ያዘዝከው ባዘዝከው መሰረት ሄዶ ህይወቱን ሊያጣ ይችላል፤ አካሉ ሊጎድል ይችላል፣ አንዳንዴ የሞት ፍርድ ትሰጣለህ። በፈንጂ ላይ እንዲረማመድ ትዕዛዝ ጥሩ! ያንተ በዐት ከሰውዬው ሞት ይከፋል..."

ሌላ የቅጠል ጭዳ የተናደደ አፉ ውስጥ አረፈች። ዳጎስ ያለ መፅሐፍ አንስቶ ለእኔ አሳየኝ፡-

"የዚህ መፅሐፍ ደራሲ ፊዮዶር ዶስትየቭስኪ ይባላል። ጥሩ! ሩሲያዊ ነው። መጀመሪያ እስረኛ ነበር፣ ከባድ የጉልበት ሥራ የተፈረደበት፤ በኋላ በውትድርና እንዲያገለግል አደረጉት። ለእርሱ ግን ሁለቱም አንድ ነበር። ለወንድሙ የፃፈው ደብዳቤ ላይ እንዲህ ይላል "In the overcoat of a soldier, I am just as much of a prisoner as before" የወታደር ካፖርት ከባድ የጉልበት ሥራ እንደተበየነበት እስር ቤት ሆኖበታል። ልዩነቱ አልታየውም። የእስር ቤትና የወታደር ቤት በትዕዛዝ መቀበልና በትዕዛዝ መፈፀም ሥርዓት ውስጥ ስለሚያልፉ"

አባቴ አርባ ዓመት ሙሉ የከባድ ጉልበት ሥራ ያሰበት እስር ቤት ውስጥ ነበር ማለት ነው? ስንት ትዕዛዞች ተቀብሎ ስንት ትዕዛዞች አስፈፀመ? ማዘዝ የማይችል ተራ ወታደር መሆን ከእንዲህ ያለዐት ጠብቆታል ማለት ነው?... ግን እንዴት አንድ ሰው ይህን ያህል ዓመት አገልግሎ በተራ ወታደርነት ይቀራል?...

"ለምን ታዘዝን? ለምን አዘዝን? ለምን ሰው ሞተ? ለምን ሰው አካሉን አጎደለ?...ከንቱ ለመትረፍ? ጥሩ! በከንቱ ትዕዛዝ በከንቱ የሞቱ ሰዎች ነፍሳቸው ከበላያችን እየተንሳፈፈ እኛ አዲስ ህይወት እንጀምራለን? እንማራለን? እናገባለን? እንወልዳለን?... ፀፀቱ እንደእርግማን እስከ ሰባት ትውልድ አይተላለፍም?..."

ሻምበል ከራሱ ጋር ያወራል። መስሐፉን የመወርወር ያህል ወጋሌሮቹ ደባለቀውና ጫፉ መዘዘ። መስሐፉ ሲስተወረወረ ያኮረፈ ይመስል ወደእኔ ፊቱን መለሰ። Fyodor Dostoevsky የሚል ፅሁፍ ግንባሩ ላይ በጉልህ ይነበባል። ከሥር ግራ አጋቢ ርዕስ አለ "The Idiot" ይደብ ያሰው አስረኞቹን ነው? ወይስ ወታደሮቹን? አሳሪዎቹን ይሆን? አዛዦቹን?...

"ጥሩ!"

"ምኑ?" ማለት አሰኘኝ።

"ስንተኛ ክፍል ነህ? ጥሩ!"

"ዘጠኝ" የማይስማኝ ወይም የማያስታውሰው ከሆነ ለምን ይጠይቀኛል?

"ጥሩ! ለማንበብ ከጎደተሃል ግን ትደርስበታለህ። በአሁኑ ጀምር ጥሩ! ትምህርት እራሱ የሚገባህ ሌሎች መጻሕፍትን በብዛት ስታነብ ነው። አእምሮህ የሚያገናዝበውን በብዛት ቢጠው ያኔ በትምህርት ቀርቶ በህይወት ብትፈተን ማለፊያ መንገድ አታጣም።"

"ጥሩ!" ካልኩት በኋላ ደነገጥኩ። ሻምበል ግን የሚነግረኝን እንደወንፊት በማጥራት ላይ እንዳለ ያስታውቅበታል። እኔን አስቦ ሲናገር ሳይሆን ለራሱ ሲያወራ የበለጠ ይመስጠኛል። እኔንም ይመለከተኛል። ግን...

"ጥሩ፣ ያኛው ሰማያዊው መጽሐፍ፣ እሱን የደረሰው ሩሲያዊ ነው። ጎርኪ ይባላል። አልተማረም። የእኔ ዩኒቨርሲቲዎች ንባብና ህይወት ናቸው ይላል። ጥሩ! የምንማረው ሰው ሁሉ እውቀትና በሰጠው መንገድ ተግዞ ስራና መተዳደሪያ ለማግኘት ነው። የምታነበው ግን

በህይወት አንተ ብቻ እንጠቀና የሰጠኸው ደረጃ ላይ ለመድረስ ነው፤ ጭሩ!"

ወደራሱ ጉዳይ እንዲያተኩር በውስጤ ተማፀንኩት።

"ጭሩ! አውጭ የሚቀመጠው ወንድማችሁ ነው?"

"አይደለም"

"እ-ህ?"

በእኔ ትዕግሥት አኳኋን የጎደለ ወታደር ነው ልበለው? እንዲያ ካስጨነኩት ይረዳ ይሆን? ዝም!

"ጓደኛህ ነው?"

እሱን የቹቼ ጓደኛ ሁን ቢሉት እሺ ይላል ማለት ነው? ስለእራሱ ብቻውን ተመስጦ ለማውራት የቹቼ ጓደኝነት ይጠቀመዋል።

"እህ?" አለቀቀኝም።

"የእኔ የተጎዳ ልጅ ነው"

"ጭሩ!"

ምን ነው ጭሩ? ልበለው?

"እንዴት ተጎዳ? ኳስ ስትጫወቱ ገፋትርከው?..."

"እ-ይ..."

"እ-ሀስ?"

"እናቴ ናት..."

"ጭሩ! ገፈተሩት?..."

"እ-ይ"

"እስኪ በደንብ አጫውተኝ" አንድ የጫት በመልማሉ አንስቶ በፍቅር ተመለከተ፤

"ልጅ ሆኜ እታመም ነበር።"

"ምን?" ምንድን ነው የሚፈትረኝ?

"እኔ እንጃ፣ እናቴና እህቶቼ ሲነግሩኝ፣ ፈዘዝኩ። አልሰቀም፣ አላለቅስም፣ ራበኝ አልልም፤ አልጫወትም... እንደቾቹ ሆንኩ። በኋላ..." ሳወራው የማይታመን ነገር እየሆነብኝ ሄደ

"እ-ሺ?"

"በኋላ እናቴ የእኔን በሽታ ወደቹቹ አዞረችው"

"ጥሩ!..." አንድ የጨት ቀንበጥ በአውራ ጣቱ ታሻሻል። ምን ይሆን ጥሩው?

"ጥሩ! እናትህ ያንን እንዴት አደረጉ?"

"እኔ እንጃ..."

"ጥሩ! አምንህ ለመቀበል አስማኝ ነገር እውነትህ መናገር አለብኝ። እንዴት እናትህ በሽታን በእናት ላይ ወደሌላ ሰው ማስተላለፍ ቻለች?"

"በጥንቆላ፣ በድግምት..."

"ጥሩ!" ያሻሻትን ቀንበጥ በአፉ ጥግ በኩል አስገባት። "በመጀመሪያ እኔ በጥንቆላና በድግምት አላምንም። በፊት እንደዚህ አይነት ታሪኮችን እየሰማሁ አረበሽ ነበር። በኋላ ግን ወታደር ቤት ያየሁት ድግምት ውሸት እንደሆነ አረጋግጦልኛል።"

ጫቱን ያስማወራረጃ ጥምጣሙ እንደሚቀመው ለመጀመሪያ ጊዜ ልብ አልኩ።

"አስር አለቃ አረጋ ጥይት እንዳይመታው የሚያደርግ ድግምት እንዳስደረገ ያወራ ነበር ጥሩ! በስለት ካልወጉኝ አልሞትም ይል ነበር። ጥሩ ለአንዳንድ ወታደሮችና የበታች መኮንኖች ይህንኑ አይነት ድግምቱን አስደርጎላቸዋል። በኋላ ይሄ ነገር በበላይ መኮንኖች አዛዦች ተሰማ። አስር አለቃ ጦሩ በተሰበሰበበት ሲጠየቅ፡-

"አዎ፣ ድግምት አስደርጌአለሁ" አለ

"እና? ጥይት አይመታህም?"

"አይነካኝም"

"ተው አስር አለቃ"

"ስንቴ ጓድ ሲረግፍ እኔ በምን ተረፍኩ መሰላችሁ"

"እሪ ተው?" ቢባል ቢሰራ፤ ጠፉ ራት ትክክለኛነቱን አረጋገጠ። በአስር ቀይቶ ነገሩ በመታደሪያዊ ችሎት እንዲታይ ሲጠብቅ

"እልዋሽሁ ጌታዬ፣ ጥፋቴ ምንድን ነው?" አልሁ።

"ጥሩ! ጠፉ ጥፋት የለውም ግን እዚሁ ድግምቱ ይግባር አሉ። አስር አለቃ አረጋ ተስማማ፤ ጥሩ! የጥይት መከራው እንደ ወንጀል ማጣራት ታየ። ተኳሽ አዝዋለት የማይገል ቦታ ላይ መታው፤ ቆሰለ። ጥሩ! ሊያምን አልቻለም። ከጥይቱ በላይ የድግምቱ ሀይለኛነት ጎዳው፤ ትንሽ ቀይቶ እራሱን ያጠፋ ይመስለኛል። ጥሩ! አንዳንዴ ለግርማ ሞገስ ድግምት ያሠራል፤ ሌላው ተናግሮ ለማሳመን... ጥሩ! መስተፋቅር እስን የሚለም አሉ... ጥሩ! እኔ ግን አላምንም"

ደረቅ ጫት እያኘከ ብዙ ሲያወራ አፉ ደርቆ ጨው እንደተወቀጠ ጌሾ መቡኑን እንዳይጀምርና ትን እንዳይለው ሰጋሁ።

"የልጁ ህመም የራሱ ነው። ጥሩ! ከአንተ ወደሱ የሚሸጋገር አይደለም። የአዕምሮ ዝግመት አለበት። ጥሩ! ብዙ ጊዜ እናት ሆድ ውስጥ ባለው የፅንስ ሂደት መስተጓጎል ችግሩ ይከሰታል። አንዳንዴ ደግሞ ልጁ ካደገ በኋላ ጭንቅላት ላይ በሚደርስ አደጋ በሽታው ይከሰታል። አይድንም፤ በስልጠናና በሰውነት እንቅስቃሴ ሊሻሻል እንደሚችል ሰምቻለሁ። ጥሩ!"

የአካል እንቅስቃሴ ለሰንት ችግር መፍትሔ ይሆናል? ለሲታሴትነት፣ ለዝሙሮት፣ አካልን ለማወንደቅ... ቻይና...

"እናቴ'ኮ አምናለች"

"ጥሩ! አስር አለቃ አረጋም አምኗል። ጥሩ! ጉዳዩ የነገርኸኝ መገጣጠም እየተከተለ እውነት የሚመስል ሳይሆን አይቀርም። በተቀራራቢ ጊዜ አንተ ድነህ እሱ ሲታመም..."

ያቃለለው መሰለኝ፦

"ነገሮች እስኪዘበራረቁብኝ ድረስ ፀፀት ያንከኛል። ለእኔ ጥፋት እሱ የታሰረ ያዘል ይሰማኛል። መሰቀሌን ተሸክሞ፤ እየተገረፈ ስለሀጢያቴ በዝምታ የሚሞት እምሳክ እየመሰለኝም መጥቷል። የእሱን ጥሩ ነገር ሁሉ ነጥቄ፤ የእኔን መጥፎ ነገር ሁሉ ያወረስኩት በደለኛ ነው። በዚህ ልጅ ላይ የተጥለው ግፍ አንተ እንዳልከው መቅሰፍት ሆኖ ለሰባት ትውልድ አይተርፍም?"

የአፉን ጫት ሳያኘክ ዝም ብሎ አየኝ።

"እራሴን ጠላሁ፣ እናቴን ጠላሁ፣ የዓለምን እናቶች ተፀየፍኩ። የእናቴ ልጅ መሆኔ አይደለም ጥፋቱ፤ ልጅ መሆኔ ነው። የትኛዋም እናት ውስጥ በልጅ ፍቅር ተመስሎ ያለው ሴይጣን ነው። በልጅ ሥም ብዙ እርኩሰት ይሠራሉ። በኋላ ለልጃቸውም የማይራሩ ይሆናሉ። እንዲያ ቢሆን ነው እንጂ የቹቹ እናት ለምን ጥላው ጠፋች? እናቴ ለምን እኔን ፈራች?..."

"ጥሩ!..."

"ጥሩ አይደለም።" ምን በእሱ አናደደኝ? "ጥሩ አይደለም፤ እናቴ እስከዛሬ ያደረገችው ሳያንስ ይቺን ልጅ (ቢፊንን) በውቃቢ እያስፈራራች የእኔ አገልጋይ፣ የእኔ ባሪያ እንድትሆን እያደረገቻት ነው። ለእኔ በማዘን አይደለም፣ የልጅቷን አዝማሚያ በማየቷ በእኔ በኩል ተባምዶ ከመንፈስ የሚገኝ ኃይሏን ለማጠናከር ነው።"

ዝም!

ፀጥ!

ቀኑስቼ ወጣሁ። ቹቹ እንደተቀመጠ እንቅልፍ የወሰደው መስሎ አገጩን ደረቱ ላይ አስደግፏል። ፀጥ ያለው የቹቹ ዓለም ሽብር ይለቃል። ህይወት ክንውኗን አስርሶ እንግር ያቋረጠች ይመስላል። ተፈጥሮ ዐዳሏን ነፍጋለች። የፈጠረችውን ሸፍጣለች። ለምን? ለምን? ለምን... ወይስ በዚህ የሚወቀስም የሚመሰገንም የለም ይሆን?...

አባቴ ፈጠን፣ ፈጠን እያለ መጣ፤ ከኋላው ብሻ እርምጃውን ከአባቴ ጋ ለማመጣጠን ይጥራል።

"ጉድ ፈሏ ጣ! መጨረሻችን እንዲህ ሆኖ አረፈው፣ ጣ! ሻምበል የለም? ጉድ ነው፣ ጣ!" ጠጅ እንደተጣመሰ የብዩ መጠማጠር ያሳብቅበታል።

"ሻምበል የት ነው? ጣ!" ሳልነግረው እኔን አልፎ በር ላይ ቆመ "እንዲህ ተፀዳድተህ ጠብታቸው እንጂ፣ ጣ! እጅ ስጡ ተብለናል፣ ጣ! ለሰላምና ለመረጋጋት አደጋ ስለሆናችሁ ወደ (የት ነው ልጄ?) እዚያ...ጣ! የት ነው ባሻ?" ዞር ብሎ ጠየቀ...

"ተሀድሶ" ባሻ ፍርሃቱን ጠጅ አቁናንቦ ግድ የሰጠው አይመስልም።

"እዎ፣ ጣ! ታድሶ ግቡ አሉን፣ ጣ! ምኑን እንደሚያድሱ እንጃ ልጄ፣ ጣ! ስሙን አለዘቡት እንጂ እጅ ስጡ ነው ነገሩ፣ ጣ! እንደ ቀንኔ ከተደበቃችሁበት ጉረኖ መንቀስን ስንማርካችሁ እጃችሁን ስጡ ነው ነገሩ፣ ጣ! አይ ታድሶ፣ ጣ!" ፊቱን መስስ አደረገ። "... ጣ! ጣ! ጣ!" ከአግሩ አኩል ጣ! ሲል ነጠላ ጫማ ያደረገ መሰለ። ወደ ትልቁ ቤት።

# ሰካሳ

## ዜኒትና ኖዲር

"እይ ለድልህ..." እናቴ እንሰፍሰፍ አለች። "እኔ ነኝ እንጂ፣ እድሌ..."

አባቴ ለምርኮ ሥጠራቱን እን[illegible]ደደው ቀይቶ ነው የገባኝ።

"እንቺስ ምን ትያለሽ? [illegible] [illegible] [illegible] ጠብቆ [illegible] አሉ፣ ጣ! የእግዜ ሰር ፍርድ ሆኖ ማ[illegible] እነሱስ [illegible] እጡት፣ ጣ! ቢበላ ላት [illegible] ማ[illegible]፣ [illegible] [illegible] [illegible] ጣ! [illegible] በጠፍ ቋንቋ ዝርተው "ታድቦ" አሉት እንጂ ይሄው ነው። ጣ!"

‹ጉር መሸባዬ› እ[illegible]ባል ነገር የቸገረው ሸኘት ሆነ። ድርቆሽ፣ ቋንጣ፣ ዳቦቆሎ፣ ቆሎ፣ በሶ.. ተዘጋጅቷል። ሸኙቱ የዘመቻ ነው። ስንቅ አደራጅቶ እጅ መበጠት ግራ ያጋባል። ለመሆኑ [illegible] ተገኔ ዛሬም [illegible]ኖሩ ኖሮ "ወንዱ!" ይሉ ነበር?

ሻምበል እልፍ-እልፍ በአባቱ ማ[illegible] በሽፍንፍን ይስቃል።

"ተውነቱ ነኝ፣ ጣ! እናንተ ሳቁ፣ ጣ!"

እጅ የመስጠት የመጨረሻው ስንት ላይ ከሽኚዎች የለቅሶ ሳግ ተሰማ። በተለይ ረቂቅ [illegible] [illegible] [illegible]ትን ነገር አደረገች። እያለቀሰች እጇን እንከርፍፋ ስትጠጋ እባታችን ላይ ልትጠመጠም ነው ብለን ስንጠብቅ ሻምበል ላይ ተገኘች። እናቴ ምራቂ ትን ብሏት ፊትሞት። ትኩረታችን የእናታችን ትን[illegible] ላይ በሆነበት ቅፅበት እነ [illegible]ቴቀ አካባቢ ምን እንደተደረገ ያወቀ የለም።

"እንጓቼ? ጣ! ምንድነው?ጣ! እንቺ? ጣ!..."

ምናልባትም የእናቴ ትንታ፣ ምርኮው እጡን በሚሆንበት የመጨረሻ ቅፅበት አባቴ ረቂቅን አይቶ ልቡ እንዳይሰበር የሚረዳ ዘዴ ይሆናል።

"ምነው? ጣ! ሳትቀብሪኝ ጣ! እንን ለማን [illegible]ለሽ? ጣ!" አለ ፋራው አባቴ። [illegible] [illegible] ሴቶች [illegible] ወንዶች ያስተሱባታል።

አዲሱ ገበያ ሄደን ለከፍተኛ 10 ሰስቱን ወታደሮች አስረክበን ተመለስን። እናቴና እህቶቼ ገና ዘወር እንዳልን ረቂትን ጠመዷት።

"ምነው? አቅልሽን ምን ነሳሽ ልጄ?..." (እናቴ)

"ችግርሽ ወንድ ነበር?" (እቴቴ)

"ብር ሊያመጣ የሚሄድ መስሰሽ እንዴ?" (ሰምረት)

"ልቤን" (አበባሽ)

"በኢየሱስ ስም" (አሸሻ)

"ዝም በይ! ዝም በይ! ዝጊ!" (ሁሉም)

ከዚህ ሁሉ ውርጅብኝ በኋላ ረቂት እኔን ሙጥኝ አለች። እራሷ ለራሷ ታጉተመትማለች፡-

"እውነት፣ ምን ነክቶኝ ነው?... ኦሆሆሆይ!" ቶሎታ አንድ የተጣጠፈ ወረቀት እጄን ፈልቅቃ አስጨበጠችኝ። ምን ይሆን?... ጥቂቱ የቢዘን ፋርጎ እንደተቀጣጠለ ሩፋኤል ገባ። እናታችን ብቻ የሀዘን ጨርቅ አላሰፋችም። የወረቀቱ ነገር ከነከነኝ። ረቂት ከሻምበሉ ፍቅር ይዞኛልና አብሬው ካልታደስኩ እራሴን አጠፋለሁ ልትል ነው? እኔ እንድነግርላት? ድርቆሽ፣ ዳቦ ቆሎ፣ ቆሎ፣ ቋንጣ፣ በሶ... አዘጋጄላት እንድልላት ይሆን?...

ረቂት "ፋርጎውን" ፈርታ ከእኔ ጋር ሙጥኝ እንዳለች ጡረታ ድልድይ ገባን። ረቂቅ በየትኛው፣ በማንኛው ዘመዳችን ወጥታ እንዲህ ቀንጆ እንደሆነች ለእኔም አይገባኝም። የአባቴ እናት አበባን ከመሰሉ... አንዳንዴ የእኛ ቤተሰብ አባል አትመስለኝም። መንፈሴ እንደባዕድ ቆጥሮ መድልኦ ይፈፅምባታል። እንደ ሲፈን የእናቴ ጓደኛ ሆና የተቀላቀለች እንጂ በእናቴ የተወለደች አይመስለኝም። አባቴ አንዳንዴ ትክ ብሎ ያያትና፡-

"መልኳ ሁሉ ባኒያን ነው፣ ጣ! ይሄ ባኒያንኮ ያልደረሰበት ቦታ የለም"

"ምን ሊሉ ነው? አሆሆሆሆይ ያልዘሩት የበቀለ ይመስል" (እናቴ)

"ምናባቴ ላድርግ አንጓቼ፣ ጣ! እስኪ እያት ያ-ጎንደር ከእንኮየ መስክ በላይ የጨርቅ መደብር ያለውን ባኒያን አትመስልም? ጣ!..."

"ህጢያቱን እንዲህ አብዙት እንጂ፣ ሹሬ አላማረቦትም ዝም ይበሉ፤ እኚህ እነካኪ፣ በስመአም እቴ፣ ምን ጉድ ነዎት? ምን ሲሉ ነው ለመሆኑ? አለማፈርዎ እቴ... ለነገሩ የበረሃ ጂኒ ነው የሚያናግርዎት..."

ካፍሪካም፣ ከእንግሊዝም፣ ከቻይናም... የተጠረቃቀመው ቤተሰብ ይሰቃል። ይሄ ሁኔታ ተረት ለመሆን እንደከጀለው የሩቅ ዘመን ትዝታ ናፍቆት ለቀቀብኝ።

ክፍሌ ስገባ ቹቹ እንደተጋደመ ነው። ቹቹ ከአልጋ ለመነሳትም ሆነ ወደ ደጅ ለመውጣት ብዙም ድጋፍ አይፈልግም። ነገር ግን ሰው ከቤት እንዲወጣ እስኪመሰንለት ይጠብቃል። እጁን ይገፔ እንዲነሳ ሳግዘው እጁን አላሳሁበት። መዘግየቱ እንጂ መነሳት አልተቸገረም። ከአልጋ ላይ እግሩን ሲያወርድም እንደዚያው። በሶስት ቀን አንዴ እንደሚያደርገው ወደ መጸዳጃ ቤት ሲሄድ ድጋፌን ቀነስኩበት። ቀስ እያለ ሁሉንም ነገር አከናወነ። ሲቀመጥ ወደ ክፍሌ ገብቼ ፍራሽ ላይ በመሆን ረቂቅ የሰጠችኝን ወረቀት ገላለጥኩ። አጭር መልእክት ነበር። ዝቅ ብዬ ከስር ስመለከት ጠናጋሻው ሺታዬ የሚል ስም አነበብኩ። የሻምበልነት ተቀጥላውን ለምን እንደተወ እየገረመኝ አነበብኩት።

> "ታከ፤ ብዙ ነገር አልነበህም። ባለፈው ውይይታችን ምን እንደተሰማኝ እኔም አላውቀውም። ነገር ግን የአንተን የጭንቀት ምንጭ የሚያሳንስና አንተ የሚያደርግ ሀሳብ አቀብለኸኛል። እኔ የተማከሁት ከሰዎች ሥርዓት ጋር ነው። አንተ ደግሞ ከተፈጥሮ፤ ጥቂት መቆየት ብችል ጥሩ እንወያይ እንደነበር ይሰማኛል። ግን አልሆነም። የሚያሳድገው ገንዘቤ እንዳለህ ሳልጠቁም አላልፍም። ይሄን ገንዘብህን በትምህርት ብቻ ሳይሆን በንግብና በህይወት ለምድም ለታደብረው ይገባል። ገንዘቡን እዚያው ካርቶኑ ውስጥ ካንተ ትቼልሃለሁ። ትምህርትህንና ንግብህን በማዩንዳ መልኩ ወጣ እያለኽ ብትዝናና ጥሩ ነው። ሲኒንና ቹቹ የአንተን ደጋፍ ሳይፈልጉ እዩቀሩምና አንዳንድ ነገር አድርግላቸው። ወደፊት እንደምንገናኝ እርግጠኛ በመሆን ቻው።"
>
> ጠናጋሻው ሺታዬ

በመጀመሪያ ንባብ ጽሁፉ እንጂ ትርጓሜው አልተያዘልኝም ነበር። ለሁለተኛ ጊዜ ያነበብኩት በቀጣዩ ቀን ነው። ካርቶኑን ከፍቼ ብሩን አየሁት። ዓለም በምፈልገው መንገድ ሊታዘዘኝ እጁን ወደኋላ አድርጎ የሚጠብቀኝ መሰለኝ። ከዚህ በፊት ስለገንዘብ አስቤ አላውቅም ነበር። የሚያስፈልጉኝ ነገሮችም የሚገዙ ከሆኑ በጣም ባነሰተኛ ዋጋ ስለሆነ ፍራንኩን ከእናቴ ወይም ከሰምረት እቀበላለሁ። ለቅብጠት እንደማልጠይቅ ስለሚያውቁ "ለምን?"

ብሰው እንኳን እንገራግረውብኝ አያውቁም። ዛሬ ግን ገንዘቡን ሳየው፤ ከዚህ በፊት ለመዝለል ያልሞከርኩት አንድ ገደብ እንደነበረብኝ ተረዳሁ። ብሩን ፈራሁት ሳልነካው ካርቶኑን መልሼ ዘጋሁት።

በሦስተኛው ቀን ከፈትኩ፤ ገንዘቡን ሳልነካ መልሼ ዘጋሁ።

በአራተኛው ቀን ካርቱኑን ብቻ እንደተዘጋ አየሁ፤ ብሩ ጭንቅላቴ ውስጥ ተቀርጾ ስለቀረ መክፈት አላስፈለገኝም እንጂ እይቼዋለሁ። ምናልባትም አባቴ አርባ አመት ሙሉ ቀላ ወርደ፣ ደጋ ወጥቶ፣ ገድሎ፣ ሰባት ጥይት ቅሞ፣ የጥይት ታርጋ ግንባሩ ላይ ታትሞ… ደሞዙ ቢጠራቀም ይሄንን ብር አያክል ይሆናል። በዚህ ሰዓት አርባ አመት የሚቆይ አስር አባል ያለው (ባልና ሚስት ሰምንት ልጆች) ማቋቋም እችላለሁ። አባቴ ሰባት ቤት ልጆቹን ሰባት ጉድ ወለድኩ እንዳለ፤ እኔም ለቀልድ የገባሁበት የቤተሰብ ምስረታ ሀብት የአውሬ ጥርስ አውጥቶ አስደነገጠኝ። ሲፈን ሰማዩ-ሰማያት ላይ በአሳንሰር ቤቱ ተሳፍሬ ዜኒት ላይ ያገኘኋት "ፍቅረኛዬ"፤ ሚስት ስትሆን ልጆች ትወልድና ከሰማየ ሰማያት ትጣልና፤ ሰው መሆን ይበዛባትና ከምድረ ምድራት ወርዳ፣ ሰባት መቀመቅ አልፋ ናዲር ላይ የምትገኝ ሴጣን ትሆናለች። እንደሄሮድስ ጨቅላዎች በሰይፍ እንዲመቱ ፍላጎቷ ይሆናል። ራሄል ስለልጆቿ ታለቅሳለች እንጂ ስለሌሎች ልጆች የሄሮድስን ግብር መድገሟ አይቀርም ነበር።

ሁለተኛውን ካርቶን ከፍቼ መፅሐፎቹን ማገላበጥ ጀመርኩ። ጠናጋሽው የሰጠኝን ልቦለድ አንስቼ ገለጥኩ። የመጀመሪያውን ክፍል ሳነብ ግራ አጋባኝ። በዓሉ የተባለው ደራሲ ትረካውን የሚጀምረው እኔ በጠበኩት አኳኋን አልነበረም። "ቤቱ የዘምታ አዘቅት ውጦታል።" ይላል። ቤት ከማስቀደም ሰውየው ማን እንደሆን መንገር አልሻልም? እንዲህ ነበር የጠበኩት፦

"በብንያም አገር በዓናቶት ከነበሩ ካህናት የሆነ የኬልቅያስ ልጅ የኤርምያስ ቃል"

ለምን በዓሉ እንዲህ አልጀመረም? እየተገረምኩ ንባቤን ቀጠልኩ፤ አንዱን ገፅ እንብቤ ስጨርስ እንዴት መጻፍ እንዳለበት በራሴ ለመጻፍ ተነሳሁ። ይሁንና ሰሙ እዚያ ገፅ ላይ የተጠቀሰው ሰው የማን ልጅ እና የት እንደሚኖር ስላልተጠቀሰ የአሰሳ ንባቤን ቀጠልኩ። ያገኘሁ ሲመስለኝ እንዲህ አሰፈርኩት።

"በሀበሻ አገር በመስፍን ሀረር መንገድ ከነበሩት ጀግኖች የሆነው የፊታውራሪ ወርቁ ባንትይርጉ ልጅ የአበራ ወርቁ ቃል።" እንዲህ መጀመር ነበረበት። ደራሲውን ባገኘው ይሄን ምክሬን እለግሥ ነበር። ይሄ ቅሬታዬ እንዳለ ሆኖ አንብቤ ጨረስኩ።

እያነበብኩ አበባ ቁቁን ስታስገባው ትገባ ይሰኛል። የማነበውን መጽሐፍ ቅዱስ አለመሆኑን ስታይ "የእግዚአብሔር ቃል አይሻልህም?" ብላ በትሬታ መሄዷ ትዝ ይለኛል። በመካከል እቴቱ እራት ስታኖርልኝ ትዝ ይለኛል። ሲፈን ያለች መሰሏት ለ"ኦህሆሆይ" አፏን ሞርዳና ግንባሯን በሰው መራሽ መከሳተር አስጊጣ ነበር። የሰም! እፍር ብላ ስትሄድ ወደ ጓባቤ።

ሌላ በጣም ግር ያለኝ ደራሲው በዓሉ የት ሆኖ እንደሆን ሳውቅ አለመቻሌ ነው። አበራ ወርቁ የተባለው ቤት ውስጥ አለ፤ እሺ. ይሁን፤ እንዴት አበራ ከሚናገረው አልፎ የሚያስበውን እቶ በዓሉ ሊያዳምጥና ሊሰፍ ይችላል? እኔ ስለአባቴ ልጻፍ ብዬ ብነሳ የሚያስበውን እንዴት ማወቅ እችላለሁ? ወይስ እቶ በዓሉ ሌላ ሰው የሚያስበውን ለማድመጥ የሚችል ድግምት አለው?...

ሰባተኛ ክፍል ስለልቦለድ የተማርኩት እንደነበር አስታውሳለሁ። ያኔ በግብር ያጋጠመኝ ነገር ስለሌለ የነገሩኝን መልሼ ፈተና ካለፍኩ በኋላ ዘንግቼዋለሁ። ያኔ እንደጠናጋሽው መፅሐፍ ሰጥቶ ለማንበብ የሚያነሳሳ መምህር ቢኖረኝኖር በሁለት ዓመት ውስጥ ስንት ልቦለድ አነብ ነበር። በጥማሽ ቀንና በግማሽ ሌሊት አንድ መፅሐፍ ከጨረስኩ...

...መወርወሪያው መሸጎር የረሳው በር በቀስታ ተከፍቶ ሲፈን ብቅ አለች። ከጀርባዋ እንደ በርኖስ የጠቆረውን ጨለማ ቀድዳ ራሷን እንደፀሐይ ብልጭ ያደረገች መሰለኝ። የሆነ ነገሬ ሲጠብቃት ነበር? ድንገት በሩ ተከፍቶ ብቅ ስትል አልደነገጥኩም። ወይም አልተገረምኩም። ይሄኔ በዘመኑ "ጥሬ" ቢሆን ተበታትኜ በየአይጡ ጎሬ በገባሁ ነበር።

"ታለ?"

ፊቷ የተጎሳቆለ ይመስላል። ድንገት የተመኘችውን የእናቴን ጓደኝነት በግብር አገኘችው። ሰባት ጎረምሳ እባቷ አስታቅፈዋት ሄዱ፤ የመጠንችው እንደ እቴቱ "እኔ ባሌ ልጆቼ ናቸው" ልትለኝ ይሆን? "ብዙ ሀሳብ አለብኝ፤ እኔ መች ወንድ አጣሁ?"

ቋቋን ገርመም አድርጋ አጠገቤ ተቀመጠች። አለተያየቷ ሀዘን አለበት። ሲፈን ለምንተኛ ልጅ ልታደርገኝ የከጀለች መሰለች።

"አባትህ ሄዱ. አይደል?"

እኔ የእሷ አባት ሲሄዱ መች አፅናናኋት? ጭራሽ መች አገኘኋት?

"አይዞህ ምንም አይሆኑም"

‹አይዞሽ አባትሽ ምንም አይሆኑም› እንድላት ሳትፈልግ አልቀረችም።

"ችላ እያልከኝ እንደሆን ገብቶሃል? ፊትሽ ስለጠማሁልህ? ናቅከኝ?"

እህቶችህ ‹እንውጣ ሲሉሽ አትውጪ› እያሉ ሲመክሩኝ ስለጠማሁልህ ናቅከኝ አትልም?

"ሀሳብ ጨመርኩብህ? እሺ ይቅርታ፣ ዝም ብለህ አቀፈኝ።"

እስካቅፋት ሳትጠብቅ ቀድማ አቀፈችኝ። እጆቼን ስርስራ መዳፎቿን ጀርባዬ ላይ ስጠፈጃቸው። እንደገመምኩትኛ ገላ እጇ በጣም ይሞቃሉ። ከእውነት የተፋታው እውነታ እሷ ከደጅ መጥታ እንድትሞቅ ሲያደርግ፤ እኔ ቤት ቆይቼ ሳልቀዘቅዝት አልቀርም። ደረቴ ላይ በግራ ጉንጯ ተለጥፋ የሱጪ ፀጉሯ አክፋይ ቀጭን የአቧራ መንገድ መስሎ ይታየኛል። ጓባቱ ከልጆቹ እልፎ በሰው ልጅ ላይ አስተያየት ቢሰጥ ኖሮ እንደረቂቅ በባኒያንነት ይጠረጥራት ነበር።

መዳፎቿ ጀርባዬ ላይ በቀስታ መንቀሳቀስ ጀመሩ። እንግዲህ ተፈጥሮ ከእርሷ ወገን ናትና መቋቋሚያ ወኔው አይኖረኝም። ከእጇ እፏ፣ ከእፏ ታፋዋ ሲጨመር አበቃ ማለት ነው። ይኸዋ፤ ከእጇ እፏ ተቀበለኝ። ያንን የመሳም ልቦሲደን አመጣችው። የሲፈን "ክአድማስ ባሻገር" በእኔ ህይወት መተረክ ጀመረ። እንደበዓሉ ጭንቅላቴ የሚያስበውን ማድመጥ ትጀምራለች እንግዲህ...

...ሲፈን የተሰጣት ከሴቶች ሁሉ ይበልጣል፤ (ማንን ሴት አውቄ?) ተፈጥሮዬ እርሷ እጅ ሲሆን ይናጋል። እውስጤ ያለው ጥይት ፋብሪካ ፈንድቶ ከባድ ፀጥታ እስኪሰፍን ድረስ መላ ሰውነቴ በነውጥ ይመታል፤ አውሬ እንደገባበት መንደር ይተራመሳል። ጭንቅ-ጭንቅ የሚለው ነገሬ ይበዛል። እንደአባቴ ሰባት ጥይቶች ያላወኩት ገላዬን በሳስቶ የሚያልፍ ጨካኝ ነገር አለ። በዚህ ውስጥ ሆኜ ሲፈን ከእኔ በላይ ገንና ትሰማኛለች "የናዝሬቷ ሲፈን..." ብዬ ለአራቱም አቅጣጫ መመስከር ያሰኘኛል።

"ጂ!" እኔም ሲፈንም የለንም። ቅሬት፣ ብናኝ፣ ትናኝ፣ ጭስ... ስዚች ዓለም ሳንተው እንጠፋለን። ያቺን ጊዜ በምንምነት እናልፋለን። ዓይናችንን እንገልፅም እንጂ ብንገልፅ ገላችን እንደልብስ ወልቆና ተጥሎ እናይ ነበር ብዬ አሰባለሁ።

# ሰካሳ ኬፃጽ

## ሌላው ዓለም

ሲፈንን "ምን ላድርግልሽ?" ስላት

"ፊልም ጋብዘኝ" አለች አቅሚን አስልታ።

"ሌላስ?"

"ቫቅላቫ ጋብዘኝ ግን ፍራንክ አለህ?"

ስንት ሺህ ብር ይሆን? ስል አሰብኩ።

"ምንድን ነው ባቅላባ?"

"ለዩት ያለ ኬክ፣ መረቅ ያለው ኬክ..."

ወታደሮች የጋገሩት መሆን አለበት። እንደነአባዬ ጨንራ፤ በጎረድ ጎረድ የተከተፈ ነገር ይኖረው ይሆናል። ከደቀቀ ምኑን የወንድ ሆነው? ሴቷ ኬክ ጋጋሪ "እኛም መብላታችን አይቀር፣ ኬክ መጋገሪያውን አጠቡት እንጂ..." ትል ይሆናል።

ሲፈን ለዩት ብላ ጠጣን፤ ልብስ የቀየረችው እኔ ክፍል ነው። አባቷ ትናንት ታሰረው ዛሬ?... እንዳይባል፤ አባቱ ትናንት ተማርኮ ዛሬ?... እንዳልባል። ብሩን ከካርቶኑ ውስጥ ለማውጣት ከፉኛ እንገራገርኩ። ስምረትን ገንዘብ ለመጠየቅ ዳድቶኝ ነበር። በመጨረሻ የመስረቅ ያህል ድፍን ሃምሳ ብር አወጣሁ።

ሲፈን እግሮቿ ሁለት የዕጌረዳ አገዳ መስለው ከጉልበቷ በላይ በአበባ ተሞልታለች። ከጉልበቷ ዝቅ ብዬ ቅልጥሟ ላይ ያገኔ ደረቴ ላይ በመለጠፍ ከኮሌጅ የተመረቀ ሰው ፎቶ መነሳት አሰኘኝ። ከረምት ዘንቦ፣ ዐደይ ገብቶ ያበቀላት እንጂ ተረግዛ የተወለደች አልመሰል አለችኝ። እሷን ሳይፎካከሩ አካባቢን ለማድመቅ የተባበሯት አደይ አበቦች በየቦታው ይታያሉ። ከእኔ ጋር የሚነፃፀሩት ከሴዎቹ ሳይሆኑ አይቀሩም። "ከሴ እና አበባ ምን አንድ አድርጓቸው አንድ ጋ ተገኙ?" የሚል አስተያየት ሰጪ የበዛ መሰለኝ። ባፍርም ሲፈንን ለማንም ጥዬ መመለስ አልፈለኩም።

በየቦታው የተበተኑ ተሸናፊ ወታደሮች ይታያሉ። አንዳንዶቹ ከነቤተሰቦቻቸው ጎርፍ የተፋቸው መስለው ከሀፍረት ጋር ይለምናሉ። የተማረኩትን ወታደሮች፣ (አነአባቱን) አንድ የሆነ ቦታ እያሰለመዷቸው ይሆን እንዴ? ተሀድሶው ይሄ ቢሆንስ? መፅሐፍ ቅዱስ ይዘው ላትደርሱብን ማሉ ከሚሉ እንዲህ በማዋረድ ለራሳቸው ዝቅ ያለ ግምት እንዲኖራቸው በማድረግ ቢለቋቸው...

...እንዲህ በሀሳብ የምባዝን ከሆነ፣ ድንገት ሲፌንን ከሚያይዋት አንዱ ወስዷት ከጎኔ ላጣት እንደምችል እራሴን አስጠነቀቅኩ። የወሰዳት የኮሌጅ ተመራቂ ፎቶ ሲነሳባት እኔ ድምጼ እንደ ሩፋኤል አውራጎዳና እያስተጋባ፤

"ሲፌን! ሲፌን! ሲፌን!..."

የሲፌን ንቃት ከቤት፣ ከመንደርና ከሰፈር የበለጠ ከተማ ውስጥ ይጨምራል። እንደ እህቶቼ የተዘጋ ቤት ውስጥ ብቻዋን አረማመድ የምትለማመድ እንጂ ተመልካች ያሰባትና የተቆጠበች አይደለችም። እኔ ከቤቴ ስወጣ እንሳለሁ፤ ከመንደሬ ሳልፍ ኢምንት እሆናለሁ...

ሲፌን ነቃ ባለ አረማመድ አንድ ትልቅ ኬክ ቤት አስከትላኝ ገባች። ከተቀመጠው የቆመው ይበዛል። ሲፌን ደረቷ ላይ የደረሰ ጠረጴዛ ተደግፋ መቆሙን መርጣለች።

"እዛ ሄደህ ክፈል፣ ሁለት ሻቅላሻ" አለችኝ።

"እንቺ ክፈይ" ብዬ ድፍን ሀምሳ ብር ሰጠኋት።

ብሩን ተቀብላ በጥርጣሬ አየችኝ። የሰረቅሁ መሰሏት ይሆን? ፊገግታዬ አረጋግቷት በዚያው "በር የተዘጋበት" አረማመድ ቤቱን ናጠችው። ብዙ ወንዱ ዓይኖች እንደ አበባ ዘር ከጭንቅላታቸው ላይ እየቦነኑ ሲፌን ላይ አረፉ። መንግሥቱ ኃይለማርያም ጠጣቱን ሁሉ የፈጀው የሚወዳትን እንዲህ ስላዩበት ሳይሆን አይቀርም። እኔም ጓድ ፕሬዝዳንት ብሆን፡-

"ና-አንት አናርኪስት" የሆዴን በሆዴ አድርጌ

"ና-አንት ቀኝ መንገደኛ" ወደ ጆሮው ጠጋ ብዬ "ማን ሲፌንን አይ አለህ?"

ባቅላባው መጣ። ከተቀቀለ ትኩስ ቢለዋና ሹካ ጋር፤ እውነትም መረቅ ያለው ነው። ግን ኬክ ሳይሆን የድሮ ዳቦ ቁራሽ። ሲፌንን እያየሁ ቀረስኩ፣ ሲፌንን እያየሁ ጎረስኩ...

"ና አንት ቀልባሽ" (እዚያ የሚያዩትን)

"ና አንት ዐረ አብዮተኛ" (ቅድም ወረፋ ያስቀደማትን) አካባቢያችን እንደግራዋ ዘር በወንዴ አይኖች ተሞላ። አንዳንዱ ሲለጠፍ የጭንነት ጠባይ አለው።

"ኑ፤ ተሰብሰቡ ተረረረረም፤ አብዮቱን ለአደጋ ያጋለጡ ለአሩምቃ ተኩስ ተጋለጡ!" (ማን በወንዴ ዓይናችሁ አየር ሙሉ አላችሁ?) አንዳንድ ጋግርቃም አብዮተኛ ሲገደልም መፈክር ያሰማ ይሆናል፦

"ሲፈንን ያየ ይሞቃል እንጂ ሲፈንን ማየት አይሞትም!"

ነገር ከጠነከረ "አንድ ዓይንና አንድ መደንቆያ እስኪቀር እንታገላለን" ማለት ። ካልሆነ...

...እንዲህ በሀሳብ የምባዝን ከሆነ፤ ድንገት...

"ሴቶች ሁሉ አይናቸው አንተ ላይ" አለችኝ በጆሮዬ...

መረቃም የሰኪር ድሮ ዳቦ እየቀረጥኩ "ማን ስለአራሱ ያውቃል?" አልኳት። ማለት የማይገባኝን አልኳት።

"ሴቶች እያዩህ ነው'ኮ ነው ያልኩህ" አለች ግራ ተጋብታ።

እሷ በሴቴ ዓይን ተከባ መትንፈሻ አጥታ ኖሯል፤ ችግሩ እኔ ሴቶቹን ሳያቸው ያላዩ ይመስላሉ። እሷም ወንዶቹን ስታይ እንደዚያው ሳይሆን አይቀርም፤ እረሩ ያለን!

ሲኒማ ኢትዮጵያ ስንሄድ ወረፋውና ግርግሩ አላስቀርብ አለን። ለአንድ (አሁን ርዕሱን ለዘነጋሁት) ህንድ ፊልም ነበር። ወደ ሲኒማ አምፒር ሄድን። ሥርዓት ያለው አጭር ወረፋ ነበር። ከፊቴ አድርጌያት እንደተሰለፍን ገባን። መልሱ እሷ ዘንድ ስለነበር ከፈለች። እጇን እጄ ውስጥ ወሽቃ ወደአዳራሹ ዘለቅን። ነፍስ ያለው ወንበር ሲነሱ "ተቀማጭ ከሌለ ምን አዘረጋኝ?" ብሎ ይታጠፋል። ስንቀመጥ ሲፈን ትከሻዬን ተንተራሰች።

"ታድሎ" የሚሉ ወንዴ ልቦች፤ በእሉ ግርማን ይመስል ቃላቶቹ ከመወለዳቸው በፊት የተፀነሱበት ድረስ ሄጄ እሰማቸው ጀመር። ያየሁት ሙብራት ሲጠፋ ሲፈን በመላም የእኔን ልብ ታጠፋ ጀመር። ያየሁት ሲኒማ አሁን ትዝ ያላለኝ ለዚህ ሳይሆን አይቀርም። እንደውም አንዳንዴ ሲኒማ ቤቱ እኔ ቤት መጥቶ እኛ ፍራሿ ላይ ተቀምጠን የተሳሳምን ይመስለኝ ጀመሮ ነበር።

...ሲፈን የተሰጣት ከሴቶች ሁሉ የበለጠ ነው። ስትስመኝ እኔ ጠፍቼ እርሷ ትገንናለች፤ ከተማ ስንወጣ እንደሚሆነው እኔ ከጥርኝነት ወደ ኢምንትነት ተሸጋግሬ እጠፋለሁ። ይሄን ጊዜ ወደፊት

በመሄድ፣ ከፊተኞቹ ወንበሮች ፊት ቆሜ "የናዝሬቷ ሲፈን..." ብዬ ለሲኒማ ተመልካቹ መመስከር ያስኘኛል።

"እንውጣ!"

"ፊልሙስ?"

"ይቅርብን"

"ጥሩ፣ ትንሽ እንረጋጋ..."

"እስኪ?..." ብላ እጇን የሱሪዬ ዚፕ ላይ አስቀመጠችው፤ የብልት መብቀያዬ በሳንቲም ተደፍኖ እንደሆን ማረጋገጧ ስለመሰለኝ መጀመሪያ በነካችው ነገር ኩራት ተሰማኝ። ሲፈን ስትስቅ ግን ሀፍረት ነካካኝ።

"እሸሸሸ..." ከኋላ።

ወጣን፣ ዓይናችን በገናኗ ፀሐይ ተጥበረበረ። አንዳንድ ወንዶች ሲፈን ስትመጣባቸው ከጨለማ ስለሚወጡ ብርሃኗን መቋቋም ይሳናቸዋል። ብረት መበየጃ መነፅር ባለመያዛቸው ይቀጫሉ።

ሲፈን እየመራችኝ ከሲኒማ እምፒር ማዶ ቁልቁል ወረድን። ብዙም ሳንርቅ ወደ ግራ ታጥፋ ሌላ ቁልቁለት ጀመርን። ወደ ናዝሬት ሲኬድ የሚያጋጥመው ቁልቁለት እንዲህ ያለ ሳይሆን አይቀርም።

"ወዴት ነው የምንሄደው?"

"አንድ የናዝሬት ልጅ እዚህ ቤት ተከራይቷል። ቁልፉ ስላለኝ ገብተን..."

"ማነው?"

"የናዝሬት ልጅ አልኩህ'ኮ፤ እዚህ አስተማሪ ሆኖ ነው የመጣው። አይዞህ..."

የናዝሬቱ ኢየሱስ የሚያንኳኳው የተዘጋ ቤት ታወሰኝ። ትልቅ ባቅላባ የመሰለ ወፍራም ሳንቃ በር።

አይደለም! አጭር የቆርቆሮ በር። ለዚህ በር ቁልፍ ማዘጋጀት ያስተርታል። "በሯን ሲያታልሏት ቁልፍ አለሽ አሏት" ሲፈን ቁልፍ ሳታወጣ ገፋ አድርጋ ገባች። ለሲፈን ቦታ የለቀቀ የሚመስል ብዙ ጭስ ወጣ። አውስጥ ሰው እንዳለ ሲገባኝ ሰውነቴ ተሸማቆ ጥሬ አከልኩ። ብዙ ጥሬ ሆኖ መበተን በስንት ጣዕሙ።

"ታለ? ግባ?"

ገባሁ።

"ተዋወቂ፣" ጠባቧ ቤት ለመረቀኑት ዓይኖች የምትበቃ አይመስልም። የዘወትር ሞላላ ቁርጓቸውን ትተው ክብ የሆኑ ዓይኖች ከተወጠሩ ጉንጮች ጋር የሰው ፊት የወረሱበት ቦታ። ለማቸውን ልብ ሳልል ሁሉንም ጨበጥኩ። አንድ ሌላ መሬት ጎዝጉዞ የተቀመጠ የሚመስል የመጽሐፍ መደርደሪያ አለ። ሲፈን እጄን ይዛ አንዲት ጥብቆ መጋረጃ ገልጣ ገባች። ሀፍረትን ቅንጣት በቅንጣት እየቆረጣጠምኩ አጣጣምኩት።

ጓዳ ሳይሆን በግድግዳ የተከበበ አልጋ አለ። ሲፈን መረበሼ ስለገባት መጋረጃውን አስተካክላ ማጨለቂያዎችን ከደፋፈነች በኋላ አጠገቤ ተቀመጠች። ስታቅፈኝ ተከላከልኩ።

"የሚያስፈራ ቢሆን ይገቢህ አመጣለሁ? አይዞህ..." ማቀፏን ብቻ ሳልከላከላት ለራሴ ነገርኩ። አጎንብሳ የእኔን ጫማ ለመፍታት ሞከረች። ብከላከልም አልሰማችኝም።

"እሺ. እኔ አወልቀዋለሁ" አልኩና አውልቄ አልጋ ላይ ወጣሁ። እጇ ሥራ ከጀመረ ለእፏ ማቀበሉ፣ አፏ ሥራ ከጀመረ ለጭኗ ማስተላለፋ ግድ ነው። እንደ ደራሽ እያሲጋ፣ ያለውዴታ ይዞ ይሄዳል። እየተወሰዱ፣ እንደሆንኩ ሳያውቁ አንዱ ዳር ተተፍቶ መገኘት።

ይኸው!

"ደ!"

ጓዳዋ በጠንካራ በር ሳይሆን እንደብረት በፀና ህግ የምትተማመን እንደሆነች ገባኝ። የማይበገር በር እንጂ ህግ ለማታውቀው ለእኔ ቤት ሳልቀስ...

...ሲፈን እንደ እሳት ከሚንቀለቀል እንደ በረዶ ወደ ረጋ ፊት ተሸጋግራ በጀርባዋ ተኛች። ቀሚሷን መች አወለቀች? ብዬ የምታክለውን አረንጓዴ የጓዳ መብራት መቼ አበራች? የሳንቃ ሳጥን ውስጥ ያለን መሰለኝ። የሳንቃ ሳጥኑ በሶስት አቅጣጫ በላስቲክ የተሸፈነ ሙሉ ልብስ ተንጠልጥሎበታል። መምህሩ ተማሪዎች ፊት የሚያቀርበው ከመኖሪያ ቤቱ በእጅጉ የተለየ ሰብእና እንደሆነ ገባኝ። ይሄን ቤት የሚመጥነው የአባቴ ካኪ ልብስ እንጂ..."

ሲፈን ድንግጥ ብላ አልጋ ላይ አንድ ነገር ትፈልግ ጀመር።

"ምነው?" አልኩ ድምጼ በህግ ከለላ ስር ያለውን መጋረጃ አልፎ እንዳይሄድ እየተጠነቀቅኩ።

"ብሩ?"

"የት ነበር ያደረግሽው?"

"ፓንቴ ላስቲክ ላይ" መቼ ቀሚሷን ገልባ ብሩን ለፓንቷ አጎረሰች? ፈልጋ አራት ቀያይ ብሮች አገኘች። ፓንቷን መቼ አወለቀችው? ሁሌም እንደ አባቴ ከሙታን ስነሳ የምጠይቀው ነው። አንዳንዴ እንዲህ መሆኔን ያየ ሄዶ እናቴን እንዳያረዳት እፈራለሁ።

"ታስ ሞቷል!"

"ውሸት!"

"ከአይኔ ወዲያ! ሲፈን ደረት ላይ ጣዕር ይዞት ግጥም!" ሲፈን አስር ብር እያሳየችኝ "ልስጣቸው?" አለችኝ።

"ስጪያቸው" አልኩ በጭንቅላቴ።

እጇን ብቻ አሾለከች። እንደባህል ስዕል ፊታቸው በክብ ዓይን የተሞላው ጎረምሶች ጎል የገባ አስመሰሉት። ለካ ፀጥታው የገንዘብ አጥረት ሁሉንም ኤሊ አድርጎት ኖሯል።

"ሲፈን፣ ትዳርሽ እንዲህ ይሙላ" አለ አንዱ.

ተረብ መሆኑ ነው። ሲፈን እየሳቀች ምላሽ ሰጠች።

"አብሽር፣ ገልጃ"

...የእኛ ውሻ? ይሄ ሴታውል እዚህ ይቀምልኛላ?... ሳቄን መቆጣጠር ተሳነኝ። በመመሪያ የፀናችው ጥብቅ መጋረጃ ሳቄን መቋቋም ተስኗት ተርገበገበች። የሲፈን አፍ አፌ ላይ ተከድኖ ሳቄን ሆዴ ውስጥ ቀበረው።

"እንውጣ!"

"ምነው?" እብድ ብር አምጥቼ ሚስቴን አሳበድኳት የሚል ተረት አእምሮዬ ፈጠረ፤ ፍቅረኛዬን ይሻላል፤ ሚስቴን? ሚስቴን ከማለት "ሴጣኔን አሳበድኳት" ይሻላል...

"በቃ-እ"

"ጥሩ ትንሽ እንረጋጋ" አውቄ

"እስኪ?..." እጇን ላከች። እጇ የቁራ መላክተኛ ሆነባት። ትስመኝ ጀመር።

"እንውጣ..." አልኳት አውቄ

"ትንሽ" አፉ ላይ ከትንፋሽ ጋር አወራች፡፡ በሲፈን ሥር ሆኖ ጊዜን ትንሽ ይሁን ትልቅ ማወቅ ያዳግታል፡፡ በዚህ ላይ ጊዜን ወደኋላ አጠንጥና ሁሉንም ነገር እንዳልተደረገ ታደርገዋለች፡፡

"እንዳልሳምኩኝ ቁጠረውና ለምነኝ"

"እሺ." ሰዓቶች ሁሉ ጥዝዝዝዝዝ እያሉ በሶስት እግራቸው ሰኮንድ፣ ደቂቃ፣ ሰዓት ማመላከቻቸውን ወደኋላ ያሽከረክራሉ፡፡ የዓለም ህዝብ የኖረውን ደግሞ እንዲኖረው ይገደዳል፡፡

"በእናትሽ"

"እምቢ!"

የልጅ ጨዋታ ይመስላል አይደል? ግን እምላለሁ ሲፈን ‹እምቢ› ስትለኝ እንዳልሳምኳት እሆናለሁ፡፡ ሰዓት ወደኋላ ቢሮጥ አይደል? ጊዜ በሲፈን ወደታዘዘው ነጥብ ቢያፈገፍግ አይደል?... እውነታ መች ለእውነት ተገዝቶ ተአምር ሳይታመን ይቀራል?

"በእናትሽ ብዬሽ?"

"እምቢ አልኩህ አይደል? እምቢ!"

"ምንድን ነው?" ሆን ብሎ የወፈረ ድምፅ

"ምናገባህ? ገልጃ! ተገኔ ይሙት ይሄ ውሃ የማያነሳ ቀልድህን..."

ጋሽ ተገኔ ዛሬ ልጅ ወለድኩ ይበሉ፡፡ ለስመንኩበት ግጥም እድጋ ሰማኝ ከሳጥኑ ውስጥ ስንወጣ የባህል ሥዕሎቹ እንደ አዲስ ተዋወቁኝ፡፡ ስለሚመሳሰሉ አምስት መሆናቸውን ያወቅሁት ቆጠራ ላይ ሶስቱ ተሳሰቹ ነው፡፡ ገልጃ ሰው ሆኖ የመጣው ከእኔ ጋር ለመወቃቀስ መሰለኝ፡፡

"ምን ሆነህ ነው ግን እኔ እዛች ሰንሰል ስር ተኝቼ አረግጠኸኝ ትሄድ የነበረው? ሰላምታ ማንን ገደለ? እ... ሰው ሆኜ የማንገናኝ መስሎህ ነው? አ?..."

እስከዛሬ ከተከናወኑ እውነታዎች በላይ ይሄ የገልጃ ታሪክ ተአምር አይሆንም! መቼም፡፡

ድጋሚ ቆጠርኳቸው፡፡ አምስት መሆናቸውን አረጋገጥኩ፡፡ እንደኛክበን ልጆች ባንድ እንዳ ቢጎድል የህይወት ስልታቸው እንደሙዚቃ ውህድ የማያነክስ ይመስላል፡፡ ጫቱን እኩል አንስተው፣ እኩል ቀነጣጥሰው፣ እኩል የመጉረስ የህይወት ስልት አላቸው፡፡ በጉራቸው፣ አይናቸው እና ውቃቢ የራቀው ሞጣጣ ፊታቸው የአንድ ሰፈር ሳይሆን የአንድ እናት ልጅ ያስመስላቸዋል፡፡ መምህሩ የቱ ይሆን?...

ከወጣን በኋላ ሲፈን አምስቱ ጃክሰኖችን እየለየች ልታስተዋውቀኝ ሞከረች። እኔ ተአምር የሆነብኝ የሲፈን እነሱን ለይቶ ማወቅ፡-

"ያኛው ኢንጂነሪንግ ሦስተኛ ዓመት ተማሪ ነው"

የተባለው ልጅ ከእራቱ ጋር እየተቀላቀለ ያስቸግረኛል።

"ይሄኛው የቴዎሎጂ ተማሪ ነበር"

አምስቱን ለይቶ ለማሰብ መሞከር አንድ እቃ ውስጥ ያለ ውሃ ለያይቶ ለማመላከት እንደመቻል ሆኖ ከብዶኛል።

"በር ስር ያለው መምህር ነው።"

"ጓዳው መግቢያ ጋ የተቀመጠው ገጣሚ ነው"

"ጥሩ" አላልሁ እንደ ጠና ጋሻው

"ገልጃ ደሞ የማይማር፣ የማይሰራ፣ ሁሉን የናቀ ፈላስፋ ነው።"

ገልጃ በፍልስፍና ይሆን ሴት ሲመጣለት አፍንጫውን ያስቀደመው? እይ አባቴ! መች ፍልስፍና ያውቃል ታዲያ… "ወንድ አስዳቢነት" ሆኖ እንጂ!…

አምፒር አፋፍ ላይ ስንደርስ ሲፈን አዲስ ግኝት ላይ እንደደረሰች አስመስላ "ፊልም እንግባ" አለችኝ።

"እንዴ?" ወይ ዛሬ! አብድ ብር አምጥቼ…

"ሁለተኛው ፊልም ላይ እንደርሳለን፤ እንግባ…"

"ጥሩ"

ገባን፤ አንዳንድ ለስላሳና በሶፍት የተጠቀለለ በርገር ይዘን፤ በፀሐይ ከተጥበረበርነው በላይ ጨለማ በርቶብን እንደ አይነ ሥውር ሆንን። እየተመራራን ቦታ አግኝተን ብንቀመጥም ቀልቤ ሲፈንን ለመታዘዝ እንዳቀበቀበ ነበር። ከያዘችው በርገር በአፏ ቀርሳ አጎረሰችኝ። ከለስላሳዋ ተጎንጭታ አጠጣችኝ።

"ምን እያደረገችኝ ነው?"

የደከማት ይመስለኛል። ሁለተኛውን ፊልም ሳትንቀሳቀስ ጨረሰችው። ታሪኩ ተበትኖ መልሶ የሚገናኝ ቤተሰብ ላይ የሚያተኩር ነበር። እኔ ያን ያህል ባይስበኝም መብራት በርቶ ሲፈንን ሳያት አልቅሳለች። ተነስቼ ላስነሳት ስሞክር፤

"ቆይ" አለችኝ ያስቀሰችበትን መንፈስ ለማስከን

"እስኪ?..." ብዬ እጇን እንደሷ ወደጭኗ ሰደድኩ። ሳትወድ በግድ ስቃ ተነሳች። ሳመችኝ። ካደረገችው በኋላ ግን በሀፍረት ቀና ማለት አቃታት። ‹ውይ ቅሌቴ!› ሳትል አልቀረችም። ከመውጣታችን በፊት ወደ ሴቶች መፀዳጃ ገባች።

ሲፈንን ስጠብቅ ከመፀዳጃ የምትወጣ ሌላ ሴት ነገር ጣል አደረገችብኝ‐

"በሀሳብ ገብተሃል ምንህ ቀረ? በእካል ብትገባ አይሻልም?" ከኋላዋ ከመጡ ጓደኞቿ ጋር ተሳሳቁ።

"ወንድ ዝንብ እንዳይገባ እየጠበቀ ነው" ሳቁ ባርቶ ሳያልቅ ሲፈን ወጣች። መጀመሪያ ሴቶቹን፣ ከዚያ እኔን

"እያሸከረመምክልኝ? ነው? ታሪ?" ፊቷ ተለዋወጠ። ሴቶቹ የተቋረጠ ሳቃቸውን ሊቀጥሉ ሲሉ ዞር ብላ አየቻቸው

ፀጥ!

መከተሌን እያረጋገጠች ወጣች። የአረማመድ ንቃቷ ወደ መቆናጠር ተለውጦ ነበር። በምን ለየሁት? መቆናጠርና እግርን ማንቃት እንደ ጃክሰኖቹ ወንድማማቾች አንድ አይደሉምን? እንደሴቶቹ ሳቅ ቀጥ ብላ ዞረች።

"እንዴት እንደሆንኩልህ አየየህ? ምን ጎደለህ? እኔ ገልጀ ወንድሞቼ ማለት'ኮ ናቸው፤ እነሱጋ እስከመውሰድ መድፈሬን እንደቀላል አየኸው? ናዝሬት የማያስገባኝ ስም ሊያስጠኝ ይችላልኮ፤ ይሄን ያደረኩት ላንተ ስል አይደለም? ምን አጎደልኩብህ?..."

ይሄን ለመንገር ሰበብ የፈለገች መሰለኝ። ዝም!

"ንገረኝ?! ምንድን ነው የፈለከው?"

"ምንም!" ሌላ ምን ይባላል?

"ምንም? እውነት?..." እጇን በወገቧ ውስጥ ከተተች። ቀሚሷ ጉርድ ነበር እንዴ? ከላይ ያለው አላባሹ ነው? እጇ የቀረንን ብር ይዞ ወጣ። ወርውራ ደረቴ ላይ በተነችውና ሄደች።

ዓይኔን ጨፈንኩ፤ ቀሚሷ በመወናወን መመናቀሯን ሲመሰክር የተጨፈነ አይኔ ላይ ታየኝ። ወደ ግራና ወደ ቀኝ እየሾለ የባለጌ ምላስ መሰሎ ፒያሳ መሃል አላገጠብኝ። አበባማ ምላስ! አበባማ ላንቃ!... ይቺኛዋ ሲፈን የት ተደብቃ ከረመች? እሷ እራሷ ታውቃታለች? እየተወነች ይሆን?...

ሲፈን ከጉርዷ አውጥታ የወረወረችው ስድብ ነው፤ ስድቧን ጎንበስ ብዬ አላነሳም፤ በእግሬም ቢሆን ወደ ሰፈሬ እሄዳለሁ፤ በስድቧ አልሳፈርም፤ ስድቧን አልፈናጠጥም...

ዞሬ ሶስት እርምጃ እንኳን መቁጠሬን እንጃ! ከበስተኋላዬ መጥታ ጀርባዬ ላይ ተለጠፈች። እጇን በብብቴ አሳልፋ መዳፏን ደረቴ ላይ ለጠፈች።

"ታለ? ታለ? ታለ?...."

የት ነበረች? ከመቼው ሃሳብ ቀየረች? አሁን ይሄ የአደባባይ ትዕይንት መሆን የሚገባው ነው? ሰዎች መሰባሰብ ሳይጀምሩ አልቀሩም። እነዚያ የፀብ ምንጭ የሆኑ ሴቶች ጭምር...

"ታለ፣ በእግዚአብሔር! ታለ፣ በቢዘን!...."

ሰዞር ጀርባዬ ላይ ተለጥፋ ትዞራለች።

"በሩፋኤል! ታለ!..."

"በቃ እሺ በላት፣ እቺን የመሰለች ልጅ እንዲህ ስትለምነው ይገግማል እንዴ?..."

ከምን ተነስቼ እዚህ እንደደረስኩ ማወቅ አልቻልኩም። ግራ አጋባኝ። ያቺ ሲፈን የት ሄዳ ይቺ ተተካች? ምን አጥፍቼ አማራሪዋ ሆንኩ? በየትኛው ቀዳዳ እነዚህ ሰዎች ገብተው ዳኒዎቻችን ሆኑ?...

ወደፊቴ ዞራ መቀሳመዷን ቀጠለች።

"አላጠፋሁም፣ ስለምወድህ ቀናሁ፣ አላጠፋሁም፣ እራሴን ስለሰጠሁህ የናቅከኝ መሰሎኝ ተናደድኩ፣ አላጠፋሁም!!"

ዝም!

"ታለ? ታለ? ታለ?..."

"አሁን ወደ ሠፈር እንሂድ"

"ሳንታረቅ ወደዛች አካባቢ ድርሽ አንልም።"

የተሰበሰቡትን ማየት አስፈራኝ፤ እንደተሰበሰቡ መበተን ሳይጀምሩ አልቀሩም።

"ወደነ ገልጄጋ እንሂድ..."

ጨነቀኝ፣ ወይ ዛሬ?

"ግዴለህም፣ እዛ እንሂድና ስንታረቅ፣ በቃ..."

እሺ ሳልል አቀጣጫውን ይዘን ስንጓዝ አንድ ሰው ጠርቶ ለሲፈን አንዳች ነገር ሰጣት። አይታ ወረቀቱን ጥላ ብሩን ይዛ መጣች።

"ታለ? ይቅርታ? እ? ይቅርታዬን ተቀበልከኝ?..."

# ሰላሳ ሁለት

## የሴቶች ኢዮር

አንድ ቀን ከትምህርት ቤት ስመለስ ቹቹ ገላውን ታጥቦ ደረስኩ። ያጠቡት እህቶቼ ነበሩ። ያላሰብኩት ስለነበር እጅግ አድርጎ ገረመኝ።

እንደመኪና ቧንቧ ላይ በተቀጠለ ጎማ ውኃ እየረጨ በቀም መጥረጊያ ሲያሹት በአይነ ህሊናዬ ታየኝ። ደሞ ጫጫታ…

"ታለ ይሙት አረፈ!"

"በታለ ሞት"

"አውቀሽ ነው እኔን የምትረጪኝ?"

"እንዳይወድቅ እንጂ በርጩማውን አስተካክይለት።"

ምናልባትም ብዙ ሰዎች ከሰንሰሉ ኋላ ሆነው እያዩ…

የአባዬን ካኒቴራ፣ ካኪ ሱሪና ኮት አልብሰውት ፀሐይ ላይ በአስቂኝነት ተቀምጧል። ወታደሮቹን መስሏል። የፈረደበት የአባዬ ልብስ "ደሞ፣ ደሞ፣ ደሞ… እ…ውኃ ይዘው መጡብኝ"

"እነማን ናቸው?" ስማቸውን ከመሬት የሚፈልግ መሰለ

"እ-ደሞ አቴቱ ናት፣ ደሞ፣ ደሞ ስምረትም አለችበት፣ ረቂቅ ደሞ አይታለች…" ስማቸውን ያውቃል፤ የእድሜ ተዋረዱን ጠብቆ ከተናገረ ምንድነው የማያውቀው?

ደብተሬን እንደያዝኩ ትልቁ ቤት ስገባ እንግሊዟ ስምረት አቴቱና ረቂቅ ሲንጎዳጎዱ አገኘኋቸው። ገንዘብ የምትወደውን መርጬ "ምን ላድርግልሽ?" አልኳት በደስታ፤

"ለምኑ?"

"ቹቹን ስላጠባችሁት?"

"እንሳምህ" አለች ረቂቅ። ተስማማሁ። እንደልጅነቱ ጉንጩን አፋቸው ውስጥ ሞልተው አስጨኸው ሳሙኝ። ማልቀስ ከጀለኝ። እንደያኔው በህመም ሳይሆን በትዝታ ደስታ።

"አላስቸገረም?"

"አሱ'ቴ" አቴቱ መለሰች። "ጭንቅላቱ ላይ ብቻ ውኃ ሲፈስ ተነስቶ ሲሮጥ ነበር። ሲደነግጥ እንዲህ ይፈጥናል እንዴ?"

ወደ እኔ ክፍል ስገባ ወለሉ ጨቅይቶ ጃንያውን አንስተውታል። ሌላ ጃንያ ለማንጠፍ እስኪደርቅ እየጠበቁ እንደሆን ገባኝ። ካርቶኖቹ አልጋው ላይ ወጥተዋል። ፍራሹ ተጠቅልሎ አልጋ ላይ ተጋድሞ ሳየው ሲፈን ተደብቃ የገባች መስሎኝ በግማሽ ልብ ድንጋጤ ነካካኝ።

በጊዜ ሂደት ከተለማመድኳት ካርቶን ውስጥ ብር አውጥቼ መልሼ ከመፅሐፎቹ ስር አድርጌ ሄድኩ። ሲፈንን ልጅ ልኬ አስጠራኋት። አኳኋኗ ትምህርት ቤት እንዳልሄደች ያሳብቃል። ረጅም ቀሚስ ለብሳ፣ በቤት ውስጥ ስራ ተጎሳቁላ መጣች። ለምን ትምህርት ቤት እንዳልሄደች ብጠይቃት እንደ እቴቱ፦

"የእኔ ትምህርቴ ልጆቼ ናቸው" የምትል መሰለኝ።

ለቹቹ ልብስ እንግዛለት

"አንቺ ሰውዬ፣ ሰሞኑን እንዴት ነው?" አለችኝ

"እንዴት?"

"ለእኔም ገዛሽ፣ የቤት ውጪ ብለሽ ሰጠሽኝ አሁን ደሞ..."

ዝም ብዬ ወደ ሩፋኤል ገበያ ቀደምኩ። እዚያ ልባሽ ጨርቆች ሞልተዋል። በብዙ አይነት ቀለሞች መካከል ስንዟዟር እንደመርካቶ ሰዎች እዙሮኝ ሲያስመልሰኝ ተናነቀኝ። መርካቶ ሳለመሄድ የወሰንኩት ስሜት እዚህ በሌላ አቅጣጫ መምጣቱ ገረመኝ። ከዕጣ-ፈንታ ማምለጥ የሚቻለው እንዴት ነው? ዛሬን እዙሮ፣ የማስመለስ ስሜት እንዲጎበኘኝ ስለተጻፈ ብሸሽም አላመለጥኩም ማለት ነው?

ሲፈን የስፖርት ቱታ ይሻለዋል ብላኝ ገዛን።

"ደሞ፣ ደሞ፣ ደሞ... እንዳጠብከኝ አቀጥረዋለሁ ደሞ..."

"ለምን?" አልኩት የአባዬ ጠረን ከልብሱ ላይ እንደትንኝ እየተነነ ወዳፍንጫዬ ሲዘምት እየታወቀኝ።

"እነ ስምረትን ደሞ ደሞ ተቆጣ ብልህ ደሞ ስመሃቸዋል ደሞ፣ አንተም ጠላቴ ነው ደሞ..." ይሄ ልጅ መሬት ለመሬት የሚያስብ ጆሮና አይን አለው እንዴ? እህቶቼ እንደሳሙኝ እንዴት ሰማ?

"እሺ. እንካ ልበስ" ቀስ ብሎ እየረሳውና እያስተወሰው መልበስ ችሎበታል። ለመልበስ ቤት መግባት እንዳለበት ያውቃል፣ ለመነሳት መጣጣር ሲጀምር

"እዚሁ ሆነህ መጀመሪያ ከላይ ልበስ" ሲፈን መቼ መጣች? ቀስ ብላ በጆሮዬ "እንደእኔ ልታለብሰው?" አለችኝ። "እምቢ!"

ብር ሰጥቻት የምትፈልገውን ልብስ የገዛች ቀን ካላለበስከኝ ብላ እንደ አሻንጉሊት ሆን ብላ ያደረቀችው ገላዋን አልብሼው ነበር፡ ፡ እንደእህቶቼ መሳም በጣም እርቂ ባይሆንም የትዝታውን ደስታ አልተነፈኩም።

ሲፈን ወደ እኔ ክፍል ስትገባ ተከትዬ...

"ለካ ለራስሽ ነው ቹቹ እንዳይገባ የተከላከልሽው? ቤቱ የሚመች መስሎሽ?"

"ምን አደረጉት ቤቱን?"

"እረ? የቤቱ ባለቤት?"

"እንክት!" አንገቷን አነከተች "ባሌ እኮ ነህ"

"እንደሱ አትበይ!"

"ስንጋባ እህቶችህ እዚህ አይደርሷትም"

የእውነት ፈራኋት፣ የቹቹን እናት መሰለችኝ ተቀይራ።

"እውቂ ነው፣ ልታበሽቀኝ ስትል እኔም..." ክንፈሬን ሳመችኝና "ዛሬ እነ ገልጆ ጋ ሄደን..."

"እዛም ጨቅይቶ ፍራሹ ተጠቅልሎ አልጋ ላይ ነው"

"አየህ አይደል እራስህን? እኔ ያልኩት አብረናቸው እንቃምና ሲያወሩ እንሰማቸው ነው። ማታም ትንሽ እየጠጣን..."

"እኔ አልጠጣም፣ እራሴን ያመኛል"

"መጣሁ" ሳታደምጠኝ እንደወፍ ቱር ብላ ሄደች። ቱር ብላ ከመምጣቷ በፊት ብር አውጥቼ ወጣሁ።

"ወዴት ነው? ምላህስ?" አቴቱ

"መጣሁ..."

"እንዳበዛኸው አልታወቀህም?..." አግር ያለው የሚከተል ቁጣ፤ ከኋላ ከኋላ የሚከታተል። "እንዳበዛኸው፣ አልታወቀህም?..."

ሲፈን ስትመጣ የቤት ልብሷን ሳታወልቅ የክት ልብሷን ሸጉጣ ነበር። ወደ እኔ ክፍል መመለስ ነበረብን። ሸጉጣ እኔ ክፍል ስንገባ የእህቶቹ "ኡሆሆሆሆሆሆይ!" ተከተለን። ከነርቭ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው ቃል! ምናልባትም "መጭ!" እንደሚባል ፈረስ፣ "ክፍ" እንደምትባል ድመት፣ "እሽ" እንደተባለ አውራ ዶሮ... ነርቭ የለመደው ይሄን "ኡሆሆሆሆይ" ይሆናል። ነርቬ ቃሉን ሲሰማ በያለበት ይራወጣል።

ላቤ ጡብ ብሎ ሲፈንን አስበስኪት። አውቃ ያደረቀችው እጇ መስቀል ቀሚስ እንደማልበስ ያለ ችግር ፈጥሮብኝ ነበር። በኋላ እየሳምኩ፣ አካሏ ሲላላ ቀሚስ አያጠለቅሁ ጨረስኩ። በድካም አልጋ ላይ ያለው ጥቅልል ፍራሽ ላይ በደረቴ ተዘረርኩ። ሲፈን ጀርባዬ ላይ ወጣች።

"ተይ፣ አበዛነው" አልኳት

አኩርፋ ከላዬ ላይ ወረደች፤ አንዳኮረፈች ሠራተኛ ስፈር ደረሰች። ምናልባት ፈረስ የመጋለብ ህልሟን ስላጨናገፍኩባት ይቅርታ ለማድረግ ክብደት ይሆን? ለመካስ ፈለኩ።

"ምን ልግዛልሽ?" በምን ልካስሽ እንደማለት "መጋለብን ምን ይተካዋል?"

"ምንም!" ከአንገት በላይ ቂቢብ ያለ ኩርፊያ እንደሆነ እያስታወቀ፦

"ስለምንሽ?"

"እንቢ" አጥር ላይ ወጥቶ አውራ ዶሮ በሆነ ኩርፊያ ዝም አልኳት። "አኮረፍክ? እሺ በቃ ጥፍር ቀለም ግዛልኝ"

"ሌላስ?"

"ቻፒስቲክ"

"ምንድነው ቻፒስቲክ?"

"አሳይሃለሁ"

"እሺ ሌላስ?"

"ኩል እና ማሪሲሊ እና... ልጨምር?"

"አዎ"

"እና - ትንሽ ሽቶ"

የሴቶች "ፀሐይ" እነዚህ "ፕላኔቶች" በዙሪያዋ የሚሽከረከሩባት ናት። ሊፒስቲክ እንደሳተርን፣ ማሪሲሊ እንደ ማርስ፣ ሽቶ እንደመሬት፣ ኩሉ እንደጁፒተር፣ ሎሽን እንደ ሜርኩሪ... አዳዲስ የሚገኙ ኮከቦችም አሉ። ለምሳሌ ቻፒስቲክ የተሰኘ ፕላኔት። ወንዶች ሰማይ ላይ ሲያንጋጥጡ ሴቶች እጃቸው በጨበጠው ዙሪያ ይሽከረከራሉ። እንኳን እናቴ የተማሩት እህቶቼም ስለወንዶች "ፕላኔት" አንድ ቀን አስበው አይቼ አላውቅም።

አንድ ትንሽ ሱቅ ገብተን ሁሉንም ገዛሁላት። የሴቶችን ዐንፌ-ዓለም ጨበጠች። ፕላኔቶቿ በዙሪያዋ አሽበሸቡ "ኮኮብን ትገዛለህ" ተብሎ የተጻፈው ይሄ ይሆን? አንድ የላስቲክ ከረጢት ያልሞላ?...

የናዝሬቶች ራስ ገዝ ወደተረጋገጠባት ቤት አመራን። ስድስተኛ፣ ቤት የባህል ሥዕል ተጨምሯ ነበር። ሁሉንም ጨብጠን ተቀላቀልን። ሰው ሲጨመርም ሲቀነስም ለውጥ የሌለው ቤት ነው። የሞላ ይመስለል ሲጨመር ግን ይይዛል። ከስድስቱም አንገር አማካኝ ቦታ ላይ የተቀመጠው ስድስት እግር የማይሞላ ጨት እጃችውን ሲሰዱ ለመቀርጠፍ ያደፈጠ አውሬ መሰሏል - ሁሉም ፈርተውታል።

ሲፈን "ፕላኔቶቿን" አውጥታ እንደ አዲስ መመርመር ጀመረች። የሲፈን አላማ ሉብቸኛዋ የባህል ስዕል ማሳየት እንደሆነ የገባኝ የልጅቷ በሳብ ጨፍ ያለ መልክ የበስጠ ሲፐለቀለትና ዓይኖቿ ነብ መሆናቸው ሲጨምር ነበር። ይሄንን ነገር እህቶቼ እርስ በእርስ ሲደራረጉም አይቻለሁ። አንዳንዴ የተደረገባት የተወጋች ያህል ስቃቃስት አሰማ ነበር፤ ስቃይ አለው?

"አንቺም የናዝሬት ልጅ ነሽ?"

"እ? አ-አዎ" አለች ቀልቧን ከፕላኔቶቹ ላይ መንቀል ተስኗት፤ ሲፈን ቀና ብላ አየችኝ። አጭር ቀሚሷ ስላላመቻት ጉልበቶቿን ገጥማ ወደጎን አስተኝታቻዋለች። ልብሷ ብልጭልጭ ነገር እንዳለው ያወኩት ጨለም ያለ ቦታ ስትሆን ነው። የስጠታ ዕቃ መሰላለች።

"ስምሽ ማነው?"

"ቢም" ምን አይነት ስም ነው?

ሲፈን ጣልቃ ገባች። "የናዝሬት ልጅ ልትባል አትችልም። ሞጆ፣ ይሻላታል፤ ስሟም ‹ቢም› ሳይሆን ‹ቢመኙ› ነው።"

"ቢመኙ አሪፍ ስም ነው"

"ይልቅ የሚጠቅማት ጫቱን ብትገዛላት..." ሲፈን ድምፅ ውስጥ መትከንከን አለ። መትከንከን የምንለው ሰው ሽር ስላልሆነ መንተክተክ ብለን ለመጥራት ስለቸገረን መሰለኝ። ሲፈን ተንተከተከች።

"ጥሩ!" (እንደጠናጋሻው)

"ደሞ አትገዛላትም"

"ለምን?"

"እኔ ስላልፈለኩ" የፐላኔቶቹን መያዣ ወርውራ ቀጭ አደረገችው። የአምስቱ ጃንሰኖች ዓይን የበለጠ ከአፎቱ ወጣ፤ የጫቱ አለመገዛት መርዶ ሆኖባቸው መሆን አለበት።

ተጀመረ አገር ሊሰበሰብ፤ የእማማ አጀቡሽ ጡሩንባ ሊነፋ። ያንን ጡሩንባ ማን ወርሶት ይሆን? ነው ጡሩንባውም ከእማማ አጀቡሽ ጋር ጥይት ፋብሪካ ሄዶ ነበር? ግን እሳቸው ለምን ሄዱ? የሸክናን ቀልድ እየሰሙ ሳያውቁት እዛ ደረሱ?....

"ና ወደ ጓዳ እንግባ" ሲፈን ስትቆጣ እንደነብር እያማረች ታስፈራለች። የልጅቷ ዝም ማለት ሆዴን በላኝ።

ሲፈን በገዛ ቀሚሷ ታስራ መነሳት ቸገራት። እጄን አልሰጠኋትም፤ ረድቼ እራሴን ላስደብድብ? ሲፈን ወደ ጓዳ ከገባች እዳው ገብሰ እንደሆነ አውቃለሁና ቀደም አልኩ። አልጋ ላይ እንደወጣች ድምፅ የሌለው ቁጣ ተጠቀመች። መንጨቅጨቅ ብላ

"ደስ ሲለኝ አትወድም አይደል?"

አውቄ እንዳናደድኳት እስታውቄ እውነት ደስ ሲላት አልወድም? ስል እራሴን ጠየኩ። እሷም ሴቶች ደስ ሲላቸው አትወድም።

ሲፈን እርቄ ከእኔ እንዲመጣ ስለፈለገች ፊቷን ወደ ግድግዳ መልሳ ተኛች። እዚህ ለቀብር የተዘጋጀ ጉድጓድ ውስጥ ምን እምጥቶ እንደከተተኝ ወደማሰቡ አዘነበልኩ። እዚች አልጋ ላይ፣ በዚች ሰዓት ከሲፈን ጋር የመተኛት ዕጣ-ፈንታ አለ? ወይስ ነገሮች እንደቦይ ውኃ አጋጣሚ በቀደደላቸው ይፈሳሉ?

"አቀፈኝ" ትዕዛዝ

ታናኘነት ያታዬ ነው፤

"በደንብ፣ በሁለት እጅህ" ሌላ ትዕዛዝ

የመጣውን ትዕዛዝ የማስተናገድ ግዴታ ከተፈጥሮ ተቀብያለሁ።

በዚህ መካከል በጫቱ ተሰፋ የቶረጡት ጃክሰኖች ወሬ መቃም ጀመሩ። እኛ ከመፃምጣታችን በፊት የጀመሩት የወሬ ቂማ መሆን አለበት።

"በጥንት ጊዜ አመክኖአዊ ዕውቀት ስላልነበረ ተአምራት በታጨቀባቸው አፈ-ታሪኮች ይታመን ነበር። እነዚያ የአማልክት አፈ-ታሪኮች በፍልስፍና በኋላም በታሪክ መስፈርቶች እየተመረመሩ ነባሩ አለም ላይ ያላቸው የበላይነት እንዲቀንስ ተደርጓል። ዘመናዊው ሰው ከተአምራት ይልቅ በሳይንሳዊ ተጠየቅ ላይ ተመስርቶ ህይወቱን እንዲመራ ግድ ይላል።"

ወንድ ይሄው ነው። አጁ ላይ የሌላ ነገር ሲቶጥር ዕድሜውን ይባጃል። ከሚኖርበትና ከሚገለገልበት ይልቅ በጊዜ ሂደት በኖ እና ተኖ ወዳለመኖር የተሸጋገረ ጉዳይ ቀልቡን ይስበዋል። አሁን አነገልጆ መፈራረስ የጀመረውን የናዝሬት ራስ ገዝ ትቶው ጥንት፣ አፈ-ታሪክ፣ ፍልስፍናና ሳይንስ ጋ ምን ወሰዳቸው? የጎፈረ ፀጉርን ልብ ብሎ መስተካከል፣ የገረጣ ፊትን በመስታወት አይቶ ሰብ መቀነስና መመገብ አይሻልም?... እኔም ይሄን ልበል እንጂ ቀልቤ የተሳበው ለእነሱ ውይይት ነው።

"አቀፈኝ አላልኩም? በደንብ ጥብቅ አድርገህ?" የሲፈን ግድ ከዚች ጎዳ አልወጣም። ሌላው ጥንታዊው ዓለም ላይ ደርዷል።

"እኔ የምለው ደግሞ ዘመናዊው የሰው ልጅ አሁንም ከአፈ-ታሪክ አልተላቀቀም ነው። ሳይንስ የተባሉት ነገሮች ሁሉ ወደጥንቱ ጭፍን እምነት እየተሸጋገሩ ነው።"

ይሄኛው ደሞ ማን ይሆን?

"ለምሳሌ?" አለ አንድ ጫት ሲጠፋ ወሬውን በትጋት ለመቃም የቶረጠ ድምፅ

"ለምሳሌ ፊዚክስን እዩት፤ ስለስንፈ-ዓለም አፈጣጠር የሚያቀርበው መላምት ከጥንቶቹ ግሪካውያንና ሜሶፖታሚያውያን አፈ-ታሪክ በምን ይለያል? የዳርዊን የዝግመተ ለውጥ ንድፈ ሀሳብ ትክክለኛነት የሚያረጋግጠው በምርምሩ ጠንካራነት ሳይሆን

የጥንታዊው ሰው በነበረው አይነት ጭፍን እምነት ነው። በሥነ ልቦናውም ዘርፍ ላይ ይሄ ጉዳይ ሲንፀባረቅ ይታያል።"

"እኔ ደግሞ የሚታየኝ የአንተ ተቃራኒ ነው..."

ይሄ ነገር እንደ ትምህርት ቤት የክፍል ሥራ በመደዳ ሁሉም የሚደርሰው ይሆን እንዴ? እኔ ብጠየቅ ምን ልል ነው? የእኔ ፕላኔቶች ቼቼ፣ ሲፈን፣ አባቴ፣ እናቴ፣ አህቶቼና ኦፊ አቡኮ አይደሉም? እርግጥ አዳዲስ የተገኙ ፕላኔቶችም አሉኝ። ጠናጋሻውና በአሉ ግርማ... ክጃክሰኖች እንኳ ሌላ አስዳቢነት ሊከሰት ነው?

"እኔ ደግሞ የሚታየኝ፣ ዳኒከን የተባለው ጀርመናዊ ፀሐፊ ያመላከተው የአፈታሪክ መፍቻ መላ ነው። የጥንቱ ሰው በነበረው ግንዛቤ መጠን ‹አማልክት› እያለ የሚጠራቸው አሁን በከፊል እኛ የደረስንበትን የሣይንስ ደረጃ አልፈው የሰለጠኑ ማኅበረሰቦችን ነው። ሳይንሳዊ ፈጠራዎችን እንደ ትንግርት በማየት ለምሳሌ መምጠቂያ መንኮራኩር ሲመለከቱ "የእሳት ሰረገላ" ይሉታል። ጀት መሰል የአየር ላይ መጓጓዣዎችን "የብረት ወፍ" እያሉ ከአስር ሺህ ዓመት በፊት ዋሻ ውስጥ የጻፏ ሕንድ አገር ተገኝተዋል። መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥም እስቅኤል እንደራዕይ የጻፈው እነዚሁኑ መብረር የቻሉ ማህበረሰቦችን ነው። ልክ አሁን በቴክኖሎጂ የተደረሰበትን መሳሪያ ይዘህ አንድ ስልጣኔ ያላየ ህብረተሰብ ዘንድ ብትሄድ የሚሰጥህ ግምት አምልኳዊ እንደሚሆነው ያኔ..."

"ተው ግን አቀፈኝ፣ በደንብ..."

እነ ጃክሰኖች እንደ ባቢሎናውያን ቋንቋቸው ተዛንቶ ለመጠፋፋት እግዚአብሔርን የማግኘት ግንባታ የያዙ መሰለኝ። ያኔ በባቢሎናውያን ዘመን መቼም ባቢሎናውያኑ ሴቶች ከቤታቸው ሳይወጡ ልጆቻቸውን እያጠቡ ነበር፣ ልጆቻቸው ሲተኙላቸው እንዮስላ የመቀባት እቅድ ይዘው ባሎቻቸው ከቤት ሲወጡ፦

"ወዴት ነው?" ይላሉ

"እባክሽ ፈጣሪ የተባለ ጥጋበኛ ሰማይ ላይ ሆኖ ዝናቡንና ፀሐዩን አልመጥን አለ። እስከመቼ እሱን ተለማምጠንና መስዋዕት አቅርበን እንዘልቀዋለን?...

"እና ምን ልታደርጉ?"

"የባቢሎን አውራጃ አስተዳዳሪ ፎሌ ነፍቷል። ትልቅ መወጣጫ ግንብ ገንብተን ሰማይ ላይ ስንደርስ ፈጣሪ እጅ ከሰጠ ጥሩ፤ ካልሆነ እንወጋዋለን ብሏል።"

"ከሆነላችሁ ደግ፣ ይሄ ልጅ ምነው ቀበጠ፣ አልተኛ አለኝ እኮ... እስኪ እንሶስላው በስሎ እንደሆን እይልኝ..."

"እሆሆይ አንቺ የደላሽ ነሽ፣ ቱምቢው የት ነው? መለሰኛ፣ ማንኪያ፣ መሮ... ይዘህና ብለውኛል..."

ጃክሰኖችን እያዳመጥኩ ሲፈንን ማቀፍ ተሳነኝ። ወንድ አይደለሁ? ቋንቋዬ ተዛንቆ፣ የገነባሁት ተደንብቶ እንደሚቀብረኝ ባውቅም ፈጣሪ ከሚታደንበት ጦርነት መቅረት አይቻለኝም።

"የመጣነው እነ ገልጃ ሲያወሩ እያዳመጥን ለመቃም አልነበር?"

"ሴት ስታይ ልውጥውጥ አልክ፣ እኔም ልውጥውጥ"

"ሴት ነበር እንዴ?"

ሲፈን ከት ብላ ሳቀች፣ ዞራ ሳመችኝ "እዚህ ቤት ስንገባ ሴት ነበረ ወይ አልክ? እይ ታለ?" እንደከባድ መሳሪያ ከጓዳ አወናጭፋ ውጭ ያለችውን ልጅ በነገር አረር መታቻት። ሲፈንን ልጠላት ነው? ግን ያቺም የባህል ሥዕል "ከባድ መሳሪያ" እጇ ከገባ ተኩሳ ሲፈንን መምታቷ አይቀርም።

"ትንሽ እንተኛና እንወጣለን"

"ጥሩ፣ መጀመሪያ ጫቱን ላኪ"

"እሺ ስጠኝ"

"ለእነሱም"

"ቢ-መ-ኙ!" ሥሟን ተፋችው። ሌላ ከባድ መሳሪያ ብሩን ከእኔ ተቀብላ በመጋረጃ በኩል ወረወረችው።

ዐጥ!

በጫት ላይ የተጣለችው ተስፋ እንደአባቱ ከሙታን ተነጥላ ተነሳች። ጃክሰኖች "ምድር" እና "አሁን" ላይ ተስፋ ሲያጡ ይሆን ወደ "ጥንት" እና "ሰማይ" የሚወጡት? ዐጥታው ለእኔና ለሲፈን ተመቸን። አቅፍ፣ ሳም አደረገችኝ። አካሌ እንዲመቻት፣ አካሌ እንዳያሸማቅቃት አደረኩ።

እኔና ሲፈን የራሳችንን የሰማየ-ሰማያት መወጣጫ ገነባን፣ ቋንቋችን ሳይዛነቅ ለዘላለማዊ ቅፅበት ፈጣሪን ሳይሆን ተአምሩን ነበኘን። ፈጣሪ ፍጥረቱና ስጦታው ውስጥ ሆኖ አጮልቶ እየን እንጂ እኛ አላየነውም። ባቢሎናዊያን ፈጣሪያቸውን በየጓዳቸው

ትተው ወደማይገኙበት ዘመቱ። ፈጣሪስ ስለምን ዝም አላላቸውም? እንዳያገኙት ፈርቶ ኖሯል?...

"ታለ?"

ሲፈንን ትቼ ጠፍቼ ኖሯል፤ ቋንቋችን ሊዛነፍ? ግንብተን እዚህ ያደረስነው ባቢሎናችን ሊፈርስ? አካላችን ተግባብቶ መጫወት ጀመረ። ሲፈን ሰገረች፡-

"ስወድህ? ስወድህ? ለምን እንዲህ ወደድኩህ? ሲያስፈራ! ሲያስፈራ!...."

በላብ የተጣበቀ ጀርባዬን ልጨፍ በስመመን የሚለፈልፍ አፏን ሳምኩ። እንዳልደርስባት የተንጠራራች መሰለኝ። ከፍ ከፍ እያለች እንደ አንቴና ተመዝዛ እዛው ቀርታ ቀጥ አለች። ብዙ የቆየች መሰለኝ፤ ከዚያ ቀጥ ያለ ትንፋሿን እየለቀቀች ከላስቲክ እንደተሰራች ሁሉ መሟሸሽ ጀመረች። የተወጣጠረ አካሏ እየረገበ ኩፍትርትር ያለ ፊቷ እየተፍታታ ስትወርድ ክብደቷ ተሰማኝ። በጉልበቷ ቆማ ነበር? አይኗን ገልጣ በፈዘዘ ሁኔታ አየችኝ፤ በጀርባዬ ሰትኛ እኩል ደርሷ ሳመችኝ። ደረቴ ላይ ፍስስ...

"ገና ነህ?"

"አ"

"ምን እያሰብክ ነበር? ለሴቶች ጠንካራ ወንድ የሚባለው በሴክስ ላይ አብሯት የማይሆን ነው። ያልኳን፣ አንዳንዴ እሷን ያላዳመጠ፤ ለመጀመሪያ ጊዜ መቆየት የፈለኩትን ያህል ቆየሁ። አንተ ግን እስከ ማታ ትቀጣለህ?"

"እንዴት?"

"አሁን መድገም አልፈልግማ!"

የሆነ፤ እንጥልጥል፣ መውረድ የሚፈልግ ነገር ውስጤ አለ። ጅምርነት ምኔን እንደሆነ ሳላውቅ ያባባኛል። እንደ ፔንዱለም ማረፊያ የተነፈገው ነገር ከወዲያ ወዲህ ይላል።

ስንቅም ትኩረቴ ሁሉ ሲፈን ላይ ይሆናል። ዓይኗን አይቼ ውብቱ ይጨክንብኛል። የተቀነጣጠሰ ጫት ይዛ እጇን ስታጎርሰው፣ እጇ እዚያው ቢቀር እፈልጋለሁ። ተነባብሮ የሞተ እግሯን ስመለከት እንደ አዲስ ተዋወቀው፣ ተዋውቀው ይለኛል። መነካካት እንዲህ ያለ ጣዕም ነበረው?....

"ትቀጣለህ" ያለችኝ ይሄንን ነው? እውነትም ቀጣት።

## ሰላሳ ሦስት

## የባቢሎኖች ሸንጎ

ጃክሰኖች ጨቱ ለዓይናቸው ሲሞላና አጥረት እንደማይከተል ሲያውቁ ወደ ኮከቦች፣ ጨረቃዎችና ፕላኔቶች መዝመት ጀመሩ። ልክ ሲፈንን እስሬ ጥዬ ለእነሱ ጠሬ ቀልቤን እንደተውኩ መሆኑ ነው። "ድሮም ወንድ እጁ የገባ አያሳስበውም" እንደሚሉት እህቶቼ፦

ጃክሰኖች ምርቃና በነብ ዓይን አመሳሰላቸው እንጂ፣ ችግር የአንድ ብራና ቅዳጅ አስመስላቸው እንጂ፣ ቡላ ዐጉራቸውና በአንድ መቀስ የሚንካኩት ሪዛቸው አመሳሰላቸው እንጂ በፊት አወራረድ እጅግ ይለያያሉ። ሲላው ቀርቶ አፍንጫቸው ብቻ ሲታይ አምስት አይነት አቀማመጥ አለው፤ እንደሲፈን ሉታይ፣ ሉታይ የሚል ንቁ አፍንጫ፣ እንደ አበባሽ "ልቤን" የሚል ሀመምተኛ አፍንጫ፣ የእማማ አጀቡሽን ጡሩንባ እንደነፉ አቢያው የቀረ አፍንጫ፣ እንደሳኮ ጭገሩን ያበጠረ አፍንጫ፣(አራት አትሉም?) የማይኮራ የማያፍር አፍንጫ። የገጣሚ፣ የኢንጂነር፣ የመምህር... አፍንጫ እንዴት ያለ ነው በሚል፤ በአፍንጫ ዱካ ሙያቸውን ማፈላለግ ጀመርኩ።

ይሄን ማሰብ ከሲፈን "ቅጣት" ያስታግሳል።

ቢም በምርቃና የስኒ ማስቀመጫ መስሎ የታየኝ ዓይኗ ጭራሽ ትናንሽ ሆነብኝ። እኔ ከእሷ በላይ መረቀንኩ ማለት ነው? የእኔ ዓይን ምን መስሎ ይሆን? እስር ሳንቲም? ሰሙኒ? ሽልንግ?...

የከሸፈ ሳቅ ተሰማ፤ እኔ በማሰበው መስሎኝ ቀና አልኩ ጭገሩን ያበጠረ አፍንጫ ያለው ነው። የሚያወራ ሳይሆን የሚያስብ መስሎ ቀጠለ፦

"በየ መለኮታዊ መጽሐፉ ውስጥ የተሰገሰጉ ተአምራትን በአዲስ መንገድ እንድመለከታቸው ያደረገኝ ዳኒክን ነው። በጣም የገረመኝን ልንገራችሁ..."

ትምህርትም በእንዲህ ባለ የጨት፣ የቡና፣ የመጠጥ ወይም የምግብ ሥነ-ሥርዓት ቢሰጥ የበለጠ ውጤታማ ሳይሆን አይቀርም አልኩ። ምክንያቱም...

"ሙሴ የሲናይ ይሁን ወይም የሴላ ተራራ... አዎ የኮሬብ ተራራ ላይ እግዚአብሔርን የሚያናግርበት ምዕራፍ ዘፀአት ውስጥ አለ። ሙሴ የአማቱን የዮቶርን በጎች እየነዳ እዚያች ተራራ ሲደርስ ቁጥቋጦ እሳት እርፎበት እየነደደ፣ ግን ቁጥቋጦው ሳይቃጠል ሲቀር አየ። ተአምሩን ለማየት ሲጠጋ አንድ ድምፅ "ወደዚህ አትቅረብ አንተ የቆምክባት ስፍራ የተቀደሰች መሬት ናትና ጫማህን ከእግርህ አውጣ" ይለዋል። ሙሴም ወደ እግዚአብሔር ያይ ዘንድ ፈርቶአልና ፊቱን ሸፈነ። "ሰው አይቶኝ አይድንምና ፊቱን ማየት አይቻልህም" ስለተባለም ነው። የእግዚአብሔርን ጀርባ ተፈቅዶለት ካየ በኋላ የፊቱ ቆርበት አንፀባራቂ ይሆናል።" ብሎ ድጋሚ የክሽፈ ሳቅ አሰምቶ የጫት ቀንበጥ ለመቀንጠስ ያሻሽ ጀመር።

የሚያወራውን ሲጠብቅ ሲፈን ነካ አድርጋ የጫት ቅንጥብጣቢ ሰጠችኝ። ቅጧቷ ትገዘ አለኝ፡-

የሚያወራ ሳይሆን ለራሱ የሚያብሰለስል መስሎ ቀጠለ።

"ዳኒከን ይሄንን ሁኔታ ከሳይንስ አንፃር ይተረጉመዋል። መጀመሪያ በእሳት ነበልባል መካከል የታየው መልአክ ከሂሊየም ጥቃት ለመዳን አብረቅራቂ ልብስ የለበሰ ሲሆን እሳት የመሰለው ከራስ መከላከያ ቆብ ላይ የስፔስ ኃይለኛ ብርሃን ያለው ባትሪ ነው። አትቅረብ ያለው ሙሴ እንደጨመረበት የቆመበት መሬት የተቀደሰች ስለሆነም አልነበረም። ለመንኮራኩሩ የሚጠቀመው የኑክሊየር ኃይል ስለሆነ፣ ሙሴ ያለመከላከያ ቢቀርብ ‹አፈክት› ስለሚያደርገው ነው። እንደተፈራውም አሰርቱ ትዕዛዛቱን የተቀበለበት ሲና ተራራ በኒውክሊየር ኃይል ቅሪት ስለተጠቃ ሙሴ ያልተሸፈነው የፊቱ ቆርበት ተጎድቷል።"

ፊጣሪን በአካል ለማግኘት ያልሆነላቸው የባቢሎናውያን ቀሪቶች እግዚአብሔርን በወሬ ዝቅ-ዝቅ ማድረግ እና ማብጠልጠል ጀምረው እንደሆነስ? ልክ አባቴ የተሸነፈበትን ጦር ዝቅ-ዝቅ እንደሚያደርገውና እንደሚያብጠለጥለው ማለት ነው።

ሲፈን እንደ እናቴ ጨቷን ለመድኃኒትነት የምትሰጠኝ አስመስላ ትመረምረዋለች። ለራሷ ግን ወገቡ ላይ ቆርጣ አጋድማ አፏ ውስጥ ትከታለች። አንዳንዴ ለስላሳውን የምታስታውሰኝ ሲፈን ናት። እኔ እንደ ጠናጋሸው ደረቅ ጫት ፈጭቼ አድቅቄ፣ አፌ ውስጥ ደርቶ እንደጓሽ ሲቦን መመልከት የፈለኩ ይመስል ፈሳሽ አላስታውስም። ጠናጋሻውን የት እንደደረሰ አለመጠየቄ የክህደት ስሜት አሳደረብኝ።

ጭንገሩን ከበጠረ አፍንጫው ውስጥ የከሸፈ ሳቅ ትንፋሽ መስሎ ወጣ፦

"የሙሴንና የፈርኦኑን ወዝግብ የሚተርከውን ስታነቡ ብዙ ሳይንሳዊ ጦር መሳሪያ የሚመስሉ ነገሮች ተግባር ላይ እንደዋሉ ታያላችሁ። በተለይ የሥነ-ህይወት ጦር መሳሪያ አከክ የሚነዙ፣ ክብቶችን የሚፈጁ፣ ሰተባዮች መፍለት ምክንያት የሚሆኑ፣ የውኃን ኬሚካላዊ ውህድ አስናክለው የሚያቀሉ… እነዚህ ሁሉ ሲደረጉ አይሁዶቹ የበር ሳንቃቸው ላይ ደም እንዲቀቡ ይታዘዙ ነበር። ያ - ደም ምን ነበረበት? ምናልባት አሁን የሰው ልጅ በሳይንስ ሊላልደረሰበት ይሆን ሰውን የሚከትበው? አንድ ቤት ሲከተብ በተወሰነ "ሬዲየስ" ያሉ ሰዎች ‹ሲፍ› ይሆን እንደሆነስ?…"

የወሬአችን ግብ የረጋን ወተት መልሶ እንደ ማፍላት፤ ብጥስጥስ ያለ ሆነ። ትውልዶች አምነው ሲቀባበሉት የቆዩትን ድንገት ሰርቶ ለመቀበል የተዘረጋውን መጪ ትውልድ ኩም ማድረግ። ከዚህ እምነት ጋር ተያይዞ የተመሰረተው ማህበራዊ ተዋረድስ? በምን ይተካ? ክፍተት መፍጠር ክፍተት የመድፈን ዝግጅት ሲኖረው አይገባም?…

ያኔ እንዲህ አስቤ ነበር? ወይስ አሁን መልሼ ሳስበው ይሄ ተሰማኝ? እንጃ!

የናዝሬት ራስ-ገዝ ለመወያየት የሚፈራው ሰው፣ ነገር፣ መለኮት የለውም። አንዳንድ ጊዜ እኔ የተረዳሁትን ወይም የማስበውን ሲፈን ብትጠይቀኝ ምን ምላሽ እንደሚኖረኝ ሳስብ ብዙ ውይይት ያመልጠኛል። ሲፈን ግን የምታዳምጥ አትመስልም። ዓይኖቿ ወይም እጆቿ የሚጋብዙኝ ሌላ ነገር ሲሆን እኛ መካከል እንደሌለች ሆኖ ይሰማኛል። አንድ ቀን በነበረው ውይይት ላይ ያየሁባት ንቃት አስገረመኝ።

የማይከራ የማይፈራ አፍንጫ ያለው፤ የቲዎሎጂ ተማሪ ነበር። የሰው ልጅ ስላለው ድብቅ ኃይል እያወራ ነበር። "behind the iron curtain" የተሰኘ መጽሐፍ ጠቅሶ ሩሲያዎች በድብቅ የሚያደርጉትን ምርምር ገለፀ። በአይናቸው ማንኪያ ስለሚያጣምሙ፣ ከአይናቸው በሚወጣ ኃይል ታላላቅ ነገሮችን ስለሚያንቀሳቅሱ፣ በእጅ ዳሰሳ የቀለም አይነት ስለሚለዩ እና በጣታቸው ጫፍ ስለሚያዩ ዓይነሥውሮች አንዳንዶቹ መጪውንና ያለፈውን ጊዜ በትክክል ማየት የሚችሉ ናቸው።

"ባለአውሊያዎች ናቸው ማለት ነዋ" አኔ ለሲፊን ጥያቄ ሀፍረት ቀረደደኝ።

"አዎ" አለ የእግዚአብሔርን ትምህርት ተሰጥሞ መልሶ እግዚአብሔር የሚያጣ ሽንነ የሚመራው። "በተለያየ ባህሉ የተለያየ ስምና ስያ ይሰጣቸዋል። በሰለጠኑት ዓለማት "ሳይኪ" ይሏቸዋል። ጊዜን ቦታን ሁኔታ ሳይገድባቸው በተለያየ "ዲያሜንሽን" ያያሉ። በእኛ ባህል ደግሞ ባለአውሊያ፣ ጠንቋይ፣ ጠጠር ጣይ፣ ደብተራ... በሚል የመጥፎ መንፈስ ተራዳኢነት እንዳላቸው ይደመደማል።

"መጥፎ መንፈስ ከሌለባቸው ታዲያ ለምን ይከደማሉ? ለምን ይለማመናሉ? ማለቴ "ጊታዬ፣ ጊታዬ" ለምን ይባላሉ?"

ለሲፈን ጥያቄ ምላሽ የሚሰጠው ጫት በእሷ ስብብ ስለተጋበዘ እንጂ ጥያቄዋ ውኃ እንስቶ አልመሰለኝም።

"ልዩ ተሰጥዖው የሚንቀሳቀሰው በተለያየ ልምድ ሲሆን ይችላል። መከደሙንም፣ መለማመኑንም ያንን ልዩ ተሰጥዖ ለማነቃቃት የሚጠቀሙበት ዘዴ አድርጎ ማየት ይቻላል። እኛ እንኳን ጫት ሳንቅምና ስንቅም ያለውን ልዩነት እዩት። አንዳንድ ችሎታ ያላቸው ሰዎች ለምሳሌ ደራሲያን ከመፃፋቸው በፊት የሚያከናውኑት የተለያየ ልምድ እንዳላቸው አንብቤአለሁ። እንደዛ ነው።"

"ስለዚህ ሲጣን አድሮባቸው፣ ጋኔን ሰክፏቸው የሚባለው እንዲህ ነዋ?"

"አንድን ነገር የምትጠቀሚበት አላማ ጥሩ እና መጥፎ የሚል ተቀጥላ ያሰጠዋል። በቃ! ሌላው ቀርቶ ውኃን ለልምሻሜና ለጥምቀት

በንጠቀምበት ስለኖርን ጥሩነቱ ብቻ ይታየን ነበር። ውስጡ ሌላ ኃይል እንዳለ ተረድተን ሐይድሮጂን ቦንብ ስንሰራበት ውኃ መጥፎ ሆነ ማለት ነው? ውኃ ጥሩም መጥፎም አይደለም። ሰው ነው ጥሩ እና መጥፎ የሚለው። ልዩ ተሰጥዖ ያላቸውም ሰዎች እንደ ውኃ ጥሩ የሚባልና በመጥፎነት የሚፈረጅ ' ኃይል ሊወጣቸው ይችላል። አንድ ሰው ከበሽታው መፈወሱን እስኪ እንየው። ፈውሱ ጥሩ የሚባለው ከማን አንፃር ሲታይ ነው? ምናልባትም በርሱት ለሚከራከረው ሰው ያንን በሽተኛ ማዳን መጥፎ ሊሆን ይችላል። መግደል ደግሞ ጥሩ! የጋኔን "አብስትራክት" የሰው ልክ ከምርጫውና ፍላጎቱ አንፃር ሲታይ የሚገኝ ተጨባጭ ያልሆነ ድምዳሜ ነው።"

ይሄንን ልጅ የትኛው ቄስ ምን አስተምሮት እዚህ ድምዳሜ ላይ ደረሰ? እንግዲህ መጥፎው ጋኔን የሰም ካለ ጥሩው ፈጣሪም መካዱ አይደለም? ከሁለት በላይ በተሰበሰባችሁት ቦታ እኔ በመካከላችሁ አለሁ የሚል ቃል የሰጠው ኢየሱስ ክርስቶስም እኛ መካከል ቀጭ ብሎ ይሄንን ጉድ እየሰማ ይሆን? እንዴ የከሸፈውን ቄስ፣ ሌላ ጊዜ ጠያቂዋን የከሸፈች ኳዳሚ በተራ በተራ እያየ ዝም? ትዕግስትም ልክ አለውና አንድ ቀን ራስገዟ ናዘሬት ከእነ ናዝሬቶቿ ትንንት፣ ብንን ማለታቸው ሳይታወቅ ድንገት ከቦታው ጥፍት ማለታቸው አይቀርም። ምናልባትም የሠራተኛ ሰፈር ጥይት ፋብሪካ ፈንድቶ፣ ነገሮች አርጎ ውስጥ ገብተው ይሟሟሉና እየሩ ሲጠራ ራስ ጊዜ ከእነ ነፃ ሀዝቦቿ የሉም። እንደ ቻይና የሚቀበር ጠፍቶ ዝም ብሎ ማመን...

# ለካሳ ክራት

## ምርኮ

አባቴና ሁለቱ ወታደሮች ጠላይ ማሰልጠኛ ሄደዋል ተባለ። ግራ ተጋባሁ፤ የአባቴ የአርባ ዓመታት አገልግሎት ተሰረዘ? እንደ ሲፈን "ወያኔዎች እንዳልወጋኸን ቁጠረውና እንደ አዲስ እንጀምር" አሉት? እነአባቴ የተሸነፉበትን ደካማ ጎን አጥንተውላቸው በማሰልጠን ጦርነት ሊገጥሟቸው? በሰብሰብ የሰለጠነ ጦር ገጥማችሁ ድል አደረጋችሁ ስለተባልን ስልጠና ውሰዱና ግጠሙን፤ የጠፋ ስማችንን እናድሳለን" አሏቸው ይሆን?

ግራ ተጋባሁ፤ አባቴ በእነሱ ላይ ያወራውን ሰምተው በእልህ ስልጠና ሰጥተው ጦርነት ሊገጥሙት ይሆን? ዘመቻ በሚመስለው የምርኮ ዝግጅት ዕለት ምን ነበር ያለው?...

"እንቺስ ምን ትያለሽ? (እናቴን) ጣ! ፈራን እጅ ጠብቅ ፈርሙልን አሉ፣ ጣ! ቢበዛ ላትተናኮሉን ማሉልን፣ ቃል ግቡልን ይላሉ፣ ጣ! ሥሙን በወፍ ቋንቋ ጠርተው ‹ታድሶ› አሉት እንጂ ይሄው ነው። ጣ!"

እናቴ እራሷ ዘማች መሰላ ዳቦ ቆሎ፣ ቋንጣ፣ ድርቆሽ፣ ቆሎ... ተዘጋጅቶላት ወደ ጠላይ ሄደች። የቤተሰቡ ገንዘብ ክፍል ኃላፊ ሰምረት የበጀት ጉዳይ ለመመርመር ይሆናል አብራ ሄደች። ረቂቅ ሰምረትን እግሯ ላይ ወድቃ አብሮ ለመሄድ ለመነቻት። "በጀት የለንም" አለች መሰለኝ እንግሊዟ። ረቂቅ እንደእኔ "እሆሆሆይ" ወረደባት። የነርብ ሰርአቷ ተናግቶ ቁጭ አለች።

እህት ቢሆኑ ቅሉ ማማት አይቀርምና ያለፈውን የረቂት ሁኔታ እያነሱ፣

"አፈር ትብላ፣ ምነው ሞታ ባለቀሰን?" አሏት።

"ታለ ይሙት፣ እኔማ ውኃ ነው የሆንኩት!"

"እኔስ?"

"እኔስ?"

"እኔስ?"

የመጨረሻውን "እኔስ?" እኔ ለራሴ ጥያቄ አቀረብኩበት። እንደ ፍርድ ቤት ረቂቅ የትግስት ማቅለያ ያስፈልጋታል። "ከዚህ በፊት ምንም አይነት የፍትር ሪከርድ የሌለባት መሆኑ ታውቆ፤ እንዲሁም እናቷ ወደ ጠላይ ሲሄዱ ሲሉ ሰንቅ በማደራጀት ረገድ ያሳየችው ትልህ አስተዋፅኦ እሷም የምትሄድ መሥሏት፣ ወይም አባዬ ለጠናጋሻው ክስንቁ እንደሚያካፍለው ቀስፋ በማድረግ ቢሆንም) ከግምት ገብቶ፣ የጠረደባትን ‹ሕሆሆሆይ› ቶቋቋማ፣ የነርብ ሥርዓቷ ከጉዳት በመጠበቋ ወንድሟ ታለ..."

"መሳፈሪያ ልሥጥሽና ሂጂ" አልኳት።

እንደ መልኳ ባዕድ የባኒያን ድንጋጤ አሳየች።

"ኢዩዘሽ፣ ከእንሰምረት ኋላ ትደርሻለሽ..." (አይተሽው ትመጫለሽ ለማለት አልደፈርኩም።) ሰምረት እግር ላይ መውደቋ ሳይቀጨት አልቀረም። በድንጋጤ የጃክሰኖች አባል መስላ ነጣች።

"እሺ?"

"እሺ!" አለች ቆራጥነት በሌለው ድምፀት።

"ጠላይ የት እንደሆነ፣ በየት በኩል እንደሚኬድ ጠይቂና ንገሪኝ። እኔ መሳፈሪያውን እሰጥሻለሁ።"

"ዳቦ ቆሎ ሲቀረጥ አይታወቅም?"

"ዳቦ ቆሎ ምን ያደርጋል? ሌላ ነገር ግዢለትና ሂጂ" ረቂቅ የእኔን ያህል ብስለት ማጣቷ አንጀቴን በላኝ።

ላኳት፤ ላኳት ከማለት ተክስኳት ይቀላል። እናቴ ቆማ ሰስቱን ወታደሮች ስታነጋግር ለምን እንደሆነ ባይታወቅም ያነበሰችው ሰምረት ጀርባ ላይ ወጥታ በመንጠር፣ በእናቴ ጭንቅላት አልፋ ጠናጋሻውን አቀፍ!! እናቴ በለመደ ዘዴዋ የደረቀ ጫት ትንታ ፈጥራ ነፍሷ ሊጠጣ ሲደርስ አባቴ ተቆጥቶ፣

"ምነው ብዜን? ጣ! ልጅሽ ረቂቅ ተሽላ፣ እኔን ላንቺ ትታ ጣ! ለኔ ያላትን ናፍቆት ጠናጋሻውን በማቀፍ ስትገልጥ ጣ! ዝም?! ጣ! ያንቺ ትንታ ምን ይበጀኛል? ጣ! ብታቅፊኝ ነበር እንጂ ጣ!"

ማታ እናት ደኢታዋ የእናት ሚኒስትሯን ቦታ ሽፍና ተጨንቃ ረቂቅን ስትጠብቅ፣ ነገርኳት።

"ምን? ታለ? እስኪ ታለ ይሙት በል?" ቢያንስ ረቂቅን ታለ ይሙት ከማለት ተገላግያለሁ። "ጠናጋሻው ይሙት" ትበል ሥትፈልግ፤

"አዎ!"

"ወይ ቅሌት! ምን አሳበዳት ልጄ?..."

"ምንድን ነው? ምንድን ነው? ምንድን ነው?..." እንደ እህቴ ከጠየቀች የሚበዛውን ይንጋጋሉ፤ ተነገራቸው።

"ቱ! ምን? እስቲ ታለ ይሙት በይ?"

"በኢየሱስ ስም!"

"ዝምበይ! ዝም በይ! ዝምበይ!.."

እንደእኔ ‹ኦሆሆሆይ› የእህቶቼ ነርቭ ሥርዓት የሚዛባው በአበባ መደንገጫ "በኢየሱስ ስም" ሳይሆን አይቀርም።

"እንዴት ሄደች? በምን ሄደች?..." የእህቶቼ ቀጣይ ጥያቄ ኢኮኖሚያዊ ሆነ። እኔ እደሆን የቀረውን ባሻ ያፈቀረች ካለች ከመላክ ወደኋላ አልልም፤ ኧረ እተኩሳታለሁ። ‹ኦሆሆሆሆይ› ያለችብኝ ሁሉ ‹ኦሆሆሆሆይ› እንዲባልባትና የነርቭ ሥርዓቷ ሲዛባ እንድትቀምስ ማድረግ ተቀዳሚ ተግባሬ ነው።

አይመስልዎትም እናት ዴኢታ እቴቴ?!! ሰው ሠራሽ መኮሳተሪያዋ ላይ አፈጠጥኩ።

"እግዚኦ፣ የእማዩ መሽማቀቅ ታየኝ፤ ምን ይውጣት ይሆን?..."

"እውነት"

"እውነት"

በቀጣዩ ቀን ከሁለት ቀን በኋላ ትምህርት ቤት ሄድኩ። በላይ ዘለቀ ትምህርት ቤት አባዬ እጁን ከሰጠበት ከፍተኛ አጠገብ ይገኛል። መማርን በሚያሰንቅ ውይይት ውስጥ ለቀየ ልጅ የትምህርት ሥርዓቱ አሰልቺና እድካሚ እንደሚሆንበት እሙን ነው።

ምሣ ሰዓት ስመለስ ሲፈን ከቹቹ ጋር ለማውራት እየሞከረች ደረስኩ። እንደ እህቶቼ ምን ላድርግልሽ ማለት አሰኘኝ።

"ዛሬ ትምህርት ቤት ሄድክ?"

"አንቺ ግን አልሄድሽም?"

መፀፀት ስጠብቅ መሰልቸት አነበብኩባት። ወዲያው ሁኔታዋን አለዋውጣ "እኔ የመጣሁት አንድ የሚያስቅ ነገር ልነግርህ ነበር"

"ምን?"

"የተባለው!"

"ማን ያለው?"

"ድፍን ሠረታ ድልድይ"

"ምን አሉ?"

"ስለእኔና ስለአንተ"

"እኮ ምን አሉ?"

"‹ሲፈን ላይ ታለ አስደግሞባት ሌሊት እንደ ጅብ በእንቅልፍ ልቧ ሄዳ እሱ ቤት ትገባለች...› እውነት ነው አባቴ ይሙት!"

"እ?"

"እም!"

"በጋሽ ተገኔ ማልክ?"

"በእሱ አይደለም፤ ባሳደገኝ አባቴ ነው"

እንደ አቴቱ፣ የሲፈን "እሶት ደኤታ" ሆኖ ያሳደጋት ተካደ ማለት ነው? የትኛው ይበልጣል? ያባቷ? ወይስ የልጇን ዕድል ለማቃናት የተናገረች እናት የጠቀመችው ሰው?

"ታለ? ይቅርታ?" አለችኝ

"ምንም አይደል?" አልኳት በሀሰት ስለማለች መስሎኝ፡፡

"ለምን ይቅርታ እንዳልኩህ አውቀሃል?"

"ለምንድን ነው?"

"ትናንትና አንጓችን ፈልጌ ሄጄ ነገርኳት"

"ምን?"

"ብር ጠፍቶብሽ እንደሆን፣ ለሞኑን ታለ ልብሰ ገዝቶልኛል ብዬ"

"ለምን?"

"እሷ ውቃቤዋ ኃይለኛ ነው። ታውቃለች። በኋላ ካዘነችብኝ ታሳቅለኛለች"

የሆነ የታሰረ ነገር እንዳሳት ከታወቀኝ ቆይቷል፡፡

"ተቀየምከኝ?"

ፒያሳ ቢሆን አፈራት ነበር። እዚህ የእማማ አጀቡሽን ሡሩንባ ብትነፋ እህቶቼ፣ ቢበዛ ጥቂት የፀብ ሱሰኞች ቢሰበሰቡ ነው፡፡

"እሷ ምን አለችሽ?"

"እኔ አልጠፋኝም፣ ሰብሰብ ሳይኖረው አይቀርም"

"ሰብሰብ ምንድን ነው?"

"ድግምት፣ አንተ የምትፈልገውን ነገር ሁሉ የሚያመጣ ጋኔን የሚታዘዝበት ነው ይላሉ..."

ዝም ብዬ አየኋት።

"በእናትህ! እንደሱ አትየኝ"

ዝም!

በሁለተኛው ቀን እናቴ አባቴን ይዛ መጣች። ድፍን ሩፋኤል መጀመሪያ ደነገጠ፣ ቀይቶ አደነቀ። "አይ-እሷ'ኮ" አለ። ምናለ በነካ እጇ ጠናጋሻውን ነፃ ብታወጣ ኖሮ?

እናቴን የተከተላት ሰው ሲጠይቃት፦

"ዘዴው መች ጠፋን? አውቀን ዝም አልን እንጂ" አለች።

እህቶቼ ሲጠይቋት በአይኗ እየጠቀሰች ዝም አሰኘች። ምሽቱ ላይ ይተኙ ብሎ ባዕድ ሁሉ ሲሄድ እናቴ እየሳቀች፦

"የእናንተ አባት እንከፍ ናቸው መቼም፤ ሳያጣሩ ስተት ብለው ሲሄዱ የጠየቃቸውም የለ፤ ከከፍተኛ ጠላይ ይዘዋቸው እብስ። ለካ ሹመት ያለው እንጂ ሌላውን አይፈልጉ ኖሮ ይሄን አውቶቡስ ላይ አልሰማም? ቀ-ጥ ብዬ ኃላፊው ጋ፤ ሹመት ቢኖራቸው እንኳን ዳግም ዘማች መሆናቸው ያስለቅቃቸዋል አይልም?... ከርፋፋ ሽማግሌዬን ይዤ ወደቤቴ..."

አባዬ በእናቴ አንቱ ተባለ? ፍቅር ነው ፀብ? አልታወቀም። አባቴ ብዩን አሹሎ ሲሰማ ቀይቶ፦

"ምን አንቺ ታስለቅቂኛለሽ? ጣ! ቀድሞኑም ስምቻለሁ፣ ጣ! ቦታው የወንድ መዋያ ነውና ትንሽ ልታደስ ብዬ ቀየሁ እንጂ ጣ!"

ከታደሰ ብዩን እንኳን አያወጡለትም ነበር? የአባቴ ነገር ግንባርዎ ይታደስልዎት ሲሉት "እንቢዮ! ጣ!" ብሎ ይሆን? "ለእናት ሀገሬ በሰርኔ የጠጣሁት ጥይት ጣ! እስከ ዕለተ ሞቴ ድረስ ጣ! ለሚቀጥለው መቶ አመት ከግንባሬ አይወርድም ጣ!" ብሎ ከእነብዩ ወደቤት።

## ሰካሳ ኬምስቶ

## <u>ህልሞች</u>

ሰው ሁሉ የየራሱ ማንቂያ ተኩስ አለው። ያ-ተኩስ ለአንዳንዱ ሰው የአብሪ ጥይት ፋና በመንገዱ ላይ ይተውስታል። ያልተጠበቀ አቅጣጫ ተከፍቶ ለመሄድ ያደፋፍረዋል። የኔ አብሪ ጥይት የወጣው ከሲፊን አፍ ነበር። በሴታሴትነቴ የነቀፈችኝ ዕለት ለእኔ ተተኩሷል። አሁን ላይ ሆኜ ስመለከተው ከዚያች ‹አብሪ ጥይት› በኋላ ሕይወቴ ሰተት ካለ ጎዳና ወደ አልተገራና ወዳልተመነጠረ ጭፍን መንገድ ገብቷል። በወጣ ገባው ጉዞ መንፈሴ ወደመንኮታኮቱ ተዳርሶ የነበረ ቢሆንም አሁን ላይ ሆኜ ሳስበው የዚያ ዘመን ውሳኔዬን መውቀስም መክሰስም አልደፍርም። እንደውም አንዳንዴ ውጤት ባገኘሁባቸው ብቻ ሳይሆን ለመንኮታኮቴ ምክንያት በሆኑ ውሳኔዎቼ መደነቅ ይዳዳኛል። ከእናት መኳረፍ፣ ዓይን ለዓይን መናቸፍ ብሎም በድርጊት መዛለፍ በተፈጥሮ ላይ ማመፅ አልነበረም? ሰው ከተፈጥሮው ጋር ተፃርሮ "እኔ" የሚለው ምኑን ነው?

ትዝ ይለኛል ለመጀመሪያ ጊዜ እናቴ ላይ የተኮስኩት ሲፊንን ነበር። ከትምህርት ቤት ስመጣ እኔ ክፍል ተቀምጣ እየጠበቀችኝ አገኘኋት። ፊት ነሳኋት! ሳላናግራት ትልቁ ቤት ስሄድ ማንም አልነበረም። ተቀመጥኩ።

"ታስ?" ደጅ ቆማ ተጣራች።

ዝም!

"ታስ?"

ፀጥ!

"ታስ!" ኃይል ያለው ጥሪ።

"ምንድን ነው?"

"ውጣ እና አነጋግረኝ?"

ወጣሁ

"ምን ሆነሃል?"

"ምንም! ምን ሆንኩ?...

"እኔ እንጃ! ያስቀየምኩህ አለ?"

"የለም፣ ግን..."

"ግን ምን?"

"በቃኝ!" ቃሌ ሰይፍ ሆኖ ልቧ ላይ... አቃሰተች።

"ለምን?" ዓይኖቿ እንባ አጋቱ። የዓይን ቀቧ ድምስር ተፋ...

"ሁሉም ነገር ውሸት ነበር። እናቴ ሆን ብላ ለእኔ ጊዜ ማሳለፊያ አመቻቸችሽ፤ በአውሊያ እያስፈራራች በብር እያባበለች። ካንቺ ጋር እስከመጨረሻው እንድቀጥል አትፈልግም። ስለዚህ በኋላ የማይቀር መለያየት..."

በዚህ መካከል እናቴ በስሎ ያልወጣለት ወጥ በማንደጃ ላይ አድርጋ ሰንሰሉን እልፋ መጣች።

"አንቺች ነበረች ብር የምትሰጥህ?"

"እ?" እልኳት በጭንቅላቴ ንቅናቄ እዎንታን አክዬ

ሲፈን ስትዞር ከእናቴ ጋር ተገጣጠመች። ቁጢጥ ብላ ጉልበቷ ላይ ተደፋች። ቀሚሷ ሲንዘፈዘፍ እያለቀሰች እንደሆን ገባኝ። ወዲያው ተነስታ እናቴ ላይ አፈጠጠች። ወጡን ብትገለብጥባት የሚል ስጋት ያዘኝ። ሲፈን ግን ትኩስ ወቀሳዋን ወደመገልበጡ አዘነበለች።

"አንቺች፣ ሴት ወልደሻል ብድራት አትፈሪም?"

እናቴ ግራ በተጋባ አኳኋን ባልንጀራዋን ታያት ጀመር።

"በልጆችሽ አትጨው!" ወደ ውጭ ለመውጣት በሚያንገዳግድ ስሜት ምከር አድርጋ ቀመች። ደሞ ሄደች። ሰንሰሉጋ እስከትደርስ እናቴ በመገረምና ግራ በመጋባት ታያታለች። ሲፈን ድንገት ዞራ፦

"እንጓች፣ መቃብሬ እንዳትደርሺ፣ መቃብርሽ አልቆምም" ብላ ሄደች። የሲፈን ሁኔታ ትንሽ አስቂኝነት ያለበት ሆነ። እናቴ በጥያቄ ሲታየኝ በጥያቄ ዓይን ተመለከትኳት። የእሷ አይን ቀድሞ ተሰበረ።

ከሰማየ ሰማያት ወርዶ፣ ወደመቀመቅ የተጣለውን እናትነት በእናቴ በኩል ማሽማቀቅ የዚያች ቀን ምኞቴ ነበር። ከሲፈን አንፃር ደግሞ ጣሪያ ላይ እንደወጣ አውራ ዶሮ ሰማየ ሰማያት ላይ ሆኖ ወደ ምድር ለመጣል የሚጣጣረውን ሴትነት ኩም ማድረግ።

ወደ ክፍሌ ስገባ ደብተሬን እንዳላስቀመጥኩ አጠኩ። ፍራሽ ላይ ወርውሬ እራሴን ስጥል እንግዳ ድምፅ ጆሮዬ ውስጥ ገባ። ወፍራም እርጥብ ጣውላ ሲቆረቆር የሚሰጠው ድምፅ ከወደ አልጋው ይመጣል። ቀና ብዬ ቹቹን አየሁት። በጆርባው ተንጋሎ አገጩ ደረቱን ሳይለት ያለቅሳል። እንባው ወደጆሮ ግንዱ ሲጣደፍ አየሁ። ፈጣኑ ነገር እንባው ብቻ ነው። ከቹቹ ተፈጥሮ ፈጣን ነገር በማየቴ መደነቅ ዳዳኝ።

"ምን ሆንክ?"

"ሲፈን አለቀሰች" አለ ለመጀመሪያ ጊዜ "ደሞ" ሳይል መሬት ለመሬት እየሰነጠቀ እግራችን ሥር ብቅ የሚል ጆሮ ሳይኖረው አይቀርም። እዚህ ተንጋሎ ምንም ማድረግ ባለመቻል የሚያለቅሰው የእኔ ግማሽ ነፍስ ነው።

በመልስ ማጣት ያንጠራራሁትን ሰውነት ሰበሰብኩ። ያ የእርጥብ ጣውላ ድምፅ ዱልዱም ጦር ሆኖ ልቤን መውጋት ስለተሳነው እየተላተመ አሰቃየኝ። የቹቹ ሁኔታ ፍቅር ነው ወይስ ምን? ተፈጥሮ ሁሉን ነገር ነፍጋ ፍቅርን መስጠቷ የማሰቃየት ፍላጎቷ ምን ያህል እንደሆነ አያሳይም? ከተፈጥሮ በላይ የጨከንኩበት እኔ አይደለሁም? ያፈቀራትን የተዳራኋት እፊቱ አይደለም? ጆሮው መሬት ለመሬት ተሰቦ እያንዳንዷን የድሪያ ቅንጣት እየተከታተለ ሲነግረው ምን ተሰምቶት ይሆን? በእናቴ ከተበደለው በላይ በእኔ አልተሰቃየም? ከሲፈን እዚህ ቤት መመላለስ፣ ከሲፈን መዳራት በላይ መጣላቴ ቹቹን ሳይጎዳው ይቀራል?...

ከዚህ ሁሉ ሰቃይ ቹቹን መሆን በቀለለ ነበር። ልቤን ከዱልዱም ለቅሶ ድብደባ ለመሸሸግ መሸሸ ሳይሆንልኝ ቀረ። ወዴት እሸሸለሁ? ቹቹ ግማሽ እኔነቴ አይደለም? ከወገዘ በሬ ጋር እንደተቀናጀ አባት በሬ በእኔና በቹቹ መካከል ከመጓተት ውጭ ሌላ ዕጣ ፈንታ ከየት

ይመጣል? ስደስት የሚያዝነው ክፋዬ ቹቹ አይደለም? ስቦርቅ የሚያዘግመው? ስሄድ የሚቀመጠው? ሳገኝ የሚያጣው? ስተኛ እንቅልፍ የሚርበው?...

በዚያን ቀን አንዲት ህልም ለማየት ብቻ ዓይኔ ሸለብ አለ። ህልሙ አስፈሪ ነበር። እኔ እንደቹቹ ተጋድሚ፤ ቹቹ ጥቁር ብርሃን ለብሶ ቁልቁል ሲያየኝ ነበር። ለመነሳት ስሞክር በእጆቹ ደረቴን ተጭኖ አስተኛኝና ቀስ እያለ የሀዘን ማቅ የመሰለውን ብርሃን ከላዩ አውልቆ እልጋ ላይ አስቀመጠ። ቀጥሎ የእኔን የነጭ ብርሃን ልብስ ያወልቅብኝ ጀመር። ከደረቴ ጋር ተያይዞ የተበጀውን ተነካካሽ ቁልፍ ፈትቶ ብርሃኔን ወደታች ሲሸለቅቀው ጭንቅ፣ ጭንቅ ይለኝ ጀመር። የእኔን ብርሃን እንደቶዳ ገፍፎ የእሱን ጥቁር ብርሃን ያለብሰኝ ጀመር። ጭንቁ ወደ ልመና ተሸጋገረ።

"ይቺ ዕዋ ከእኔ ትለፍ" ያልኩ ይመስለኛል።

ቹቹ ፊቱ ላይ ሀዘን እየተነበበ የእኔን ነጭ ብርሃን ለራሱ አጠለቀ። የሚያስገድደው ያለ ይመስል ብርሃን ሲቀይረኝ ደስ ሳይለው ነበር። መንቀሳቀስ የምችልበት ጊዜ እልፏል ስል አሰብኩ፡ ፡ አገጩን ደረቴ ላይ አገኘሁት፤ ሴኮንዶች ሰዓታት መሆን ጀመሩ፤ ደቂቃዎች ሌትና ቀን ያቀፉ መዘዞች...

ቹቹ የብርሃን ኮሌታውን እያስተካከለ ከቤት ሲወጣ ብቸኝነት ቁር ሆኖ ተተከ። አቤት ብርድ! እግዚኦ ቆፈን!... ሰው ሊገኝ የማይችልበት ኢየር ላይ እንደተንጋለልኩ ዝልግልግ ቀሰስተኛ ጊዜ ዋጠኝ። በቀን አስራ ስድስት ጊዜ የሚመታው መቀመቅ ልቤ ላይ አንዲት ነጥብ እሮይታ እንዳለች ገባኝ። ብድር የመከፈልና ከዕዳ የመላቀቅ እሮይታ።

ዓይኔን ስገልዕ አካሌ መንቀሳቀስ ስለአለመቻሉ እርግጠኛ ነበርኩ። የተኛሁት ፍራሽ ላይ እንጂ እልጋ ላይ አለመሆኑ ከእውነታው ጋር አቀራረበኝ። በደንብ አካባቢዬን ስቃኝ ሲፈን በሩን ተደግፋ አየኋት። ስታለቅስ መቆየቷን የዓይኗ መነፍረቅ ያሳብቃል። የዓይኗ ቆብ በእጥፋት መኳሉ ቀርቶ በደምስር ተሞልቷል።

"ይቅርታ አድርግልኝ?" አለችኝ።

ሰው በድዬ እንጂ መች ተበድዬ አውቅና ይቅርታ አደርጋለሁ?

"በእግዚአብሔር፣ ይቅርታ አድርግልኝ" እንደአዲስ ማልቀስ ጀመረች ገና ከህልሜ ተፅዕኖ አልተላቀቅሁም። አካሌ መንቀሳቀስ መቻሉን አላረጋገጥኩም። ዓይኔን ጨፈንኩ። አንድ ቀን በእኔ ስበብ የዘነቡ እንባዎች አካል ቦድሶ በሚገባ ፍላት አላዬ ላይ መውረዳቸው እንደማይቀር አውቃለሁ።

"ቼቼን ይቅር በለኝ በይው" አልኳት። እሷ ምን አደረገችው? እንጃ!! እኔን ተክታ ይቅርታ ብትለው ስለሚፈልገው... እንጃ!!

"እሺ" ብላ ወደ አልጋው ራስጌ ሄዳ እያለቀሰች "ቼቼ! ይቅርታ አድርግልኝ" አለችው። አንድ ያደረገችው ነገር ይኖር ይሆን? ብዬ እስከጠራጠር ድረስ አቅፋው "ይቅርታ! ይቅርታ! ይቅርታ!" እያለች በዐዐት አለቀሰች።

ይሄም ለእኔ ግፍ እንደሆነ አውቃለሁ። አንድ ቀን በይቅርታ ንፍገት ተጠራሙቼ ዝልግልግ የጊዜ እርጎ ውስጥ በመስጠም እና በመንሳፈፍ መካከል እዋልላለሁ። አውቃለሁ!!

ሲፈን ከቼቼ ይቅርታን እንዳገኘች ቀጥራ ወደእኔ መጣች። ተንበረከከች፣ እንዳታፍር የነፈረቀ ዓይኗን ጨፈነች። አቀፈችኝ። እንደቼቼ ሁሉ ይቅርታዬን ከዝምታዬ ተቀብላ፤ በደስታ አለቀሰች። እንባዋ የደስታ መሆኑ በምን ገባኝ? እንጃ!!

የእኔ ቼቼን የዝምታ ይቅርታ ለእሱ የሚያስፈልገውን በማድረግ አገኛለሁ። የአካል እንቅስቃሴ ልምምድ የሚያገኝበትን ሁኔታ አመቻቻለሁ። እንደ ሴታሴትነቱ አስሮ የያዘውን የእኔን ጦስ ቀስ በቀስ ይገፍፋል። እርሱ ሲፈጥን እኔ እዘገያለሁ?.. ይሁን!

የሲፈን እንባ የማያስዝበኝ ጭንጫ መሬት ሆኜ አደርኩ። በየንቃቃቴ የሚገባው እምባ እያረረ ያልተለቀሰ ያህል ወደ መዘንጋት አዘቅት ይወርዳል። ካለመገንዘብ ዓለም ወደ መገንዘብ ዓለም ስሄድ ስለእኔ የፈሰሰ እምባ የእሳት ኩሬ ሆኖ ይጠብቀኝ ይሆናል።

በመካከሉ ድካም ሸለብ ሲያደርገኝ ከእውነታዬ ጋር ጨርሶ ያልተፋታ ሕልም ውስጥ እገባለሁ። ሲፈን ደረቴ ላይ እንደተኛች እጇን ወገቤ ላይ ጠምጥማ (ይሄ እውነት ነው) ሕልሙ ደግሞ ለሲፈን ክንፍ ይጨምርላታል፣ ፍራሹን ከስሬ ነቅቶ ይወስዳል። አየር ላይ እንዳለሁ ሲፈን ይዛኝ ወደታች ትወርዳለች። ክንፏ ከተርገበገበ

ይሄ ሁሉ ማሽቆልቆል እንዴት? እያልኩ እራሴን እጠይቃለሁ። ከመቀመቅ አልፈን ናዲር እንደርሳለን።

"ታስ?"

"እ?" (በሕልም? በእውን?)

"ንቃ፣ አንድ ነገር ልንገርህ"

"ጥሩ!" (እንደ ጠናጋሻው) "ንገሪኝ" ሆዴ ባባ?

"አርግዤአለሁ"

ሲፈን ሞተች፤ የእናትነት መቃብር ትሉንና ምስጡን አዘጋጅቶ ዋጣት። ከእንግዲህ ሲፈን የምስጥና የትል እንጂ የማንም አይደለችም። ከእንግዲህ ሲፈን በልጅ ስም ልጅ የሚታረድላት የናዲር ጣዖት ናት፤ ከእንግዲህ ሲፈን በልጆች መካከል ዘላለማዊ ጠላትነት የምታበጅ መጥፎ ቆሌ ናት። ራምሴስ፣ ሄሮድስ፣ ወቶቴ፣ አቴቴ...

...ቆዳዬ በእያንዳንዱ ፀጉር ማብቀያው እሾህ ሲያወጣ ታውቀኝ። ይሄንን ሲፈን ተረድታዋለች። እቅፏን አላላች፣ ተነሳች፣ በር ከፈተች፣ ወጣች... ወደእኔ ቤት ብቻ ሳይሆን ወደጡረታ ድልድይ፣ ወደ ጡረታ ድልድይ ብቻ ሳይሆን ወደሩፋኤል፣ ወደሩፋኤል ብቻ ሳይሆን ወደ ጉለሌ አልተመለሰችም...

# ሰካሳ አጽሌቱ

## <u>ሐሠሣ ሥጋ</u>

...ወደ ‹ናዝሬት ራስ ገዝ› ብቻ ሳይሆን ወደ ሠራተኛ ሰፈር፣ ወደሠራተኛ ሰፈር ብቻ ሳይሆን ወደ ፒያሳ አልተመለሰችም። ሲፈንን የሚወጋ እሾህ ብቻ ሳይሆን እሷኑ የሚፈልግ አንቴና አበቀልኩ። የሚወጋት ነፍሴ ነው፤ የሚፈልጋት ደግሞ አስከሬኔ...

...ናዝሬት ራስገዝ ተቀምጬ የጃክሰንን ቅዠት እንደ ኦኬስትራ ተቀናብሮ አዳምጣለሁ። ጓዳው መጋረጃውን ገጥሞ ሲታይ ወደአፉ "ሕልም" ያልዞረ ፅዋሚ ይመስላል። እንደቀብር የፀጥታ ቁር ወርዶበታል። እዚያ ቀዝቃዛ ፀጥታ ውስጥ የናዝሬቷ ሲፈን መስጠምና መንሳፈፍ ተሰኗት የረጋ እንባ ስታንከባልል፤ ትራሷ ስር ብዙ የእንባ ፈርጦች ተከማችተው ይታዩኛል።

ጓዳ ጓዳውን ስመለከት ቢም (ቢመኙ) በትዝብት አየችኝ። ምን ያስተዛዝባል? እንኳንም ነፍሴ አልፈለጋት እንጂ... ቢፈልጋትስ? ጦርነት ነው እንዴ? እኔ ሳልጨርስ እሷ ጨርሳ፣ እሷ ሳትፈልግ እኔ ብፈልግ ሽንፈት ነው እንዴ?... በጦርነት እንደተሸነፈው አባቴ ማስተባበል አለብኝ?

"የእግዚአብሔር ፍርድ ሆኖ ማሸነፏን ሲፈንስ መች አጣችው? ጣ! ቢበዛ ሳትተናኮለኝ ማልልኝ፣ ቃል ግባልኝ ትላለች ጣ!..." ማለት አለብኝ? ነፍሴ ባይሆን አካሌ እየፈለጋት አይደለም? ይሄ የነፍስ ባይሆን የአካል መሸነፍ አይደለም? ግን ለምንድን ነው አንቴና አብቅዬ የምፈልጋት? እንደ እናቴ ከሲፈንም ጋር ለመኳረፍ? ዓይን ለዓይን ለመናቸፍ? ብሎም በድርጊት ለመዛለፍ?... ነው?

ጃክሰኖች በጨት መንኮራኩር መጥቀው ከዋክብትንና ፈጣሪያቸውን ማሰስ ቀጥለዋል። ተረኛው ተናጋሪ እግዚአብሔር ጉያ ሆኖ የሚወጋው የሥነ-መለኮት ተማሪ ነው። የማይኮራ የማይፈራ አፍንጫውን ኮፍሶ ቀጠለ፡-

"...ዘፍጥረት ላይ እግዚአብሔር አዳምን መልካምንና ክፉን ለማወቅ ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ ይለዋል። ምን ማለት ነው? በሥነ

መለኮት ትምህርታችን የኢየሱስን ከሰውና ከእግዚአብሔር መወለድ የሚተነብይ ነው ይሉታል። ግን ሌላም አተያይ አለው።" የቅጠል መንኮራኩሩን ቀንጣጥቦ "ነዳጅ" ሞላና ቀጠለ፡-

"ይሄ ጥቅስ የሚያመለክተው አሁን የጀመርነውን የሳይንስ ዘመንና ሰዎችን ነው። አዳም በትዕምርት የተጠቀሰውን የበለስ ፍሬ ሲበላ መልካምና ክፉን አውቋል። መልካምና ክፉ ተቀጥላዎች ናቸው። አውቋል፣ እውቀትን አግኝቷል። እውቀትን ያገኘው የሰው ልጅ ውስጡ ካለው መሻት ጋር ሲያገናኘው ምን እንደሚፈጠር ፈጣሪ በራሱ ያውቀዋልና በሳይንስ የሚገዳደረው እንደሚሆን ገብቶታል። ወደፊት የሰው ልጅ ምድር ሲጠበው ክኮቦችን ማሰስና ለህይወት የሚስማሙትን ቅኝ መግዛቱ አይቀርም። ያኔ ከፈጠረን "ሳይንቲስት" (ፈጣሪ) ጋር በጥቅም መጋጨትና ምናልባትም መዋጋት አይቀርልንም። ስለዚህ ከእኛ እንዳንዱ ሆነ ያለን ይሄንን ተንተርሶ ነው።"

የእግዚአብሔር ታጋሽነት የታየኝ ስለናዝሬቱ ራስገዝ ትዕቢት የሠራተኛ ሰፈር ጥይት ፋብሪካን አለማፈንዳቱ ነው። ቢያንስ እነዚህን የናዝሬት ራስገዝ ህዋ አሳሾች ቋንቋቸውን አዛንቶ ጨት ሲሉ ውሃ፣ ውኃ ሲሉ ጨት እንዲቀባበሉና እንዲጣሉ ማድረግ ነበረበት።

ልታይ፣ ልታይ የሚል አፍንጫ ያለው የጃክሰን አባል ከመጠየቅ አልፎ ለማብራራት በረጅሙ ተነፈሰ።

"የፈጣሪዎች እንዲህ ያለ ፖጋት በግሪኮች አፈታሪክ ውስጥም ይንፀባረቃል እኮ።" ጃክሰኖች ለጥፋት የሚያሳዩት መከባበርና መጠባበቅ ለጥሩ ቢሆን ያስመኛል። አንዱ ሲያወራ ሌላው የሚያውቀው ቢሆን እንኳ አባቱ ጠናጋሻው ላይ እንዳደረገው አፍ አፉን አይለውም። በዝምታ አውርቶ እስኪጨርስ ጠብቆ ይጠይቃል ወይም ማብራሪያና ተጨማሪ ያክላል።

"ዚየስ የተባለው የሁሉ አማልክት የበላይ መሬትን ያለከሰማ፣ ሰማይን ያለማማ አቁሞ ከጨረሰ በኋላ ፕሮሚቲየስና ወንድሙን ኢፒሚቲየስን ጠርቶ ያማረችውን ምድር በሚንቀሳቀስ ፍጡር እንዲሞሉት ትዕዛዝ ሰጠ። ኢፒሚቲየስ ምን አደረገ? ዝሆን፣ ቀጭኔ፣ አንበሳ፣ ወፍ፣ አሣ... እነዚህን ፈጠረ። ፕሮሚቲየስስ ምን አደረገ?...."

እንደእኔ አባት ይሄ የጃክሰን አባል ለሁለት ተሰንጥቆ ጠያቂና መላሽ ሲሆን ነው አልኩ።

"...ሰውን ፈጠረ፤ ወንድሙ ለፈጠራቸው ቀንድ፣ ጋማ፣ ጥፍር፣ ኩምቢ ሰጥቷል። እሱ ለፈጠረው ሰው ምን ይስጥ? ጨነቀው፤ በኋላ ክሎሎምፐስ ተራራ እሳት ሰርቆ ሰጠው። እሳት ምንድን ነው? ማብሰያና ብርሃን ነው። የዚህ እሳት ምስጢራዊ ፍቺ ምንድን ነው? እውቀት ነው።"

አባዬ የጥያቂና መልስ አተራረብ ስልጠና ሰጥቶት ይሆን? ግራገባኝ።

"ዚየስ እሳትን ምድር ላይ ሲያይ ደነገጠ፤ እሳቱ እጁ የገባው ደግሞ ፕሮሚቲየስ በአማልክት አምሳል የፈጠረው ሰው ነው። አንደኛ ኮከብን ቀና ብሎ የሚያይ አድርጎታል። ሁለተኛ እሳትን /ዕውቀትን/ ሰጥቶታል። ዚየስ ለቅጣት ተነሳ። እንሰሶች ሁሉ ከእናታቸው ማኅፀን ከወጡ እንሰቶ ምድርን እንጂ ሰማይን አያዩም ይሄ የአማልክት አምሳይ ሰው የሚሉት ፍጡር ግን ኮከቦችን ያያል፣ ከዚያስ? ኮከቦችን ይመኛል፣ ከዚያስ? ኮከቦችን ቶኝ መያዝ ይጀምራል..."

እግዚአብሔርንና ዚየስን የናሳ ዲያሬክተር አደረጓቸው።

ቢም የምታዳምጥ አትመስልም። የእኔን አይን እንደበረኛ ሰትጠባበቅ የቶየች ይመስል ወደሷ ስሲጋው ቀብ።

"ሲፈንስ?"

"እዚህ ያለች መሰሎኝ ነበር"

"እረ አልመጣችም።" ከዓይኗ ዝቅ፣ ከጉንጯ ከፍ ብሎ የሚያንገጫብብ ጥቁር ደመና ያየሁ መሰለኝ።

"ጥሩ ልጅ ናት፤ ሰው ሲቸገር ይጨንቃታል፣ አዛኝ ናት።"

ምን ልታስተባብልልኝ እንደሆን ለማወቅ ንግግሯ ላይ አተኮርኩ። መለያየታችንን አውቃ እንዲቶጨኝ? ወይንስ ሲፈን ሲታመናጭቃትና፣ ከባድ መሳሪያ ስትተኩስባት ለምን ዝም እንዳለች ሊታሰረዳኝ?

"ግን ትቆጣለች፣ ሰው ታስቀይማለች። ቶይቶ ደግሞ ይቶጨትና ይቅርታ ትጠይቃለች" ከዓይኖቿ ዝቅ ከጉንጮቿ ከፍ ያለው ጥቁር ደመና ማደያት ሳይሆን አይቀርም። በሆነ የሴቶች ዘዴ ያለዘበችው ቢሆንም በጫት ሙቀት የተቀበረበትን ፈንታትሎ እየወጣ ነው።

"ተጣልታችኋል?"

የእህቶቼ ወንድም ነኝ። የሴቶችን አካሄድ ሳልወድ ተገቼ ያደኩ ነኝ።

"አልተጣላንም"

"ውይ በእናትህ አትጣላት"

ዝም! እስካሁን ቢም ልትነግረኝ ወደፈለገችው እንዳልገባች አውቂአለሁ። ሴቶች በጥሩ ጀምረው በጥሩ ማሳረግ የማይደፍሩት የፆታቸው ጉድለት ነው። ማዲያቷ ላይ አተኮርኩ።

ጫት ቀነጣጥሳ ሰጠችኝና

"እንዳልኩህ አወዳታለሁ። ታሳዝነኛለች።"

ተጀመረ፣ እንደማዲያቱ በወሬ ግለት መካከል እየደመቀ...

"ለሰው ሚች ናት እንዳልኩህ፣ አዛኝ ናት፣ ሰው ግን እንደሷ አይሆንላትም። እኔን የጠመደችኝ ይሄንኑ አንስቼ ስለመከርኳት ነበር። ተይ ሰውን ሳትመረምሪ ልሙትልህ አትበይ አልኳት። ካንዷም ስንቱ ትጎጂ? እኔ ወድጄ ነው አገሬን ሰብስቤ እዚህ የምውለው? የሚታመን ስለሌለ ነው..."

እያወኩት ተናደድኩ። ለእኔ ያደረገችውን ሁሉ ለስንት ወንድ አድርጋው ይሆን? አሁንስ? የትኛው ወንድ የእኔ የልጅት ብሂል አርፎበት እንደ ጥሬ ክምር ይፈርስላት ይሆን?... ከዚህ በፊት ሲፈንን ሳስብ የሚታየኝ የቀዘቀዘ አንገዋ ጠፍቶ የፈላ ሳቋ ሲፍለቀለቅ ወላፈኑ ላፈኝ። ቢም ቅናት በማባዛት ማድያቷን በሰዎች ዘንድ በማስራጨት ላይ እንደምትገኝ አሰቤ የቅናት ማለዘቢያ ቀልድ ሆነልኝ። ቢም ወልዳ ይሆን እንዴ? ለልጁ አባት እየፈለገች ይሆን እንዴ?...

"ልጅሽ ደህና ናት?" አልኳት።

"ማን ነገረህ?" በሲፈን እንደተቀደመች ሳትገምት አትቀርም። አዛኝ ምስሏን ትታ በሚታዘንለት ድምፀ "ወንድ ነው" አለችኝ።

ፊቷ ላይ የማይዘንብ ጥቁር ደመና እንዲያንዣብብ አድርጎ "አባቱ የት ሄደ?"

"ይሄን አልነገረችህም?"

ወሬ የማታጣራ ወሬኛ! ልትለኝ ይሆን?

"ግ'ቷል"

አባትነትህ ከባላጋራ ነፃ ነው ማለቷ ሳይሆን አይቀርም። ከዚህ በፊት ከተዋወቀን አልቆየም እንጂ የጨበጥኳት ቢሆን ኖሮ እንኳን ልጁ ሲያድግ ትልክብኝ ነበር። ሲፈን ጋሽ ተገኜን እንዳባባችው...

ጫት ቀነጣጥላ ስትሰጠኝ "በቃኝ" አልኳት። ፊቷ ቅይም ቢል ማዲያቷ ቦግ ብሎ ታየኝ። ማንም ያተመው ማዲያት በእኔ ሲሳበብ?...

...ከወንዶች ህዋ ወርደህ ማን አናቶች ናዲር ተገኝ አለኝ? ትበለኝ! እረ ትበለኝ!... ጃክሰኖች ተምኔታዊው ዓለም ላይ በጫት ፈረስ በመመላለሳቸው እንደገፉ ናቸው።

* * *

እቤት ስደርስ ቀኑ መሰስምለም ጀምሮ ነበር። የትልቁ ቤት ደጃፍ ላይ ረቂት እና ስምረት ተቀምጠዋል። አቀማመጣቸው የበሩን ግራና ቀኝ ይዘው ነው። ልብ ብዬ ስመለከት ሁለቱም ቢላዋ ይዘዋል።

"አርድሻለሁ! ታለ ይሙት ቱ በይኝ!" ስምረት ምራቅ የሌለው ዋሾ መትፋት አሳየች።

"ታለ ይሙት፣ እኔም አለቅሽ መስሎሻል" ረቂት ቢላዋን ነቀነቀች።

ከጠላይ የሚያስተራርድ ምን ጂኒ ይዘው መጡ? ወይስ የሲፈን እርግማን በእናቴ ላይ ደርሶ በሴት ልጆቿ ብድራት ልታገኝ?

"ሴት አሰዳቢ!" ስምረት

"አንቺ እንጂ፣ እሱስ ምን ይልሻል? አይታዘብሽም? ስሰሙ እህትሽ እኮ ነኝ?"

"እንዳንቺ አልተንጠለጠልኩበት፣ አራሱ..."

"አያደርገውም፣ ሀፍረተ ቢስ..."

"አንቺ ሀፍረትን ታውቂያለሽ? ኡሁሁሁ... አሃሃሃ..."

የቢዘንን ፋርጎ የሚበጣጠስ ምን ጉድ መጣ? አባዬ ልጆቹን የሚያስተራርድ ገዳፋ ቤቱ ድረስ ይዞ ይምጣ? ሲፈንም ጠናጋሻውን ብላ ይሆን የሄደችው?

እህቶቼን ኡሆሆሆሆሆይ ብዬ የነርብ ሥርዓታቸውን ማሳከር አምሮኝ ነበር። እኔ ግን እንደነሱ ጨካኝ አይደለሁም። ሳያዩኝ ሾልኬ ወደ ክፍሌ ገባሁ። ቤቱ ጭር አለብኝ። ቹቹ የለም። አለመኖሩ

ወደ ሽንት ቤት ሄዶም ሊሆን ይችላል፤ ግን መኝታው ፍራሹ ሲቀር ብርድልብሱና አንሶላው ተገፍፎ ተወስዷል። አንዳች አልሮ ሂያጅ የነገር ተባራሪ ጭንቅላቴ ላይ አርፎ ሳይቆይ በነነ።

"ምን?"

ወጣሁ፤ እህቶቼ ፊት ተገተርኩ። እግራቸው አቧራ ቅሟል። የነጠላ ጫማቸው መዳፍ ከላብ ጋር በተዋሃደ አቧራ ጨቅይቷል። ሲያዩኝ ተደናግጠው ቢላዋቸውን ሸሸጉ።

"ቼቼስ?"

ዝም!

"ቼቼስ?"

"ፈ-ፈረንጆች ወሰዱት ሲሉ ሰምቻለሁ" ስምረት ሁኔታዬ አደነጋገጣት።

"ማን ሰጣቸው?"

"እማዬ መሰለችኝ፣ ምነው? ታስ? አንተ?..."

ቀኑ ጨለመ፣ የኦፋ አቡኮ መጋረጃ ለሁለት ተከፈለ፣ ጉንጮቹ ለመጀመሪያ ጊዜ ታዩ፣ በጫት ተወጥረው ፊቱን ወደጎን ለጥጠውታል፤ ሴቶች በሀፍረት ስጋቸው መገለጥ እንዲያፍሩ ሆኖ ኦፋ አቡኮ በፊቱ አፈረ። የቼቼ እናት ጣውላ ፊቷ ላይ ጉጥ አይኖቿ ተንጠለጠሉ፤ የቢም ማዲያቶች ከፊቷ ላይ ተነስተው እንደ ሴሊት ወፍ ከግድግዳ ግድግዳ ይላተማሉ፤ ሲፈን ደም ትካድማለች፤ የአጀቡስ ጡሩንባ ለመስዋዕት የቀረበ አራስ መሰሎ እንደተጠቀለለ ተኝቷል፣ የታመመ የወታደሮች ጫማ በጫት እንቱፍቱፍታ ተዥጎርጉሯል፣ የእናቴ ረከቦት በሳንቲሞቹ ፋንታ በአተላ የጠቆሩ ዓይኖች ተቀልሎበታል፣ ዓይኖቹ የሲፈን ናቸው፤ የዓይን ቆባቸው በደም ስር ተሞልቷል። የደረቅ ጫት ብናኞች አረንጓዴ ትንኝ ሆነው ከአፏ ውስጥ ይዥጎደጎዳሉ፤ የቼቼ ጥቁር ብርሃን ያሳቅላል "ስንቴ ልበደል?" ይላል። ማሳቀሉን ሰምቶ የሸጎሌ ጥይት ፋብሪካ ይፈነዳል። ዷ! ወናው የሩፋኤል ጎዳና ጬኸቱን እንደማስተጋ ያኘካል።

"ዷ! ዷ! ዷ! ዷ! ዷ!"

የእናቴ ጬኸት ያላግጣል።

ሰካሳ ሰባት

## ፊውጥውጥ

ጂኒ በልጆች እንቁልልጬ ያዜማል...
...ሁለት ማኅፀን እቁብ ተጣጣ
አንድ አካል፣ ሌላው መንፈስ አመጣ
መንፈስ ከገላ ተዛንቀ
ባዕድ ባዕድ ውስጥ ጠለቀ።
በመንፈስ የቹቹ እናት ወለደችህ
በአካል የታለ እናት ደገመችህ
የሰው ልጅ ማሳደግ የሰለቻት
አንዷ ጠፋች፣
ሌላዋ አጠፋች፤
አንተ የቱ ነህ?
የቱ አንተ ነህ?
ግራ የገባህ
ግራ ታጋባለህ።
"ደሞ" የማን ነው?
ማን የሲፈን ነው?
ዛሬ ቹቹ ነህ?
ነገ ማንን ትሆናለህ?

ስነቃ ቹቹ ነኝ፤ የጂኒ ንግር ያዘኝ፤ አንገቴ ተቶልምሟል፤ ጊዜዬ ደርበብ ብሏል። ጨካኝዋ! የታለ እናትና እህቶቹ ከበውኛል። ከእንዴም ሁለት ጊዜ የታለ እናት "ምነው አልሞት አልክ?" ብላኛለች። ለመግደል ተቋምጥልኛለች። አንዳንድ ሰሞን ስትናገር አልሰማትም፤ ስትራመድ አላያትም። ንግግሯ "ጭጭጭጭጭ..." የሚል ድምፅ ነው፤ አካሄዷ እንደ ሸረሪት ድር የቀጠነ መስመር ነው። አንዳንድ ጊዜ ያ የሸረሪት ድር ሡልብ ብሎ ሲያልፍ ጭኔ ላይ ዝርግ ሰሀን አገኛለሁ።

አሁን "ጭጭጭጭጭ...." ትላለች። ጆሮዬ እሷ ፍጥነት ላይ አይደርስም። የከንፈሯን ንቅናቄ አጤንኩት፤ በጭንቅላቷ ቀርጬው ስደግመው አዘገየሁት። በልጇ ስም እየጠራችኝ ነው።

"ታለ? ታለ? ታለ?..."

ልጄን ገደልኩ ብላ ልትገድለኝ አሰባለች?

"ደሞ ቹቹ ነኝ" አልኳት እንደ እሷ ጭጭጭጭ ካላልኩ ላትሰማኝ

ልጆቿን ምስክር ቆጠረች።

ትሁት ለመምሰል የምትጥረው ልጇ መዳፏን ግንባሬ ላይ ጫነች።

"ማነህ?"

"ቹቹ ነኝ"

"ማነህ?"

"ቹቹ ነኝ"

"በኢየሱስ ስም ውጣ"

"ደሞ ከየት ልውጣ?" እንደእነሱ ለመፍጠን እሞክራለሁ ይደክማል እተኛለሁ። እንደነሱ ብንቀዠቀዥ ስልሳና ሰባ ዓመታት ቀርቶ አንድ ሳምንት እድሜ አይኖረኝም ነበር። ልቤ ፈንድቶ ዐጥ!

"ደሞ ታለ የት ሄደ?"

"ሲፈንስ ደሞ? ደሞ ደሞ ደሞ ደሞ ደሞ... ደሞ ደሞ ደሞ... ደሞ ደሞ ደሞ... ደሞ ደሞ... ደሞ ደሞ... ደሞ ደሞ ደሞ... ደሞ ደሞ ደሞ... ደሞ ደሞ ደሞ... ደሞ ደሞ... ደሞ ደሞ... ደሞ ደሞ... ደሞ ደሞ ደሞ... ደሞ ደሞ ደሞ... ደሞ ደሞ... ደሞ... (ሁለት ጠራት)

## ሰካሳ ሰምፃቱ

### <u>መልስ</u>

ልቦለድ ቢሆን እንዲህ ባልጨረስኩት ነበር። ግን ህይወት ነው። ያውም እውነት የማይገባው እውነታ የታከለበት። ምን ማድረግ እችላለሁ? ለሁለት ወር ያህል እኔ ቹቹን ሆኜ ነበር፤ ወይም ቹቹ እኔን ሆኖ ነበር። ልክ ስለአንተ የሚቸነከረው ጌታ አቅም ሲያንሰው መስቀሉን በሽክም የማገዝ እድል ቢገጥምሀ እንደማለት ነው። ሁለት ወሩን እንዲያ ነው የተመለከትኩት።

ሁለተኛ ወር ላይ ቹቹን ሆኜ አልጋ ላይ እንደተኛሁ ፍራሽ ላይ ነቃሁ። ቀስ ብዬ፣ እንደ እንቴና ተመዝዤ ወደአልጋው ሰማትር እዚያ ቹቹ በጀርባው ተጋድሞ አይኖቹ ፈጦ ተመለከትኩት።

ሁለት ቹቹ ከየት መጣ? እንዱ ቃለ ነው። የፍራሹ ነው፤ እንዴት እርቦኛል?" እየተንጠራራሁ ወጣሁ። እናቴ ለሁለት ወር ያደረችው እኔ ክፍልና እኔ ደጅ ላይ ነው።

ሰታየኝ እምሽክሽክ አለች። እንኩሮ ሆነች።

ሰሰማ ከፀበልና ከቃልቻ በኋላ የአእምሮ ሐኪም ዘንድ አቀረቡኝ። የሥነ አእምሮ ሐኪም ጋ መራኝ።

“ማነህ?”

“ደሞ ቹቹ ነኝ” አልኩት

“ቹቹ ማነው?” ብሎ ከእናቴና ከእህቶቼ ተረዳ።

“ቹቹን መልሱት” አላቸው።

እናቴ ቾቾን የሰጠችበት የረድኤት ድርጅት ሄዳ እያለቀሰች መልሱልኝ አለች።

"ዘመድ፣ አዝማድ የለውም ተብሎ ተፈርሟል ቀበሌም ደብዳቤ ፅፏል ብለው በአንቢታቸው ፀኑ፤ በኋላ ከሥነ-አእምሮ ሐኪሙ ደብዳቤ ተፅፎ ቾቾን መለሱት። ቾቾነቴን ለቾቾ አስረክቤ ታለን ሆንኩ?

ህይወት ከዚህ በላይ ተአምር አላት፤ ይሄ ምን ሊጨንቃት? ሕይወት ተረት እራሷ የሌላት ብዙ ውሸት አላት። ለመዋሸት ከቤቱ የወጣ ሕይወትን ሲያይ ተመልሶ ይገባል። ሕይወትን ያያት የእሱን ውሸት ማን ውሸት ሊላት? ካላመንክ አንድ ትልቅ ውሸት ዋሽተህ ሞክራት። ውሸትህ እውነት ተብሎ አንዱ የሕይወት ጥጋት ሥር ተከናውኖ ታገኘዋለህ።

• • •

"ችቼ" ትላለች እናቴ እኔ ክፍል በር ላይ ቆማ

"እምቢ፣ እምቢ፣ ደሞ፣ ደሞ፣ ደሞ፣ ለፈረንጅ ልትሰጠኝ ደሞ"

"ምናባቱ፣ ተወዋ ቤተክርስቲያን ነበር የምወስድህ" ብላ ትታው ትሄዳለች። እኔን ለቾቾ ይቆጨኛል። መቼ እንቺ አላት?

"ችቼ" ትላለች ቀይታ

"እምቢ፣ እምቢ.... ደሞ..."

ፈረንጆቹ የመደቡት ሀበሻ መጥቶ የእካል እንቅስቃሴ አሰርቶት ይሄዳል። በእስር ደቂቃ ይደክማል። የኛ እስር ደቂቃ በእርሱ ሰንት እንደሆነ የማውቀው እኔ ነኝ። አንድ ቀን እናቴ "ችቼ!" ስትል፣

"እምቢ፣ እምቢ..." ሲል

"ሂድ፣ ለፈረንጅ አትሰጥህም" እልኩት ቃሌን በግማሽ ልብ የተቀበለው በሶስተኛው ጥሪ፣ በሶስተኛው ማበረታታቴ ነበር። ነጠላ

አከናንባ አንገቷ ላይ ቋጠረች፡፡ የነጠላዋን ጫፍ አስይዛ ቀደመች፡፡ ሲሄዱ ከበስተኋላ አየኋቸው፡፡ ቹቹ ለሲፈን የገዛሁላትን የሽቶ ጠርሙስ ይመስላል፡፡ ድቡልቡል ክዳን ያለው የሽቶ መያዣ፤ ነጭ አረፋ ተሞልቶ... አንዳንዴ ቹቹና እናቴ ሩፋኤልን አልፈው፣ በሱሉልታ አድርገው፣ ግሼን ደርሰው፣ በላሊበላ በኩል፣ ፅዮን አርፈው፣ በደብረዳሞ አድርገው፣ ኩክ የለሽ ማሪያም ሰንብተው ታቹን በጊቋሳ አቦ ወደ ቤት ሲመለሱ ይታዩኛል፡፡

"እህ እንደት ደከምኻል፤ ልጆች እስኪ ቡና አጫጭሱ፣ ቁርስም አቅርቡ" ስትል እሷና ቹቹ ከሄዱ በኋላ የተወለዱ የማታውቃቸው የልጅ ልጆቿ ጋር ብለው ወጥተው...

...ህይወት ከዚህ በላይ ተአምር አላት፤ ምን ሊደንቃት? ካላመንክ ቁጭ ብለህ እንደዚህ በቀን አልምላት፡፡ ህልምህን ሰርቃ፣ ጨምራና አሽሞንሙና አንድ ጥግ ውሸት እያጠጣች አስይዛ የህልምህን ቅጠል ትውልድ ፍየል ሆኖ ሲቀመው ትደርሳለህ፡፡



# ክፍል ፫

## ከልውጥውጡ በኋላ

**"..ሸክሞቻችሁ ለደካማ እንስሳ ከባድ ጭነት ሆነዋል። ተጎነበሱ በአንድነትም ተዋረዱ ሸክሙን ለማዳን አልቻሉም፤ ራሳቸው ግና ተማረኩ።"**

**ትንቢተ ኢሳያስ 46፡1-2**

# መታሰቢያነቱ

ይሄ ክፍል ሥጋዬንና ነፍሴን ላስለጠነችው

ለሲፈን ተገኔ መታሰቢያ ይሁን

# XXXIX

## የሲፈን ነገር

**ተፈፀመ**


የብርሃን
ፈለጎች





ዓለማየሁ ገላጋይ የጦማራዊ ልቦለድ (EPISTOLARY WRITING) አጻጻፍን ከተለመደው አተራረክ ጋር አዋሕዶ፣ የመጀመሪያ ልቦለዱ የሆነችውን አጥቢያን በመጽሐፍ ካቀበለን እነሆ አስረኛ ዓመቱን ይዟል፡፡ ...

ከመጀመሪያ ልቦለዱ ጀምሮ በደራሲዎቻችን ያልተሞከሩ ወይም የማይዘወተሩ የአጻጻፍ ቴክኒኮችን፣ ለምናባዊ ተረኮቹ መባያነት በመጠቀም፣ በስነጽሑፋችን ውስጥ የራሱን የፋና ወጊነት አሻራ ያሳረፈ EXPERIMENTAL NOVELIST ነው፡፡ በቅበላ፣ በየብርሃን ፈለጎች፣ በወረሳ ረጃጅም ልቦለዶቹ የድኅረ ዘመናዊ ድርሰቶች መገለጫዎች የሆኑ እንደ ዲበልቦለዳዊነት (META-FICTION)፣ እንደ ቅጥጥብ (PARODY)፣ በእውናዊው እና በልቦለዳዊው ዓለም መሐል የተሰመረውን ድንበር እንደመደምሰስ ባሉ ስልቶች የቀረቡ ናቸው፡፡ በሁሉም የዓለማየሁ ድርሰቶች የምናየው፣ ከእሱ ዘመነኛ ጸሐፊዎች በተለየ ወደ ስነጽሑፋችን ፋና ወጊዎች ዘመን የሚመልሰን፣ የአማርኛን ቋንቋ የመግለፅ አቅም የሚመሰክር፣ የደራሲውንም እንደልቡ በቋንቋ የመጫወት ክህሎት የሚያሳይ ድንቅ የቋንቋ ብቃቱን አይተናል፤ ...

እነዚህን በይነ ዲሲፕሊናዊ ጥናቶችን የሚጋብዙ ድርሰቶቹን ተከትሎ በመጣው "በፍቅር ሥም" ዓለማየሁ ህይወትን ባልተለመደ/በተገለለ የማኅበረሰባችን አካል ዐይን እንድናይ ዕድል የሰጠን፣ ሌላኛው ድኅረ ዘመናዊ ድርሰቱ ነው፡፡ ...በምናባዊ እና በእውናዊው ህይወት መሐል ያበጀነውን መስመር አጥፍቶ የሁለቱን ዓለሞች ግንኙነት ደግመን እንድንጠይቅ ቀስቁሶን ወደ ትረካው ይሸገራል፡፡...

ቴዎድሮስ አጥላው

(የስነጽሑፍ ተመራማሪ)

ሐሪቱጀ ኅትመትና ንግድ ኃ/የተ/የግል ማኅበር

ዋጋ 71.00 ብር